አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የአማርኛ የቃላት አፈታትን
# በሁለተኛ ደረጃ መለኪያ
# ፈተና መገንባት

ትንግሼ ብርሀኔ

ሰኔ 1983 ዓ.ም.

3203

# የአማርኛ የቃላት አፈታተን - በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት ።


በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት


በቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አማርኛን በማስተማር ዘዴ

ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ።

ሰኔ ፤ 1988 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
# ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## የአማርኛ የቃላት አፈታተን-በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት


በ

ትንሣኤ ብርሀኔ

የቋንቋ ጥናት ተቋም


## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

## ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ..........

አጠቃሎ (Abstract) ..........

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ .......... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ .......... 1

1.2. የጥናቱ ዓላማ .......... 3

1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት .......... 3

1.4. የጥናቱ ወሰን .......... 4

1.5. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች .......... 5

1.6. የቃላት ትርጓሜና የምሕፃረቃላት አጠቃቀም .......... 6

1.6.1. የቃላት ትርጓሜ .......... 6

1.6.2. ምህፃረ ቃላት .......... 7

ምዕራፍ ሁለት

2. የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሣ .......... 9

2.1 ቋንቋን ማስተማርና ቋንቋን መፈተን .......... 9

2.1.1 ቋንቋን ማስተማር .......... 10

2.1.2 ቋንቋን መፈተን .......... 11

2.2 የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች .......... 13

2.2.1 የችሎታ መለኪያ ፈተና .......... 14

2.2.1.1 ብያኔ .......... 14

2.2.1.2 የፈተናውይዘት መሠረቶች ........................................ 16
2.2.1.3 ናሙና ........................................ 17
2.2.1.4 የጥያቄ አቀራረብ ስልት ........................................ 18
2.2.1.5 የአዘገጃጀት ዝርዝር መርሆዎች ........................................ 20

2.2.2 ብቃትን መለኪያ ፈተና ........................................ 21
2.2.3 ጥንካሬና ድክመትንመለኪያ ፈተና ........................................ 22
2.2.4 ቅድመ ችሎታን መለኪያ ፈተና ........................................ 22
2.3 የጥሩ ፈተና ባህርያት ወይም መስፈርቶች ........................................ 23

2.3.1 አስተማማኝነት ........................................ 24

2.3.1.1 የይዘት አስተማማኝነት---------------------- 24
2.3.1.2 ላሕያዊ አስተማማኝነት ---------------------- 25

2.3.2 ህያውነት------------------------------------26
2.3.3 ተተግባሪነት------------------------------------27

2.4 ቃላትን ማስተማርና መፈተን ........................................ 28
2.4.1 ቃላትን ማስተማር ........................................ 29
2.4.2 ቃላትን መፈተን ........................................ 31

2.5 የቋንቋ ፈተናዎችን የገመገሙ ቀደምት ጥናቶች ........................................ 35

## ምዕራፍ ሦስት

3. የአጠናን ዘዴ ........................................ 38

3.1 የትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎችና የፈተናዎች ናሙና አመራረጥ .......... 38

3.1.1 የት/ቤቶች ናሙና አመራረጥ ........................................ 38

3.1.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........................................ 40

3.1.3 የፈተናዎች ናሙና አመራረጥ ........................................ 40

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ........................................ 41

3.2.1 መጠይቆች ........................................ 42

3.2.1.1 የመምህራን መጠይቅ ........................................42

3.2.1.2 የተማሪዎች መጠይቅ ........................................44

3.2.2 ቃለ መጠይቅ ........................................45

3.2.3 የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መማሪያ መጻሕፍት ........ 46

3.2.4 የተፈታኞች ውጤት ........................................46

3.2.5 ፈተናዎች ........................................ 46


## ምዕራፍ አራት


4. የጥናቱ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ -----------------------48

4.1 አስተማማኝነት ........................................ 48

4.1.1 ላህያዊ አስተማማኝነት ........................................ 48

4.1.2 የይዘት አስተማማኝነት ........................................ 50

4.1.2.1 የፈተናዎአላማ ግልጽነት ........................................ 62

4.1.2.2 የፈተናው የቃላት አመራረጥ ........................................ 67

4.1.2.3 የተገቢ አውድ አዘገጃጀት ........................................ 75

4.1.2.4 የአሳሳቾች ተአማኒነት ........................................ 80

4.1.2.5 ትክክለኛው መልስ አንድ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ ........ 82

4.2 ሀያውነት ........................................ 89

4.3 ተተግባሪነት ........................................ 97

ምዕራፍ አምስት

5. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት ........................................ 99

5.1 መጠቃለያ ........................................ 99

5.2 መደምደሚያ ........................................ 105

5.3 አስተያየት ........................................ 107

- ዋቢዎች ........................................ 110

- አባሪዎች ........................................ 117

አባሪ ሀ. የፈተናዎቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ........................................ 117

አባሪ ለ. የቀድሞዎቹ እና የአሁኖቹ መማሪያ መጻሕፍት የቃላት መልመጃዎች .... 139

አባሪ ሐ. የቀድሞዎቹ እና የአሁኖቹ ሲለበሶች ስለቃላት ትምህርት ያሏቸው ነጥቦች ........................................ 169

አባሪ መ. የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መምህራን መጠይቅ ........................................ 173

አባሪ ሠ. የተማሪዎች መጠይቅ ........................................ 176

አባሪ ረ. የአማርኛው ፓናል ሐላፊ ቃለመጠይቅ ........................................ 178

አባሪ ሰ. የተፈታኞች ውጤት ........................................ 179

አባሪ ሸ. መረጃ ቅጽ 01 ........................................ 183

# የሰንጠረዥ ዝርዝር


| ሰንጠረዥ | ርዕስ | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| 1. | የመምህራን መጠይቅ ስርጭት፣ ተሞልተው የተመለሱ ቁጥርና መቶኛ | 44 |
| 2. | የትምህርት ይዘቶች በማስተማሪያ መማሪያዎችና በፈተናዎች ውስጥ ያላቸው ውክልና | 51 |
| 3. | ሲለበሶቹ ለቃላት ትምህርት የነደፏቸው ይዘቶች | 54 |
| 4. | የቀድሞዎቹ (ቀ) እና የአሁኖቹ (አ) መማሪያ መጻሕፍት ስለቃላት/ፈሊጥ ትምህርት ያቀረቧቸው መልመጃዎች | 56 |
| 5. | ከ1980-1987 ዓ.ም. የተዘጋጁት የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. ቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች አቀራረብ፣ ቁጥርና መቶኛ | 60 |
| 6. | መምህራን ስለቃላት /ፈሊጦች ትምህርት አሰጣጥ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች | 61 |
| 7. | የቃላት አመራረጥ መስፈርቶችንበተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችና መምህራኑ የሰጧቸው መልሶች | 67 |
| 8. | ከፈተናዎቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ በመማሪያ መጽሐፍቱ መልመጃዎች ተዛምደው የተገኙ ቃላትና ፈሊጦች | 68 |
| 9. | ዘዬ ቃላትን በተመለከተ መምህራኑ የሰጧቸው መልሶች | 71 |
| 10. | ያለአውድ የቀረቡ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎችን በተመለከተ መምህራኑ የሰጧቸው መልሶች | 76 |
| 11. | አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች | 83 |
| 12. | የቃላት ጥያቄዎች ውጤት ትንተና | 90 |
| 13. | ዘዬ ቃላትን በትክክል የመለሱ ተፈታኞች ብዛት በአፍ መፍቻ ቋንቋ | 94 |

# ምስጋና

ከሁሉም በላይ የጥናቱን ረቂቅ ደጋግመው እያነበቡ በማረም የማያቋርጥ ድጋፋቸውን ለሰጡኝ አማካሪዬ ዶ/ር ደጀኔ ለታ ጥልቅ፣ ከፍተኛና ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በተጨማሪም ዶ/ር ተሾመ ደምሴ ለሰጡኝ ሙያዊ ድጋፍ ላቅ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጨረስ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በሀሳብና በሞራል በመደገፍ የበርካታ ግለሰቦች ውለታ አለብኝ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ መረጃ ቅጽ 01ን ያስሞሉልኝ 17 የድኅረ ምረቃው ክፍል ተማሪዎች፣ መጠይቁን በመሙላት የተባበሩኝ መምህራንና ተማሪዎች፣ ቃለመጠይቁን የመለሱልኝ የአማርኛው ፓናል ሐላፊ፣ ለፈተናዎቹ መልስ በመስጠት የረዱኝ 6 ባለሙያዎች፣ ባለው አቅም ሁሉ መረጃዎችን እንዳገኝ በግሉ ቀና ጥረት ያሳየኝ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ጽ/ቤት ሪኮርድ ክፍል ሀላፊ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች መረጃዎችን ለማሰባሰብ ያበረከቱልኝ አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

በሀሳብና በሞራል እየደገፉ እስከ ጥናቱ መጨረሻ ድረስ ከጎኔ ያልተለዩት ውድ ጓደኞቼ የአቶ ጥላዬ ካሣሁን፣ የአቶ አለማየሁ ቢሻው፣ የአቶ ጌትነት ደምሴና የቤተሰቦቼ ውለታ ታላቅና ምንጊዜም የማልረሳው ነው፡፡

በመጨረሻም ጽሑፉን በጥንቃቄ የተየቡልኝ ወ/ሮ አሰፋሽ፣ ወ/ሮ ብርቄ እና ወ/ሮ አልማዝን ከልቤ አመሰግናለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ውስጥ የሚቀርቡት የቃላት ጥያቄዎች ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ መሆን ወይም አለመሆናቸውን መመርመር ነበር፡፡

ለጥናቱ በናሙናነት የስምንት አመታት (1980-87 ዓ.ም. የተዘጋጁ ናቸው) የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተናዎች ተመርጠዋል፡፡ የእነዚህን ፈተናዎች 269 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በጥሩ የፈተና ባህርያትና በቃላት አፈታተን መርሆዎች በመገምገም የጥናቱን አላማ ለማሳካት ተሞክሯል፡፡ በግምገማው ሂደት ከመምህራንና ከተማሪዎች መጠይቅ እንዲሁም ከአማርኛው ፓናል ሐላፊ ቃለመጠይቅ የተገኙ መልሶች ተተንትነዋል፡፡

ፈተናዎቹን በጥሩ የፈተና በሕርያትና በቃላት አፈታተን መርሆዎች በመገምገም እንዲሁም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን በመተንተን የተገኘው ውጤት አብዛኞቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ አለመሆናቸውን አመልክቷል፡፡ በተለይ ያለአውድ የቀረቡት 187 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በመመዘኛ መስፈርቶቹ ሲገመገሙ ከጠንካራ ጎናቸው ይልቅ ደካማ ጎናቸው እንደሚያይል ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች አላማ ግልጽ ያለመሆን፣ አቀራረባቸው የትምህርቱን አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና የመማሪ መጽሀፍቱን መልመጃዎች መሠረት አለማድረግ፣ አመራረጣቸው ዘፈቀዳዊ መሆን (በዚህ ስር 23 ቃላት ዘዬ ቃላት መሆናቸው፣ 18 ቃላትና ፈሊጦች መደጋገማቸውና 18 ቃላትና ፈሊጦች ብቻ ከመማሪያ መጻሕፍቱ መልመጃዎች መመረጣቸው ተጠቅሷል)፤ ለጥያቄው ተገቢ አውድ አለማዘጋጀትና ለ55 ጥያቄዎች ባለሙያዎች የሚስማሙበት አንድ ትክክለኛ መልስ አለማቅረብ በግምገማው ከታዩት ዋና ዋና ድክመቶች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሣ ለሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ የቃላት ትምህርት አሰጣጥ አንድን ቃል ወይም ፈሊጥ ያለአውድ እያቀረቡ መፈተን ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ አለመሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

በሌላ በኩል በአውድ የቀረቡት 87 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በመመዘኛ መስፈርቶች ተገምግመው ጠንካራ ጎናቸው አይሎ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም በአውድ የቀረቡት ጥያቄዎች

ለሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ የቃላት ትምህርት አሰጣጥ ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ መሆናቸውን ጥናቱ አመልክቷል፡፡

በጥናቱ ውጤት ላይ በመመርኮዝም ያለአውድ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በአውድ እንዲተኩ ለፈተና የሚመረጡት ቃላትና ፈሊጦች በአብዛኛው በመማሪያ መጻሕፍቱና በክፍል ውስጥ ልምምድ ላይ እንዲመሠረቱ፣ ፈተናዎቹ ልዩ ልዩ የአጠያየቅ ስልቶችን እንዲያካትቱ፣ የመፍትሔ ሐሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን ዓላማ፣ የጥናቱን አስፈላጊነት፣ የጥናቱን ወሰን፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን እና የቃላትና የምህፃረ ቃላት አጠቃቀምን በቅደም ተከተል ያቀርባል።

### 1.1 **የጥናቱ ዳራ** / Background of the study /.

ሂተን /1975/፣ ሂዩዝ /1989/ ና ዴቪስ /1968/ እንደሚያረጋግጡት ፈተና ከማስተማር ጋር ጥብቅ ግንኙነት አለው። በተለይ ከፈተና አይነቶች ውስጥ የችሎታ መለኪያ ፈተና /Achievement test / የሚባለው መሰረት የሚያደርገው ተማሪው የተማረውን ትምህርት ወይም ይማረዋል ፃተባለውን የትምህርት ፕሮግራም በመሆኑ ከማስተማር ጋር ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖረው ይጠበቃል ። በአጠቃላይ ፈተና የመማር ማስተማሩ ሂደት አንድ አካል ነው በሚለው ሐሳብ በርካታ ምሁራን ይስማማሉ። ስለዚህ የአንድ ፈተና በወጉ መዘጋጀትና አለመዘጋጀት በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚያስድረው ተፅእኖ /ካሁን በኋላ ባክዋሽ እያልን የምንጠራው/ አይቀሬ ነው። በርግጥ ባክዋሹ ጠቃሚ ወይም ጎጂ ሊሆን ይችላል። ፈተናው በጥሩ ሁኔታ ሲዘጋጅ ባክዋሹ ጠቃሚ ነው። በተቃራኒው ሲሆን ደግሞ ጎጅ ይሆናል።

በመሆኑም የአንድን ፈተና በብቃት መዘጋጀት ወይም አለመዘጋጀት መገምገም የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማቃናት ለሚደረገው ጥረት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል ተብሎ ይታመናል። ለምሣሌ እንደ ግሮንላንድ /1988:8/ እምነት አንድ ፈተና በተገቢው መንገድ ከተገመገመ ከግምገማው የሚገኙት መረጃዎች ለትምህርቱ ግምገማና መሻሻል አጋዥ ናቸው። በዚህም መረጃዎቹ አንደኛ የትምህርቱን አላማዎች ተግባራዊነትና

ተገቢነት፣ ሁለተኛ የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ጠቃሚነትና ሶስተኛ የማስተማሩን ዘዴ ውጤታማነት ለመገምገም ያስችላሉ።

በዚህም መሠረት በየጊዜው የሚዘጋጁ የቋንቋ ፈተናዎች በባለሙያዎች ሲገመገሙ ቆይተዋል። በውጭ ሀገር የተደረጉ የግምገማ ጥናት ውጤቶችን መሠረት አድርገው ሂዩዝ /1989:1/ እንደሚመሰክሩት የአብዛኛዎቹ ፈተናዎች አዘገጃጀት ደካማ ነው። በዚህም የተነሣ ባክዋሹ ጎጅ ነው። ስለዚህ ለማስተማር ዘዴያችን የምንጠበበውን ያህል ለአፈታተናችንም እንድንጠበብ ይመክራሉ።

በሀገራችንም የቋንቋ ፈተናዎችን ድክመት ጥንካሬ የገመገሙ ጥናቶች አያሌ ናቸው። የሚከተሉትን ለአብነት ያህል እንጠቅሳለን። አበበ /1975/፣ ንጉሤ /1978/፣ ወርቁ /1979/፣ መንገሻ /1984/፣ አለም /1983/ እና ደጀኔ /1990/። እነዚህ ጥናቶች ለየተነሱበት ርዕስ ጉዳይ የየፈተናዎቹን ድክመትና ጥንካሬ በመገምገም ውጤቶቻቸውን አቅርበዋል። የአብዛኞቹ ውጤት የሚጠቁመው የፈተናዎቹን ደካማነት ነው።

ይህ ጥናት ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ጥናቶች ጋር ቢያንስ ፈተናዎችን በመገምገሙ ተመሳሳይነት አለው። ይሁን እንጂ አጥኚው ባደረገው አሰሳ እስካሁን የአማርኛ ቃላትን አፈታተን በተናጠል ወስዶ የመረመረ ጥናት ስላላጋጠመው ከሌሎች ጥናቶች ይለያል። የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተናዎች ቃላትን ከሌሎች የቋንቋ ዘርፎች እየነጠሉ በመፈተን ይታወቃሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከፈተናዎቹ ጥያቄዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ የቃላት ጥያቄዎች ናቸው። ስለዚህ እነዚህን ጥያቄዎች በተናጠል ወስዶ ብቃት ያላቸው መመዘኛዎች መሆን አለመሆናቸውን በመመርመር የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማቃናት ለሚደረገው ጥረት መጠነኛ አስተዋጽኦ ማድረግ ይቻል ይሆን? የሚል ጥያቄ ለማንሳት አስገድዷል። በዚህም መሠረት በጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞከራል።

1. የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መማሪያ መጻሕፍት ለቃላት /ፈሊጦች ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው? ፈተናዎቹስ?

2. የፈተናዎቹ የቃላት / ፈሊጥ ጥያቄዎች ከጥሩ የፈተና ባህርያትና ከቃላት አፈታተን መርሆዎች አንፃር ሲመዘኑ ጠንካራ ጎናቸው ያይላል ? ወይስ ደካማ ጎናቸው?

3. አማርኛን በአፍ መፍቻነት መናገር ወይም አለመናገር የፈተናዎቹን የቃላት/ፈሊጥ ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ ያለው ተጽዕኖ ምን ያህል ነው?

## 1.2 የጥናቱ አላማ /Objective of the study /

የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና የቃላት/ፈሊጥ ጥያቄዎች ተገቢ ወይም ጥሩ የመመዘኛ መሣሪያ መሆን አለመሆናቸውን መመርመር ነው። አጠቃላይ አላማውን መሠረት በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አለማዎች አሉት።

1. የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መማሪያ መጽሐፍት ስለቃላት/ፈሊጦች ትምህርት የሚያነሷቸውን ነጥቦች መመርመር ።

2. ፈተናዎቹን ከጥሩ የፈተና ባህርያትና ከቃላት አፈታተን መርሆዎች አንፃር መመርመር ።

3. የተፈታኞችን የመልስ ትንተና ውጤት መሠረት በማድረግ አማርኛን በአፍ መፍቻነት መናገር ወይም አለመናገር የፈተናዎቹን የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ለመመለስ የሚኖረው ተጽእኖ ካለ መመርመር።

4. የተሻለ የአፈታተን ስልት የሚቀየስበትን መንገድ መጠቆም።

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት / Importance of the Study/

በየጊዜው የሚዘጋጁ ፈተናዎችን መገምገም የማስተማሪያ መሣሪያዎችንና ዘዴዎችን ለማሻሻል ከመርዳቱም በላይ ፈተናዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ወይም ባክዋሹ አዎንታዊ እንዲሆን ያግዛል። ስለዚህ ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ስላሉት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

1. ፈተና አውጭዎች ተግባራቸውን በታላቅ ጥንቃቄ እንዲያከናውኑ በመገፋፋትና የሚያዘጋጇቸው ፈተናዎችም ለጥሩ ማስተማር ድጋፍ ሰጪ እንዲሆኑ በማበረታታት፣
2. የተሻሉ የአጠያየቅ ስልቶችን በመጠቆም፣
3. የአማርኛን ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ይበልጥ የተቃና ለማድረግ ለሚደረገው ጥረት የበኩሉን ጠቃሚ ሀሳብ በማስገኘት፣
4. እንዲሁም ለመሰል ጥናቶች መነሻ በመሆን ጥናቱ መጠነኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል።

## 1.4 የጥናቱ ወሰን / Delimitation of the study /.

የዚህ ጥናት ዐቢይ ትኩረት በ8 አመታት የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. ውስጥ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ መሆን አለመሆናቸውን መገምገም ነው። ግምገማው ከጥሩ የፈተና ባህርያትና ከቃላት አፈታተን መርሆዎች አንፃር ይከናወናል። ከጥሩ የፈተና ባህርያት አስተማማኝነትን ህያውነትንና ተተግባሪነትን ይመረምራል። በአስተማማኝነት ሥር የቃላት አፈታተን መርሆዎች በዝርዝር ይመረመራሉ ። በህያውነት ስር ደግሞ በሀገራችን በተለያዩ ክልሎች የሚማሩ ተማሪዎች በ1987 ፈተና ውስጥ ለቀረቡ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች ይተነተናሉ።

ይሁን እንጂ ጥናቱን በስፋት ለማካሄድ በሚጠይቀው ሰፊ ጊዜና ወጪ ምክንያት በሁሉም የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን ናሙና ውጤት መውሰድ አልተቻለም ። ስለዚህ ጥናቱ ከ20 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተወሰዱ የ200 ተፈታኞችን ውጤት ብቻ የሚመለከት ነው። ጥናቱ በፈተናው ግምገማ የተገኙ ውጤቶችን ማመልከት እንጂ አዲስ የቃላት ፈተና በማዘጋጀት ውጤቱን አነፃፅሮ የሚያመለክት አይደለም። ከዚህም በተጨማሪ ጥናቱ በአብዛኛው በአፈታተን ስልት ላይ የሚያተኩር ስለሆነ የማስተማሪያ መሣሪያዎቹን በብቃት መዘጋጀት/ አለመዘጋጀት በጥልቀት የሚመረምር አይደለም።

## 1.5 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች / Limitations /.

ይህ ጥናት በ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የ2ኛ ደረጃ ጽ/ቤት አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ይተባበራል የሚል ተስፋ ነበር። ይሁን እንጂ ለጥናቱ አስፈላጊ ከሆኑ መረጃዎች ውስጥ:

1ኛ. የእያንዳንዱን አመት ፈተና የመልስ ቁልፍ / Answer Key/ እና

2ኛ. የተፈታኞችን የመልስ ወረቀት / Answer Sheet /ጽ/ቤቱ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑ በጥናቱ ወቅት ያጋጠመ ጉልህ ችግር ነበር።

ጽ/ቤቱ ባለው ምስጢራዊ አሰራር የየፈተናውን የመልስ ቁልፍና የተፈታኞችን የመልስ ወረቀት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑ የሚከተሉትን ችግሮች አስከትሎ ነበር ።

- ፈተና አዘጋጁ ለየጥያቄው የሰጠው መልስ ባለሙያዎች የሚስማሙበት መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻል፣
- አማርኛን በአፍ መፍቻነት መናገር ወይም አለመናገር በቃላት ጥያቄ ውጤት ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ ለመመርመር አለመቻል፣
- ተፈታኙ በአውድ የቀረቡትን የቃላት/የፈሊጥ ጥያቄዎች ነው በትክክል የሚመልስ ወይስ ያለአውድ የቀረቡትን የሚለውን አወዳድሮ ትንታኔ ለመስጠት አለመቻል።

እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ሲባል ቢያንስ ጥናቱ ለአንድ አመት መዘግየት ነበረበት። ይህም የሆነበት ምክንያት ጽ/ቤቱ የ1987 ዓ.ም. የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. የመልስ ቁልፍና የተፈታኞችን የመልስ ወረቀት እንደሚሰጠኝ ቃል ስለገባ ነበር። ጽ/ቤቱ በገባው ቃል መሠረት በጥቅምት ወር 1988 ዓ.ም. ሁሉቱን መረጃዎች ስለሰጠኝ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ከሞላ ጎደል ሊቃለሉ ችለዋል። ሆኖም ጽ/ቤቱ የየፈተናዎቹን የመልስ ቁልፍና ቢያንስ የሶስት ዓመት ተፈታኞችን የመልስ ወረቀት/የተፈታኞችን የመልስ ወረቀት የዘመኑ ፈተና ውጤት ከተነገረ በኃላ ስለሚቃጠል ማግኘት አይቻልም የሚል መልስ ጽ/ቤቱ

አለው/ ለመስጠት ፈቃደኛ ቢሆን ኖሮ አሁን የተደረሰበትን የጥናት ውጤት ይበልጥ ማጠናከር ይቻል ነበር። ቢዚህ አጋጣሚ ጽ/ቤቱ ለጥናትና ምርምር ሥራዎች በሩን ክፍት ቢያደርግ መልካም መሆኑን ለማሳሰብ እንወዳለን።

1.6 የቃላት ትርጓሜና የምህፃረ ቃላት አጠቃቀም /Definition of terms/

1.6.1 የቃላት ትርጓሜ

. የቃላት አፈታተን /Testing Vocabulary/

በዚህ ጥናት የቃላት አፈታተን የሚለው ሐረግ የሚመለከተው የይዘት ቃላትን /ስም፣ ግስና ቅጽል/ ሆኖ ጽንሰ ሐሳቡ ድርብ ቃላትን /compound words/ ፣ ፈሊጦችን /idioms/ እና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሐረጋትን ያጠቃልላል። በዚህም መሠረት በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ውስጥ ለአንድ ቃል፣ ፈሊጥ ወይም ሐረግ ፍች እንዲሰጥ የሚጠይቁ ጥያቄዎች የቃላት አፈታተን በሚል መጠሪያ ተመልክተዋል። ዋላስ /1982 :119/ እና ካርትና ሚክካርዚ /1988:19/ ለቃላት የሰጡት ብያኔ ለጽንሰ ሐሳቡ ትርጓሜ በመሠረትነት አገልግሏል ።

. ቃላትን በአውድ መፈተን

ቃላት ወይም ፈሊጦች በዐ. ነገር አገባብ ወይም በምንባብ ውስጥ ወይም የተለየውን ቃል አወጣ በሚል ለፈተና መቅረባቸውን ያመለክታል። በአውድ የሚለው የእንግሊዝኛውን 'with context' የሚተካ ነው።

. ቃላትን ያለአውድ መፈተን

ቃላት ያለምንም ዐ.ነገራዊ ወይም ምንባባዊ አውድ ለፈተና መቅረባቸውን ያመለክታል። ለምሳሌ ነፈረቀ ሀ. አለቀሰ ለ. ሳቀ ሐ.. አዘነ መ. ፈረከሰ፤ ያለ አውድ የሚለው የእንግሊዝኛውን 'without context' የሚተካ ነው።

. የቃላት አመራረጥ

ፈተና አውጭው ለፈተና የሚቀርቡ ቃላትን እንዴት እንደሚመርጣቸው የሚያመለክት ነው። ይህም አመራረጡ በመማሪያ መጻሕፍት፣ ሲለበሶች፣ ወዘተ. መመስረት አለመመስረቱን ለመመርመር የተሰጠ መጠሪያ ነው።

. ዘዬ ቃላት

በተለያዬ አካባቢ የሚነገሩ የአማርኛ ቃላትን ይመለከታል። አንዳንድ ሰዎች ቀበሌኛ በሚል ይጠሩታል። የእንግሊዝኛው ቃል dialect ነው።

. ተደጋጋሚ ቃላት

በየአመቱ በሚዘጋጁ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተናዎች ውስጥ አንድ ቃል ቢያንስ በሁለት ዓመት ፈተናዎች ውስጥ ለፈተና መቅረቡን የሚያመለክት ነው።

. አሳሳቾች /distractors/

ከዋናው መልስ ጋር በአማራጭነት የሚቀርቡ መልሶችን ይመለከታል። ተአማኒ አሳሳቾች ሲባልም በአማራጭነት የቀረቡ መልሶች መልስ የመምሰል ባህርያቸውን ይመለከታል።

1.6.2 ምህፃረ ቃላት

ሁ.ደ.መ.አ.ፈ. = የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና/ዎች/።

ሁ.ደ.መ.ጽ/ቤት = የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ጽ/ቤት

ቀ. = ለማስተማሪያ መሣሪያዎች ሲውል የቀድሞዎቹ የ2ኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍትና ሲለበሶች ማለት ነው። የተዘጋጁበት ዘመን ከ1972 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ አገልግሎት ሰጥተዋል።

ለፈተናዎቹ ሲውል ደግሞ ከ1980 - 83 ዓ.ም. ድረስ የተዘጋጁትን ይመለከታል።

ኡ፦ ለማስተማሪያ መሣሪያዎች ሲውል የአሁኖቹ የ2ኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍትንና ሲለበሶችን ይመለከታል። የተዘጋጁበት ዘመን ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን እስካሁን አገልግሎት እየሰጡ ነው። ለፈተናዎች ሲውል ደግሞ ከ1984 - 87 ዓ.ም. ድረስ የተዘጋጁትን የአማርኛ ፈተናዎች ይመለከታል።

ጥ. ጥያቄ

k.፦ The No. of items in the test

p.፦ Item Difficulty or proportion of correct responses to a particular item.

q.፦ Proportion of incorrect responses to a particul ar item

$S^2$ ፦ Variance

## ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሑፎች ክለሣ

ይህ ምዕራፍ ምሁራን በፈተና በተለይም ደግሞ በቋንቋ ፈተና መስክ ባካሄድዋቸው ንደፈ ሐሳባዊና ምርመራዊ ሥራዎች ላይ ያተኩራል። በመስኩ ከተካሄዱ በርካታ ንድፈ ሐሳባዊና ምርመራዊ ስራዎች ደግሞ ለጥናቱ ዓላማ መሠረት የሚሆኑትን ወይም የሚዛመዱትን ለመምረጥ ተሞክሯል። ምዕራፉን በአምስት ንዑሳን ክፍሎች በመከፈል እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞከራል ።

### 2. 1. ቋንቋን ማስተማርና ቋንቋን መፈተን

በርካታ ምሁራን መፈተንና ማስተማር ጥብቅ ግንኙነት እንዳላቸው ይመስክራሉ። ለምሣሌ ሂተን (1975) ሲገልፁ "መፈተንና ማስተማር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። በዚህም የተነሳ አንደኛውን መስክ ከሌላው ነጥሎ ለመስራት በፍፁም የሚቻል አይደለም። ይልቁንም የሁለቱን ቁርኝት በውል በመገንዘብ ለሁለቱም መስኮች ተገቢውን ትኩረት መስጠት የዘወትር ተግባራችን መሆን አለበት።" ብለዋል። ሂተን( 1975:15 )

በተመሣሣይ ሁኔታ ሃሪስን (1983:1) ሲያስረዱ " መፈተንና ማስተማር ጥብቅ ግንኙነት አላቸው። ፈተና የክፍል ክንውኑ ቀጣይ ስራ ተደርጎ መታየት አለበት። በዚህም ፈተናው ለመምህሩና ለተማሪው ጠቃሚ መረጃዎችን በመስጠት ለትምህርቱ ሂደት መሻሻል መሠረት ነው። " ብለዋል። ሜክአርተር (1983:12) እና ኢብል (1979:22) ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ የሚጋሩ ናቸው።

"ዴቪስ (1968:7) በበኩላቸው " ጥሩ ፈተና ማስተማርን ስለሚከተልና ያስተማርከውንም ጠይቅ ስለሚል የትምህርቱ ቅን ታዛዥ ነው። " ብለዋል። በሌላ በኩል ሂዩዝ ( 1989) ግን የዴቪስን ( 1968 ) ሀሳብ መሉ ለሙሉ አይቀበሉትም። እንደ እርሳቸውም እምነት "እኛ ሁልጊዜ መፈተን ማስተማርን እንዲከተል መጠበቅ የለብንም በምትኩ የፈተናው ተግባር ዘወትር ለጥሩ ማስተማር ድጋፍ ሰጪ እንዲሆን መጣር አለብን። አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ፈተናው በመጥፎ ማስተማር ላይ በጎ ተጽእኖውን በማሳደር ማስተማሩ የሚስተካከልበትን መንገድ የሚጠቁም እንዲሆን ይጠበቃል።" ይላሉ። ( ሂዩዝ ፣1989 :2 )

በዚህ የሂዩዝ አመለካከት መፈተን ከማስተማር ጋር ያለውን ግንኙነት ሳይክዱ ግንኙነቱ ግን የአዛዥና የታዛዥ ወይም የሽርክና ባህርይ መላበስ እንደሌለበት ያስገነዝቡናል::

በአጠቃላይ ከላይ ከጠቀስናቸውና ከሌሎች ምሁራን እንደምንገነዘበው መፈተንና ማስተማር ጥብቅ ዝምድና አላቸው:: በእርግጥ እንደሚዘጋጀው ፈተና አይነት፣ እንደፈተናው አላማ፣ እንደፈተናው የአዘገጃጀት ጥራት ወዘተ. የግንኙነቱ መጠን ጥብቅ ወይም ልል ሊሆን ይችላል:: ያም ሆኖ ግን ጆን (1973፣8) እንዳሉት መፈተንና ማስተማር የትምህርቱ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ስለሆኑ ግንኙነታቸው አይቀሬ ነው:: ግንኙነት መኖር ብቻ ሳይሆን አንደኛው በሌላው ላይ ተጽእኖ እያሳደሩ እስከዛሬ መዝለቃቸውም የሚያጠያይቅ አይደለም::

## 2.1.1. ቋንቋን ማስተማር

ቋንቋን ማስተማር ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን ቋንቋን ለማሳወቅ የሚድረግ ዝግጅት ያለው ክንዋኔ ነው:: በጥቅሉ ሲታይ ቋንቋው አፍ መፍቻቸው የሆኑትን ተማሪዎች የምናስተምርበት ዓላማ በቋንቋው ጥሩ ተናጋሪዎች፣ ጥሩ አድማጮች፣ ጥሩ አንባቢዎች፣ ጥሩ ጸሐፊዎችና ጥሩ ተመራማሪዎች እንዲሆኑ ለመርዳት ነው:: (ተስፋዬ፣ 19 81.) ተስፋዬ በገጽ 62 ሃሊዲይና ስትሬቪንስ ን (1964:223–25) በመጥቀስ እንደሚገልጹት የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለማስተማር እንደመርህ የሚቆጠሩ ዘዴዎችችዕዛዛዊ (Rescriptive ) ፣ ገላጭ ( Descriptive) ና ውጤታዊ ( Productive) ናቸው::

የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለማስተማር ከሚረዱ ዘዴዎች ይልቅ በስነጽሑፉ አለም በብዛት የምናገኛቸው ሁለተኛ ወይም የውጭ ቋንቋን ለማስተማር የሚረዱ ዘዴዎችን ነው:: የዘዴዎቹ ብዛት ከፀሐፊ ፀሐፊ ቢለያይም ሪቻርደስና ሮጀርስ (1991) ባቀረቧቸው አሥራ ሶስት ዘዴዎች ይጠቃለላሉ :: እነሱም ሰዋስው ወትርጉም ዘዴ፣ ቀጥተኛ ዘዴ፣አዳምጦ የመመለስ ዘዴ፣ የአረምሞ ዘዴ፣ ሀሳብ ጠቋሚ ዘዴ፣ማህበረሰባዊ ዘዴ፣ አካላዊ ምላሽ ሰጭ ዘዴ፣ተግባቦታዊ ዘዴ፣ሁነታዊ ዘዴ፣ ንባባዊ ዘዴ፣ ተፈጥሯዊ ዘዴ፣ ምስለ-ዕዝነ ዘዴ እና ግንዛቤያዊ ዘዴ ናቸው::

የአፍ መፍቻ ቋንቋንም ሆነ ሁለተኛን ቋንቋ በማስተማር ሂደት አንድ ወይም ብቸኛ ዘዴ ተጠቅሞ ማስተማሩ ያመጣው ውጤት አመርቂ አይደለም:: ስለዚህ ቋንቋውን እንደምናስተምርበት ዓላማ ተስማሚውን የማስተማሪያ ዘዴ እየመረጡ አስፈላጊም ሲሆን እየቀየጡ ማስተማሩ፣አንድ ዘዴ ብቻውን ከሚያመጣው ውጤት የተሻለ

መሆኑን ምሁራን ያስገነዝባሉ:: ለምሣሌ ዴቪስ (1985) ይህንን ሐሳብ ከሚሰነዝሩ ምሁራን አንዱ ናቸው::

ለማጠቃለል በት/ቤት ቋንቋን ማስተማር ሰፊ ዝግጅትና መስተጋብርን የሚጠይቅ ክንውን ነው:: ዝግጅቱ በሙያው የሰለጠነ መምህርን፣ ሲለበስን፣ መማሪያ መጽሐፍን፣ የመርጃ መሣሪያን፣ ድጋፍ ሰጪ አካልን፣ የተወሰነ ጊዜና ቦታን ወዘተ .ሲያጠቃልል መስተጋብሩ ደግሞ መምህሩ ከተማሪዎች ጋር እና ተማሪዎች እርስ በርሳቸው በሚያደርጉት ግንኙነት ይገለጣል:: ከዚህም በላይ ቋንቋን በቀለጠፈ መንገድ ለማስተማር ከሚረዱ ዘዴዎች ውስጥ የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ተስማሚና አመቺ የሆኑ ዘዴዎችን እየመረጡና እየቀላቀሉ መጠቀሙ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ያግዛል ::

## 2.1.2. ቋንቋን መፈተን

ካሮልን (1968: 46) በመጥቀስ ባችማን (1990) ፈተናን ሲበይኑ " ስነልቦናዊ ወይም ትምህርታዊ ፈተና የአንድን ግለሰብ የተወሰነ ባህሪ ለማወቅ ስርዓት ባለው መንገድ የሚዘጋጅ ሂደት ነው:: " ይሉና የራሳቸውን ብያኔ በማከል የሚከተለውን ይላሉ:: ፈተና አንድ የመመዘኛ መሣሪያ ሆኖ የትምህርቱን ሂደት ግብ መምታት በአሃዝ በተደገፈ መረጃ የሚያመለክት ነው :: ይሁን እንጂ የሚሰጠው መረጃ ፍፁም ምሉዕ አይደለም:: እንዲሆንም አይጠበቅም:: ፈተናን ከሌሎች የመመዘኛ መሣሪያዎች የሚለየውም የተወሰነ ናሙናዊ ባህሪን ለመለካት ተብሎ መዘጋጀቱ ነው:: (ባችማን፣1990:20 –21)

እንደሌሎች የትምህርት ዓይነት ፈተናዎች ሁሉ የቋንቋ ፈተናዎችም ቀዳሚ ተግባር የተማሪውን የቋንቋ ችሎታ ለመመዘን በመሣሪያነት ማገልገል ነው:: (አለር ፣1979 ና ሂዩዝ ፣1989) ቋንቋን በማስተማር የታዩት ልዩ ለዩ ዘዴዎች በሲለበሶችና በመማሪያ መጻህፍት አዘገጃጀት ላይ ካሳደሩት ተጽእኖ በተጨማሪ በቋንቋ አፈታተን ዘዴዎችም ላይ ተጽእኖ አሳድረዋል:: በዚህም የተነሳ ቋንቋን መፈተን የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችን እንዳሳለፈ በምሁራኑ መካከል የጋራ ስምምነት አለ:: ሆኖም በእድገት ደረጃዎች ቁጥር ክፍፍልና ስያሜ አሰጣጥ ግን ምሁራኑ ይለያያሉ:: ለምሣሌ ስፓልስኪ (1976 ) የዕድገት ደረጃዎቹን በሶስት በመክፈል የራሳቸውን ስያሜ ሲሰጡ ማድሰን ( 1983) በበኩላቸው የዕድገት ደረጃዎችን በሶስት ከፍለው ከስፓልስኪ የተለየ ስያሜን ይጠቀማሉ:: ይሁን እንጂ ለዚህ ጽሁፍ በመነሻነት እንዲያገለግል የተመረጠው የሂተን (1988) ክፍፍል ነው:: ለዚህም ምክንያቱ ክፍፍሉ የበርካታ ምሁራንን ሀሳብ አጠቃሎ ስለሚይዝ ነው::

ሂተን (1988) የቋንቋን ፈተና የዕድገት ደረጃዎች ወይም ዘዴዎች እንደሚከተለው በአራት ይከፍሏቸዋል ።

1. ድርሰት ወትርጉም ዘዴ ( the Ess ay Translation approach)

2. መዋቅራዊ ዘዴ (the Structuralist approach)

3. ውህዳዊ ዘዴ (the Integrative approach)

4. ተግባቦታዊ ዘዴ ( the communicative approach) ( ሂተን ፣1988:15)

እነዚህ የዕድገት ደረጃዎች በጊዜ ቅደም ተከተል የተሰደሩ ቢሆኑም አንደኛው ዘዴ ከሌላው ዘዴ ጋር ፈፅሞ በማይገናኝ ድንበር የተከለሉ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ግን ሂተን ያስረዳሉ። እያንዳንዱን ዘዴም በጣም ባጭሩ እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞከራል።

1. ድርሰት ወ ትርጉም ዘዴ-ይህ በብዙ ምሁራን ዘንድ ቅድመ ሳይንሳዊ የፈተና ዘዴ በመባል ይታወቃል። በሰለጠነ የፈተና ባለሙያ አለመዘጋጀቱና ለመምህሩ ሕሊናዊ ዳኝነት ( Subjective judgement ) ከፍተኛ ቦታ መስጠቱ ዓይነተኛ ባሕሪው ሲሆን በአብዛኛው ለፈተና የሚቀርቡትም ጥያቄዎች ድርሰት መጻፍ ፣መተርጎምና የሰዋሰው ትንተና ናቸው ። (ገጽ፣15)

2. መዋቅራዊ ዘዴ:- ይህ በአብዛኞቹ ምሁራን ዘንድ ሳይንሳዊ የፈተና ዘዴ በመባል ይታወቃል። በሰለጠነ የፈተና ባለሙያ መዘጋጀቱ ፣ ከመምህሩ ሕሊናዊ ዳኝነት ይልቅ ሰፋ ያለ ናሙና ለማቅረብ በሚያመች ኦብጀክቲቭ (Objective) ጥያቄዎች ላይ ማተኮሩ ፣የቋንቋውን ክፍሎችና ክሂሎች እየነጠለና ከአውዳቸው እያፋታ ማቅረቡ እንዲሁም ለህያውነት ( Reliability) ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱ ዓይነተኛ ባሕሪዎቹ ናቸው። (ገጽ16)

3. ውህዳዊ ዘዴ :-ይህ መዋቅራዊ ዘዴ የቋንቋን ክፍሎችና ክሂሎች እየነጠለና ከአውዳቸው እያፋታ ማቅረቡን በመቃወም የተፈጠረ ዘዴ ነው። ትኩረቱ ለፍቺና ለአጠቃለዩ የንግግር (discourse) ውጤት ነው። የቋንቋውን ክፍሎችና ክሂሎች

ሳይነጣጥል በውሕደት ማቅረቡና ሁልጊዜም ጥያቄዎቹን እውዳዊ ማድረጉ ዓይነተኛ ባህሪዎቹ ናቸው ። (ገጽ 16-18)

4. ተግባቦታዊ ዘዴ ፦ ይህ አንዳንድ ጊዜ ከውህዳዊ ዘዴ ጋር ይዛመዳል። በተለይ ሁለቱም ዘዴዎች ከቅርጽና ከመዋቅር ይልቅ ለአጠቃላዩ የንግግር ውጤትና ፍች ትኩረት ስለሚሰጡ ይመሳሰላሉ። ይሁን እንጂ የተግባቦታዊ ፈተና ዘዴ የቅድሚያ ትኩረት ተፈታኙ ቋንቋውንበተግባቦት ውስጥ እንዴት እንደሚጠቀምበት መመርመር ነው። ይህም ከውህዳዊ ዘዴ ይለየዋል። ቋንቋውን ለማስተማር ለተፈለገበት ዓላማና ለተማሪዎች ፍላጎት ከፍተኛ ግምት መስጠቱ፣ የፈተናው ተግባራት ከዕለት ተዕለት የመግባቢያ ቋንቋ ጋር በእጅጉ መዛመዳቸውና መቀናጀታቸው የዘዴው ዓይነተኛ ባህሪዎች ሊባሉ ይችላሉ። (ገጽ 18-19)

እንደ ሂዩዝ (1989) እምነት ጥሩ ፈተና ወይም የፈተና ዘዴ የሚባል የለም። ምክንያቱም አንድ ፈተና ወይም የፈተና ዘዴ ለአንድ ዓላማ በጣም ጠቃሚና ጥሩ ሆኖ ሲገኝ በአንፃሩ ያው ፈተና ወይም የፈተና ዘዴ ለሌላ ዓላማና ሁኔታ ጥሩ ላይሆን ይችላል። ስለዚህ ፈተና ስናዘጋጅ ተስማሚ ሆነው የምናገኛቸውን የፈተና ዘዴዎች ሁሉ መጠቀሙ ተገቢም ተመራጭነትም ያለውም ነው። ይህም ማለት ከተግባቦታዊ፣ ከውህዳዊ፣ ከመዋቅራዊና ከሰዋስው ወትርጉም ዘዴ ጠቃሚ የሆኑትን እየመረጥንና እየቀላቀልን መጠቀሙ አስፈላጊ ነው ማለት ነው። ( ሂተን ፣1988)

በጥቅሉ ለማስተማር ዘዴያችን የምንጠበበውን ያህል ለአፈታተን ዘዴያችንም መጠበብ ይኖርብናል። ቋንቋን መፈተን ዛሬ ሰፊ ጥናትና ምርምር እየተደረገበት የሚገኝ የሙያ ዘርፍ መሆኑ ለሙያው የተሰጠውን ትኩረት የሚያስገነዝብ ነው። በተለይ ከ1970ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ከተግባራዊ ስነልሳንና ከስነልቦና ጋር በመተባበር የተጻፉት አያሌ የቋንቋ ፈተና መጻህፍት፣ በየጊዜው የሚታተሙት ጆርናሎች፣ የጥናትና የምርምር ጽሁፎች፣ የሰሚናር ወረቀቶች፣ ወዘተ. ለመስኩ የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት የሚያመለክቱ ናቸው ።

## 2.2 የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች

የቋንቋ ፈተናዎች ቢያንስ በሚሰጡት መጠነኛ መረጃና በሚዘጋጁበት ዓላማ የተነሣ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች ብዛት ከፀሐፊ ፀሐፊ ቢለያይም አብዛኞቹ ምሁራን በአራት ይከፍሏቸዋል። እነሱም " የችሎታ መለኪያ ፈተና (achievement test)፣ የብቃት መለኪያ ፈተና ( proficiency test) የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና ( diagonstic test ) እና የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና

(Aptitude test) ናቸው:: ሂተን ፤1975፤ ሂዩዝ፡1989፤ሃሪስን ፤1983 ይህንን ክፍፍል ከሚደግፉ ምሁራን ጥቂቶቹ ናቸው:: የሌሎች ምሁራን ክፍፍልም ቢሆን አንደኛውን በሌላው ውስጥ የማካተት ወይም የመዘርዘር እንጂ መሠረታዊ ልዩነት አይታይበትም::

ይህ ጥናት ሁሉንም የቋንቋ ፈተና አይነቶች በዝርዝር አይመለከትም :: ይሁን እንጂ ከጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ጋር የሚዛመዱትን በዝርዝር ሌሎችን ደግሞ በጥቅል ለመመልከት ይሞከራል ::

## 2.2.1. የችሎታ መለኪያ ፈተና / Achievement test /

### 2.2.1.1 ብያኔ

በርካታ ምሁራን የችሎታ መለኪያ ፈተናን በተመሳሳይ መንገድ በይነውታል:: የሂተንን (1975) ብያኔ መጥቀሱ ብቻ በቂ ይሆናል:: "ብዙዎቹ በየዓመቱ የሚሰጡ የት/ቤት ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ ፈተናን ቅርፅ ይወስዳሉ:: እንዲሁም ማንኛውም የተወሰነ የትምህርት ዝርዝር መዳበሩን ወይም መጠናቀቁን ለማወቅ በብሔራዊ ደረጃ የሚሰጡ ፈተናዎቹ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ናቸው::" (ሂተን፤1975 ፡153)

በብያኔያችንም መሠረት የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተናዎች (ካሁን በኃላ ሁ.ደ.መ.አ.ፈ.) የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ናቸው:: ለዚህ በርካታ ማስረጃዎች ማቅረብ ቢቻልም ጽ/ቤቱ ያወጣውን የመመሪያ መጽሐፍ (ሀንድ ቡክ) መመልከቱ ብቻ በቂ ነው:: "የችሎታ መለኪያ ፈተና በአንድ የተወሰነ ደረጃ የሚሰጥን ትምህርት ወይም የስልጠና ተግባር ላጠናቀቁ ተማሪዎች የሚዘጋጅ የመመዘኛ ፈተና ነው:: በዚህም መሠረት የኢ.ሁ.ደ.መ.ፈ የዚህ ፈተና ዓይነት አካል ነው::" (ሁ.ደ.መ.ፈ. ጽ/ቤት ፤1985 :7)

ጽ/ቤቱ ካወጣው የመመሪያ መጽሐፍ ሳንወጣ የፈተናዎችን ዓላማ ፤ፈተናው የሚመሰረትበትንና የሚያቅፋቸውን የትምህርት ዓይነቶች እንዲሁም አዘገጃጀቱን ለመመልከት እንሞክራለን ::

የሁ.ደ.መ.ፈ ሌሎቹ ጉዳዮችን ጨምሮ ስድስት ዋና ዋና ተግባራትን ያከናውናል :: እነሱም የሚከተሉት ናቸው::

1ኛ. የከፍተኛ ሁለተኛደረጃ ትምህርትን ለሚያጠናቅቁ ተማሪዎች በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች አማካኝነት የዕውቀትና የክሂሎት ደረጃቸውን በመመዘን መረጃ ወይም ሰርተፊኬት መስጠት ፤

2ኛ. የተማሪዎችን ደረጃ በማውጣት ወደ ድኅረ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋሞች የሚገቡ ተማሪዎችን ማወዳደር፣

3ኛ. የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችና ወኪሎቻቸው ጀማሪ ተማሪዎቻቸውን በተወሰነ ቦታ ለመመደብ የሚያደርጉትን መረጣ ለመርዳት፣

4ኛ. በአንድ ት/ቤት ውስጥም ሆነ በሁሉም ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል የተመሳሰለ የትምህርት አሰጣጥ እንዲኖር ማገዝ፣

5ኛ. መምህራንና የትምህርት አስተዳደር ባለሙያዎች ለሥርዓተ ትምህርቱ ታማኝ እንዲሆኑና የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዲያሻሽሉ መርዳት ፤

6ኛ. አጠቃላይ የትምህርት አሰጣጡን መገምገም ፤ በተለይም ደግሞ በከ/2ኛደረጃ ት/ ቤቶች በጊዜና በቦታ ተመጥኖ ለሚሰጠው ትምህርት ምዘናዊ ውሳኔን ማሳለፍ ። (ገጽ፤11)

ፈተናው የሚመሠረትበትንና የሚይዛቸውን የትምህርት ዓይነቶች በተመለከተ የሚከተለውን እናገኛለን ።

የሁ.ደ.መ.ፈ የሚመሠረተው በከ/2ኛደረጃ ት/ቤት (ከ9ኛ–12ኛ) ባለው የትምህርት ሚኒስቴር ስርዓተ ትምህርት ላይ ነው። ከ1977 እስከ ዛሬ (1986) የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች አማርኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ግዕዝ፣ ፈረንሳይኛ፣ ሂሳብ፣ ኮመርሻል ሂሳብ፣ ፊዚክስ፣ ኬምስትሪ ፣ጄኔራል ሳይንስ፣ ባይሎጂ፣ ጆግራፊ፣ ታሪክ፣ ኢኮኖሚክስና ቡክኪቢንግ ናቸው ። እስከ 1978 ድረስ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከሂሳብና ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ፈተና ጋር እንደ ዋና ትምህርት (Compulsory subject ) ይቆጠር ነበር። ከ1978 በኋላ ግን የአማርኛ ፈተና እንደዋና ትምህርት መቆጠሩ ቀርቷል። (ገጽ፤12)

የፈተናውን አዘገጃጀት በሚመለከት ደግሞ የሚከተለውን እናገኛለን። የፈተናው አመራር ለዩኒቨርስቲው በኃላፊነት ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በየትምህርት ዓይነቱ በቂ ችሎታና ልምድ ያላቸው ሰዎች ከዩኒቨርስቲው የተለያዩ ፋኩልቲዎች ተመርጠው

ፈተናውን ያዘጋጃሉ ። ፈተናውን የሚያዘጋጀው ከአንድ ሰው በላይ በሚሆንበት ጊዜ ዋናው አዘጋጅ ማን እንደሆነ ተለይቶ ይታወቃል ። ጽ/ቤቱ በሙያው ልምድ ያላቸውን አዘጋጆች ለበርካታ ዓመታት እንዲያገለግሉት ጥረት ያደርጋል ። የሁሉንም ፈተና አዘጋጆች ስም ደግሞ በሚስጢር ይይዛል ወይም እንዳይታወቅ ያደርጋል ። (ገጽ፤13)

### 2.2.1.2. የፈተናው ይዘት መሠረቶች

የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ይዘት ቀጥተኛ ተዛምዶን በተመለከተ በመስኩ ምሁራን መካከል የአመለካከት ልዩነት አለ ። ይኸውም አንዳንድ ምሁራን ለምሣሌ ሂተን (1975)፣ሃሪሰን(1983) እና ማድሰን (1983) ተዛምዶው ከዝርዝር የሲለበሱ ይዘትና ከመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘት ጋር መሆን አለበት ይላሉ። በአንፃሩ እንደ ሂዩዝ (1989) እና ባችማን (1990) እምነት ተዛምዶው ከትምህርቱ ዓላማ ጋር መሆን አለበት። ሂተን የ1975 እምነታቸውን በ1990 መጽሐፍቸው ለውጠው በእነሂዩዝ ሀሳብ ይስማማሉ ።

እንደ ሂዩዝ (1989) እምነት የፈተናው ይዘት በዝርዝር ሲለበሱና የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘት ላይ መመስረቱ ቢያንስ ተማሪው ምን ተማረ? ምንስ አወቀ የሚለውን ለመመዘን ጥሩ ቢሆንም ዘዴው አንድ ደካማ ጎን አለው። ይኸውም ሲለበሱ ወይም መማሪያ መጻሕፍቱ በጥሩ ሁኔታ ካልተዘጋጁ ከፈተናው የሚገኘው ውጤት ወደተፈለገው ግብ የማያደርስ እንዲያውም ወደ ተሳሳተ መደምደሚያ የሚያመራ ይሆናል። በሌላ አገላለጽ ፈተናውን በጥሩ ውጤት ማለፍ የትምህርቱን ዓላማ ጠንቅቆ ማወቅን ላያመለክት ይችላል። (ሂዩዝ ፣1989:11).

ስለዚህ የፈተናውን ይዘት በሲለበሱና መማሪያ መጻሕፍቱ ይዘት ላይ ከመመስረትይልቅ በትምህርቱ ዓላማ ላይ መመስረቱ ተገቢና ጠቀሜታ ያለው ነው። ከበርካታ ጠቀሜታዎቹም መካከል አላማ ነዳፊውን ግልፅ አላማ እንዲነድፍ የግድ ማለቱና የፈተናዎቹ ክንዋኔዎች (performance ) ተማሪው ምን ያህል የትምህርቱን ዓላማ እንዳወቀ መመዘናቸው የሚጠቀሱ ናቸው። (ገጽ 11-12)

ሂዩዝ ን (1989) በዋቢነት በመጥቀስ ደጀኔ (1990) እንደሚያስረዱት የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን ይዘት በዓላማው ላይ መመስረቱ በርካታ ጠቀሜታዎች ቢኖሩትም ዘዴውን ሁል ጊዜ እንከተል ብንል ግን ችግርም ያጋጥመናል ይላሉ። ለዚህም በአስረጅነት የሚጠቀሱት የእንግሊዝኛን ቋንቋ በኢትዮጵያ ከፍተኛ 2ኛ

ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ለማስተማር የተነደፉት ዓላማዎች እጅግ ጥቅልና ግልጽ ያለመሆናቸውን ነው፡፡ በዚህም የተነሣ የእንግሊዝኛን ቋንቋ ፈተና ይዘት በትምህርቱ ዓላማ ለመመስረት አስቸጋሪነቱን ገልጸው በምትኩ የፈተናውን ይዘት በመማሪያ መጻህፍቱ ይዘት ላይ መመስረቱ ተገቢ መሆኑን ይመሰክራሉ፡፡ (ደጀኔ ፣1990 :59)

በአጠቃላይ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪው ምንተምሮ ምን እንዳወቀ ለመመዘን የሚዘጋጁ በመሆናቸው ግልፅ የሆነ ዓላማ ለተነደፈላቸው የቋንቋ ትምህርቶች የፈተናውን ይዘቶች በዓላማዎች መመስረት ያስፈልጋል ፡፡ የትምህርት ዓላማቸው በእጅጉ ጥቅልና ኢግልፅ ለሆኑት ደግሞ የፈተናውን ይዘቶች በሲለበሶችና በመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘቶች ላይ መመሥረቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ከቶውንም ግን ሂልናዱቢን (1981 :135) እንዳሉት የችሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት ከትምህርቱ አላማ ወይም ከሲለበሶቹና ከመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘት ውጭ መሆን አይኖርበትም፡፡

### 2.2.1.3 ናሙና /Sampling /

እንደ ሂተን (1990:14) እምነት ከሌሎች የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች ይልቅ በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ውስጥ ምን ማካተት እንዳለብን መወሰን ያዳግታል፡፡ ይህም ያለምክንያት አይደለም፡፡ ፈተናው ተማሪው ለረጅም ጊዜ ሲማረው የቆየውንና ይማረዋል ተብሎ የሚገመተውን እንዲመዝን ስለሚጠበቅ በምናቀርባቸው ጥያቄዎች ውስጥ የትምህርቱን ወካይ ናሙናዎች በብርቱ ጥንቃቄ መርጦ ማካተት ስለሚያስፈልግ ነው፡፡

በተመሳሳይ አገላለጽ ላዶ (1961)፣ዴቪስ (1977)፣ ማድሰን (1983)ና ባችማን (1990) እንደሚሉት የፈተናውን ናሙናዎች ስንመርጥ ትምህርቱ ለየክሂሎቹና ዘርፎች የሰጠውን ትኩረት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል፡፡ በሌላ አገላለጽ በትምህርቱ ሂደት ለየክሂሎችና ዘርፎቹ የተሰጠውን ትኩረት በሚመጥን መልኩ ጥያቄዎችን መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ጥያቄዎቹ ወካይ ናሙና እንዲሆኑ ይረዳል፡፡

በአጠቃላይ በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ውስጥ የናሙና አወሳሰድ ብርቱ ጥንቃቄን ይጠይቃል፡፡ ሁሉንም የትምህርት ይዘቶች ለፈተና ማቅረብ ባይቻልም በተቻለ መጠን ባዛ ያሉ ጥያቄዎች በማቅረብ የትምህርት ይዘቶችን ለማዳሰስ መጣር አስፈላጊ ነው፡፡ የጥያቄዎቹ መብዛት ብቻ ሳይሆን ጥያቄው ለትምህርቱ ወካይ ናሙና መሆኑንም ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ ከፈተና አዘጋጆች የሚጠበቅ

ኃላፊነት አለ:: ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ በታላቅ ትዕግስት የትምህርቱን ዓላማ ፣የመማሪያ መጻሕፍቱንና የሲለበሰቹን ይዘቶች በውል መመርመር ያስፈልጋል:: ቀጥሎም የሚፈትኑበትን አላማ ተረድቶ የመረመሯቸውን ይዘቶቸ ወደ ጥያቄ ለመለወጥ ሰፋ ያለ ጊዜ መውሰድ ያስፈልጋል:: በመጨረሻም ጥያቄዎቹ የትምህርቱ ወካይ ናሙናዎች ለመሆናቸው ሳይሰለቹ፣ እየደጋገሙ መመልከትና አስፈላጊም ሲሆን ከሙያ ባልደረቦች ጋር መመካከር ያሻል:: (ሃሪሰን፣1983:137).

## 2.2.1.4 የጥያቄ አቀራረብ ስልት

ለአንድ አይነት ፈተና ብቸኛው የጥያቄ አቀራረብ ስልት ይህ ነው ብሎ ለመናገር ያዳግታል :: ይሁን እንጂ በተወሰነ ሁኔት ውስጥ አንደኛው የጥያቄ አቀራረብ ስልት ከሌላው የተሻለ ሰለሚሆን ምርጫችንን መወሰን ተገቢ ነው:: (ዴቪስ፣1984 እና አጉኒ ፣1990)

በፈተናዎቻችን ውስጥ የምንከተለውን የጥያቄ አቀራረብ ስልት ለመወሰን በቅድሚያ የቋንቋ ፈተናዎች የሚቀርቡበትን የአጠያየቅ ስልት ከነጠቀሜታቸውና ጉዳታቸው ማወቅን ይጠይቃል:: ቀጥሎም ለጥሩ የችሎታ መለኪያ ፈተና ከሁሉም የጥያቄ አቀራረብ ስልቶች ተስማሚው እየተመረጠና እየተቀላቀለ ቢቀርብ ጠቃሚ መሆኑን መረዳት ያሻል:: በመጨረሻም የፈተናውን የጥያቄ አቀራረብ ለመወሰን የፈተናው አስተማማኝነት ፣ህያውነትና ተተግባሪነት ከግምት ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ያስፈልጋል:: (ዊር፣1988:2)

ግሪን (1963) እንደሚያስረዱት ዋና ዋናዎቹ የጥያቄ አቀራረብ ስልቶች ኦብጀክቲቪ (Objective) ቃላዊ (Oral)፣ ድርሰታዊ (Subjective) እና ተግባራዊ (Functional) ናቸው:: ይሁን እንጂ ሂተን (1975) እንደሚገልጹት ብዙ የቋንቋ ፈተናዎቸ የሚጠቀሙበት የጥያቄ አቀራረብ ስልት ኦብጀክቲቭ የተባለውን ነው:: ከኦብጀክቲቭ ውስጥ ደግሞ ምርጫ ሰጭ (Multipile choice ) በጣም የተለመደ ነው::

ኦብጀክቲቭ የጥያቄ አቀራረብ ስልት ምርጫ ሰጭ፣ እውነት/ውሸት፣ አዛምድ፣ ክፍት ቦታ ሙላ እና አጭር መልስ የሚሹ (Short answer) ጥያቄዎችን እንደሚያጠቃልል ማድሰን (1983) ያስገነዝባሉ ::

ለምርጫ ሰጭ ጥያቄ አማራጭ (Options) የሚሆኑ መልሶችን አራት ወይም አምስት ማድረጉ ይመረጣል:: ለአቀራረብ ስልቱ አንደ መርህ የሚቆጠሩት ነጥቦች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው ::

1. እያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ መያዙን አረጋግጥ::

2. ጥያቄዎቹ በተቻለ መጠን አጭርና ግልጽ እንዲሆኑ አድርግ::

3. አሳሳቾች (Distracrors ) ትክክለኛ መልስ የመምሰል ተአማኒነታቸውን አረጋግጥ::

4. ከአማራጮች ውስጥ ሆን ተብሎ የገባና ትክክለኛውን መልስ የሚጠቁም ፍንጭ አለመኖሩን አረጋግጥ ::

5. ጥያቄዎቹ ከቀላል ወደከባድ የሚሄዱ መሆናቸውን አረጋግጥ ::

6. ሁሉም መልስ አይደሉም ወይም ናቸው የሚለውን አማራጭ አስወግድ :: (ሂተን ፣ 1975 :30 ና ትሮንዳይክና ሄገን ፣1977 :222-24).

ምርጫ ሰጭ የጥያቄ አቀራረብ በብዛት የተለመደ ቢሆንም ዘዴው ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት:: አብዛኞቹ ምሁራን ጠንካራ ጎን የሚሉዋቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው::

1. ህያውና አፋጣኝ በሆነ ስልት ሊታረም መቻሉ ፣

2. ያለማስመሰልና መዘላበድ በፍጥነት ለመመለስ አመቺ መሆኑ፣

3. በርካታ ተፈታኞችን በአንድ ጊዜ ለመፈተን ማስቻሉ፣

4. በስታስቲካዊ ስሌት ውጤቶችን ለመተንተን አመቺ መሆኑ ፣

5. ብዙ ጥያቄዎችን ለማቅረብ ማስቻሉ፣ (ጆን፣1973፤ ሂተን፣1975ና ሂዩዝ ፣1989)

የምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች ደካማ ጎኖች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው::

1. የሚፈትነው በማስታወስ ላይ የተመሰረቱ ዕውቀቶችን ብቻ መሆኑ ወይም የሀሳብ አቀነጃጀት ችሎታን አለመመዘኑ ፤

2. ምን መፈተን እንዳለብን በእጅጉ የሚገደብ መሆኑ ፣

3. ግመታን ስለሚያደፋር የፈተናውን ውጤት መሠረት በማድረግ የተማሪውን ዕውቀት ለመለካት ሳንካ መፍጠሩ፣

4. ጥሩ ጥያቄዎችን ለመጻፍ አስቸጋሪና አድካሚ መሆኑ ፣

5. በክዋሹ ጎጅ ሊሆን መቻሉ፣

6. ለመኮራረጅ በር ከፋች መሆኑ ፣ (ሂዮዝ፣1989 እና ጆን፣1973)

እንደ ሂዩዝ (1989 :60) እምነት የምርጫ ሰጭ የጥያቄ አቀራረብ አንዳንድ ጠቀሜታዎች ቢኖሩትም ዛሬ ቋንቋን ለመፈተን በተደረሰበት የዕድገት ደረጃ ግን ጉዳቱ ያመዝናል። ይህ ማለት ግን በፈተናዎቻችን ውስጥ የምርጫ ሰጭ ጥያቄዎችን መጠቀም የለብንም ማለት አይደለም። ይልቁንም የዘዴውን ጎጂ ጎን ተገንዝቦ በአግባቡ መጠቀም እንድንችል ለማሳሰብ ነው ። ስለዚህ ዋናው ጉዳይ የፈተናው አቀራረብ ስልት አብጀክቲቭ ወይም ድርሰት ነክ መሆኑ ሳይሆን ለሚዘጋጀው ፈተና የትኛው የጥያቄ አቀራረብ ስልት እንደሚስማማው መምረጡ ላይ ነው ። ጥሩ የችሎታ መለኪያ ፈተና ደግሞ የተለያዩ የጥያቄ አቀራረብ ስልቶችን እንዲያካትት ይጠበቃል ።

## 2.2.1.5. የአዘገጃጀት ዝርዝር መርሆዎች

በዚህ ክፍል የሚቀርቡት ነጥቦች ማንኛውንም የቋንቋ ፈተና ዓይነት ለማዘጋጀት ሊረዱ ይችላሉ። ይሁን እንጂ አብዛኞች ነጥቦች በጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግ ተሞክሯል። እያንዳንዱ ነጥብ የተወሰደበትን ምንጭ በተደጋጋሚ ከመጥቀስ ይልቅ ብዙዎቹ ነጥቦች የተወሰዱባቸውን ምንጮች መጥቀሱ ተመርጧል። ዝርዝር መርሆዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

- ለምን እንደምትፈትን እወቅ ወይም የምትፈትንበትን ዓላማ እወቅ።
  ይህ መርህ የትምህርቱን ዓላማ ጠንቅቆ በመረዳት አንድ ፈተና አዘጋጅ ምን ለመፈተን እንደፈለገ ግልጽ የሆነ ዓላማ እንዲኖረው የሚጠይቅ ነው። በዚህም ፈተናው ጠቃሚ ችሎታዎችን እንዲመዝን ይጠበቃል።

- የፈተናው መመሪያዎች ግልጽ ፣አጭርና ቀላል መሆናቸውን አረጋግጥ::

- ፈተናው በተስማሚ የጥያቄ አቀራረብ ስልት መዘጋጀቱን አረጋግጥ ::

- ሰፋ ያለና ወካይ ናሙና አቅርብ ::

  ሰፋ ያለ ናሙናለማቅረብ በርከት ያሉ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ጠቃሚ ነው ጥያቄዎቹ ወካይ ናሙና እንዲሆኑ ለማድረግ ደግሞ ጠቅላላ ፈተናውን ለዓላማናይዘት ከፋፍሎ ከየይዘቱ ተመጣጣኝ የሆነ ቁጥር መውሰድ አስፈላጊ ነው ::

- በፈተናው ውስጥ አላስፈላጊ ወገናዊነትን (Bias) የሚያሳዩ ጥያቄዎችን አስወግድ::

  ይህ መርህ በፈተናዎቻችን ውስጥ የጾታ ፣የባህል ፣የእምነት ወዘተ . ወገናዊነትን እንድናስወግድ የሚጠይቅ ነው:: ለምሣሌ ለአጠቃላይ ተግባቦታዊ ፈተና በሚዘጋጁ የቃላት ጥያቄዎች ውስጥ ሙያ ነክ ወይም ዘዬ ቃላትን ብናቀርብ ለተወሰኑ ተፈታኞች አድሎአዊነት ስለሚኖራቸው ተቀባይነት የላቸውም::

- ፈተናውን ለማዘጋጀት ሰፊ ጊዜና ትዕግስት ይኑርህ::
- ፈተናው በምርጫ ሰጭ የጥያቄ አቀራረብ ስልት የሚቀርብ ከሆነ አንድ ትክክለኛመልስ ብቻ መኖሩን አረጋግጥ::

- የፈተናው ባክዋሽ ጠቃሚ እንዲሆን ጣር:: ይህ መርህ በተቻለ መጠን ፈተናው ለጥሩ ማስተማር ድጋፍ እንዲሰጥ መጥፎ ማስተማርን ደግሞ እንዲያስተካክል የሚጠይቅ ነው:: (ሪቨርስ ፣1968፣ትሮንዳይክና ሄግን ፣1977 ፣ሂዩዝ ፣1989፣ ማድሰን ፣1983 እና ደጀኔ፣ 1994)

### 2.2.2 ብቃትን መለኪያ ፈተና (Proficiency test)

ይህ ምንም ስልጠና ወይም ትምህርት ከመቅረቡ በፊት የተማሪውን ብቃት ወይም ችሎታ ለመመዘን የሚቀርብ ፈተና ነው:: ስለሆነም የፈተናው ይዘት በትምህርቱ ዓላማ ወይም ይዘት ላይ የተመሠረተ አይደለም:: ይልቁንም ተፈታኞች በዚያ ቋንቋ

ለመገልገል ብቁ መሆን አለመሆናቸውን በሚያረጋግጡ መመዘኛዎች ላይ ይመሰረታል። (ሂዩዝ፣1989:9)

ይህ ፈተና ጥያቄዎችን ለመምረጥ የሚያግዙ ናሙናዎችን ለማግኘት የሚያስችል የተነደፈ ሲለበስ የለውም። ወይም ተፈታኙ ቀደም ሲል በተማረው ትምህርት ላይ የተመሰረተ አይደለም። ይሁን እንጂ የፈተናው ሲለበስ ከፈተና አዘጋጁ አእምሮታዊ ክሂሎት በመመንጨት ተማሪው በዚያ ቋንቋ ለመገልገል ወይም የተወሰነ የትምህርት ደረጃን ለመከታተል ያለው ብቃት ይመዘንበታል። ከቋንቋ ፈተና ወጣ ብንል የመንጃ ፍቃድ ፈተና ጥሩ ምሣሌ ይሆነናል። ምክንያቱም በመንጃ ፍቃድ ፈተና የሁሉም ተፈታኞች ዳራ አንድ ይሁን ወይም ይለያይ የሚለካው ነገር ብቃት ብቻ ነውና። (ባችማን ፣1990:46)

በአጠቃላይ ከላይ ከጠቀስናቸው ምሁራንና ከሌሎች እንደምንገነዘበው ብቃትን የመለኪያ ፈተና ተማሪው ቀደም ሲል በተማረው ትምህርት ላይ አይመሰረትም። በምትኩ ፈተናው መሠረት የሚያደርገው የቋንቋን ብቃት ንድፈሀሳብና በዚህ የፈተና ዓይነት መመዘን የሚገባቸውን ችሎታዎች ነው። በሌላ አገላለጽ ለዚህ ፈተና መሠረት የሚሆነው ቀደሞ የተሰጠ ትምህርት ሳይሆን ለአንድ ለተወሰነ ደረጃ ይገባል ወይም ያስፈልጋል ተብሎ የተወሰደ የደረጃ ግምት ነው። ከታወቁት የዚህ ፈተና ምሣሌዎችም መካከል "እንግሊዝኛን እንደውጭ ቋንቋ መፈተን " (TOEFL) አይነተኛ ምሣሌ ይሆነናል።

### 2.2.3 ጥንካሬና ድክመትን መለኪያ ፈተና /Diagonstic test /.

የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተናዎች ከችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ጋር በእጅጉ ይመሳሰላሉ ። የሚለዩበት አንድ መንገድ ቢኖር አላማቸው በቋንቋው ውስጥ በተወሰኑ የቋንቋው ክሂሎች ወይም ንጥረ ነገሮች (elements)ተማሪው ያለበትን ድክመትና ጥንካሬ ለመመርመር የታቀዱ መሆናቸው ነው ። (ላዶ ፣1961:369).

በተመሳሳይ አገላለጽ ሂተን (1975 :163) እና ሂዩዝ (1989:13) እንደሚያስረዱት የዚህ ፈተና የቅድሚያ ትኩረት የተማሪውን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ተጨማሪ ትምህርት የሚያስፈልግበትን የቋንቋ ክሂልና ክፍል ማሰስ ነው። በዚህ የቅድሚያ ትኩረቱ ከችሎታ መለኪያ ፈተና ሲለይ በአብዛኛው ባህሪው ግን ከችሎታ መለኪያ ፈተና ጋር ይመሳሰላል ።

### 2.2.4 ቅድመ ችሎታን መለኪያ ፈተና /Aptitude Test/

ይህ ፈተና ተማሪዎች ገና ለመማር ያልጀመሩትን የውጭ ቋንቋ ለመማር ሊኖራቸው የሚችል ተፈጥሯዊ ችሎታ መኖር አለመኖሩን የሚመዝን ነው። ቋንቋን የመማር ቅድመ ችሎታ (Language learning aptitude) የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በእጅጉ ውስብስብ ነው። ጽንስ ሐሳቡ እንደ ኢንተለጀንስ ፣ ዕድሜ ፣መቀስቀስ (Motivation) ፣ ማስታወስ ወዘተ. ጉዳዬችን ያካትታል። ለእነዚህ ጉዳዩች የሚሰጠው ክብደትና ቅለት ከግለሰብ ግለሰብ መለያየቱ ደግሞ ነገሩን በእጅጉ ውስብስብ ያደርገዋል። ስለዚህ እንደ ብዙ የቋንቋ ፈተና ባለሙያዎች እምነት በቋንቋ ቅድመ ችሎታን ለመመዘን እንድም አይቻልም ወይም ማዘጋጀቱ አስፈላጊ አይደለም። (ሂተን ፣1988:173)

## 2.3. የጥሩ ፈተና ባህርያት ወይም መስፈርቶች

ፈተናዎች ጥሩ የመመዘኛ መሣሪያ እንዲሆኑ በውል ልናዘጋጃቸው ይገባል። ለዝግጅቱ ደግሞ የጥሩ ፈተና ባህርያትን ጠንቅቆ መገንዘብ ያሻል። "ቼዝ ለመጫወት ስንፈልግ ፈረሱ እንዴት እንደሚሄድ ካላወቅን መጫወት እንደማንችል ሁሉ ፈተና ስናዘጋጅም መሠረታዊ መርሆዎችን ማወቅ ግድ ይሆናል ። ’’
"(ሃሪሰን ፣1983:10)

በመሆኑም አንድ ፈተና ሲዘጋጅ በጥሩ ሁኔታ መዘጋጀት አለመዘጋጀቱን ለመፍረድ አብዛኞቹ ምሁራን በዓቢይነት የሚያነሷቸው መስፈርቶች ሶስት ናቸው። እነሱም አስተማማኝነት፣ ህያውነትና ተተግባሪነት ናቸው። አንዳንድ ምሁራን ለምሣሌ ፊኖቺሪና ሳኮ (1983) አጠቃላይነትን (Comprehensiveness) በመጨመር ባህርያቱን አራት ያደርጓቸዋል። ሆኖም ይህንን ባህርይ አብዛኞቹ ምሁራን በአስተማማኝነት ስር ይመለከቱታል። ስለዚህ የዚህ ጥናት አቅራቢም አጠቃላይነትን በተናጠል አይመለከትም።

አንዳንድ ፈተናዎች ከሌሎቹ የተሻሉ ሆነው ተዘጋጅተዋል ሲባል ሶስቱን የጥሩ ፈተና ባህርያት አሟልተዋል ማለት ነው። ስለእያንዳንዱ መስፈርት ምንነት እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞከራል ።

### 2.3.1 አስተማማኝነት /Validity /

ሁሉም ምሁራን አስተማማኝነትን የበየኑት በተመሣሣይ አገላለጽ ነው:: አንድ ፈተና አስተማማኝ ነው የሚባለው መመዘን የሚገባውን ነገር በትክክል የመዘነ እንደሆነ ነው:: ለምሣሌ የጽሕፈት ክሂልን ለመመዘን ታስቦ ተማሪው " ፎቶግራፍ ማንሳት ጥበብ ነው ወይስ ሳይንስ? ተብሎ ቢጠየቅ አስተማማኝ ምዘና እንዳልተካሄደ ይታወቀናል:: ምክንያቱም ተማሪው እንዲጽፍ የተጠየቀበት ርእስ ጉዳይ ከጽሕፈት ክሂሉ ውጭ የፎቶግራፍ ዕውቀትን የሚጠይቅ ነውና::" (ሂተን ፣1975 :159)

በሌላ አገላለጽ አንድ ፈተና የቋንቋውን ድምፅ አነባበብ ( pronuncation) ለመመዘን ታልሞ የተዘጋጀ ቢሆን ፈተናው አስተማማኝነት አለው የሚባለው በትክክል የቋንቋውን ድምጸ ች አነባበብ ሲመዝን እንጂ ለቃላት አገባቡ ወይም ፍቺው ሊሆን አይገባም :: (ላዶ ፣1961)

የአንድን ፈተና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ በመጀመሪያ ከቋንቋው ትምህርት ውስጥ ትክክለኛ የቋንቋውን አጠቃቀምና የትምህርቱን ዓላማዎች መወሰን፣ ቀጥሎም ፈተናው የቱን ችሎታና እውቀት እንደሚጠይቅ መመርመር፣ በመጨረሻም ፈተናዎቹ ከትምህርቱ ዓላማዎችና ይዘቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት መመርመር ያስፈልጋል:: (ትሮንዳይክና ሄግን፣1977 :58).

የአስተማማኝነት ዓይነቶች በርካታ ናቸው:: ይሁን እንጂ ዴቪስ (1984) እንደሚመስክሩት የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን ለመገምገሚያነት የሚውሉት የይዘትና የላሀያዊ አስተማማኝነት ናቸው:: የዚህ ጥናት ትኩረትም የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ናቸው:: ስለዚህ ከአስተማማኝነት አይነቶች ውስጥ ለጥናቱ መሠረት የሚሆኑትን ብቻ (የይዘትና የላሀያዊ አስተማማኝነት) እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞከራል::

#### 2.3.1.1. የይዘት አስተማማኝነት/Content validity /

አንድ ፈተና የይዘት አስተማማኝነት አለው የሚባለው የፈተናውን ናሙና አወሳሰድና ይዘቱን ለግምገማው መሠረት ስናደርግ ነው:: ይህ ግምገማ መከናወን ያለበት ደግሞ ቋንቋውን በማስተማርና በመፈተን የረጅም ጊዜ ልምድ ባላቸው ሰዎች ነው:: ይህ ማለት ግን ፈተናውን በቀጥታ ያዘጋጁት ሰዎች ግምገማውን ማካሄድ አለባቸው ማለት አይደለም :: በአጠቃላይ ተገቢ ናቸው በተባሉት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች

ላይ ተመስረቶ ይዘቶችን በተመጣጠነና ወካይ በሆኑ ናሙናዎች የሚያቀርብ ፈተና የይዘት አስተማማኝነት አለው ሊባል ይችላል። (ሂዩዝ፣ 1989፡ 22 ና ሃሪሰን፣ 1983፡11).

በተመሳሳይ አገላለፅ ካርሚንስና ዜለርን (1985) ጠቅሰው ደጀኔ (1990) እንዳቀረቡት የይዘት አስተማማኝነትን ለመጠበቅ አንድ ፈተና የግድ ይህን ያህል ቁጥር ያለው ጥያቄ መያዝ አለበት ብሎ ለመወሰን ያስቸግራል ። ይሁን እንጂ ፈተናው ጥቂት ጥያቄዎችን ከሚይዝ ይልቅ በርካታ ያሉ ጥያቄዎችን ቢይዝ ተመራጭነት አለው ።

በሌላ በኩል አለር (1979) እንደሚሉት " የይዘት አስተማማኝነት የሚመለከተው ፈተናው የቋንቋውን ተገቢ ጠቀሜታ እና በሕብረተሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ማንፀባረቁን መመርመር ሆኖ ይህም ከተፈታኙ ክሂል ጋር የተዛመደ እንዲሆን ይጠበቃል ።"(አለር ፣1979፡70).

ለማጠቃለል የይዘት አስተማማኝነት የሚመረምረው የትምህርቱ ዓላማና ይዘት በፈተናው ውስጥ ወካይ በሆኑ ናሙናዎች መቅረቡን ነው ። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በርከት ያሉ ጥያቄዎችን ማዘጋጀቱ ተመራጭም አመችም ነው ። በአንድ ፈተና ውስጥ የይዘት አስተማማኝነት መጠበቁን ለመገምገም የሚደረገው ጥረት በጣሙን አስፈላጊ ቢሆንም አድካሚ መሆኑ ግን ሊታወቅ ይገባል ። ያም ሆኖ ግን ግምገማው ትምህርቱን ለረጅም ጊዜ በማስተማርና በመፈተን ልምድ ባላቸው ሰዎች ቢካሔድ ውጤታማ ይሆናል ። ከዚህም በላይ ዴቪስ (1968) እንደሚገልጹት "የቋንቋን ፈተና ለመገምገም የተወሰነ መስፈርት በሌለበት ሁኔታ ፈተና አውጭው የይዘት አስተማማኝነትን መቃኘት ግድ ይለዋል ።"( ዴቪስ፣1968፡159)

## 2.3.1.2. ላሀያዊ አስተማማኝነት /Face Validity/

ተማሪዎችና መምህራን ስለፈተናው ምን ያስባሉ? የሚለው ጥያቄ አይነተኛ ትኩረቱ ነው። ይህም ማለት ፈተናው የተማሪዎችን ችሎታ ለመለካት ተገቢ የመምሰል ባህሪ አለው ወይስ የለውም? ፈተናው በጣም ቀሏቸዋል ወይስ ከብዷቸዋል? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች አፋዊ በሆነ መልኩ የሚመልስልን ነው ማለት ነው። በአንድ ፈተና ውስጥ ላሀያዊ አስተማማኝነት መኖሩን ለማረጋገጥ የመምህራንና የተማሪዎችን አመለካከት ማወቅን ይጠይቃል። አመለካከታቸውን ለማወቅ ደግሞ በመጠይቅ ፣በውይይት ፣በቃለመጠይቅና በመሳሰለው ዘዴ መጠቀም ይቻላል ።

ፊኖቺሮና ሳኮ ን (1983) ጠቅሰው ደጀኔ (1990) እንዳቀረቡት አንድ ፈተና ላህያዊ አስተማማኝነት አለው ለመባል ፈተናው ትክክል ወይም ተገቢ መሆን ብቻ ሳይሆን ትክክል ወይም ተገቢ የመምሰል ባህሪም ሊኖረው ይገባል ። ስለዚህ ላህያዊ አስተማማኝነት የሪፓርተርና የህዝብ ግንኙት ተግባርን የሚፈጽም ነው ማለት ይቻላል:: (ደጀኔ ፣1990:64).

በአጠቃላይ አንድ ፈተና ላህያዊ አስተማማኝነት አለው የሚባለው ፈተናው ለሌሎች ባለሙያዎች፣ ለመምህራንና ለተፈታኞች ተገቢ መምሰል የቻለ እንደሆነ ነው:: ይህንን ለማወቅ ደግሞ መጠይቅ ፣ ውይይት ፣ ቃለመጠይቅና የመሳሰሉትን ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል:: ፈተናው ቢያንስ በተፈታኞቹ ዘንድ አፋዊ ተቀባይነት ካገኘ ደግሞ ተፈታኞች ፈተናውን ለመስራት ስለሚነቃቁ ላህያዊ አስተማማኝነት ጠቀሜታ ይኖረዋል::

## 2.3.2. **ህያውነት** /Reliability /.

ይህ ሌላው የጥሩ ፈተና ባህርይ ወይም መስፈርት ነው ። ከአስተማማኝነት ጋርም በእጅጉ ይዛመዳል ። አብዛኞቹ ምሁራን እንደሚከተለው ይበይኑታል ። ህያውነት አንድ ፈተና ለተፈታኞች በቀረበበት ጊዜ ሁሉ የውጤቱ ዘላቂነት (Consistency) ምን ያህል እንደሆነ የሚመዝን መስፈርት ነው:: በሌላ አገላለጽ ፈተናው በተለያየ ጊዜ ወይም ሁኔታ ለተፈታኞች በሚቀርብበት ጊዜ የሚገኘው ውጤት ምን ያህል ተመሳሳይ መሆኑን ወይም በአንድ ፈተና ውስጥ ለሚገኙ ጥያቄዎች ተፈታኙ በዘላቂነት የሰጣቸውን መልሶች መመርመር የህያውነት ተግባር ነው:: ሂተን (1975)፣ ኢብል (1979)፣ጋይ (1980)፣ ፊኖቺሮና ሳኮ (1983) እና ሂዩዝ (1989) ከላይ በተጠቀሰው ብያኔ ከሚስማሙ ምሁራን ጥቂቶቹ ናቸው::

ምንም እንኳን በርካታ የህያውነት ዓይነቶች ቢኖሩም (ለምሣሌ ቴስት-ሪቴስት፣ ውስጣዊና ውጫዊ-አራሚዘላል(Inter-marker andlor intra marker)ወዘተ) ለዚህ ጥናትአስፈላጊ የሆነው የህያውነት ዓይነት ውስጣዊ ዘላቂነትየተባለው ነው:: ውስጣዊ ዘላቂነት (Internal Consistency) በአንድ ፈተና ውስጥ በተመሳሳይ ክፍሎች (ለምሣሌ በቃላት ፈተና በቻ) (ወይም በተለያዩ ክፍሎች (ለምሣሌ ቃላት ፣ ስዋስው አንብቦ መረዳት ፣ ወዘተ...) ለቀረቡት ጥያቄዎች ተፈታኙ የሰጠውን መልስ በመተንተን ህያውነቱን የሚመረምር ነው:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል:: መሳለመሳ ቅርደዳ ዘዴ (Split half method ) እና የኩደር ሪቻርደሰን ($KR_{20}$) ቀመር በጣም የተለመዱ ዘዴዎች እንደሆኑ ኢ ብል

(1979፣278) ይገልፃሉ:: ይህ ጥናት የኩደር ሪቻርድስንን ቀመር መሠረት በማድረግ የፈተናዎችን ህያውነት ለመመርመር ይሞክራል ::

እንደ ሂተን (1975:164) እምነት "ከአስተማማኝነትና ከህያውነት ምረጡ ብንባል ቅድሚያ የምንሰጠው ለአስተማማኝነት ሆኖ ፈተናው ህያውነት እንዲኖረው ደግሞ ብርቱ ጥረት እናደርጋለን:: "በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ሃሪሰን (1983:11) ሲያስረዱ" አንድ ፈተና አስተማማኝ ሳይሆን ህያው ሊሆን ይችላል:: በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ፈተና ህያውነት ሳይኖረው ግን አስተማማኝ ሊሆን አይችልም::"በሌላ አገላለጽ " አስተማማኝ ፈተና ሁል ጊዜም ህያው ነው :: ነገር ግን ህያው ፈተና ሁል ጊዜ አስተማማኝ ሳይሆን ይችላል" (ጋይ ፣1980:202)

## 2.3.3. ተተግባሪነት / Practicality /.

ይህ መስፈርት በተለይ ፈተናው ለበርካታ ተፈታኞች የሚቀርብ ከሆነ በጣሙን አስፈላጊ ነው:: የፈተናው ተተግባሪ አለመሆን ኢ-ህያውና ኢ-አስተማማኝ የሆኑ የፈተና ውጤቶችን ሊያስገኝ ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: (ግሮንላንድና ሮበርት ፣ 1990 )

እንደ ሂዩዝ (1989) እምነት የፈተናውን ተተግባሪነት ለመጠበቅ የሚከተሉት ሁለት ነጥቦች ሊሟሉ ይገባል::

ሀ. ዝግጅት -ይህ ነጥብ ፈተናው ሰፋ ያለ ጊዜ ተሰጥቶት በጥንቃቄ እንዲዘጋጅ የሚያሳስብ ነው:: በዝግጅቱም ሂደት አንደኛ ፈተናውን ለማዘጋጀት የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ፣ ሁለተኛ የረዳትና ዋና ፈታኞች ምደባ፣ ሶስተኛ የተፈታኞች አቀማመጥ፣ አራተኛ የመፈተኛ ክፍሎች አዘገጃጀት ሊታሰብበት ይገባል::

ለ. የፈተናው አስተዳደር :- ይህ ፈተናው በሚሰጥበት ጊዜ ያለውን አስተዳደር ይመለከታል :: ለምሣሌም ያህል ከፈታኝና ከተፈታኞች የሚጠበቅ ዲስፒሊን ፣ የአርፋጅ ተማሪዎችን ሁኔታ፣የጸጥታ አጠባበቅ ሁኔታ፣ወዘተ. በምን መልክ እንደሚካሄድ የምንወስንበት ነው:: ( ሂዩዝ ፣ 1989 : 152)

## 2.4 ቃላትን ማስተማርና መፈተን

ቃላትን ስለማስተማርና መፈተን ከመመልከታችን በፊት የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክር ። ቃላት ስንል ምን ማለታችን ነው? በአፍ መፍቻ ቋንቋም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ አንድ ሰው ቃላትን አወቀ የሚባለው ምን ችሎታ ሲኖረው ነው?

ዋላስ (1982:19 )፣ ማድሰን (1983: 14) ና ካርትና ሜክ ካርዚ (1988:19) እንደሚያስገነዝቡት በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ድርብ ቃላት (Compound Words) እና ፈሊጦች (Idioms) የቃላት አንድ ክፍል ናቸው ። ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ የአማርኛን ቃላት ማስተማር ወይም መፈተን ስንል ፅንስ ሐሳቡ በተለይ የሚመለከተው የይዘት ቃላትን (ማለትም ግስ፣ ስም፣ ቅጽል..) ሆኖ ድርብ ቃላትንና ፈሊጦችን ወይም ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ሙሉ በሙሉ ሲይዝ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሐረጋትን ሊጨምር ይችላል።

አንድ ሰው በአፍ መፍቻ ቋንቋውም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋው ቃላትን አወቀ ማለት የሚከተሉትን ችሎታዎች አገኘ ማለት ነው።

ሀ. በንግግር ወይም በጽሁፍ ቅርፁ ቃሉን ማወቅ፣

ለ. ቃሉን በተፈለገው ጊዜ ለማስታወስ መቻል፣

ሐ. ቃሉን ከትክክለኛው ፅንስ ሀሳብ ጋር መዛመድ መቻል፣

መ. በትክክለኛው ሰዋሰዋዊ ቅርፅ ለመጠቀም መቻል፣

ሠ. በንግግር ወይም በንባብ ጊዜ ቃሉ በሚታወቅባቸው የአነባበብ ስልት ለመጥራት መቻል፣

ረ. በጽሕፈት ጊዜ የቃሉን ትክክለኛ የሆሄያት አፃፃፍ ጠብቆ ለመፃፍ መቻል፣

ሰ. ከሌላ ቃል ጋር ተጣምሮ በሚነገርበት ጊዜ (አብዛኛውን ጊዜ ፈሊጥ ሲሆን) የሚሰጠውን ውስጣዊ ፍቺ ማወቅ፣

ሸ. በትክክለኛው የመደበኛ አጠቃቀም ለመጠቀም መቻል፣ እና

ቀ. የቃሉን አግሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ለመረዳት መቻል ናቸው። (ዋላስ፣1982 :27)

እንደ አቼስን (1987)፣ ዋላስ (1982) ና ብራይትና ግሪነር (1978) እምነት ማንኛውም ጤናማ ሰው አፉን በፈታበት ቋንቋ (በተለይ ከሁለተኛ ቋንቋው ጋር ሲነፃፀር የዕውቀቱ መጠን በጣም ከፍተኛ ነው) በርካታ ቃላትን ያውቃል። የተማሩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚያውቋቸው የቃላት ብዛት ከተመራማሪ ተመራማሪ ቢለያይም አብዛኞቹ የሚገምቱት ከመቶ ሽህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ባለው ነው።

አቼሰን (1987) እንደሚያምኑት ግን የአንድ የተማረ ጎልማሳ የቃላት ዕውቀት ከሃምሳ አምስት ሽህ እንደማያንስና እስከ ሁለት መቶ ሃምሳ ሽህ ከፍ ሊል እንደሚቻል ግምታቸውን ያስቀምጣሉ። ፀሐፊዋ ፎደር ን(1981) በመጥቀስ እንደሚያስረዱት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተናጋሪዎቹ ስለ ቃላቱ እጅግ ብዙ ያውቃሉ። ዕውቀታቸው በአውዳዊ አጠቃቀምና ትክክለኛ ፍቻቸውን በመስጠት ይንፀባረቃል። ይህም ማለት ተናጋሪዎቹ ስለአንድ ቃል በመዝገበ ቃላት ከተገለጸው ፍች የበለጠ በአእምሯዊ መዝገበ ቃላቸው (Mental lexicon) አማካኝነት ብዙ ያውቃሉ ማለት ነው። (አቼስን፣ 1987:7)

## 2.4.1. ቃላትን ማስተማር

የቃላት ትምህርት ሁለት ገፅታዎችን ይይዛል። የመጀሪያው ገጽታ ለቋንቋው ለመዳ የሚያስፈልጉትን ቃላት ጥልቅና ትክክለኛ ፍች ማወቅ ሲሆን ሁለተኛው ገፅታ ደግሞ የማስተማሩ ቅንብር በተቻለ መጠን ቃሉን ለማስታወስ በሚያስችል መንገድ እንዲከናወን ማድረግ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በቃላት ትምህርት የአንድን ቃል ፍችና አጠቃቀም በተሟላ ሁኔታ ለመረዳት አንደኛ ቃሉን ማስታወስ፣ ሁለተኛ የራስን ፈጠራ መጠቀም፣ ሶስተኛ ቃሉን ከሌሎች ቃላት ጋር አዛምዶ መገንዘብ እና አራተኛ ከቃሉ የሚፈጠሩትን እርባታዎች መገንዘብ አስፈላጊ ናቸው። (ኮርኑ፣ 1978: 262)

ቃላትን በአውድ ማስተማር ጠቃሚ ዘዴ መሆኑን በርካታ ምሁራን ይመስክራሉ። ለምሳሌ ብራይትና ግሪነር (1978:151) "ተገቢ አውድ የቃላትን ትክክለኛ ፍች ለመረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።" ሲሉ አንደርሰንና ኦርቶኒ (1975:72) ደግሞ "አውድ አሻሚ ፍችን ግልጽ ለማድረግ አንድን ቃል በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ይጠቅማል።" ላዶ (1964:118) በበኩላቸው "ለፍች ህያውነት አወድ በጣሙን አስፈላጊ ስለሆነ የማስተማር ዘዴያችን አውዳዊ መሆን አለበት።" ብለዋል። ዋላስም (1982:13) "አንድ ቃል በቅርፁ ተመሣሣይ ሆኖ የተለያየ ፍች ሊሰጥ ይችላል። የቃሉን ትክክለኛ ፍች የምናውቀው ቢያንስ ቃሉ በዐረፍተ ነገራዊ ዐውድ ውስጥ ሲገባ

እንደመሆኑ የማስተማሪያ ዘዴያችን አውዳዊ ሊሆን ይገባል።" ይላሉ፡፡ ሳሙኤልስ (1968:361) ደግሞ በአጭሩ "አውድ የንባብ ፍጥነታችንን ያሳድግልናል" ብለዋል።

ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ተናጋሪዎችም ሆነ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ተገቢው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ የሚከተሉትን ያጠቃልላል። አንደኛ ተማሪዎች ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ የሚጋለጡበትን ሁነት (situation) ማመቻቸት ። ሁለተኛ ቃላቱን ፍቺያቸው በሚታወቅበት አውድ ማዘጋጀት፡፡ ሶስተኛ የአዳዲስ ቃላትን ፍች ከአውዱ መገመት እንዲችሉ መገፋፋት። (ዋላስ፣ 1982:28-31)

ምንም እንኳን ፈሊጦች የቃላት አንድ ክፍል መሆናቸው ባይካድም ስለአማርኛ ፈሊጦች አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳቱ ተገቢ ይመስላል። ምክንያቱም አንደኛ የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. ፈሊጦችን የሚያቀርቧቸው ከቃላት ለይተው በመሆኑ ግምገማው በተናጠል የሚካሄድበት ጊዜ ያጋጥማል። በሁለተኛም ደረጃ ፈሊጦቹ ከተራ ቃላት በተለየ መልክ የሚታዩበት ሁኔታ አለ። ያም ሆኖ ግን አንድ ሰው ቃላትን አወቀ ስንል የሚያገኛቸው ችሎታዎችና ቃላትን ስለማስተማር ያነሣናቸው ዘዴዎች ለፈሊጦችም እንደሚውሉ መዘንጋት የለበትም።

በርካታ ምሁራን ፈሊጦችን (idioms) በተመሣሣይ መንገድ በይነዋል። ለምሳሌ ያህል ሰይድ /1978:4/ "ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቃላት በአንድነት ተገጣጥመው የሚፈጥሩት አንድ ነጠላ ፍች ፈሊጥ ይባላል። ፍቺው የሚገኘው የየቃሉን ተናጥላዊ ፍች በማገጣጠም ሳይሆን በውህደት መሆኑ የፈሊጥ ባህሪ ነው።" ይላሉ።

አምሳሉና ዳኛቸው (1979 ) ደግሞ ስለፈሊጦች እንደሚከተለው በሰፊው ያስረዳሉ። ፈሊጣዊ አነጋገር በቃላት በልዩ ልዩ ዘዴ የመጠቀም አንደኛው መንገድ እንደመሆኑ ባጠቃላይ ይዘቱ እያንዳንዱ ቃል ከሌሎች ጋር በሚቀናጅበት ጊዜ በመሠረቱ ከነበረው ፍች የተለየ ፍች የሚሰጥበት ሁኔታ ሲሆን በዝርዝር ይዘቱ ደግሞ ቃላት መጀመሪያ ለቆሙለት እሳቤ ተመሳሳይ ለሆኑ ለሌሎች እሳቤዎች በመዋል ትርጉማቸውን እያሰፉ የሚያድጉበት ዘዴ ነው። ባጠቃላይ ይዘቱ ለምሳሌ "ሆደ ሰፊ" በምንልበት ጊዜ በሁለቱ ቃላት እየቅል ትርጉም የአንድን ሰው ሆድ መስፋት ሳይሆን የምናስገነዝበው ሰውየው ቻይና ታጋሽ መሆኑን ነው። በዝርዝር ይዘቱ ደግሞ ለምሳሌ "ዐይን" የሚለውን ቃል ብንወስድ መጀመሪያ ቃሉ የዋለው ለማየ ለሚያገለግል ህዋስ መሆኑን እንረዳለን። ስለሆነም ከጊዜ በኋላ ይኸው ቃል ለሌሎች ተመሳሳይ እሳቤዎች በመዋል የእንጀራ ዐይን፣ የመርፌ ዐይን፣ የእንጨት ዐይን በማስኛት ይሠራበታል። (አምሳሉና ዳኛቸው፣ 1979:3)

ፊሊጦችን በእንዴት ያለ ዘዴ እናስተምር የሚለው ጥያቄ በተደጋጋሚ ሲነሣ ቆይቷል። አንዳንድ ምሁራን ከአንድና ከተመሣሣይ ቃል የሚፈጠሩ ፊሊጦችን በአንድነት እየቦደኑ ማስተማሩ ጠቃሚ ነው በሚል ሙከራ ማድረጋቸውን ዋላስ /1982/ ይገልፃሉ። ይኸውም ለምሣሌ በአማርኛ "ሆደ ሰፊ" "ሆደ ቡቡ" "ሆደ መጋዝ" ወዘተ. ፊሊጦችን በአንድነት ቦድኖ እንደማስተማር ማለት ነው። ይሁን እንጂ ይህ ዘዴም ቢሆን ያመጣው ውጤት በጣም ዝቅተኛ ነው። ምክንያቱም በአንድነት የተቦደኑት ፊሊጦች የሚመሳሰሉት በቅርጽ እንጅ በፍች ስላልሆነ የጉዳዩን አስቸጋሪነት ሊፈታው አልቻለም። (ዋላስ፣ 1992:118)

ስለዚህ ፊሊጦችን በቅርፃቸው እየቦደኑ ከማስተማር ይልቅ እያንዳንዱን ፊሊጥ እንደ አዲስ በመቁጠር ፍቺያቸውን በሚያሳይ አውድ ማስተማሩ ተማራጭነት እንዳለው ዋላስ ያስገነዝባሉ። በርግጥ ከፊሊጦች ለየት ያለ ባህሪ አንፃር የተሻለ የማስተማሪያ ዘዴ ሊነደፍ በተገባ ነበር። ይሁን እንጂ እስከዛሬ ይህን ማድረግ አልተቻለም። በመሆኑም ለጊዜው ያለው አማራጭ እያንዳንዱን ፊሊጥ እንደ አንድ የተለየ ቃል ቆጥረን በማስተማሩ ሂደት ተገቢ አውድ ማዘጋጀት እንዲሁም ቃላትን የምናስተምርባቸውን የተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም እንደሆነ ዋላስ (1982) ይመክራሉ።

ለማጠቃለል ቃላትን በማስተማር ሂደት አይነተኛው የማስተማሪያ ዘዴ አውዳዊ የተባለው ነው። ቃላትን በአውድ ውስጥ በማስተማር ተማሪው የመዝገበ ቃላት ወይም የመምህር እርዳታ በማያገኝበት ጊዜ የቃሉን ፍች ከአውዱ እንዲገምት ማድረግ በአብዛኛው ምሁራን ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ዘዴ ነው። ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ጥቅል መርህ ነው። ስለዚህ ቃላትን በማስተማር ሂደት ተስማሚውን ዘዴ ለመምረጥ ቃላቱን የምናስተምርበት አላማ በውል ሊታወቅ ይገባል። ለምሣሌ በተለየ ሙያ ለማሰልጠን፣ አገር ለመጎብኘት፣ ወይም በቋንቋው ጥሩ ተናጋሪና ፀሐፊ ለማድረግ ወዘተ. ይህ በውል ተለይቶ ሲታወቅ ተስማሚውን ዘዴ መንደፍ ይቻላል። ያም ሆኖ ግን የቃላት ትክክለኛ ፍች የሚታወቀው በአውድ እስከሆነ ድረስ የአውድ አዘገጃጀት ሊተኮርበት እንደሚገባ ዋላስ (1982) በአጽንኦት ይገልፃሉ።

## 2.4.2. ቃላትን መፈተን

በርካታ ምሁራን የቋንቋን ክሂሎችናዘርፎች እየነጠሉ መፈተንን ይኮንናሉ። ለምሳሌ ኬሌ (1978)፣ ሬአ (1978) እና ሞሮው (1979) እንደሚያስረዱት የቋንቋን ክሂሎችና የዕውቀት ንጥረ ነገሮች (elements) ነጣጥሎ ለመፈተን መሞከር ተማሪው በቋንቋው ለመጠቀም ያለውን ችሎታ ስለማያሳዩ እውነተኛ የተግባቦት መመዘኛዎች

አይደሉም። ይህም ማለት ለምሳሌ ቃላት፣ ሰዋሰው፣ ስነድምፅ፣ ንግግር፣ ጽሕፈት፣ ወዘተ. እያሉ በመነጣጠል ለመፈተን መሞከር ተገቢ አይደለም ማለት ነው።

አያሌ ምሁራን የቋንቋን ክሂሎችና ዘርፎች እየነጠሉ መፈተንን በእጅጉ ቢቃወሙትም ዛሬም ድረስ ግን በርካታ የቋንቋ ፈተናዎች ክሂሎችንና ዘርፎችን እየነጣጠሉ እንደሚያቀርቡ ሂዩዝ (1989) እና ሂተን (1975) ይመሰክራሉ። እኛም የምናየው ነው። ሩቅ ሳንሄድ የኢ.ሁ.ደ.መ.አ.ፈ ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል። ንጥል ፈተናዎችን የሚቃወሙ ምሁራን እንዳሉ ሁሉ የአፈታተን ስልቱን የሚደግፉ ምሁራንም አሉ። እንደ ደጋፊዎቹ (ሃሪስ፣ 1969፤ ኩበር፣ 1968፤ እና አለር፣ 1976) እምነት ክሂሎችንም ሆነ የዕውቀት ዘርፎችን እየቅል መፈተኑ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት። ከጠቀሜታዎቹም ውስጥ የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

1. የእያንዳንዱን ተማሪ ተጨባጭ ችግሮች በተናጠልና በዝርዝር ለመረዳት ማስቻሉ እና
2. በዛ ያሉ ጥያቄዎችን በተፈለገው ርዕስ ለማቅረብ ማስቻሉ። (አለር፣ 1979:70 )

እነዚህንና መሰል ጠቀሜታዎችን ለማስገኘት የሚዘጋጁት ንጥል ፈተናዎች ምን ምን ነጥቦችን መያዝ እንዳለባቸው ምሁራኑ የየራሳቸውን ሞዴል አቅርበዋል። በሁሉም ሞዴል ውስጥ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው "ቃላት" ይገኝበታል።

የቃላት ዕውቀት የሥነልሣን ክሂሎቻችንን ለማዳበር አስፈላጊ ነው። የቃላት ፈተናም የሚመዝነው ቃላትን የመፍታት ችሎታ ነው ማለት ይቻላል። በተጨማሪም ቃላቱ በተለያየ አውድ ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ አብረዋቸው ከሚመጡ ሌሎች ቃላት ጋር በማጣመር የፍች ልዩነት ማምጣት አለማምጣታቸውን ተማሪው የሚመዘንበት ነው። (ዋላስ፣ 1982 እና ሂዩዝ፣ 1989 )

የቃላት ፈተናን በምርጫ ሰጭ የጥያቄ አቀራረብ ዘዴ መፈተኑ የተሻለ እንደሆነ ሂተን (1975) ይናገራሉ። ምርጫ ሰጪ የቃላት ጥያቄዎችን ስናዘጋጅ ልንከተላቸው የሚገቡ መርሆዎችና ቅደም ተከተሎች የሚከተሉት ናቸው።

1. ለምን እንደምንፈትን በግልጽ ማወቅ፣
2. ለፈተና የሚቀርቡ ቃላትን መምረጥ፣

3. ለተመረጡት ቃላት ተገቢ አውድ ማዘጋጀት፣

4. ተአማኒ አሳሳቾችን ማዘጋጀት፣

5. ግልጽና ቀላል መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣

6. በመጨረሻምአንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ መኖሩን ማረጋገጥ፣
(ማድሰን፡1983፡17)

የቃላት ፈተና ሲዘጋጅ የፈተናው አላማ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል። ይህም ማለት ከተማሪዎች የሚጠበቀው ችሎታ ምንድን ነው? የትምህርቱን አላማ ግብ ለመምታት የሚዘጋጀው ጥያቄ ተገቢ ነው ወይ? በጥቅሉም ፈተናው ምን ለማስገኘት እንደሚዘጋጅ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል።

የፈተናው አላማ በግልጽ ከታወቀ በኋላ ለጣቂው ሥራ በፈተናው ውስጥ የሚካተቱትን ቃላት መምረጥ ነው። ፈተና አውጭው የሚመርጣቸው ቃላት ለትምህርቱ ወካይ እንዲሆኑና ተፈላጊውን ዓላማ ግብ ለመምታት እንዲያስችሉ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል። ቃላቱንም ከሚከተሉት ምንጮች መምረጥ ይቻላል። አንደኛ ከሲለበሱ /በተለይ ሲለበሱ ተደጋጋሚ የቃላት ዝርዝር የሚሰጥ ከሆነ አመቺ ነው/፣ ሁለተኛ ከተማሪው መጻሐፍት፣ ሦስተኛ ለተማሪው ከሚቀርቡት ተጨማሪ የንባብ መጻሕፍት እና አራተኛ ተማሪው ከሚጽፋቸው ነጻ ድርሰቶች። (ሂተን፣ 1975፡51)

በተመሳሳይ አገላለጽ ሂዩዝ (1989)ና ማድሰን (1983) እንደሚያስረዱት በቃላት ፈተናችን ውስጥ የሚካተቱትን ቃላት ስንመርጥ በመጀመሪያ በትምህርቱ ውስጥ ቃላቱ ያላቸውን ተደጋጋሚነትና ጠቃሚነት መለየት፣ ቀጥሎም በጣም የሚደጋገሙትንና በንግግርም ሆነ በጽሕፈት አዘውትረን የምንገለገልባቸውን መለየት፣ በመጨረሻም የፈተናው አይነት የችሎታ መለኪያ ፈተና ከሆነ ትምህርቱ በምንጭነት የሚገለግልባቸውን ሲለበሶች፣ መማሪያ መጻሕፍትንና ተጨማሪ የንባብ መጽሐፍትን መዳሰስ ያስፈልጋል ። ከቶም ቢሆን ግን የቃላት አመራረጣችን ዘፈቀዳዊ መሆን እንደሌለበት፣ ሂልና ዱቢን(1981) ያስረዳሉ።

ለፈተና የሚቀርቡት ቃላት በጥንቃቄ ከተመረጡ በኋላ ተከታዩ ተግባር ለቃላቱ ተገቢ አውድ ማዘጋጀት ነው። በርካታ ምሁራን ቃላትን በተገቢ አውድ ውስጥ መፈተን አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ። ለምሳሌ ማድሰን (1983፡12) እንደሚያስገነዝቡት " በጥቅሉ ቃላትን እንዴት እንፈትን? የሚለውን የሚወስነው ቃላትን እንዴት

እናስተምራለን? የሚለው ቢሆንም በቃላት ፈተናችን ውስጥ ግን አውዳዊ ያልሆኑ ጥያቄዎችን ማስወገድ ይኖርብናል።"ብለዋል። እንደ ሂዩዝ (1989:146 ) እምንትም "ቃላት በአብዛኛው ቢፈተኑ ጠቃሚ የሚሆኑት ከአውድ ጋር ነው። ምክንያቱም ለአንድ ቃል ውሱን ፍች የሚሰጥልን ዐውድ ነውና። ለዚህ ደግሞ ስነልሣናዊና ማህበራዊ ተቀባይነት ያለው ሁኔትና አውድ መፍጠር ያስፈልጋል" ዋላስ (1982) አለን (1983)ና ሂተን (1975) ቃላትን በአውድ የመፈተኑን አስፈላጊነት ከገለጹ ምሁራን ጥቂቶቹ ናቸው።

የቃላት ትክክለኛ ፍች የሚታወቀው ቃላቱን በተገቢው አውድ ውስጥ ስንጠቀምባቸው እንደመሆኑ የአውድ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም። ይልቁንም የሚያሳስበን ጉዳይ እንደምን ተገቢ አውድ እናዘጋጅ የሚለው ነው።

ተገቢ አውድ የማዘጋጀቱ ሥራ አድካሚና አስቸጋሪ እንደሆነ ይታመናል። ይሁን እንጂ ሥራው አድካሚና አስቸጋሪ ነው ተብሎ የሚተው ደግሞ አይደለም። ስለዚህም ስፊ ጊዜ ወስዶ የቃላቱን ፍች የሚያሳይ ዐ.ነገራዊ አውድ ማቅረብ ይኖርብናል። ተገቢ አውድ ለማዘጋጀት ሌላው መንገድ ደግሞ የተማሪዎችን ደረጃ የሚመጥን ምንባብ ማዘጋጀት ነው። አብዛኛውን ጊዜ የቃላት ፈተናዎች ከምንባብ ጥያቄዎች ጋር ተዳብለው ይሰጣሉ። በዚህ ጊዜ ተፈታኙ ቃሉን እሱ በሚያውቀው ወይም በሚስማው ስሜት እንዲፈታው ሳይሆን በምንባቡ መሰረት እንዲፈታ የሚገደድበት ነው። ምንም እንኳን የምንባብ ጥያቄዎች አይነተኛ አላማ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመፈተን ቢሆንም ተገቢ አውድ ለቀረበላቸው ቃላት የቃላትን ፍች ለመጠየቅ አመቺ ናቸው። ስለሆነም አፈታተኑን መጠቀሙ ተገቢነት አለው። (ሂተን፣ 1975)

እንደሌሎች የምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች ሁሉ በቃላት ፈተናም ባማራጭ መልስነት የሚቀርቡ አሳሳቾች መልስ የመምሰል ባህሪ ሊኖራቸው ይገባል። ወይም ተአማኒ አሳሳቾችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

አሳሳቾች ተአማኒ መሆን አለባቸው ሲባል ከዋናው መልስ ጋር በቅርጽ ተመሳሳይ፣ በርዝማኔና በክብደት ደረጃቸው ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው ማለት ነው። ይህንን ለማድረግ በመጀመሪያ አማራጭ መልሶቹ በሙሉ በመሪ ዐ.ነገሩ ከተሰጠው ቃል ጋር ተመሳሳይ ምድብ ውስጥ ቢገኙ ይመረጣል። ለምሳሌ መሪው ቅጽል ከሆነ በመልስነት የሚቀርቡ አማራጮችም ቅጽል ቢሆኑ ይመረጣል። ይህም አሳሳቾች በቅርጽ መመሳሰላቸውን ያሳየናል። ከልምድ እንደታየው ትክክለኛ መልስ የያዘውን አማራጭ ከሌሎች አማራጮች ማስረዘምና ማክበድ ይዘወተራል። ይህ ዓይነቱ አጠ

ያየቅ ተማሪው ሌሎችን አማራጮች ወይም አሣሣቾች ትቶ ወደ መልሱ የሚመራው ስለሆነ የአሳሳቾችን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል። ስለዚህም አሳሳቾች ከትክክለኛው መልስ ጋር በአርዝማኔና በክብደት ደረጀ ተመጣጣኝ እንዲሆኑ መጣር ያስፈልጋል። (ማድሰን ፣1983:24 )

የቃላት ጥያቄ መመሪያዎች ማንኛውም ተማሪ ያለምንም ችግር ሊረዳቸው የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል። በዚህም መመሪያዎች አጭርና ግልጽ እንዲሆኑ ይጠበቃል። የጥያቄ አቀራረቡ ያልተለመደ ከሆነም በመምሪያው ስር ግልፅ ምሣሌ ማቅረብ ያስፈልጋል። እያንዳንዱ ጥያቄ ባለሙያዎች የሚስማሙበት አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ መያዙ ሊረጋገጥ ይገባል። ይህንንም ለማረጋገጥ ጥያቄውን መላልሶ ማየት አስፈላጊ ቢሆንም ጥያቄውን ለሙያ ባልደረባ ማሣየቱ ደግሞ ይበልጥ ጠቀሜታ አለው። (ማድሰን፣1983:25)

በመጨረሻም በቃላት ፈተናዎቻችን ውስጥ የሚካተቱት ቃላት ወገናዊነት ወይም አድሎአዊነት እንዳያሳዩ መጠንቀቅ ይኖርብናል። ይህም ማለት ለፈተና የሚቀርቡት ቃላት የሙያ፣ የዕምነት፣ የፆታ ወዘተ ወገናዊነት ሊኖራቸው አይገባም ማለት ነው። ለምሳሌ ከሙያ ቃላት የተወሰዱ እንደ "አካውንቲግ"፣ "ዴቢት"፣ "ባላንስ" ወዘተ ቃላትን በአጠቃላይ የቃላት ችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ውስጥ ብናቀርብ ለነዚህ ቃላት ቀረቤታ ያላቸው የኮሜርስ ተማሪዎች ይበልጥ ተጠቃሚ ስለሚሆኑ ቃላቱ ሙያዊ ወገናዊነት ይኖራቸዋል። በተመሳሳይ መንገድ ለወንዶች ብቻ ቅርበት ያላቸውን እንደ "ካርብሬተር" ያሉትን ቃላትም ብንጠይቅ ፆታዊ ወገናዊነትን (gender bias) ስለሚያሳዩ ተገቢነት የላቸውም። ( ሂተን፣ 1975 እና ማድሰን:1983)

## 2.5 <u>የቋንቋ ፈተናዎችን የገመገሙ ቀደምት ጥናቶች</u>

በዚህ ክፍል በሀገራችን ከተካሄዱ የቋንቋ ፈተና ግምገማ ጥናቶች ውስጥ ከአጥኚው ጥናት ጋር የሚዛመዱት ይቀርባሉ። ቅኝቱን ጠበብ በማድረግ በአብዛኛው በአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ላይ አትኩረናል። ሆኖም ጥቂት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፈተናዎችን የገመገሙ ጥናቶችንም ለመቃኘት ተሞክሯል።

የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን ድክመትና ጥንካሬ ከገመገሙ ጥናቶች ውስጥ በቀደምትነት የሚገኘው /የጥናቱ አቅራቢ በገኘው መረጃ መሰረት/ ፃተስፋዬ ሐይሌ በ1964 ዓ.ም "የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ተፈታኞች ለምን በአማርኛ ፈተና ጥሩ ውጤት አያመጡም" የሚለው ጥናት ነው። ጥናቱ የ8 አመት የፈተና ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ለምን ወደቁ? ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ የማስተማሪያ

መሳሪያዎች በብቃት አለመዘጋጀት፣ አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመሆንና ያለመሆን እንዲሁም ፈተናው ስርዓተ ትምህርቱንና የትምህርቱን ይዘት መሰረት አድርጎ አለመዘጋጀት አብይ ምክንያቶች እንደሆኑ ጠቁሟል።

ዋጋዬ ገ/አምላክ (1972) እና አበበ ከበደ (1975) ቀጣዮቹ ጥናቶች ናቸው። ዋጋዬ "ከ1963 –71 ዓ.ም ለ8ኛ ክፍል የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች ግምገማ " በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት የ9ኙን ዓመት ብሔራዊ ፈተናዎች ድክመት ጥንካሬ ይገመግማል። አበበ "የ6ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ያማርኛ ፈተና ግምገማ" በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት የ10 ዓመት ፈተናዎችን ይገመግማል። ሁለቱም አጥኚዎች የፈተናዎቹን ደካማና ጠንካራ ጎን ካቀረቡ በኃላ የፈተናዎቹ ደካማ ጎን እንደሚያይል አረጋግጠዋል።

ስለሞን ደስታ በ1976 ዓ.ም "በአዲስ አበባ በ4 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ1975 ዓ.ም የተሰጡ የአማርኛ ፈተናዎች" በሚል ርዕስ የሚኒሊክ፣ የእንጦጦ፣ የናዝሬት እና የቅዱስ ዮሴፍ ት/ቤቶችን በመምረጥ ያዘጋጁዋቸውን ፈተናዎች ገምግመዋል። የግምገማው ውጤት እንደሚያመለክተው ባራቱ ት/ቤቶች የተሰጡት የአማርኛ ፈተናዎች ከጥንካሬያቸው ይልቅ ድክመታቸው ጎልቶ ታይቷል። በተለይ ደግሞ የሁ.ደ.መ.አ.ፈ.በየት/ቤቶች ፈተናዎች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ማሳደራቸውን አጥኚው አመልክተዋል። በየት/ቤቱ ለተዘጋጁ ፈተናዎች በአብይነት የሚጠቀሱት ደካማ ጎኖች የፈተናው አላማ በውል አለመታወቅ፣ፈተናዎች በሥርዓተ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘት ላይ አለመመስረትና ፈተናዎቹ ከቋንቋ ትምህርት ውጭ ጥያቄ ማቅረባቸው ናቸው።

ንጉሴ ዳኣታ በ1978 ዓ.ም "የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና አቀራረብና የመማሪያ መፃህፍቱ ዝምድና " በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናት ከ1973 –77 የተዘጋጁትን ፈተናዎች ገምግመዋል። በግምገማው ከመማሪያ መፃህፍቱ ይዘት ውጭ የሆኑ የትምህርት ይዘቶች በየፈተናዎቹ መቅረባቸው ተጠቁሟል። በአጠቃላይ ግን በመማሪያ መፃህፍቱና በፈተናዎቹ መካከል ያለው ዝምድና በተመሳሰሎ ላይ ስለሚያተኩር ግንኙነቱ አዎንታዊ መሆኑን አረጋግጠዋል።

ወርቁ ዓለሙ በ1979 ዓ.ም "በጎልማሶች ትምህርት መምሪያ ስር በርቀት ትምህርት ዋና ክፍል የሚሰጠው የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ፈተና ግምገማ " በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ደግሞ የፈተናዎቹ ደካማ ጎን እንደሚያይል ያረጋግጣል ።አጥኚው ለፈተናዎቹ ደካማነት በማስረጃነት ካቀረቧቸው ጥያቄዎች በተጨማሪ ድርጅቱ በሙያው የሰለጠኑ ፈተና አዘጋጆች ስለሌሉት፣ ፈተናው ለምን ዓላማና ምን መፈተን እንዳለበት ለማወቅ አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጎታል ብለዋል።

መንገሻ ከበደ በ1984 " የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና የምንባብ ጥያቄዎች ግምገማ " በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ከቅርብ ሥራዎች ውስጥ አንዱ ነው። ይህ ጥናት በአንድ ዘርፍ ብቻ በማተኮሩ ከኔው ጥናት ጋር ይመሳሰላል። ይሁን እንጂ መንገሻ ያተኮሩት በምንባብ ላይ ሲሆን የኔ ግን በቃላት ላይ በመሆኑ ልዩነት አለው። መንገሻ እግረ መንገዳቸውን ስለቃላት በጣም ውሱን ነጥቦችን ቢያነሱም የኔ ጥናት ቃላትን በስፋት ስለሚመለከት ተመሳስሎ ሊኖረው አይችልም። የመንገሻ ጥናት

ውጤት የፈተናዎቹ ጠንካራ ጎን እንደሚያይል አመልክቷል። በዚህም ምንባቦቹ የተለያዩ ይዘት ያላቸው መሆናቸው፣ ወቅታዊ መሆናቸውና አጠር አጠር ማለታቸው ለአብነት ተጠቅሰዋል። በደካማ ጎን የታዩት ደግሞ በአብዛኛው የምንባቡን ክብደትና ውስብስብነት ግምት ውስጥ አለማስገባትና ቅደም ተከተላቸውም ከቀላል ወደከባድ ያለመደራጀት ናቸው።

አለሙ ፀጋው (1983)" የ6ኛና የ8ኛ ክፍል ብሔራዊ የእንግሊዘኛ ፈተናዎች ግምገማ " በሚል ርዕስ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ለማስተርስ ዲግሪ ሟሟያ ያቀረቡት የጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው አንደኛ በመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘትና ፈተናዎቹ ይዘት መካከል ያለው ዝምድና በጣም ዝቅተኛ ነው። ሁለተኛ ለየይዘቶች የተሰጠው ትኩረት ተመጣጣኝነቱን የጠበቀ አይደለም። ሦስተኛ ፈተናዎች በተማሪዎች መካከል ሊኖር የሚችለውን የችሎታ ደረጃ በመለየት በኩል ደካማ ናቸው። ባጠቃላይ አጥኚው የፈተናዎችን ደካማነት ካረጋገጡ በኋላ የመፍትሄ ሃሳቦችን ሰንዝረዋል።

ደጀኔ (1990) "ችሎታ፣ ወሸባክና ብቃት በኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናዎች ውስጥ" በሚል ርዕስ ለ PHD ዲግሪ ሟሟያ ያቀረቡት የጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው አንደኛ አጥኚው ያዘጋጁት አዲሱ ፈተና ከሁለተኛው ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ይልቅ ችሎታን በመለካት ረገድ የተሻለ ሆኗል። ሁለተኛ ብቃትን በመለካትም ረገድ ቢሆን አዲሱ ፈተና የተሻለ ሆኗል። በአጠቃላይም የተማሪዎችን ችሎታና ብቃት ለመለካት አሁን በሥራ ላይ ያለው የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ደካማ መሆኑ ተመልክቷል። በዚህም የተነሳ አጥኚው አዲስና የተሻለ ፈተና የሚዘጋጅበትን ሥልትና ሞዴል አቅርበዋል።

ይህ ጥናት ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ጥናቶች ጋር የተወሰነ ዝምድና ቢኖረውም ይዞት በተነሳው ውሱን ርዕስና አላማ ከሌሎች ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል። ቀጥለን ለመመልከት የምንሞክረው ይህንን ጥናት ለማካሄድ የምንከተለውን ያጠናን ዘዴ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ገላጭ የምርምር ዘዴን መሠረት በማድረግ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ገምግሞ ይተነትናል ። ማጠቃለያም ያቀርባል ።

### 3.1 የትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎችና የፈተናዎች ናሙና አመራረጥ

### 3.2 ③.①.①. የት/ቤቶች ናሙና አመራረጥ

አጥኚው በነበረው አነስተኛ የገንዘብና የጊዜ ወጭ በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ ት/ቤቶችን ለመምረጥ ቢያዳግተውም 23 ት/ቤቶች በጥናቱ ታቅፈዋል ። የት/ቤቶች የናሙና አመራረጥ በአብዛኛው ተራ የዕጣ ናሙና (simple random sampling ) አመራረጥ ስልትን የተከተለ ሲሆን በከፊል ደግሞ ስርዓታዊ የናሙና ስልትን (systematic sampling) የተከተለ ነበር ። በመጀመሪያ ሙሉ ለሙሉ በተራ የዕጣ ናሙና ስልት የተመረጡትን ት/ቤቶች እናቀርባለን ።

ከክልል 14 መስተዳደር ቢሮ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ክፍል በተገኘው መረጃ መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 25 ናቸው ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ (የግንቦት 20 ት/ቤት) የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን አስፈትኖ ስለማያውቅ ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃ ላያስገኝ ይችላል በሚል ግምት ከጥናቱ ውጭ ሆኗል ።

የቀሪዎቹ 24 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ስም ዝርዝር በአማርኛ ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት ከአንድ እስከ ሃያ አራት ከተጻፈ በኃላ ከጠቅላላው 25 በመቶ የሚሆኑት 6 ት/ቤቶች ተመረጡ ። የናሙናው የአመራረጥ ቅደም ተከተልም በየአራተኛው ተራቁጥር ላይ የሚገኘውን አንድ ት/ቤት በመምረጥ ተካሄዷል ። ይህ አይነቱ አመራረጥ ለየት/ቤቶች እኩል ዕድል እንደሚሰጥ ይታመናል ። የተመረጡትም ት/ቤቶች ሽመልስ ሐብቴ፣ አቃቂ፣ እንጦጦ፣ ከፍተኛ ሰባት፣ኮከበ ጽባሕ እና የካቲት 12 ት/ቤቶች ሲሆኑ የእነዚህ ት/ቤቶች የአማርኛ መምህራን የተዘጋጀውን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል ።

ስርዓታዊ ናሙናን በመከተል የተመረጡት ት/ቤቶች ደግሞ 17 ናቸው ። ይህ የናሙና አመራረጥ ስልት የተመረጠበት ምክንያት የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ መለያየት የሁ . ደ.መ.አ .ፈ . የቃላትና የፊደል ጥያቄዎችን በመመለስ ላይ ያለውን ተጽእኖ ለመመርመር አመቺ በመሆኑ ነው ። በዚህም መሠረት አማርኛ በአብዛኛው የአፍ መፍቻቸው ነው ከሚባሉ ክልሎች 10 ት/ቤቶችን (ቀደም ሲል ከአዲስ አበባ የተመረጡትን ሦስት ት/ቤቶች ይጨምራል)፣ አማርኛ በአብዛኛው የአፍ መፍቻቸው አይደለም ከሚባሉ ክልሎች ደግሞ 10 ት/ቤቶችን ለመምረጥ ታቀደ ።

ከሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ጽ/ቤት በተገኘው መረጃ መሠረት በ1987 ዓ.ም. መደበኛ ተማሪዎች የሚፈተኑባቸው ጣቢያዎች ወይም ት/ቤቶች ጠቅላላ ቁጥር 232 ነው ። ከእነዚህ ውስጥ አማርኛ በአመዛኙ የአፍ መፍቻቸው የሆኑ ክልሎች 82 የመፈተኛ ጣቢያ አላቸው (ክልል 3 ፌ59 እና ክልል 14 ፌ23) ። አማርኛ በአመዛኙ የአፍ መፍቻቸው ያልሆኑት ክልሎች ደግሞ 150 የመፈተኛ ጣቢያ አላቸው ( ክልል 1 ፌ 14፣ ክልል 2ፌ1፣ ክልል 4ፌ91፣ክልል 5 ፌ 2፣ ክልል 12 ፌ2፣ ክልል ደቡብ ህዝቦች ፌ 35 እና ክልል ድሬዳዋ ፌ1)።

የመፈተኛ ጣቢያዎችን ወይም ት/ቤቶችን በአመዛኙ አማርኛ በአፍ መፍቻነት የሚነገርባቸውና የማይነገርባቸው ብሎ በመለየት ብቻ የተፈታኙን እውነተኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማወቅ እንደሚያዳግት እሙን ነው ። ስለዚህ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ላሉ 20 የመፈተኛ ጣቢያዎች የ1987 ዓ.ም. የሁ .ደ .መ. ፈ . ፈታኞችን ቀና ትብብር በመጠየቅ ( በአብዛኛው የድኅረ ምረቃው ክፍል ተማሪዎች ናቸው) መረጃ ቅጽ 01ን ሞልተው እንዲያመጡ ተደረገ ። (የመረጃውን ቅጽ ዝርዝር በአባሪው ይመለከቷል) ። ክልል 6 እና ድሬዳዋ ከተላኩት ፈታኞች በስተቀር 17ቱ መረጃ ሰብሳቢዎች ቅጹን ሞልተው በማምጣታቸው መረጃው ምሉዕ ሆኗል ። የተሟላ መረጃ ለማግኘት ያልተቻለባቸው ሁለቱ ክልሎች ደግሞ ከጥናቱ ውጭ ሆነዋል ።

መረጃ ቅጽ 01ን መሠረት በማድረግ ጥናቱ ሊያቅፋቸው ያለማቸው ክልሎች በቂ ተጠኝዎች ይዘው ሲቀርቡ ይመረጣሉ ። በዚህም መሠረት አማርኛ በአብዛኛው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከሆኑት ውስጥ ከክልል 3 ፣ 7 ት/ቤቶች ተመርጠዋል ። እነሱም ቆላድባ፣ጎጃም በር፣ አዴት፣ መካነየሱስ (እስቴ)፣ላሊበላ፣ መሐል ሜዳእና አረርቲ ናቸው። እንዲሁም ከክልል 14 ቀደም ሲል ከተመረጡት ት/ቤቶች ውስጥ በሙሉ ቁጥር የሚገኙት አቃቂ ፣ከፍተኛ ሰባት እና የካቲት 12 ት/ቤቶች ተመርጠዋል ። በድምሩ 10 ት/ቤቶች ተመርጠዋል ።

አማርኛ በአብዛኛው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ካልሆኑት ውስጥም 10 ት/ቤቶች ተመርጠዋል። እነሱም ከክልል 1 አዳጋ ሀሙስ፣ ከክልል 2 ዱብቲ፣ ከክልል 4 ቀርሣ ፣ቦጂ ደርመጂና ጊንጪ ፣ከክልል 5 ጅጅጋ ፣ ከክልል 12 ጋምቤላ፣ ከክልል ደቡብ ሕዝቦች እንድብር፣ ሳውልና ጂንካ ናቸው።

### 3.1.3.የተማሪዎች አመራረጥ

የተማሪዎች አመራረጥም ሁለት መልክ ነበረው ። የመጀመሪያው ለተማሪዎች የተዘጋጀውን መጠይቅ የሚሞሉ ተማሪዎችን የመምረጥ ሂደት ነበር ።ካለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት የተነሣ ጥቂት ቁጥር ያላቸው ተማሪዎችን ቀደም ሲል ከተመረጡት 6 የአ.አ.ከተማ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምረጥ የግድ ነበር። በተለይ አጥኚው በእንጦጦ ት/ቤት የ1987 ዓ.ም. የሁ.ደ.መ. ፈተናን ይፈትን ስለነበር በዚህ ት/ቤት የሚማሩ ተማሪዎችን መምረጥ አመቺ ሆኖ ተገኘ ። አመራረጡ ተራ የዕጣ ናሙና ስልትን የተከተለ ነበር ። በዚህም በ40 የመፈተኛ ክፍሎች እንዲፈተኑ ከተመደቡት ተማሪዎች ውስጥ በተራ ቁጥር 20 ወይም በክፍል 20 የተመደቡት ተማሪዎች ዕጣው ስለደረሳቸው በጥናቱ ታቀፉ ። የተማሪዎቹ ቁጥር 30 ስለነበር ሁሉም ፈተናውን ተፈትነው ከጨረሱ በኋላ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል ።

በሁለተኛደረጃ የተመረጡት ተማሪዎች ከ20ዎቹ የመፈተኛ ጣቢያዎች በመረጃ ቅጽ 01 የተመዘገቡት ናቸው ። እነዚህ ተማሪዎች የተመረጡት ተራ የዕጣ ናሙና ስልትን በመከተል ነበር ። ለምሳሌ መረጃው 50 ተፈታኞችን መዝግቦ ከሆነ በየ5ኛው ተራ ቁጥር የሚገኘው ተፈታኝ ይመረጣል ። ሆኖም የተመረጠው ተፈታኝ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የተፈለገው ባይሆን፣/ለምሣሌ በአመዛኙ አማርኛ አፍ መፍቻቸው በሆኑት ክልሎች መረጃው ተልኮ የተፈታኙ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከአማርኛ ሌላ ቢሆን/እንደ አመቺነቱ ተከታዩ ወይም ለጣቂው ቁጥር ላይ የተመዘገበው ተፈታኝ ይመረጣል ። በዚህ አይነት ከ20ዎቹ የመፈተኛ ጣቢዎች አስር አስር ተማሪዎችን በመምረጥ ጠቅላላ ቁጥራቸው 200 ሊሆን ችሏል። የተማሪዎቹ አመራረጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ከመሆኑም በተጨማሪ መደበኛ የቀን ተማሪዎች እንዲሆኑ ያስፈለገበት ምክንያት አለ ። ይኸውም የተፈታኙ ያለፈ ዳራ (Back ground ) በውጤቱ ላይ የሚያመጣው ተጽእኖ ካለ አስቀድሞ ለመቆጣጠር ነው።

### 3.1.2.የፈተናዎች አመራርጥ

ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ እንደተጠቀሰው የጥናቱ አላማ የሁ .ደ.መ.እ.ፈ. የቃላት ጥያቄዎች ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ መሆን አለመሆናቸውን መመርመር እንደመሆኑ ለጥናቱ ወካይ የሚሆኑ ናሙና ፈተናዎችን መምረጥ የግድ ነበር ።በዚህም መሠረት በርካታ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተናዎች ከታሰሱ በኃላ ለጥናቱ አለማ ወካይ ናቸው የተባሉ -የስምንት አመት ፈተናዎች ተመርጠዋል ።እነሱም በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከ1980 - 87 ዓ.ም. የተዘጋጀ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተናዎች ናቸው ።

እነዚህ ፈተናዎች በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች የተነሣ ሊመረጡ ችለዋል ።

1. በስምንት አመታት ከቀረቡት 655 ጥያቄዎች ውስጥ 269 ወይም 41.1 በመቶ የሚሆኑት የቃላት ጥያቄዎች ናቸው። የጥቂዎቹ መብዛት ደግሞ ጥናቱ ወካይ ናሙና እንዲኖረው ይረዳል ።

2. በትንታኔው ሂደት ማወዳደር አስፈላጊ ቢሆን የተመረጡት ፈተናዎች አመች መሆናቸው። ይህም ማለት በቀድሞዎቹ መማሪያ መጻሕፍትና ሲለበሶች መሠረትንት የተዘጋጁትን የአራት አመት ፈተናዎች (ከ1980 - 83 ዓ.ም.)፣ በአሁኖቹ መማሪያ መጻሕፍትና ሲለበሶች መሠረትንት የተዘጋጁትን የአራት አመት ፈተናዎች ( ከ1984 - 87) ለማወዳደር አመቺ ናቸው ማለት ነው።

3. በመጨረሻም በቅርብ አመታት ፈተናዎች፣ ላይ ማትኮሩ መረጃዎችን ለማግኘትና ችግሮች ካሉ በተጨባጭ ለማሳየት ና ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ ለመወሰድ አመቺ ሆነው በመገኘታቸው ፈተናዎቹ ተመርጠዋል ።

በአጠቃላይ ካለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት አንፃር በተወሰኑ ፈተናዎች ላይ ማትኮሩ ተገቢ ስለሆነ የስምንት አመት ፈተናዎችን መርጠናል። ፈተናዎቹ በርካታ የቃላት ጥያቄዎችን መያዛቸው ፣የቅርብ አመታት መሆናቸውና ከማስተማሪያ መሣሪያዎቹ ጋር ለማወዳደር አመቺ መሆናቸው ለመመረጣቸው ምክንያቶች ናቸው።

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለዚህ ጥናት አግባብነት አላቸው ተብለው የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች መጠይቆች፣ ቃለመጠይቅ፣ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና

መማሪያ መጻሕፍት፣ የተመረጡ የሁ.ደ.መ.አ.ፈ ዎች እና የተፈታኞች ውጤቶች ናቸው ። ስለ እያንዳንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ አጠቃቀም ዘዴ እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞከራል

### 3.2.1. መጠይቆች

ለጥናቱ የሚረዱ መረጃዎችን ለማሰባሰብ በመምህራንና በተማሪዎቹ የሚሞሉ ሁለት መጠይቆች ተዘጋጅተው ነበር።

#### 3.2.1.1. የመምህራን መጠይቅ

የመምህራን መጠይቅ የሚከተሉት ዋና ዋና አላማዎች አሉት።

1. ቃላትና ፈሊጦችን ለማስተማር መማሪያ መጽሐፍቱና ሲለበሶቹ የሚሰጡት ድጋፍ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ፣
2. መምህራኑ አዳዲስ ቃላትና ፈሊጦችን የሚያስተምሩባቸውን ዘዴዎች ለማወቅ፣
3. መምህራኑ የሚሰጡት የቃላት ትምህርት ከሁ.ደ.መ.አ.ፈ.የቃላት ጥያቄዎች ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ለማወቅ፣
4. በፈተናዎቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ የቃላቱን አመራረጥ፣ዘዴን ፣አውዳዊነትን፣ አንድ መልስ ለመስጠት አዳጋች መሆንን ወዘተ...በተመለከተ መምህራኑ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ፣
5. በአጠቃላይ ስለፈተናዎቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ና ስለትምህርቱ ሂደት ያላቸውን አስተያየት ለማወቅ የታቀዱ ናቸው።

በዚህም መሠረት መጠይቁ በአጥኚው ከተዘጋጀ በኋላ በሦስት ባለሙያዎች እንዲገመገም ተደርጓል። ባለሙያዎቹ ያቀረቧቸው ማሻሻያዎች ከታከሉ በኋላ በዋናው ጥናት ላልታቀፉ 15 መምህራን መጠይቁ ቀርቦላቸው ነበር። ይህ ወቅትየጥናቱ የመነሻ ጥናት (pilot study) የሚካሄድበት ስለነበር የመጠይቁ ጥያቄዎች በከፊል መልስ አስመራጭ በከፊል ደግሞ የተሰጠውን ክፍት ቦታ መሙላት (open ended ) ላይ ያተኮሩ ነበሩ ።

መጠይቁ በመነሻ ጥናቱ ከተሞከረ በኃላ መምህራኑ የሰጧቸውን መልሶችና አስተያየቶች መሠረት በማድረግ ለጥናቱ አስፈላጊ ያልሆኑ ጥያቄዎችን በማውጣት፣ ግልጽ ያልሆኑ ቃላትና ሐረጋትን በመለወጥ እና በክፍት ቦታ ሙላ የተጠየቁትን ጥያቄዎች ወደ መልስ አስመራጭነት በመቀየር ለመጨረሻ ጊዜ መጠይቁ ተሻሽሎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል ፡፡

ለመጨረሻ ጊዜ ተሻሽሎ የቀረበው መጠይቅ (ዝርዝሩን በአባሪ መ ይመለከቷል) "መግቢያ " በሚለው ክፍል የመጠይቁን አላማ በግልጽ አስቀምጧል ፡፡ በመጠይቁ ክፍል አንድ " የግል ሁኔታ " በሚል ርዕስ ስለ መምህራኑ .

የት/ደረጃ፣የስራ ልምድ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወዘተ...በመጠየቅ የመምህራኑን ዳራ ለማወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመጠይቁ ክፍል ሁለት " የቃላት ትምህርት አሰጣጥንና " አፈታተንን በተመለከተ 25 ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ሃያ አምስቱ ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው አራት አማራጭ መልሶች አሏቸው፡፡ አማራጭ መልሶቹም አራት የውሳኔ ሀሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡ እነሱም በጣም እስማማለሁ (4)፣ እስማማለሁ (3)፣ አልስማማም (2) እና በጣም አልስማማም (1) ናቸው ፡፡ መጠይቁ ከላይ በተጠቀሰው ተዋረድ ተዘጋጅቶ እንደተጠናቀቀ ቀደም ሲል በተመረጡ 6 ት/ቤቶች ቋንቋውን በሚያስተምሩ መምህራን ልክ ተባዝቶ ተሠራጨ፡፡ አጥኚው መጠይቆችን ካሠራጨ በኃላ በሰጠው የሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ መጠይቆች ተሞልተው ተመልሰዋል ፡፡ የሚከተለው ሰንጠረዥ ለየት/ቤቱ የተሠራጩትን መጠይቆች ቁጥርና ተሞልተው የተመለሱትን ቁጥር ያመለክታል፡፡

ሰንጠረዥ 1 የመምህራን መጠይቅ ስርጭት፣ ተሞልተው የተመለሱ ቁጥርና መቶኛ

| ተ.ቁ | የት/ቤቱ ስም | የተሠራጨው ቁጥር | የተመለሰው ቁጥር | መቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሽመልስ ሐብቴ | 6 | 5 | 83.3 |
| 2 | አቃቂ | 7 | 6 | 85.7 |
| 3 | እንጦጦ | 14 | 12 | 85.7 |
| 4 | ከፍተኛ ሰባት | 9 | 8 | 88.9 |
| 5 | ኮከበ ጽባሕ | 12 | 11 | 91.7 |
| 6 | የካቲት 12 | 10 | 8 | 80 |
| | ድምር | 58 | 50 | 86.2 |

ሰንጠረዡ እንደሚያመለክተው በ6ቱም ት/ቤቶች ቋንቋውን ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ 58 መምህራን መጠይቁ ቢሰራጭም ተሞልተው የተመለሱት 50 መጠይቆች ወይም 86.2% የሚሆኑት ናቸው። ስለዚህ ይህ ጥናት በመረጃነት የሚገለገልባቸው 50 የመምህራን መጠይቆችን ይሆናል ማለት ነው።

### 3.2.1.2. የተማሪዎች መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ ተፈታኞቹ ስለፈተናው ያላቸውን ጥቅል አስተያየት በማወቅ የፈተናዎቹን ሳህያዊ አስተማማኝነት ለመመዘን ለሚደረገው ጥረት አጋዥ መረጃ ለማግኘት ነው። በዚህም መሠረት መጠይቁ በአጥኚው ከተዘጋጀ በኋላ በሶስት ባለሙያዎች እንዲገመገም ተደርጓል። ባለሙያዎቹ የሰጧቸውን ማሻሻያዎች መሠረት በማድረግ መጠይቁ ተሻሽሎ ከተዘጋጀ በኋላ በጥናቱ ባልታቀፉ 10 ተማሪዎች ተሞልቶ ተመልሷል። ተማሪዎቹ የሰጧቸውን መልሶች መሠረት በማድረግ ደግሞ ለመጨረሻ ጊዜ መጠይቁ ተሻሽሎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

ለመጨረሻ ጊዜ ተሻሽሎ የቀረበው መጠይቅ (ዝርዝሩን በአባሪ ሠ ይመለከቷል) ሁለት ክፍሎች አሉት። "መግቢያ" በሚለው የመጀመሪያ ክፍል መጠይቁ ስለተዘጋጀበት ዓላማና ከመጠይቁ ስለሚገኙ ትክክለኛ መረጃዎች ጠቀሜታ የተገለፀበት ሲሆን በመጠይቁ ላይ ስም፣ ክፍል ወይም ተራ ቁጥር መጻፍ እንደሌለበት ማሳሰቢያ ቀርቦበታል። በዚህም ተማሪዎች በተረጋጋ መንፈስ መጠይቁን አንዲሞሉ ጥረት ተደርጓል። በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከሳህያዊ አስተማማኝነት ጋር

በማድረግ መጠይቁ ተሻሽሎ ከተዘጋጀ በኋላ በጥናቱ ባልታቀፉ 10 ተማሪዎች ተሞልቶ ተመልሷል። ተማሪዎቹ የሰጧቸውን መልሶች መሠረት በማድረግ ደግሞ ለመጨረሻ ጊዜ መጠይቁ ተሻሽሎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

ለመጨረሻ ጊዜ ተሻሽሎ የቀረበው መጠይቅ (ዝርዝሩን በአባሪ ሠ ይመለከቷል) ሁለት ክፍሎች አሉት። " መግቢያ " በሚለው የመጀመሪያ ክፍል መጠይቁ ስለተዘጋጀበት ዓላማና ከመጠይቁ ስለሚገኙ ትክክለኛ መረጃዎች ጠቀሜታ የተገለፀበት ሲሆን በመጠይቁ ላይ ስም፣ ክፍል ወይም ተራ ቁጥር መጻፍ እንደሌለበት ማሳሰቢያ ቀርቦበታል። በዚህም ተማሪዎች በተረጋጋ መንፈስ መጠይቁን እንዲሞሉ ጥረት ተደርጓል። በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከላህያዊ አስተማማኝነት ጋር የተያያዙ 8 ጥያቄዎች ቀርበዋል ። የመጨረሻው ጥያቄ ነፃ አስተያየትን የሚጠይቅ ከመሆኑ በስተቀር ሰባቱ ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው ሶስት አማራጭ መልሶች አሏቸው። አማራጭ መልሶችም ሦስት የውሳኔ ሀሳቦችን የያዙ ናቸው። እነሱም እስማማለሁ (3)፣ አልስማማም (2) እና መልስ የለኝም (1) ናቸው።

መጠይቁ ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን ተዘጋጅቶ እንደተጠናቀቀ በተማሪዎች ልክ ተባዝቶ ተሠራጨ። ተማሪዎቹ የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. ተፈትነው ከጨረሱ በኋላ አጥኚው በተገኘበት መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል። ስለመጠይቁ አላማና ስለአሞላሉ አጥኚው ገለፃ ደረገላቸው ሲሆን ጥያቄ ካላቸው እንዲጠይቁ ዕድል ተሰጥቷቸዋል። ሆኖም ምንም ዓይነት ጥያቄ ስላልነበራቸው በ30 ደቂቃ ውስጥ መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል። ቀደም ሲል በተማሪዎች አመራረጥ እንደተገለፀው መጠይቁን የሞሉት ተማሪዎች በ20ኛው ክፍል የተመደቡት የእንጦጦ ት/ቤት ተማሪዎች ናቸው።

### 3.2.2.ቃለ መጠይቅ

ቃለመጠይቅ የቀረበው በስርዓተ ትምህርት ምርምርና ጥናት ተቋም ለአማርኛው ፓናል ሐላፊ ነው። የቃለ መጠይቁ ዋና አላማ ተቋሙ የሚያዘጋጃቸው የማስተማሪያ መሣሪያዎች ከሁ.ደ.መ.አ .ፈ.በተለይም ደግሞ ከቃላትና ፈሊጦች ጥያቄዎች ጋር ያላቸውን ዝምድና ለማወቅ ነው። አጥኚው ቃለ መጠይቁን ካዘጋጀ በኋላ ሐላፊው አስቀድመው እንዲዘጋጁበት ጽሑፉን ሰጥቷቸዋል። አመቺ በሆነው የጊዜ ቀጠሮ ሐላፊው ለእያንዳንዱ ጥያቄ በቃል የሰጡት መልስም በጥንቃቄ ተመዝግቧል። ዝርዝሩን በአባሪ ረ ይመለከቷል።

### 3.2.3. የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መማሪያ መጻሕፍት

የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. መሠረት ያደርጉት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መማሪያ መጽሐፍትን እንደሚሆን የሁ.ደ.መ.ፈ .ጽ/ቤት ያዘጋጀው መመሪያ መጽሐፍ /ሀንድቡክ/ ይመሰክራል ። ስለዚህ እነዚህ የመረጃ ምንጮች ጠቃሚ መረጃዎችን እንደሚያስገኙ ይገመታል።

በዚህም መሠረት የቀድሞዎቹ (ቀ) እና የአሁኖቹ (አ) መማሪያ መጽሐፍትና ሲለበሶች ስለቃላት ትምህርት ያነሷቸው ነጥቦች በየክፍል ደረጃው በዝርዝር ተመርምረዋል። የተነሱት ነጥቦች በየክፍል ደረጃው በአባሪ ለ እና ሐ ተመልክተዋል። በትንታኔው ክፍል ደግሞ አበይት ነጥቦችን በማንሳት ለትንተናው በመረጃነት ተጠቅመንባቸዋል።

### 3.2.4. የተፈታኞች ውጤት

ተፈታኝ ተማሪዎች ከ20 የመፈተኛ ጣቢያዎች ከተመረጡ በኃላ እያንዳንዱ ተፈታኝ በ1987 ዓ.ም. የሁ.ደ.መ.አ.ፈ . ለቀረቡት 33 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የሰጠው መልስና በአማርኛ ፈተና ያገኘው አጠቃላይ ውጤት ከሁ.ደ.መ.ፈ . ጽ/ቤት በጥቅምት ወር 1988 ዓ.ም. ተወስዷል። ይህ መረጃ የፈተናዎችን ህያውነት ለመመዘን ለሚደረገው ጥረት አጋዥ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ከዚህም በተጨማሪ ተፈታኞች የሰጡትን መልስ በመተንተን (item analysis) የትኞች ጥያቄዎች ተፈታኞችን በጉልህ እንደሚፈታተኗቸው ለመለየት የሚያግዙ ናቸው።

### 3.2.5. ፈተናዎች

የጥናቱ አላማ ፈተናዎችን መገምገም እንደመሆኑ የተመረጡት የስምንት አመት ፈተናዎች የጥናቱ አይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ናቸው። ፈተናዎቹን ለመገምገም ደግሞ ከላይ የተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አጋዥ ስለሚሆኑ እንደአስፈላጊነቱ በተናጠልና በቅንጅት እየተተነተኑ ግምገማው ተካሂዷል። ለግምግማው በአቢይ የመመዘኛ መስፈርትነት የተጠቀምነው አስተማማኝነት / validity/፣ህያውነት /Reliability/ እና ተተግባሪነትን /practicality/ ነው ።

በእነዚህ የጥሩ ፈተና ባህርት ስርም የተሰበሰቡት መረጃዎች ማለትም የመምህራንና የተማሪዎች መጠይቆች፣የአማርኛው ፓናል ሐሳፊ ቃለመጠይቅ፣ የማስተማሪያ መሣሪዎችና የተፈታኞች ውጤት አግባብ ባለው ቦታ ሁሉ እየተተነተኑ ለግምገማው መሠረት ይሆናሉ። ከነዚህም በተጨማሪ ምሁራን ስለቃላት አፈታተን ያነሷቸው መርሆዎች በንዑስ ርዕስነት እየቀረቡ አቢይ የመመዘኛ መስፈርቱን ያጎላሉ።

በአጭሩ ይህ ጥናት እያንዳንዱን የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ በተናጠል የሚተነተን ሳይሆን በጥሩ የፈተና ባህርት ስር መረጃዎቹን እንደአስፈላጊነቱ እየነጠለና አያቀናጀ ንተን የጥናቱን ውጤት የሚያቀርብ ነው። የጥናቱን የውጤት ትንተናና ማብራሪያ ለጣቂው ምዕራፍ በዝርዝር ያቀርባል።

# ምዕራፍ አራት
# የጥናቱ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ

በምዕራፍ አንድ እንደተገለጸው የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና የቃላት ጥያቄዎች ተገቢ ወይም ጥሩ የመመዘኛ መሣሪያ መሆን አለመሆናቸውን መመርመር ነው ::

የዚህ ምዕራፍ ትኩረት ደግሞ ጥናቱን ዓላማ መሠረት በማድረግ መረጃዎቹን እየተነተኑ የተገኘውን ውጤት ከነማብራርያው ማቅረብ ነው:: ለመረጃ አቀራረብና አተናተን ይመች ዘንድም ምዕራፉን በሶስት ንዑሳን ክፍሎች ለመክፈል ተሞክሯል::

በመጀመሪያው ንዑስ ክፍል አስተማማኝነትን (Validity) እንደ አንድ የመመዘኛ መስፈርት በመውሰድ ፈተናዎችን ለመገምገም ይሞከራል :: በግምገማውም አግባብነት ባለው ባታ ሁሉ ከመጠይቅ ፣ ከቃል መጠይቅ ፣ ከማስተማሪያ መሣሪያዎቹ እና ከፈተናዎቹ የተገኙ መረጃዎች በተናጠልና በቅንጅት ይተነተናሉ ::

በሁለተኛው ንዑስ ክፍል ህያውነትን (Reliability) እንደ አንድ የመመዘኛ መስፈርት በመውሰድ የ200 ተፈታኞችን ውጤት ለመተንተን ይሞከራል:: በሦስተኛው ንዑስ ክፍል ደግሞ ተተግባሪነትን (Practicality) እንደ አንድ የመመዘኛ መስፈርት በመውሰድ ፈተናዎችን ለመገምገም ይሞከራል ::

## 4.1 አስተማማኝነት (Validity)

በምእራፍ ሁለት ለማገለጽ እንደተሞከረው አንድ ፈተና አስተማማኝ (Valid) ነው የሚባለው መመዘን የሚገባውን ነገር በትክክል መመዘን የቻለ እንደሆነ ነው::

አንድ ፈተና አስተማማኝ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ደግሞ ሁሉንም የአስተማማኝነት ገጽታዎች መዳሰስ አስፈላጊ ይሆናል:: ይሁን እንጂ የችሎታ መለኪያ

ፈተናዎችን (ይህ ጥናት የሚመለከተው መሆኑ ሊታወስ ይገባል) አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ላህያዊና የይዘት አስተማማኝነትን ብቻ መመልከቱ በቂ እንደሆነ ዴቪስ (1984) ይመሰክራሉ። በዚህም መሠረት ጥናቱ በላህያዊና በይዘት አስተማማኝነት ላይ በማትኮር ትንታኔውን እንደሚከተለው ያቀርባል።

## 4.1.1. ላህያዊ አስተማማኝነት ( Face Validity)

አንድ ፈተና ላህያዊ አስተማማኝነት አለው ለመባል ፈተናው መመዘን የሚገባውን ነገር በትክክል መመዘን መቻል ብቻ ሳይሆን ትክክል ወይም ተገቢ የመምሰል ባህሪም ሊኖረው ይገባል። በሌላ አገላለጽ ፈተናው ተማሪዎችና መምህራን የሚቀበሉት ዓይነት ሲሆን ላህያዊ አስተማማኝነቱ ጥሩ ነው ይባላል። ይህንን ለማረጋገጥ ደግሞ መጠይቅ ፣ቃ ለ መጠይቅ ፣ ውይይትና የመሳሰሉትን ዘዴዎች መጠቀም እንደሚቻል በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል።

በዚህም መሠረት ከስምንቱ ዓመታት ፈተናዎች ውስጥ የ1987 ዓ.ም. ፈተናን በመምረጥ ላህያዊ አስተማማኝነቱን ለመመርመር ተሞክሯል። ይህ ፈተና የተመረጠበት ምክንያት ተፈታኞችንና መምህራንን በቀላሉ ለማግኘት አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ለተማሪዎቹና ለመምህራን መጠይቅ ፣ ለአማርኛው ፓናል ኃላፊ ደግሞ ቃ ለ መጠይቅ በማቅረብ የተገኘው የትንታኔ ውጤት እንደሚከተለው ይቀርባል።

ለተማሪዎች በቀረበው መጠይቅ ውስጥ ካላህያዊ አስተማማኝነት ጋር የተያያዙ ስምንት ጥያቄዎች ቀርበዋል/ ዝርዝሩን በአባሪ ሠ ይመለከቷል/ ። እነሱም በመጠይቁ ተራ ቁጥር 1-8 ላይ ይገኛሉ ። መጠይቁን የሞሉት ተማሪዎች 30 ሲሆኑ ለየጥያቄው የሰጡት መልስም የሚከተለውን ይመስላል።

ለመጀመሪያው ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተፈታኞች 37.3% ፈተናው የምማረውን የአማርኛ ትምህርት በማንጸባረቅ ችሎታዬን ለመመዘን ጥሩ ነው ብለዋል ። ይህም ተፈታኞቹ ለፈተናው ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው የሚጠቁም ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ለመምህራን በቀረበው መጠይቅ ተራ ቁጥር 11 ውስጥ ተመሳሳይ ጥያቄ ተጠይቆ 84 % የሚሆኑ መላሾች ፈተናው የተማረውን ችሎታ ለመለካት ተገቢ አለመሆኑን አረጋግጠዋል። የአማርኛው ፓናል ኃላፊ መልስም ከመምህራኑ አመለካከት ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ ተፈታኞቹ ፈተናው ተገቢ ይመስላል ሲሉ መምህራኑና የአማርኛው ፓናል ኃላፊ ግን ተገቢ አይመስልም ብለዋል።

ለሁለተኛው ጥያቄ 43.3 % የሚሆኑ ተፈታኞች ፈተናው ይከብደናል ሲሉ 23.3 % የሚሆኑት ደግሞ ቀላል ነው ብለዋል ፡፡ መልስ የለኝም ያሉት 33.4% ናቸው ፡፡እነዚህ ተፈታኞች ፈተናውን በመካከለኛ ደረጃ የሚመለከቱት ይመስላል፡፡

ለሦስተኛው ጥያቄ አብዛኞቹ ተፈታኞች / 80% / ስምምነታቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህም ማለት ተፈታኞቹ የቃ ላት ጥያቄዎችን በትክክል ለመመለስ የተቸገሩበት እንዱ ምክንያት ቃላቱ ለተማሪው አካባቢ እንግዳ በመሆናቸው ነው ማለት ነው፡፡

ለአራተኛው ጥያቄ አብዛኞቹ ተፈታኞች / 86.6% / ስምምነታቸውን ገልጸዋል ፡፡ ይህም ቃ ላትና ፈሊጦችን በትክክል ለመመለስ የተቸገሩበት እንድ ምክንያት በክፍል ውስጥ ቃ ላትና ፈሊጦችን አለመማራቸው መሆኑን የሚገልጽ ነው ፡፡ ይህ የተፈታኞች መልስ ከጥያቄ 1 መልስ ጋር የሚጋጭ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኞቹ መምህራን /ለጥያቄ12እና 13 በሰጡት መልስ / የፈተናዎቹ የቃ ላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በክፍሉ ውስጥ ከማስተማራያቸው ቃ ላትና ፈሊጦች ጋር የጠበቀ ዝምድና የላቸውም ካሉት ጋር የሚስማማ ነው ፡፡

ለአምስተኛው ጥያቄ አብዛኞቹ ተፈታኞች /76.6 %/ የማይስማሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህም ማለት ቃ ላትና ፈሊጦቹን ያለአውድ መቅረባቸው ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ ችግር አልሆነባቸውም ማለት ነው፡፡ በአንጻሩ አብዛኞቹ መምህራን እና የጋናሉ ኃላፊ ቃ ላትና ፈሊጦችን ያለአውድ እያቀረቡ መፈተን ጉልህ ችግር መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

ለስድስተኛው ጥያቄ ተፈታኞች የሰጡት መልስ ግማሽ በግማሽ ነው ማለት ይቻላል፤ ይኸውም 53.3% የሚሆኑት የአማራጭ መልሶቹ አሻሚ መሆን ትክክለኛው መልስ ለመምረጥ አስቸግሮናል ሲሉ 47.7% የሚሆኑት ደግሞ ችግር አልፈጠረብንም ብለዋል፡፡ ለሰባተኛው ጥያቄ ደግሞ የአብዛኞቹ ተፈታኞች መልስ /70%/ አሉታዊ ነው፡፡ ይህም ማለት የፈተናዎቹ የቃ ላትና የፈሊጥ ጥያቄዎችን በትክክል ለመመለስ ትምህርቱን በሚገባ አለመማርና አለማጥናት እንደችግር አልተቆጠረም ማለት ነው፡፡ ይህ የተፈታኞች መልስ ከጥያቄ 5 ጋር የሚመሳሰል ይመስላል፡፡

የመጨረሻው ጥያቄ ስለፈተናው የቃ ላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡ የሚጋብዝ ነበር ፡፡ አብዛኞች ተፈታኞች /80%/ የባላገር ቃ ላትን በመጠ

የቃ ችን ግራ ገበቶናል"እና " ፈተናው በአዲስ አበባ አማርኛ ላይ ቢያተኩር ጥሩ ነው "የሚል አስተያየት ሰጥተዋል። ይህም ለፈተናው የቃ ላትና የፊሊጥ ጥያቄዎች ጥሩ አመለካከት እንደሌላቸው የሚጠቁም ይመስላል።

ለማጠቃ ለል አብዛኞቹ ተፈታኞች በጥቅሉ ለፈተናው ጥሩ አመለካከት ስላላቸው ላህያዊ አስተማማኝነት ያለ ይመስላል። ሆኖም አብዛኞቹ ተፈታኞች ለፈተናው የቃ ላትና የፊሊጥ ጥያቄዎች ጥሩ አመለካከት ስለሌላቸው የጥያቄዎቹን ላህያዊ አስተማማኝነት አጠያያቂ ያደርገዋል። በሌላ በኩል አብዛኞቹ መምህራንና የፓናሉ ኃላፊ ፈተናው በጥቅልም ሆነ የቃ ላትና የፊሊጥ ጥያቄዎች በዝርዝር የተማሪውን ችሎታ ለማንጸባረቅ ተገቢ አይደሉም ስለሚሉ ላህያዊ አስተማማኝነት ያለመጠበቁን ይመሰክራሉ። ስለዚህ የፈተናዎቹን የይዘት አስተማማኝነት በጥልቀት መመርመር አስፈላጊ ይመስላልና ወደዚያው እናመራለን ።

## 4.1.2. የይዘት አስተማማኝነት(Content Validity)

አንድ ፈተና የይዘት አስተማማኝነት አለው የሚባለው የትምህርት ይዘቶች ተመጣጣኝና ወካይ በሆኑ ናሙናዎች ሲቀርብ ነው ።ከዚህም በተጨማሪ የፈተናዎቹ ጥያቄዎች የሚቀርቡበት የአቀራረብ ስልት ለይዘት አስተማማኝነት ግምገማው መለኪያ ይሆናል። /ሂዩዝ፣1989፣ሂተን ፣1975 እና ባችማን፣ 1990/ ከዚህ መሠረት ሃሣብ በመነሳት የፈተናዎቹን የይዘት አስተማማኝነት ለመመርመር ተሞክሯል። በዚህም ቋንቋውን ለረጅም ጊዜ ያስተማሩ መምህራንን አስተያየት፣ የፓናሉን ኃላፊ አመለካከት፣የማስተማሪያ መሣሪያዎቹን ዓላማና ይዘቶች እና ተፈታኞቹን በመረጃ ምንጭነት ተጠቅመናል። መምህራኑ በክፍል ሁለት ለቀረቡት ጥያቄዎች የሰጡት መልስ አግባብነት ባለው ቦታ ሁሉ ተተንትኖአል። ሆኖም በክፍል አንድ የሰጡት መልስ ቀጥሎ በመግቢያ መልክ ይቀርባል።

ለመምራን በቀረበው መጠይቅ ክፍል አንድ ውስጥ የመምህራኑ የት/ ደረጃ ፣አማርኛን በሁለተኛ ደረጃ ያስተማሩባቸውን ዓመታት ብዛት፣አሁን የሚያስተምሩበትን የክፍል ደረጃ ወዘተ ጥያቄዎችን በማቅረብ ዳራቸውን (Back ground) ለማወቅ ተሞክሯል። የመምህራኑ መልስ እንደሚያመለክተው 38ቱ መምህራን የቢ.ኤዲግሪ ያላቸው ሲሆኑ 12ቱ ደግሞ ዲፕሎማ ዲግሪ አላቸው። አማርኛን በሁለተኛ ደረጃ ያስተማሩባቸው ዓመታት በአማካይ 18 ነው። ትንሹ የአገልግሎት ዘመን 12 ሲሆን ትልቁ ደግሞ 29

ዓመት ነው። በተጨማሪም አብዛኞቹ መምህራን በሁሉም የክፍል ደረጃዎች አማርኛን እንዳስተማሩ አረጋግጠዋል። ሂዩዝ /1989/ የይዘት ግምገማ ሲከናወን ቋንቋውን ለረጅም ጊዜ ያስተማሩ መምህራን ቢሳተፉበት መልካም ነው ይላሉ ። ስለዚህ እነዚህ መምህራን በክፍል ሁለት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሚሰጡት መልስ ጠቃሚ ነው ተብሎ ይታመናል።

በይዘት አስተማማኝነት ግምገማ በመጀመሪያ የሚታየው የትምህርት ይዘቶች ተመጣጣኝ በሆነ መልክ በፈተናው ውስጥ መንጸባረቅ አለመንጸባረቃ ቸውን መመርመር ነው። ይህንን ለመመርመር ደግሞ ሲለበሶችና መማሪያ መጻሕፍቱ የሚያቀርቧቸውን የትምህርት ይዘቶች ማመሳከር ያስፈልጋል። የሲለበሶቹንና የመማያ መጸሐፎችን ይዘቶች በ10፣ የፈተናውን ይዘቶች ደግሞ በ6 ማጠቃ ለል ይቻላል። ዝርዝር የማመሳከሩ ተግባር የዚህ ጥናት ትኩረት ባይሆንም የሚከተለውን ሠንጠረዥ በመመልከት ጥቅል መረጃ ማግኘት ይቻላል።

ሰንጠረዥ 2 የትምህርት ይዘቶች በማስተማሪያ መሣሪያዎችና በፈተናዎች ያላቸውን ውክልና በመቶኛ የሚያሳይ።

| ተ.ቁ | የትምህርት ይዘት | በሲለበሶች ይዘትነት | | በመማሪያመጽሀፍት መልመጃነት | | በፈተናዎች ጥያቄነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቀ | አ | ቀ | አ | ቀ | አ |
| 1 | ቃላት | 24.7 | 20.7 | 36.4 | 44.7 | 26.2 | 29.6 |
| 2 | ፈሊጦች | – | – | 0.3 | 2.7 | 10.8 | 14.4 |
| 3 | አገባብና አጻጻፍ | 6.9 | 15.1 | – | 15.7 | 7.8 | 13.9 |
| 4 | ተረትና ምሣሌ | 2.3 | 1.9 | – | 1.9 | 11.4 | 9.3 |
| 5 | ቅኔ | 2.3 | 1.9 | – | 0.8 | 8.3 | 7.4 |
| 6 | አንብቦ መረዳት | 30.2 | 26.4 | 38.1 | 28.1 | 35.5 | 25.4 |
| 7 | መናገር | 4.6 | 11.3 | 11.7 | 3.2 | – | – |
| 8 | መጻፍ | 19.8 | 17.0 | 12.7 | 3.8 | – | – |
| 9 | ማዳመጥ | 2.3 | 1.9 | 0.4 | 0.1 | – | – |
| 10 | ዕውቀት አዘል | 6.9 | 3.8 | – | – | – | – |
| | ድምር | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

* ዕውቀት አዘል የተባለው የቋንቋ መሠረታዊ ጠባዩችን ፣የግጥምና የልብ ወለድ ባህርያትን የሚያቀርበው የትምህርት ይዘት ነው ።ይዘቱ በመማሪያ መጸሀፍቱ ውስጥ በአንብቦ መረዳት ተጠቃሏል። በፈተናዎቹ ይዘት ውስጥ ግን አይታይም።

* በሲለበሶችና በመማርያ መጻህፍቱ ውስጥ አንድ ይዘት በመቶኛ የተተመጠው የክፍል ደረጃው /ከ9ኛ-12ኛ/ ያሉት ይዘቶች ተቆጥረው ለአራት ከተካፈሉ በኋላ ወደ መቶኛ በመለወጥ ነው ::

* የትምህርት ይዘቶች በቀድሞቹ ፈተናዎች /1980-83 ዓ.ም/ በጥያቄነት የቀረቡትን በመቶኛ በዝርዝር የሚመለከት ሲሆን በአሁኖቹ ፈተናዎች ያለውም ዝርዝር ቀጥሎ መቅረቡን ያጤኗል።

ከሠንጠረዥ 2 መረዳት እንደሚቻለው አንዳንድ የትምህርት ይዘቶች ተመጣጣኝነት ባለው መንገድ ሲወከሉ ቀርቶ በፈተናው ውስጥ ፈጽሞ አይታዩም። እነዚህም ይዘቶች ማዳመጥ፣መናገር፣መጻፍና የእውቀት አዘል ናቸው። በአንጻሩ አንዳንድ ይዘቶች ደግሞ ተመጣጣኝነት ባለው መንገድ ሲወክሉ እናገኛለን። ለምሳሌ የቃ ላትና አንብቦ የመረዳት ይዘቶች በማስተማሪያ መሳሪያዎች የተሰጣቸውን ትኩረት ያህል በፈተናዎችም ውስጥ ትኩረቱ እንዳልተነፈጋቸው ሰንጠረዥ ያመለክታል። በሌላ በኩል ግን የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ በቂ ትኩረት ሳልሰጧቸው ይዘቶች የፈተናው ይዘቶች ትኩረት ሲሰጧቸው እናገኛለን። እነዚህም ይዘቶች ቅኔ፣ ተረትና ምሳሌ፣ ፈሊጦች እና አገባብና አጻጻፍ ናቸው።

እንደ ሂዩዝ/1989/ እና ሂተን/1975/ እምነት የትምህርት ይዘቶችን ተመጣጣኝነት ለመጠበቅ ለእያንዳንዱ የትምህርት ይዘት በማስተማሪያ መሳሪያዎቹ የተሰጠውን ትኩረት በሰንጠረዥ መንደፍ እንዲሁም በማስተማሩ ሂደት ለይዘቱ የተሰጠውን ትኩረት ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ከላይ በሰንጠረዥ 2 ለማሳየት እንደተሞከረው ግን ፈተናዎቹ ይህን መርህ የሚያከብሩ አይመስሉም። ምክንያቱም ለአንዳንድ የትምህርት ይዘቶች የማስተማሪያ መሳሪያዎች በቂ ትኩረት ቢሰጡም ይዘቶቹ በፈተናዎች ውስጥ ፈጽሞ አይታይም። በሌላ በኩል ደግሞ የማስተማሪያ መሳሪያዎች በቂ ትኩረት ሳልሰጧቸው ይዘቶች ፈተናዎቹ ከፍተኛ ትኩረተ ሲሰጡ ይታያሉ። ስለዚህ የትምህርት ይዘቶች /ከጥቂት የትምህርት ይዘቶች በስተቀር/ በፈተናዎቹ ውስጥ ተመጣጣኝነት ባለው መንገድ እንዳልተወከሉ የትንታኔው ውጤት አመልክቷል።

የዚህ ጥናት ትኩረት በቃ ላት /ፈሊጦችን ይጨምራል/ ትምህርት አሰጣጥና አፈታተን ላይ እንደመሆኑ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች ተመጣጣኝነትና ወካይነት ባለው መንገድ በፈተናዎቹ ውስጥ መካተት አለመካተታቸውን በጥልቀት መመርመር አላስፈለገም። ስለዚህ በጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ላይ በማተኮር የአማርኛ የቃ ላት ትምህርት አሰጣጥ ምን መልክ አለው? የፈተናዎቹስ የአቀራረብ ስልት ምን ይመስላል? የአፈታተኑ መሰረት

የትምህርት አሰጣጡ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመለስ የይዘት አስተማማኝነት መጠበቅ አለመጠበቁን ለማረጋገጥ ይሞክራል።

. በሌላ አገላለጽ የአማርኛ የቃ ላት ትምህርት አላማ ምንድን ነው? ለአላማው ምን ምን ይዘቶች ተመርጠዋል? የትምህርት መሳሪያዎቹ የቃ ላትን ትምህርት የሚያቀርቡት መንገድ ምን ይመስላል? መምህራኑስ የሚያስተምሩበት ዘዴ ምንድን ነው? የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. የቃ ላት ጥያቄ አላማ የትምህርቱን አላማ ከዳር ለማድረስ ተገቢ ነው? የአቀራረብ ስልቱስ በማስተማሪያ መሳሪያዎች የቀራረብ ስልት ላይ የተመሰረተ ነው ወይስ የተለየ? በፈተናዎቹ አንድ ቃል ወይም ፈሊጥ በጥያቄነት የሚመረጠው በምን መስፈርት ነው? ወዘተ... ጥያቄዎችን ስንመልስ የይዘት አስተማማኝነት መጠበቅ አለመጠበቁን ለማረጋገጥ እንችላለን።

ከላይ ያነሳናቸው ጥያቄዎች በርካታ እንደመሆናቸው አንዳንድ ጊዜ በተናጠል ሌላ ጊዜ በቅንጅት ለመመለስ እንሞክራለን። በመጀመሪያው ጥያቄ እንጀምር። ለመሆኑ የአማርኛ የቃላት ትምህርት አላማ ምንድን ነው?

በቀድሞዎቹም ሆነ በአሁኖቹ ሲለበሶች አጠቃ ላይ ዓላማ ውስጥ ስለቃ ላት ትምህርት የተነደፈ ዓላማ የለም። ሆኖም በሁለቱም ሲለበሶች ዝርዝር ዓላማ ውስጥ የቃ ላት ትምህርት /ፈሊጦችን አይጨምርም / ሰፊ ቦታ ተሰጥቶት እናገኛለን። የተነደፉትን ዝርዝር ዓላማዎች በሚከተሉት ነጥቦች ማጠቃ ለል ይቻላል። /በዝርዝር ለመረዳት ደግሞ አባሪ ሐን ይመለከቷል/

- የቃላት ችሎታውን ያዳብራል።
- የቋንቋውን አስካክ ያውቃል።
- ምዕላዶችን ያውቃል።
- የሥነጽሁፍ ችሎታውን ያዳብራል ።
- ድርሰት መጻፍ ይችላል።
- ቋንቋ ነክ ሃሳቦችን ያዳብራል።

እነዚህን ዓላማዎች በመመልከት ብቻ የቃ ላት ትምህርቱን ዓላማ ለማወቅ ያዳግታል። ዓላማው ይብልጥ ግልጽ የሚሆንልን ይዘቶችንና የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውኖችን (activities) ስንመለከት ነው። የሚከተለው ሠንጠረዥ ለቃ ላት ትምህርት የተነደፉትን ይዘቶች ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 3 ሲለበሶቹ በቃ ላት ትምህርት የነደፏቸውን ይዘቶች በክፍል ደረጃ የሚያሳይ፡፡

| ይዘት | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀ | አ | ቀ | አ | ቀ | አ | ቀ | አ |
| 1. የቃላት አመሰራረት | X | X | X | X | X | X | X | X |
| 2. የቃላትን ትርጉም ከአገባብ መረዳት | X | X | X | X | X | X | X | X |
| 3. በውስጠ ታዋቂነት የቀሩ ሐሳቦችን የሚገልጹ ቃላት የጎደላቸውን ዐ.ነገሮች መለየት | X | X | X | X | X | X | X | X |
| 4. የቃላት በስርዓት መደርደር የትርጉም ለውጥ ምጣት | X | X | X | X | X | X | X | X |
| 5. የቃላት ቀጥታ ትርጉም | X | X | X | X | X | - | - | - |
| 6. ቃላትን አገጣጠም ዐ.ነገር መጻፍ | X | X | X | X | X | - | - | - |
| 7. ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት | X | X | X | X | X | - | - | - |
| 8. በቃል ውስጥ የድምፅ መጥበቅና መላላት | X | X | X | X | X | - | - | - |

(–) ይህ ምልክት ያለባቸው ይዘቱ በክፍል ደረጃው አለመኖሩን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

(×) ይህ ምልክት ያለባቸው ደግሞ ይዘቱ በክፍል ደረጃው መኖሩን ያመለክታሉ፡፡

በሰንጠረዥ 3 ከተዘረዘሩት ዋና ዋና የቃ ላት ትምህርት ይዘቶች በተጨማሪ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውኖቹ የማስተማሪያ ዘዴውን ሲጠቁሙ እናገኛለን፡፡ በሁለቱም ሲለበሶች የተዘረዘሩትን ክንውኖች በዝርዝር ማቅረቡ የሚፈጀውን ጊዜና ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ዋና ዋናዎቹንና ለአብነት የሚሆኑትን ብቻ እንጠቅሳለን፡፡

አንድ ቃ ል በቀጥታና በአገባብ ትርጉም የሚገኝበትን ሁኔታ ስጥቶ ተማሪዎች የቃ ሉን ቀጥተኛና አገባባዊ ትርጉም ለይተው ማውጣት እንዲችሉ ማድረግ፡፡

የአንድ ቃ ል አገልግሎት ከቀጥታ ትርጉም ይልቅ የአገባብ ትርጉም ይበልጥ የሰፋና ጠቃሚ መሆኑን ማስገንዘብ፡፡

በዐ.ነገር ውስጥ የማያስፈልግ የቃ ላት መደጋገም ጽሁፉንም ሆነ ንግግርን እንደሚያበላሽ አስገንዝቦ ድግግሞሹን ለማስቀረት በተለያዩ መለመጃዎች ማስተማር፡፡

ለደረጃው ከሚመጥን ጽሁፍ ውስጥ በውስጠ ታዋቂነት የቀሩ ሀሳቦችን የሚገልጹ ቃ ላት ያጎደሏቸውን ዐ.ነገሮች ለይተው እንዲያወጡና ማሟያዎችን ልዩ ልዩ ቃ ላትም እንዲሰጡ ማድረግ፡፡

ዐ.ነገሮችን አቅርቦ ከውስጣቸው የተወሰኑ ቃ ላትን በማውጣት በአገባቡ መሰረት ለቃላቱ ትክክለኛ ትርጉም መስጠት እንዲችሉ ማድረግ፡፡

ባዶ ስፍራ ያላቸውን ዐ.ነገሮች ሰጥቶ ተማሪዎች ቀጥሎ ባሉት ምሳሌዎች መሠረት አሟልተው እንዲያቀርቡ በማድረግ ማለማመድ፡፡

ምሳሌ 1. ላሟ ወተት —፡፡ /ጠጣች፣ታለበች፣አፈሰሰች/.

የሲለበሶችን ዝርዝር አላማ ይዘት እና ክንውኖች በውህደት በመመልከት የአማርኛ የቃ ላት ትምህርት አላማ ምን እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ አላማው ባጭሩ ለቋንቋው ክሂል አዘል እና ዕውቀት አዘል ዘርፎች መዳበር የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ይመስላል፡፡ ይህም ማለት ተማሪው ቃ ላትን እንዲማር የሚፈለግበት ዋና አላማ በተለየ ሙያ ለመሰልጠን የሚያስፈልጉ ሙያነክ ቃ ላትን /Technical words/ እንዲያውቅ ሳይሆን ተራ ቃ ላትን /Common words/ አውቆ አጠቃ ላይ የተግባቦት ክህሎትን እንዲያዳብር ነው ማለት ነው፡፡

በሌላ አገላለጽ የቃ ላት ትምህርቱን ዓላማ አጠቃ ላይ የትምህርቱ ዓላማ በመመርኮዝ ተማሪው በቋንቋው ጥሩ አድማጭ፣ ተናጋሪ ፣አንባቢና፣ ጸሐፊ እንዲሆን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሣሌ የቃ ላት ትምህርት ከማንበብ ክሂል ጋር ስለሚዛመድ ተማሪው በሚያነብበት ወቅት የሚያጋጥሙትን አዳዲስ ቃ ላት ከአውዳቸው እንዴት እንደሚፈታቸው በማስተማር የንባብ ክሂሉን ለማዳበር አንድ መንገድ ይሆናል፡፡

ሲለበሶቹ ተደጋጋሚ የቃላት ዝርዝር /List/ ስለማያቀርቡ ተማሪው የትኞቹን ቃላት በትኩረት መማር እንዳለበት አይቁሙም። እንዲሁም ሲለበሶቹ ስለፈሊጦች ትምህርት በዓላማዎቻቸው፣ ይዘቶቻቸውና ክንውናቸው የሚያነሱት ነጥብ ስለሌለ የፈሊጦችን ትምህርት ሀላማደ በግልፍ ለመረዳት ያዳግታል። ይሁን እንጂ ፈሊጦችኝ የቃላት አንድ ክፍል ለሆኑ ለቃላት ትምህርት የተነደፈው ዓላማ ለፈሊጦችም እንደሚያገለግል ይገመታል።

ከዚህ በላይ የአማርኛ የቃላት ትምህርት ዓላማ ምንድነው? የሚለውን ጥቄ በሲለበሶች አማካይነት ለመመለስ ተሞሯል። ቀጥለን ደግሞ የመማሪያ መጻሕፍቱን የቃላት ትምህርት አሰጣጥና የአቀራረራ ስልት ለመመልከት እንሞክራልን። መማሪያ መጻሕፍቱ የቃላት /የፈሊጦች ትምግትርንፀ የሚያቀርቡት በመልመጃዎቻቸው አማካይነት ነው። ምንም እንኳን በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ቀረቡት የቃላት /ፈሊጦች ዝርዝር በአባሪ ለ የቀረበ ቢሆንም በየመልመጃው መመሪያ የቀረቡትን ቃላት፣ ቁጥርና የአቀራረቡብስልት ለማወቅ የሚከተለውን ሰንጠዥ መመልከቱ ይጠቅማል።

ሰንጠረዥ 4 የቀድሞቹ /ቀ/ እና የአሁኖቹ /አ/ መማሪያ መጻሕጽፍት ስለቃላት /ፈሊጥ ተምህርት ያነሳቸውን ነጥቦች በቁጥርና በክፍል ደረጃ የሚያሳይ።

| | የመልመጃው መመሪያ ወይም የተነሳው ነጥብ | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | | ድምር | | የመምሪያው ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቀ | አ | ቀ | አ | ቀ | አ | ቀ | አ | ቀ | አ | |
| 1 | በሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች ዐ.ነገት ሠርተህ አሳይ | 69 | 59 | 101 | 50 | 12 9 | 44 | 32 | 56 | 331 | 209 | 540 |
| 2 | ለሚከተሉት ቃላት ፍች ስጥ | 6 | 85 | 30 | 74 | 30 | 74 | 3 | 32 | 69 | 265 | 334 |
| 3 | በጥንዱ ቃላት መካከል ያለውን የፍቺ ልዩነት አስረዳ ወይም በዓ.ነገት አስገብተህ አሳይ | 22 | 26 | 12 | 10 | 12 | 46 | 61 | 677 | 107 | 149 | 256 |
| 4 | ቃላትን አዛምድ | 15 | 30 | 11 | 31 | | 17 | 43 | 34 | 69 | 112 | 181 |
| 5 | ከተጠቀሱት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ መልስ ምረጥ። | 35 | 26 | 14 | 44 | 7 | 1 | | 12 | 56 | 83 | 139 |
| 6 | ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ስጥ። | | | 1 | 2 | 2 | 17 | 2 | 34 | 5 | 53 | 58 |
| 7 | ሌሎች ልዩ ልዩ መምሪያዎች /ለምሳሌ የተለየው ቃል አውጣ፣ ቃላትን መሥርት ወዘተ..../ | 29 | 8 | 18 | | | 29 | 13 | 2 | 60 | 39 | 99 |
| | ጠቅላላ ድምር | | | | | | | | | 697 | 910 | 1607 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው መማሪያ መጻሕፍቱ ለቃላት ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተዋል። የቀድሞዎቹ መማርያ መጻሕፍት 692 ቃላትን እንዲሁም የአሁኖቹ መማርያ መጻሕፍት 857 ቃላትን ለልምምድ ማቅረባቸው ይህንኑ የሚጠቁም ነው። በአንፃሩ መማሪያ መጻሕፍቱ ለፈሊጦች ትምህርት ዝቅተኛ ትኩረት ሰጥተዋል። በቀድሞዎቹ 5 ፈሊጦች፣ በአሁኖቹ ደግሞ 53 ፈሊጦች መቅረባቸው ይህንኑ ይጠቁማል ። የየመምሪያው ዝርዝር አቀራረብ የሚከተለውን ይመስላል።

ሰንጠረዡ እንደሚያመለክተው በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው መልመጃ ዐ. ነገር ሥራ የሚለው ነው። ዐ.ነገር ሰርተህ አሳይ በሚለው መመሪያ ስር ተማሪው ዐ.ነገር የሚሰራው በምንባቡ መሠረት፣ ከምንባቡ ውጭ፣ ቃላቱ ሲጠብቁና ሲላሉ በሚሰጡት ፍቺ፣ የቃላቱን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በመስጠት እና ቃላቱ ከአንድ የበለጠ ፍች እንዲሰጡ በማድረግ ነው። ይህ ዓይነቱ የቃላት ልምምድ ለውጤታማ /Productive/ የቃላት ትምህርት አሰጣጥ ጠቃሚና ተገቢ መሆኑን ማድስን /1983/ ይመሰክራሉ። ከሌሎች መምሪያዎች ይልቅ መማሪያ መጻሕፍቱ ውጤታማ ለሆነው ልምምድ ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸው ትምህርቱ በተግባራዊ ልምምድና የተግባቦት ችሎታ ላይ መመስረቱን የሚጠቁም ነው።

የመልመጃዎቹ መምሪያዎች በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ ቁጥር /69/ ቀ/ እና 265 /አ/ በድምሩ 334/ ያላቸውን ቃላት የሚያቀርቡት የቃላትን ፍቺ ስጥ በሚል ነው። በዚህ ስር ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ ስጥ፣ የቃላቱን ፍቺ አብራራ እና በራስህ አባባል ግለጽ የሚሉ መምሪያዎችን እናገኛለን። በመልመጃነት የቀረቡት ቃላት በሙሉ ከተለያዩ ምንባቦች የወጡ ናቸው። በዚህም ተማሪው ቃላት በተለያየ አውድ ውስጥ ሲገቡ የሚሰጡትን ፍቺ ይለማመዳል። የአቀራረብ ስልቱ ማድስን /1983/ እና ሂተን /1975/ የቃላት ትምህርትና ፈተና ከአንብቦ መረዳት ክሂል ጋር ተዳብሎ ቢሰጥ የንባብ ክሂልን ያዳብራል የሚሉትን የሚያሟላ ነው።

በመመሪያ ሦስት የቀረቡት ጥንድ ቃላትን የመፍታት መልመጃዎች በስራቸው ዐ.ነገር ሠርተህ አሳይ፣ ፍቺያቸውን ግለጽ ወዘተ...መምሪያዎች ስላሉት ከመምሪያ አንድና ሁለት ጋር አዛምድ፡፡ የዚህ መምሪያ አይነተኛና ልዩ ጠባዩ ተቀራራቢ የሆኑ ቃላትን በማቅረብ ተማሪው በቃላቱ መካከል ያለውን የፍች አንድነትና ልዩነት እንዲገነዘብ መታቀዱ ነው፡፡ ለምሳሌ ማዳመጥ እና መስማት ተቀራራቢ ቃላት ናቸው በእነዚህ ቃላት መካከል ያለውን የፍች ተመሳሳይነትና ልዩነት እንዲያውቅ ዐ.ነገር ይሰራል፡፡ ስው ይጠይቃል ወይም መረጃ መጻህፍትን ተጠቅሞ ፍችያቸውን ያብራራል ወይም ይገልጻል፡፡ በመልመጃው ውስጥ ከሚቀርቡት ተቀራራቢ ቃላት ቢያንስ አንዱ በምንባቡ ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህ ዓይነቱ አቀራረብ ተማሪው በሚናገርበትንና በሚጽፍበት ጊዜ የትኛው ቃል ለንግግሩ ወይም ለጽሁፉ ይበልጥ የሚስማማ መሆኑን እንዲያውቅ ስለሚረዱት ሲለበሱ ለነደፈው ዓላማ ተገቢ መልሥጃዎች ይመስላሉ፡፡

በአራተኛው መምሪያ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ የሚለውን እናገኛለን ፡፡ በዚህ መምሪያ ስር ቃሉ በአረፍተ ነገር ውስጥ ቀርቦ ይሰመርበትና ለቃሉ ተመሣሣይ ወይም ተቃራኒ ፍች እንዲሰጥ መጠይቅ ፣ በዐ.ነገር ውስጥ አንድ ቃል ጎድሎ ወይም ከፍት ቦታ ተሰጥቶ ይቀርብና የጎደለውን ቃል በትክክል የሚያሟላ የትኛው እንደሆነ መምረጥ ፣ እና የመሳሰሉት መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ በዚህም መልመጃ የሚቀርቡት አብዛኞቹ ቃላት ቢያንስ ዐ.ነገራዊ አውድ ስላላቸው ተማሪው ቃላትን ከአውድ የመፍታት አቅሙን ለማጎልበት የታቀዱ መሆናቸው አያጠያይቅም፡፡

በስድስተኛው መምሪያ ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ስጥ የሚል እናገኛለን ፡፡ በዚህ መምሪያ ስር 58 ፈሊጦች መቅረባቸውን ሠንጠረዥ ያመለክታል፡፡ሆኖም ከቀድሞዎቹ መማርያ መጻህፍት መልመጃዎች ውስጥ ይህን መምሪያ በየትኛውም የክፍል ደረጃ አናገኘውም፡፡ የቀረቡት 5ፈሊጦችም አባባሎች በሚል በመምሪያ ሁለት ከቀረቡት የተለቀመ ፈሊጦች ናቸው ፡፡ በአሁኖቹ የ9ኛ ና የ10ኛ ክፍል መልመጃዎች መምሪያውን አናገኘውም ፡፡ ስለዚህ የቀድሞዎቹ መማሪያ መጻህፍትና የአሁኖቹ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት ሆን ብለው ፈሊጦችን አያለማምዱም ማለት ይቻላል፡፡

በአንጻሩ የአሁኖቹ የ11ኛ ና የ12ኛ ክፍል መልመጃዎች 51 ፈሊጦችን በመመሪያ ስድስት አማካኝነት በማቅረብ ሆን ብለው ፈሊጦችን ያለማምዳሉ ፡፡ የፈሊጦች ልምምድ በ11ኛ ክፍል የተጀመረበት ምክንያት ግልጽ ካለመሆኑም በላይ ልምምዱ

በአውድ ላይ ላለማትኩሩ ምክንያት ማግኘት የሚያስቸግር ይመስላል:: የፈሊጦች ልምምድ አነስተኛ ከመሆኑ ባሻገር የቃ ላት ትምህርቱን ዓላማ ለማዳበር የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ በግልጽ ለማየት ያዳግታል::

በሰባተኛው መመሪያ ልዩ ልዩ መምሪያዎች የሚል እናገኛለን :: በዚህ መምሪያ ስር የተለየውን ቃ ል አውጣ ፤ የስም ገላጮችን ስጥ ፤ቃ ላትን መስርት ና አርባ በሚል 99ቃ ላት መቅረባቸውን ሰንጠረዥ ያመለክታል:: በዚህ መምሪያ የቀረቡት መልመጃዎችም ለቃ ላት ትምህርቱ አላማ መዳበር ጠቃ ሚ ይመስላሉ :: ለምሳሌ የተለየውን ቃ ል አውጣ በሚል መመሪያ ከሚቀርቡት ቃ ላት መካከል አንዱ ቃ ል በፍቺ ወይም በአገባብ ስለማይዛመድ ቃ ሉን ማመልከት ተፈላጊው ነጥብ ነው:: ዋላስ /1982/ አንድ ሰው ቃ ላትን አወቀ ሲባል የሚዛመዱና የሚቀራረቡ ቃ ላትን አወቀ ማለት ነው ባሉት መሠረት ይህ መልመጃ ጠቃሚ ይሆናል::

ከዚህ በላይ መማሪያ መጽሀፍቱ ስለቃላት /ፈሊጦች ትምህርት ያነሷቸውን ነጥቦችና የአቀራረብ ስልታቸውን ለማመልከት ሞክረናል:: ቀጥለን ደግሞ የሁ.ደ.መ.አ.ፈ.የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎችን የአቀራረብ ስልት ለማመልከት እንሞክራለን::

በስምንቱ አመታት ፈተናዎች የተጠየቁት ጥያቄዎች ጠቅላላ ብዛት 655 ነው:: ከእነዚህ ውስጥ 269 ወይም 41.1% የሚሆኑት የቃ ላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ስለሆኑ ጥናቱ የሚመለከታቸው ናቸው:: ሁሉም የቃ ላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በምርጫ ስልቢ የጥያቄ አቀራረብ ስልት የቀረቡ ቢሆኑም ጥያቄዎቹ በአውድ ውስጥ/With Context/ እና ያለአውድ (With out Context) ሲቀርቡ ተስተውሏል:: የየፈተናዎቹን የቃ ላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ዝርዝር የአቀራረብ ስልት ለመረዳት የሚከተለውን ሰንጠረዥ መመልከቱ ይጠቅማል:: /ዝርዝሩን ደግሞ በአባሪ ሀ ይመለከቷል:: /

ሰንጠረዥ 5 ከ1980 - 1987 ዓ.ም. የተዘጋጁትን የሁ.ደ.መ.እ.ፈ. የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች አቀራረብ፣ ቁጥር እና መቶኛ የሚያሣይ።

| የተዘጋጀበት ዓ.. ም | ቃላት | | | ፈሊጦች | | ጠቅላላ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ብዛት | መቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአውድ | ያለአውድ | | በአውድ | ያለአውድ | | |
| | ተመሳሳይ | ተመሳሳይ | ተቃራኒ | ተመሳሳይ | ተመሳሳይ | | |
| 1980 | 12 | 5 | – | 2 | 5 | 24 | 32 |
| 1981 | 29 | 5 | – | 1 | 5 | 40 | 44.4 |
| 1982 | 7 | 14 | – | 1 | – | 22 | 27.5 |
| 1983 | 9 | 6 | – | – | 20 | 35 | 43.8 |
| ድምር | 57 | 30 | – | 4 | 30 | 121 | 37.2 |
| 1984 | 4 | 8 | 10 | 1 | 10 | 33 | 42.3 |
| 1985 | 4 | 15 | 11 | 1 | 16 | 47 | 52.2 |
| 1986 | 6 | 10 | 10 | – | 9 | 35 | 43.8 |
| 1987 | 4 | 7 | 10 | 1 | 11 | 33 | 41.3 |
| ድምር | 18 | 40 | 41 | 3 | 46 | 148 | 41.8 |
| ጠቅላላ ድምር | 75 | 70 | 41 | 7 | 76 | 269 | 41.1 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በአውድ የቀረቡ የቃላት ጥያቄዎች 75 ናቸው። በአውድ የቀረቡት ፈሊጦች ደግሞ 7 ናቸው። ያለአውድ የቀረቡ የቃላት ጥያቄዎች 111 ሲሆኑ ያለ አውድ የቀረቡ የፈሊጥ ጥያቄዎች ደግሞ 76 ናቸው። በጠቅላላው በአውድ የቀረቡ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች 82 ሲሆኑ ያለአውድ የቀረቡት ደግሞ 187 ናቸው። ይህም የሚያመለክተው ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በአውድ ከቀረቡት 128% ያህል መብለጣቸውን ነው።

---

* ይህ ምልክት ያለባቸው ፈሊጦች በፈተናዎች ውስጥ ቃላትና ሐረጋት ተብለው ቢጠየቁም ቃላቱ ፈሊጦች መሆናቸው ስለተረጋገጠ በተጠቀሰው ክፍል እንዲታዩ ተደርጓል።

ሰንጠረዡ እንደሚያመለክተው በየዘመኑ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተርበዋል። ከፍተኛውን የመቶኛ ቁጥር የያዘው የ1985 ዓ.ም. ፈተና (52.2%) ነው። ዝቅተኛውን የመቶኛ ቁጥር የያዘው ደግሞ የ1982 ዓ.ም. ፈተና (27%) ነው። አማካኙ መቶኛ 41.1% እንደመሆኑ የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. የቃላት እፈታተን ብቃት መመርመር ከፈተናዎቹ ጥያቄዎች ግማሹን ያህል እንደመመርመር ሊቆጠር ይችላል።

ከዚህ በላይ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን የቃላት ትምህርት አላማ፣ ይዘት፣ የማስተማሪያ ዘዴ እና የመልመጃ አቀራረብ ተመልከተናል። እንዲሁም የስምንቱን ዓመታት ፈተናዎች የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የአቀራረብ ስልት ለማየት ተሞክሯል። ቀጥሎ ደግሞ የ2ኛ ደረጃ የአማርኛ መምህራን ስለቃላት /ፈሊጦች ትምህርት አሰጣጥ ያላቸውን አመለካከት ለመመርመር ይሞከራል። ለመምህራኑ በቀረበው መጠይቅ ውስጥ የማስተማሪያ መሣሪያዎቹ ቃላትን ለማስተማር ድጋፍ መስጠታቸውን እና የመምህራኑን የማስተማሪያ ዘዴ ለማወቅ ተሞክሯል። የሚቀጥለውን ሠንጠረዥ መምህራኑ ለየጥያቄው የሰጡትን መልስ ያቀርባል።

ሰንጠረዥ 6 መምህራን ስለቃላት/ፈሊጦች ትምህርት አሰጣጥ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጧቸውን መልሶች በመቶኛ የሚያሳይ።

| | የጥያቄው ተራ ቁጥርና ጥያቄው | የሚስማሙ(%) | የማይስማሙ(%) | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቃላትን በየክፍል ደረጃው ለማስተማር መማሪያ መጽሐፍ ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጡኛል ብዬ አምናለሁ። | 88 | 12 | 100 |
| 2 | ፈሊጦችን በየክፍል ደረጃው ለማስተማር መማሪ መጽሐፍቱ ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጡኛል ብዬ አምናለሁ። | 2 | 98 | 100 |
| 3 | በት/ቤቱ የአማርኛ በአማርኛ መዝገበቃላት ይገኛል። | 10 | 90 | 100 |
| 5 | የቃላትን ፍች የማስተምርበት አይነተኛ ዘዴዬ አውዳ ነው። | 68 | 32 | 100 |
| 6 | የፈሊጦች ፍች የማስተምርበት አይነተኛ ዘዴዬ አውዳ አይደለም። | 74 | 26 | 100 |
| 7 | መማሪያ መጽሐፉም ሆነ ሲለበሱ ምንም ድጋ ስለማይሰጡኝ ፈሊጦችን የማስተምረው በግል ጥረቴ ነው። | 92 | 8 | 100 |
| 9 | በማስተምርበት ት/ቤት በሚዘጋጅ የአማርኛ ፈተናዎ ውስጥ ቃላትን የመፍታት ጥያቄዎች አብዛኛውን ጊ ይጠየቃሉ። | 100 | | 100 |
| 10 | በማስተምርበት ት/ቤት በሚዘጋጅ የአማርኛ ፈተናዎ ውስጥ ፈሊጥን የመፍታት ጥያቄዎች አብዛኛውን ጊ ይጠይቃሉ። | 100 | | 100 |

ከስንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ለመጀመሪያው ጥያቄ አብዛኞቹ መምህራን ስምምነታቸውን ገልፀዋል። ይህም ቀደም ሲል አጥኚው መማሪያ መጻሕፍቱ ቃላትን ለማስተማር ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ ያለውን የሚያጠናክር ነው። በአንፃሩ አብዛኞቹ መምህራን ለጥያቄ 2 ስምምነታቸውን አልገለፁም። በዚህም የተነሣ ይመስላል አብዛኞቹ መምህራን ፊደሎችን የማስተምረው በግል ጥረቴ ነው ብለዋል (ጥያቄ 7)። ይህም አጥኚው መማሪያ መፃሕፍቱ ፊደሎችን ለማስተማር በቂ ድጋፍ አይሰጡም ያለውን የሚያጠናክር ነው።

በሌላ በኩል አብዛኞቹ መምህራን በት/ቤታቸው የአማርኛ በአማርኛ መዝገበ ቃላት አለመኖሩን አረጋግጠዋል። ከሽመልስ ሐብቴ ት/ቤት በስተቀር በሌሎች ት/ቤቶች መዝገበ ቃላት የለም። ይህም ለቃላት ትምህርት አሰጣጥ መምህራን በቂ የመረጃ መሣሪያ የማያገኙ መሆኑን ይጠቁማል። ሰንጠረዡ እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ መምህራን ቃላትን የሚያስተምሩበት ዘዴ አውዳዊ ሲሆን የፊደሎቹ ግን አውዳዊ አይደለም። በመጨረሻም ሁሉም መምህራን የቃላትና የፊደል ጥያቄዎች በት/ቤት ደረጃ በሚዘጋጁ ፈተናዎች እንደሚካተቱ ማረጋገጣቸውን የመጠይቁ የትንተና ውጤት አመልክቷል።

ክሮንባችን (1971:449) በመጥቀስ ባችማን /1990/ እንደሚያስገነዝቡት የይዘት አስተማማኝነት የሚመለከተው ይዘቱ የሚሸፍናቸውን ነጥቦች /Content Coverage/ ብቻ ሳይሆን የአቀራረቡን ተገቢነት /content relevance/ ጭምር ነው። ይዘቱ የሚሸፍናቸውን ነጥቦች በተመለከተ ቀደም ሲል የማስተማሪያ መሣሪያዎቹንና የፈተናዎቹን የቃላት ትምህርት በመተንተን ለማመልከት ተሞክሯል። ቀጥሎ ደግሞ የአቀራረቡን ተገቢነት ለመመርመር ይሞከራል። የይዘቱ የአቀራረብ ተገቢነት ሲባልም የፈተናው አላማ ከትምህርቱ አላማና የማስተማሪያ ዘዴ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን፣ ፈተናው የተፈታኞችን ችሎታ በጉልህ ለመለየት በሚያስችል ዘዴ መቅረብ አለመቅረቡን፣ ፈተናው ከጾታ፣ ከባህልና ከማህበራዊ አድሎዊነት የፀዳ መሆኑን ወዘተ...የሚመለከት ነው።

በመሆኑም በይዘት አስተማማኝነት ግምገማ ስር የፈተናውን የአቀራረብ ተገቢነት በመመርመር የቃላት ጥያቄዎች የይዘት አስተማማኝነት መጠበቅ አለመጠበቁን ለማረጋገጥ ይቻላል። ይህም ምሁራን ለቃላት ጥያቄዎች አዘገጃጀት እንደ መርህ ያቀረቧቸውን ነጥቦች እንድንመረምር የሚጋብዝ ነው። ስለዚህ የአዘጋጃጀት መርሆዎችን ይዘቱ ከሚሸፍናቸው ነጥቦች ጋር በመመርመር የይዘት አስተማማኝ ነት መጠበቅ አለመጠበቁን እና የጥያቄዎቹን ተገቢ መሆን አለመሆን ለማረጋገጥ ይቻላል። የቃላት ጥያቄዎች የአዘገጃጀት መርሆዎች አምስት ናቸው። እያንዳንዱንም መርህ በተናጠል እንደሚከተለው ለመመርመር ይሞከራል።

### 4.1.2.1 የፈተናው አላማ ግልጽነት

የአንድን ፈተና አላማ ግልጽ መሆን ወይም አለመሆን ለማረጋገጥ ጥያቄዎቹን ከትምህርቱ አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴ እና ከመልመጃዎቹ አቀራረብ ጋር በማመሳከር መተንተን ያስፈልጋል። በዚህም

መሠረት ሁ.ደ.መ.እ.ፈ. የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎችን ከትምህርቱ አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴ እና የመልመጃ አቀራረብ ጋር ለማመሳከር ጥረት ተደርጓል።8

ፈተናዎቹ ካቀረቧቸው 269 ቃላትና ፈሊጦች ውስጥ 187ቱ ያለአውድ፣ 82ቱ ደግሞ በአውድ መቅረባቸው ቀደም ሲል ተገልጿል። ስለዚህ በመጀመሪያ በአውድ ውስጥ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች አላማ ግልጽ መሆን ወይም ያለመሆኑ ይመረመራል። ቀጥሎም ያለአውድ የቀረቡት ጥያቄዎች ይመረመራሉ።

ፈተናዎቹ በአውድ ካቀረቧቸው 82 ቃላትና ፈሊጦች ውስጥ 75ቱ ቃላት ናቸው። ከ75ቱ ቃላት ውስጥ ደግሞ 58ቱ ምንባባዊ አውድ ያላቸው ናቸው። ይህ አይነቱ አጠያየቅ ተማሪው በንባብ ወቅት የሚያጋጥሙትን አዳዲስ ቃላት እንዴት እንደሚፈታቸው ለመመዘን የታቀደ ይመስላል። የአጠያየቁም ስልት ለሲለበሱ አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና የመልመጃ አቀራረብ ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ ይመስላል። ምክንያቱም አንደኛ በሲለበሱ የቃላት ትምህርት አንዱ አላማ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ማጎልበት ነው። ሁለተኛ በሲለበሱ የማስተማሪያ ዘዴ ተደጋግሞ የሚጠቀሰው ተማሪው ቃላትን ከአገባባቸው እንዲረዳ ማለማመድ ነው። ሶስተኛ አብዛኞቹ መምህራን ቃላትን የሚያስተምሩበት አይነተኛ ዘዴ አውዳዊ ነው። እንዲሁም የመማሪያ መጽሐፍቱ የመልመጃ አቀራረብ በአብዛኛው በምንባብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ስለዚህ የምንባብ አውድ የተዘጋጀላቸው 58ቱ የቃላት ጥያቄዎች ከሲለበሱ የቃላት ትምህርት አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና ከመማሪያ መጽሐፍቱ የመልመጃ አቀራረብ ጋር በእጅጉ የሚመስል በመሆኑ የፈተናው አላማ በግልጽ ይታወቃል። ይኸውም ተማሪው ቃላትን ከአውዳቸው እንዴት እንደሚፈታቸው መመዘን ነው። የአጠያየቁ ስልት የትምህርቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ጠቀሜታ ስላለውም ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ ነው እንላለን።

ፈተናዎቹ በአውድ ካቀረቧቸው 75 ቃላት ውስጥ 15ቱ በአገባብ ወይም በፍች የማይዛመደውን ቃል አውጣ የሚሉ ናቸው። በሲለበሶቹ ውስጥ የሚዛመዱ ቃላትን ፍች በማወቅ ተማሪው ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ እየተጠቀመ ዐ.ነገር፣ አንቀጽ ወይም ድርሰት እንዲጽፍና እንዲናገር አላማ ተነድፏል፣ ይዘት ተመርጧል፣ የማስተማሪያ ዘዴም ተጠቁሟል። እንዲሁም በመማሪያ መጽሐፍቱ መልመጃዎች ውስጥ በተቀራራቢ ወይም በጥንድ ቃላት መካከል ያለውን የፍች አንድነትና ልዩነት ተማሪው እንዲያውቅ በርካታ ልምምዶች ቀርበዋል። ስለዚህ የፈተናዎቹ የአጠያየቅ ስልት የትምህርቱን አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴውንና የመማሪያ መጽሐፍቱን መልመጃዎች መሠረት ያደረገ በመሆኑ አላማውን በግልጽ ለማወቅ አ..ዳግትም።

ፈተናዎቹ በአውድ ካቀረቧቸው 75 ቃላት ውስጥ 2ቱ ዐ.ነገራዊ አውድ የተዘጋጀላቸው ናቸው። በዚህም ተፈላጊው ቃል ከስሩ ተሰምሮበት ለቃሉ ተመሣሣይ ፍች እንዲሰጥ ተጠይቋል። ይህ አይነቱ አጠያየቅ ተማሪው ቃላትን ከአውዳቸው እንዴት እንደሚፈታ ለመመዘን የታቀደ መሆኑ አያጠራጥርም። ቀደም ሲል ምንባባዊ አውድ ያላቸው ጥያቄዎች ስንመረምር እንደገለጽነው ሁሉ

አጠያየቁ ከትምህርቱ አላማ፣ ማስተማሪያና ዘዴና ከመማሪያ መጽሐፍቱ የመልመጃ አቀራረብ ጋር በጣሙን የሚመሳሰል ስለሆነ አላማውን በግልጽ ማወቅ ይቻላል።

ፈተናዎቹ በአውድ ካቀረቧቸው 75 ቃላት በተጨማሪ 7 ፈሊጦች በአውድ መቀረባቸው በሠንጠረዥ 5 ተመልክቷል። 7ቱም ፈሊጦች ምንባባዊ አውድ ያላቸው ናቸው። በሲለበሶቹ ውስጥ የፈሊጥ ትምህርት አላማና የማስተማሪያ ዘዴ በግልጽ አልተቀመጠም። እንዲሁም መማሪያ መጻሕፍቱ መልመጃዎች ውስጥ አንድም የማይቀርቡበት ጊዜ አለ። ቢቀርቡም ደግሞ አነስተኛ ናቸው። /ሠንጠረዥ 4ን ያጤኗል/ ይሁን እንጂ ፈሊጦች የቃላት አንድ ክፍል እስከሆኑ ድረስ የቃላት ትምህርት ዓላማ ለፈሊጦችም እንደሚያገለግል ይገመታል።

አምሳሉና ዳኛቸው (1979:5) ስለፈሊጦች ትምህርት አላማ ያነሱት ነጥብ ለዚህ ዋቢ ሊሆን ይችላል። "በአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎቹም ረገድ የአማርኛን ፈሊጣዊ አነጋገር ማጥናት ከፍተኛ ጥቅም ያስገኝላቸዋል፣ ገለፃውን በኃይል ቃል በማጠናከር ንግራቸውንም ሆነ ጽሑፋቸውን ይበልጥ ሐሳብ ጨባጭነትና አስጨባጭነት እንዲኖረው ስለሚያደርገው።"

ምንም እንኳ በሲለበሶቹ የቃላት ትምህርት ዓላማ በግልጽ ባይታይም ከአጠቃላዩ የቃላት ትምህርት ዓላማና ከእነ አምሳሉ ነጥቦች በመነሳት ፈሊጦችን በአውድ ውስጥ መፈተኑ ጠቀሜታ ያለው ይመስላል። ምክንያቱም ምዘናው ተማሪው ፈሊጦችን ከአገባባቸው መረዳት መቻል አለመቻሉን ስለሚያረጋግጥልን ነው። ስለዚህ በአውድ የቀረቡት የፈሊጥ ጥያቄዎች አላማ ግልጽ ነው ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ግን የማስተማሪያ መሣሪያ አዘጋጆች ለፈሊጦች ትምህርት ግልጽ አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና በቂ መልመጃዎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

በአጠቃላይ በፈተናዎቹ ውስጥ በአውድ የቀረቡት 82 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች አላማ ግልጽ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። የፈተናዎቹ የአጠያየቅ ስልት የትምህርቱን አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና የመልመጃ አቀራረብ መሠረት ማድረጉ ለጥያቄዎቹ አላማ ግልጽነት ዋቢ መሆኑ ተጠቁሟል። ቀጥሎ ደግሞ ያለአውድ የቀረቡት ጥያቄዎች ይመረመራሉ።

ፈተናዎቹ ያለአውድ ካቀረቧቸው 187 ቃላት ፈሊጦች ውስጥ 121ዱ ቃላት ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ 70ዎቹ ተመሳሳይ ፍችን የሚጠይቁ ሲሆኑ 41ዱ ደግሞ ተቃራኒ ፍችን የሚጠይቁ ናቸው። የጥያቄዎቹ አላማ የቃላት ችሎታን ለመመዘን ይመስላል። ይሁን እንጂ የአጠያየቁ ስልት የትምህርቱን አላማ የማስተማሪያ ዘዴውንና የመማሪያ መጽሐፍቱን የመልመጃ አቀራረብ መሠረት ስላላደረገ አላማውን በግልጽ ለማወቅ ያዳግታል። ለዚህም የሚከተሉትን አበይት ነጥቦች በዋቢነት ማቅረቡ በቂ ይሆናል።

1. በቃላቱ ትምህርት አላማ ውስጥ ተማሪው ሁሉንም የአማርኛ ቃላት የግድ ማወቅ እንደሚጠበቅበት ወይም የተወሰኑ ቃላትን በትኩረት ማወቅ እንዳለበት የሚያስገነዝብ አላማ አልተነደፈም። አላማው ተማሪው በቃላት የመጠቀም ሐይሉን ማዳበር ነው።

2. በሲለበሱ የማስተማሪያ ዘዴ በተደጋጋሚ የሚጠቆመው ቃላትን በአውድ ውስጥ ማስተማር ነው። ለምሳሌ "ለደረጃው ከሚመጥን ምንባብ ውስጥ የተወሰኑ ቃላትን መርጦ በመስጠት ተማሪዎች እንደሁኔታው ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ እንዲፈልጉ ማድረግ።" /የአማርኛ ሲለበስ 9ኛ ክፍል 1972:5/ እንዲሁም አብዛኞቹ መምህራን ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴያቸው አውዳዊ ነው።

3. በመመሪያ መጽሐፍቱ የቃላት መልመጃዎች ሙሉ ለሙሉ የሚቀርቡት በአውድ ውስጥ ነው። አውዱ አብዛኛውን ጊዜ ምንባባዊ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ዐነገራዊ ነው።

ከእነዚህ ነጥቦች በመነሳት አንድን ቃል ያለአውድ አቅርቦ የመፈተን አላማ ምንድን ነው? ብለን ብንጠየቅ ግልጽ የሆነ ምክንያት ለማግኘት እንቸገራለን። በመጀመሪያ ደረጃ ከቃላት ትምህርቱ አላማ አንፃር ብናየው ምዘናው ተገቢ አይመስልም። ምክንያቱም የቃላቱ ትምህርት አላማ ተማሪው በቃላት የመጠቀም ችሎታውን ማዳበር እንደመሆኑ ይህን ችሎታ ማግኘት አለማግኘቱን በቃላቱ ዐነገር እንዲሠራ፣ ቃላትን ከአውድ እንዲፈታ፣ እንዲያዛምድ፣ ወዘተ... በመጠየቅ ካልተመዘነ አላማው ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ ስለሚያዳግት ነው። አንድ ቃል ያለአውድ ቀርቦ ተማሪው ለቃሉ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍች እንዲሰጥ መጠየቅ የተማረውን ሁሉንም የአማርኛ ቃላት የማወቅ ችሎታ ለመመዘን የታቀደ ያስመስላል። ይህ ደግሞ የትምህርቱ አላማ ስለላልሆነ ምዘናው የተማሪውን ችሎታ ለማወቅ የሚያስችል አይደለም። ስለዚህ የአጠያየቅ ስልቱ ተማሪው የትምህርቱን አላማ ጠንቅቆ መረዳቱን ለማወቅ አመቺ ካለመሆኑም በላይ የፈተናው አላማ ግልጽ አለመሆኑን ያመለክታል።

በሁለተኛ ደረጃ ቃላትን ያለአውድ መፈተን ከሲለበሶች የማስተማሪያ ዘዴና ከመምህሩ የማስተማሪያ ዘዴ ጋር የሚቃረን ነው። በሶስተኛም ደረጃ አፈታተኑ ተማሪው ቃላትን ከሚለማመድበት ዘዴ ጋር ይቃረናል። ይህ ተቃርኖ ደግሞ የፈተናውን አላማ ግልጽነት ያደበዝዘዋል።

ስለዚህ ያለ አውድ የቀረቡት 121 የቃላት ጥያቄዎች ከተማሪው የሚጠበቀውን ችሎታ በግልጽ የማያመለክቱ ናቸው። ለዚህም ዋናው ምክንያት የፈተናዎቹ አጠያየቅ በትምህርቱ አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና ልምምድ ላይ አለመመስረት ነው። በመሆኑም ጥያቄዎቹ አንድም የትምህርቱን አላማ ጠንቅቆ ካለመረዳት በመዘጋጀታቸው፣ ሊያም አመቺ ያልሆነ የአጠያየቅ ስልት በመከተላቸው አላማቸውን በግልጽ ለማወቅ ያዳግታል እንላለን።

ፈተናዎቹ ያለአውድ ካቀረቧቸው ጥያቄዎች ውስጥ 75ቱ ፈሊጦች ናቸው። ሁሉም ፈሊጦች ተመሳሳይ ፍችን የሚጠይቁ ናቸው። የአጠያየቁ ስልት የትምህርቱን አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና የመልመጃ አቀራረብ መሠረት ያደረገ ነው ወይ? ብለን ብንጠይቅ ቁርጥ ያለመልስ ለመስጠት ሊያዳግተን ይችላል። ምክንያቱም የትምህርቱ አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና ልምምዱ በሲለበሶቹና በመማሪያ መጽሐፍቱ በግልጽ ስለማይታይ ነው። ያም ሆኖ የቃላት ትምህርቱ አላማ ለፈሊጦችም ይውላል እስካልን ድረስ አንድን ፈሊጥ ያለአውድ መፈተኑ ለትምህርቱ አላማ ተስማሚ ዘዴ እንደማይሆን መናገር ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ጥያቄዎቹ የመምህራንን የማስተማሪያ ዘዴና የቀረቡትን ጥቂት መልመጃዎች መሠረት ያደረጉ ይመስላሉ። ይህም ማለት የአጠያየቁ ስልት በመጠይቁ አብዛኞቹ መምህራን ፊደሎችን የምናስተምረው ያለአውድ ነው ካሉት እና በአሁኖቹ የ11ኛና የ12ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት መልመጃዎች ውስጥ ያለአውድ ከቀረቡት ፊደሎች ጋር ይመሳሰላል ማለት ነው። ይሁን እንጂ አንደኛ ከቀድሞዎቹ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ምንም የፊደል መልመጃ ሳይኖር ተማሪው ተመዝኖአል። ሁለተኛ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለፈተና ከማዘጋጀት ጉጉት ፊደሎችን በግል ጥረታቸው የሚያስተምሩ ይመስላል እንጂ ለትምህርት አሰጣጡ ተስማሚ ዘዴ መከተላቸው የሚያጠያይቅ ነው። ሦስተኛ በሲለበሱ ይዘት ሳይጠቀሱ በድንገት ደራሽነት በመማሪያ መጽሐፉ  የቀረቡት ጥቂት የፊደል መልመጃዎች ያለአውድ የቀረቡበት ምክንያት ግልጽ አይደለም።

ስለዚህ ያለአውድ የቀረቡት 75 የፊደል ጥያቄዎች አምሳሉና ዳኛቸው /1979፡5/  ለገለጹት የፊደል ትምህርት አላማም ሆነ ለአጠቃላዩ የቃላት ትምህርት አላማ ተስማሚ የመመዘኛ መሣሪያዎች አይመስሉም። በመሆኑም ጥያቄዎቹን ለመመለስ ከተማሪው የሚጠበቀው ችሎታ እስካልታወቀ ድረስ አላማቸው ግልጽ አይደለም እንላለን።

በሌላ አንጻር ተማሪው ሁሉንም የአማርኛ ፊደሎች ማወቅ አለበት በሚል አላማ ጥያቄዎቹ ተዘጋጅተው ከሆነ አስቸጋሪነቱ ሊታየን ይገባል። ምክንያቱም አንደኛ ለፊደሎች ትምህርት ሲለበሱቹና መማሪያ መጽሐፍቱ በቂ ድጋፍ ስለማይሰጡ ተማሪው በቂ ልምምድ ማድረጉ አጠራጣሪ ነው። ሁለተኛ የስነልሣን ባለሙያዎች ለምሳሌ አቼሰን /1987/ እንደሚያስገነዝቡን የቋንቋ ለመዳ በተለይም የቃላትና የፊደሎች ሊመዳ የዕድሜ ልክ ሂደት  በመሆኑ "ተማሪው ሁሉንም የአማርኛ ፊደሎች ያውቃል።" የሚል አላማ ለመንደፍና ያንን አላማ መሠረት በማድረግ ለመመዘን አስቸጋሪ ነው።

ለማጠቃለል በስምንቱ አመታት ፈተናዎች በአውድ የቀረቡት 82 የቃላትና የፊደል ጥያቄዎች አላማ ግልጽ መሆኑን የጥናቱ የትንተና ውጤት አመልክቷል። ስለሆነም እነዚህ የቃላትና የፊደል ጥያቄዎች ቢያንስ ለቃላት ትምህርቱ አሰጣጥ ተስማሚ የመመዘኛ መሣሪያ ይመስላሉ። በአንጻሩ ያለአውድ የቀረቡት 187 የቃላትና የፊደል ጥያቄዎች አላማ ግልጽ ያለመሆኑን የጥናቱ የትንተና ውጤት ጠቁሟል። ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፊደል ጥያቄዎች አላማ ግልጽ አይደለም

የሚለውን የትንታኔ ውጤት ይበልጥ ግልጽ የሚያደርግልን ሰጣቂውን መርህ ስንመረምር ስለሆነ ወደዚያው እናመራለን።

### 4.1.2.2 የፈተናው የቃላት አመራረጥ

ለመምህራን በቀረበው መጠይቅ ውስጥ የፈተናዎችን የቃላትና የፈሊጥ ጥቄዎች የአፈመራረጥ መስፈርት በተመለከተ 4 ጥያቄዎች ቀርበው ነበር። እነሱም በመጠይቁ ተራ ቁጥር 12፣ 13፣ 18፣ እና 19 ላይ ይገኛሉ። የሚከተለው ሰንጠረዥ መምህራኑ ለየጥያቄው የሰጡትን መልስ በመቶኛ ያሣያል።

**ሰንጠረዥ 7 የቃላት አመራረጥ መስፈርትን በተመለከተ የቀረቡትን ጥያቄዎችና መምህራኑ የሰጧቸውን መልሶች በመቶኛ የሚያሳይ።**

| | የጥያቄው ተራ ቁጥርና ጥያቄው | የሚስማሙ (%) | የማይስማሙ (%) | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 12 | የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. የቃላት ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ከማስተማራቸው ቃላት ጋር በአብዛኛው ይመስላሉ። | 18 | 82 | 100 |
| 13 | የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. የፈሊጥ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ከማስተምራቸው ፈሊጦች ጋር በአብዛኛው ይመስላሉ። | 38 | 62 | 100 |
| 18 | የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. የቃላት ጥያቄዎች የሚመረጡት በአብዛኛው ከመማሪያ መጽሐፍቱ መልመጃዎች ነው። | 12 | 88 | 100 |
| 19 | የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. የፈሊጥ ጥያቄዎች የሚመረጡት በአብዛኛው ከመማሪያ መጽሐፍቱ መልመጃዎች ነው። | - | 100 | 100 |

ከሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኞቹ መምህራን የፈተናዎቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ልምምድም ሆነ በመማሪያ መጽሐፍቱ ላይ ተመስርተው የሚመረጡ አለመሆናቸውን አረጋግጠዋል። ለአማርኛው ፓናል ሐላፊ ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦላቸው በመምህራኑ አመለካከት ተስማምተዋል። ሐላፊው ለጥያቄው የሰጡትን ሙሉ መልስ እዚህ ላይ መጥቀሱ ተገቢ ይመስላል።

> አንዳንድ ጊዜ ፈተና አውጭዎች መማሪያ መጽሐፍቱንና ሲለበሉቸን ማየታቸውን እንኳ እጠራጠራለሁ። አሁን ለጠየቅኸኝ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የምሰጠው መልስ ይህንኑ ነው። ፈተና አውጭው እንደፈለገ ቃላትን መርጦ ለፈተና ያቀርባል እንጂ በማስተማሪያ መጽሐፉ የተማረውን ደረጃ ይመጥናሉ የሚባሉት ቃላት በፈተናው ውስጥ ሲካተቱ አላይም።
>
> (የካቲት 21፣1988 ከተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘ መልስ)

ከሁለቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በተጨማሪ አጥኚው የፈተናዎቹን የቃላት አመራረጥ መስፈርት ለመመርመር ሞክሯል። በዚህም በየዘመኑ በተዘጋጁት መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙትን ቃላትና ፈሊጦች ከፍተኛዎቹ ቃላትና ፈሊጦች ጋር አመሳክሯል። የሚከተለው ሰንጠረዥ ተዛምዶአቸውን በቁጥርና በመቶኛ ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 8 ከፈተናዎቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ በመማሪያ መጽሐፍቱ ተዛምደው የተገኙትን ቃላትና ፈሊጦች በቁጥርና በመቶኛ የሚያሳይ።

| ፈተናው የተዘጋጀበት ዓ.ም. | የተዛመደው ቃል ወይም ፈሊጥ በቁጥር | መቶኛ (%) |
|---|---|---|
| 1980 | 2 | 8.3 |
| 1981 | 2 | 5 |
| 1982 | 1 | 4.6 |
| 1983 | 2 | 5.7 |
| ድምር | 7 | 5.8 |
| 1984 | 2 | 6.2 |
| 1985 | 3 | 6.4 |
| 1986 | 3 | 8.6 |
| 1987 | 3 | 9.1 |
| ድምር | 11 | 7.4 |
| ጠቅላላ ድምር | 18 | 6.9 |

ከ1980 - 83 የተዘጋጁት ፈተናዎች ከቀድሞዎቹ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት መልመጃዎች ጋር ሲዛመዱ ከ1984-87 ዓ.ም. የተዘጋጁት ፈተናዎች ደግሞ ከአሁኖቹ የመማሪያ መጽሐፍት መልመጃዎች ጋር ተዛምደዋል። ሰንጠረዡ እንደሚያመለክተው በስምንቱ አመታት ፈተናዎች ከቀረቡት 269 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ በመማሪያ መጽሐፍቱ መልመጃዎች የተገኙት ወይም የተዛመዱት ቃላትና ፈሊጦች 18 ወይም 6.9% የሚሆኑት ብቻ ናቸው።

በሰንጠረዡ እንደተመለከተው ከ1980 - 83 ዓ.ም. በተዘጋጁት ፈተናዎች ውስጥ ከሚገኙት 121 ቃላትና ፈሊጦች መካከል በመማሪያ መጽሐፍቱ መልመጃዎች የተገኙት ሰባት ቃላትና ፈሊጦች ናቸው። እነሱም "መደንበር"፣ "አዛጋ"፣ "ቸነፈር"፣ "መንደል"፣ "ደለበ"፣ ቅንጣት እና

"ዓይነ ቁራኛ " ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ "ዓይነ ቁራኛ " ፈሊጥ ሲሆን ሌሎቹ ቃላት ናቸው። መማሪያ መጽሐፍቱ ለልምምድ ካቀረቧቸው 692 ቃላት ውስጥ ፈተናዎች ለጥያቄነት የመረጧቸው 6 ቃላትን ብቻ ነው። እንዲሁም መማሪያ መጽሐፍቱ ካቀረቧቸው 5 ፈሊጦች ውስጥ ፈተናዎች አንዱን ፈሊጥ በጥያቄነት መርጠዋል። በአጠቃላይ በአራቱ አመታት ለጥያቄ ከቀረቡት 121 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ በመማሪያ መጽሐፍቱ የተገኙት 7 ወይም 5.8% ያህሉ ብቻ ናቸው። የቁጥሩ እጅግ አነስተኛ መሆን ደግሞ የፈተናው ቃላትና ፈሊጦች የሚመረጡት መማሪያ መጽሐፍቱን መሠረት በማድረግ አለመሆኑን የሚጠቁም ነው።

በሰንጠረዥ እንደተመለከተው በአራቱ አመታት (ከ1984 87 ዓ.ም.) በተዘጋጁት ፈተናዎች ውስጥ ከቀረቡት 148 ቃላትና ፈሊጦች ውስጥ በመማሪያ መጽሐፍቱ መልመጃዎች የተገኙት 11 ቃላትና ፈሊጦች ወይም 7.4% ብቻ ናቸው። እነሱም "ነቀዘ"፣ "ወፍ ሲንጫጫ"፣ "ግልጽ"፣ "ምርቃት"፣ " የምሥራች"፣ "ዘከረ"፣ "እንከን"፣ "ቀጠፈ"፣ "አግቦ"፣ "ቀምጣላ"፣እና "ወረዛ"፣ ናቸው። ከእነዚህ ቃላት ውስጥ ፈሊጥ የሆነው አንድ ብቻ ነው። ይኸውም "አግቦ" የተባለው ነው። የተዛምዶው ቁጥር አነስተኛ ነው። ይህም የፈተናዎቹ ቃላትና ፈሊጦች የሚመረጡት መማሪያ መጽሐፍቱን መሠረት ሳያደርጉ መሆኑን የሚጠቁም ይመስለናል።

በምርጫ ስጭ የቃላት ፈተናዎች ውስጥ ለፈተና የሚቀርቡትን ቃላት ስንመርጥ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ሂተን /1975/ እና ሂዩዝ /1989/ ያስገነዝባሉ። እንደ ሂተን እምነት የቃላት መረጣው ሀ/ ከሲለበሱ ለ/ ከመማሪያ መጻሕፍቱ ሐ/ ከክፍል ውስጥ ልምምድ እና መ/ ከተጨማሪ የንባብ መጻሕፍት ሊከናወን ይችላል። ሂዩዝም በበኩላቸው የትምህርቱን አላማ ጠንቅቆ በመረዳት አላማውን ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ቃላትን መምረጥ ተገቢ መሆኑን ይናገራሉ። በሌላ አገላለጽ የቃላቱን ትምህርት አላማ መሠረት በማድረግ በክፍል ውስጥ ሰፊ ልምምድ የተደረገባቸውና ስርጭታቸው ሰፊ በሆኑ ቃላት ላይ በማትኮር የቃላት መረጣውን ማከናወን እንደሚቻል ሂዩዝ ያስገነዝባሉ።

የስምንቱን አመታት የሁ.ደ .መ.አ .ፈ . የቃላትና የፈሊጦችን አመራረጥ ስንመለከት ግን ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የቃላት መምረጫ መርሆዎች እንዳልተጠበቁ መረዳት አያዳግትም። በርግጥ የአማርኛ ሲለበሶች ተደጋጋሚ የቃላት ዝርዝር ስለማያቀርቡ የቃላት መረጣውን በሲለበሶች ላይ

መመስረት አይቻልም። ይሁን እንጂ ሌሎቹ የመምረጫ ምንጮችን በወጉ ስላልተጠቀምንባቸው መረጣው ጥንቃቄ የጎደለው ይመስላል። ይህም ማለት፣

1ኛ/ ከ269 የቃላትና የፊሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ 18ቱ ብቻ በመማሪያ መጽሐፍቱ መገኘታቸው አመራረጡ በመማሪያ መጽሐፍቱ ላይ ላለመመስረቱ ፍንጭ ይሰጣል። እንዲያውም የተዛምዶው ጉልህ አለመሆን 18ቱ ቃላት ሆን ተብለው /consciously/ ከመማሪያ መጻሕፍቱ ለመመረጣቸው ዋቢ ሊሆን አይችልም። ይልቁንም ተዛምዶው የአጋጣሚ ነው ቢባል ያስኬዳል።

2ኛ/ የቃላት መረጣው በክፍል ውስጥ በቂ ልምምድ ከተደረገባቸው ቃላት ተመርጠዋል እንዳይባል አብዛኞዎቹ መምህራን ይህ እንዳልተከናወነ አረጋግጠዋል።

3ኛ የቃላት መረጣው መሠረት ተጨማሪ የንባብ መጽሐፍት ናቸው እንዳንል ለዋናዎቹ የመማሪያ መጻሕፍት የተሰጠው ትኩረት 6.9% ሆኖ እያለ ለተጨማሪ የንባብ መጻሕፍት 93.1% ትኩረት ይሰጣል ብሎ ለማሰብ አዳጋች ነው። ቢታሰብና ቢደረግም ተገቢ አይሆንም።

ስለዚህ የፈተናዎቹ ቃላት/ፈሊጦች በአብዛኛው የሚመረጡት ከማስተማሪያ መማሪያዎቹ ያለመሆኑን የጥናቱ የትንታኔ ውጤት አመልክቷል። የቃላት መረጣው በትምህርት መረጃ ምንጮች ላይ ካልተመሠረተ ደግሞ ጥንቃቄ የጎደለው ነው ቢባል ያስኬዳል። በተለይ ያለአውድ የቀረቡት 187 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ጉልህ በሆነ ቁጥር ከመማሪያ መጻሕፍቱ አለመመረጣቸው የፈተናውን አላማ ግልጽነት ይበልጥ ያደበዝዙታል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁሉንም የአማርኛ ቃላትና ፈሊጦች በቃል ማወቅ ከተፈታኙ የሚጠበቅ ይመስላል። ይህ ደግሞ ከሲለበሱ የቃላት ትምህርት ዓላማ ውጭ ስለሆነ የፈተናውን ተገቢነትና የአላማ ግልጽነት አጠያያቂ ያደርገዋል።

ያለአውድ የቀረቡት 187 ቃላትና ፈሊጦች የሚመረጡበት መስፈርት ግልጽ አይደለም ብለናል። ይኸውም ጉዳይ ይበልጥ ጎልቶ የሚታየን የፈተናዎቹን ዘዬና ተደጋጋሚ ቃላት ስናጤን ነው።

ለመምህራን በቀረበው መጠይቅ ውስጥ የፈተናዎቹን ዘዬ ቃላት በተመለከተ 3 ጥያቄዎች ቀርበው ነበር። እነሱም በመጠይቁ ተራ ቁጥር 4፣ 8 እና 17 ላይ ይገኛሉ። የሚከተለው ሰንጠረዥ መምህራኑ ለየጥያቄው የሰጡትን መልስ በመቶኛ ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 9 ዘዬ ቃላትን በተመለከተ መምህራኑ የሰጧቸውን መልሶች በመቶኛ የሚያሳይ።

| | ጥያቄው | የሚስማሙ (%) | የማይስማሙ (%) | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 4 | በቃላት ትምህርት የአማርኛ ዘዬ ቃላትን ማስተማር ጠቃሚ ነው ብዬ ስለማምን አስተምራለሁ። | 16 | 84 | 100 |
| 8 | የአማርኛ ዘዬ ቃላትን ለማስተማር ቢያስፈልግ በት/በቴም ሆነ በአካባቢዬ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ማግኘት አይቸግረኝም። | 10 | 90 | 100 |
| 17 | በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ውስጥ ዘዬ ቃላት ለጥያቄ መቅረባቸው ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ። | 30 | 70 | 100 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኞቹ መምህራን ዘዬ ቃላትን አያስተምሩም። በዚህም የተነሳ ይመስላል በሁ.ደ.መ.አ.ፈ. ውስጥ መጠየቃቸው ተገቢ አይደለም ብለዋል። በሌላም በኩል ዘዬ ቃላትን ለማስተማር ቢያስፈልግ መርጃ መሣሪያዎችን የማግኘት ችግር እንዳለባቸው የአብዛኞቹ መምህራን መልስ ያመለክታል።

የማስተማሪያ መሣሪያዎች ዘዬ ቃላትን ለማስተማር በቂ ድጋፍ መስጠት አለመስጠታቸውን አጥኚው ለመመርመር ሞክሯል። በዚህም መሠረት ሲለበሶቹ ስለ ዘዬ ቃላት ያነሱት ነጥብ ስለሌለ ምንም ትኩረት እንዳልሰጡ ለማረጋገጥ ተችሏል። በመማሪያ መጽሐፍቱ መልመጃዎች ውስጥ የቀረቡትን 1549 (692 ቀ + 857አ) ቃላት ስንመረምር ደግሞ አብዛኞቹ በተለመዱ ወይም መደበኛ በሆኑ ቃላት ላይ ያተኮሩ ሆነው እናገኛቸዋለን። በርግጥ አንዳንድ ያልተለመዱና የግዕዝ ቃላት በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ መቅረባቸው የሚካድ አይደለም። ይሁን እንጂ አንዳችም ጊዜ በመልመጃዎቹ መምሪያዎች ተማሪው ዘዬ ቃላትን ሰብስቦ ፍች እንዲሰጥ ወይም በሌላ ዘዴ እንዲለማመድ ዕድል ሲሰጡ አናገኝም። ስለዚህ መማሪያ መጻሕፍቱም ለዘዬ ቃላት ትኩረት አልሰጡም ማለት ይቻላል።

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአማርኛ የቃላት ትምህርት አሰጣጥ ውስጥ መምህራንና የማስተማሪያ መሣሪያዎቹ ለዘዬ ቃላት ትኩረት እንደማይሰጡ የትንታኔው ውጤት አመልክቷል። ይሁን እንጂ በስምንቱ አመታት ፈተናዎች ውስጥ አልፎ አልፎ ዘዬ ቃላት ለጥያቄ ቀርበዋል። የአማርኛን ዘዬ ቃላት ጠብሰቅ ባለ መንገድ አጥንቶና ሰብስቦ ያስቀመጠ ጥናት የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ባያጋጥመውም አልፎ አልፎ ከተሰሩ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች፣ በባለደረቦች እገዛና በራሱም እምነት የሚከተሉት 23 ቃላት ዘዬ ናቸው በሚል ተፈርጅዋል። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

ከ1981 ዓ.ም. ፈተና 'አጋሚደ' 'ገነገነ' እና 'አከላላ'፤ ከ1982 ዓ.ም. ፈተና 'ደበተ'፣ 'ደለቀ' እና 'ለበጣ'፤ ከ1985 ዓ.ም. 'ፈተና' 'ቀግ'፣ 'ዲካ'፣ 'ወላንሳነት'፣ 'እዳሪ' 'ልምጭ'፣ 'ማጓን' እና 'ቧጓች'፣ ከ1987 ፈተና 'ልጨኛ'፣ 'ጣፍርዴ'፣ 'ወበራ'፣ 'ትንኩሽት'፣ 'ሙሽት'፣ 'አተረ''፣ 'ጎባን'፣ 'ቡልኮ'፣ 'ትካር' እና 'የሻጉራ'። ከእነዚህ ዘዬ ቃላት ውስጥ ፆስቴ/ወላንሳነት፣ 'ትካር' እና የሻጉራ/አውድ ሲኖራቸው ሌሎቹ ግን አውድ የላቸውም። የሚከተሉትን ምሳሌዎች ከፈተናዎቹ እንጠቅሳለን።

ምሳሌ 1. ገነገነ ( ተመሳሳይ ፍች ስጥ).

ሀ. ጠረጠረ ለ. በረገገ መረመረ መ. ገመገመ

2. ሙሽት (ተቃራኒ ፍች ስጥ)

ሀ. ቁርስ ለ. ምሳ ሐ.. ቀንኛ መ. ጉርሻ

በምሣሌዎቹ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ለመስጠት የሚችሉት ተፈታኞች ቃላቱን ከአካባቢያቸው የሚያውቋቸው ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ቃላቱን በክፍል ውስጥ በቂ ልምምድ ያላደረጉባቸውና ከአካባቢያቸውም ለማወቅ ያላቸው ዕድል ውሱን ስለሆነ ነው። ከሁሉም በላይ የአማርኛ ዘዬ ቃላትን ማስተማር የትምህርቱ አላማ ባለመሆኑ ተማሪው የሚፈተነው ያልተማረውን ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ ዋናው ጉዳይ የዘዬ ቃላት በፈተናዎቹ ውስጥ መብዛት ወይም አለመብዛት ሳይሆን ጥያቄዎቹ ለትምህርት አላማ ተገቢ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ነው። በአጥኚው እምነት ዘዬ ቃላትን ለማስተማር ሲለበሶቹና መማሪያ መጽሐፍቱ በቂ ድጋፍ ስለማይሰጡ፤ እነሱን ለማስተማር በቂ የመረጃ መሣሪያዎች ስለሌሉና መምህራንም ስለማያስተምሩ ለፈተና መቅረባቸው ተገቢ አይደለም።

ባጠቃላይ ተማሪው ሲማር ሁሉንም የአማርኛ ዘዬ ቃላት ማወቅ እንደማይጠበቅበት ሁሉ ሲፈተንም ያልተማረውን ጉዳይ እንዲመልስ መጠበቅ አግባብነት የለውም። በተለይ በሀገራችን በብሔራዊ ደረጃ በሚቀርበው ፈተና ውስጥ አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑና ያልሆኑ ተማሪዎች መኖራቸው እየታወቀ በአንድ አካባቢ የሚነገሩ ዘዬ ቃላትን ለፈተና ማቅረቡ አድሎዊነትን /bias/ ሊያመለክት ይችላል። ማለትም አንደኛው ወገን ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የማስተማሪያ መማሪያዎቹ በቂ ድጋፍ ሳይሰጡ ዘዬ ቃላትን በፈተናዎቹ ውስጥ ማካተት የቃላት አመራረጡ ጥንቃቄ የጎደለው መሆኑን የሚጠቁም ነው።

የቃላት አመራረጡ ጥንቃቄ የጎደለው መሆኑን የሚጠቁመው ሌላው ነጥብ በፈተናዎቹ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ቃላትና ፈሊጦች ናቸው። በርካታ ተፈታኞች በአንድ ጊዜ በሚፈተኗቸው ፈተናዎች ውስጥ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ ጥያቄዎችን እልፎ አልፎ መደጋገሙ የተለመደ ክስተት ነው። ለምሳሌ በእንግሊዝኛው የTOFEL ፈተና ውስጥ አንዳንድ የቃላትና የሰዋስው ጥያቄዎች ሲደጋገሙ እንመለከታለን። ጥያቄዎቹን የመደጋገም ሂደት የሚከናወነው ግን በዘፈቀደ አይደለም። ይልቁንም ተፈታኞቹ በየጊዜው ለየጥያቄው የሚሰጧቸው መልሶች ተተንትነው /አይተም አናሊስስ ተካሂዶ/ ጥያቄው ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ የሚከናወን ነው።

በሀገራችን እስከአሁን የተዘጋጁ የሁ.ደ.መ.አ.ፈን የመልስ ትንተና ያደረገ ጥናት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሁ.ደ.መ. ጽ/ቤትንና የዩኒቨርስቲውን ሲስተም ዲዛይን ጠይቀናል። ይሁን እንጂ ከሁለቱም የተገኘው መልስ ጥናቱ አለመካሄዱን አረጋግጧል። በዚህም የተነሳ በፈተናዎቹ ውስጥ ለሚደጋገሙት የቃላት/የፈሊጥ ጥያቄዎች መሠረታዊ ምክንያት ማግኘት ያዳግታል።

በስምንቱ አመታት ፈተናዎች ውስጥ 18 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ለፈተና ሲቀርቡ አናገኛለን። አንድ ቃል ወይም ፈሊጥ በከፍተኛ መጠን ሲደጋገም የተገኘው ለሦስት ጊዜ ያህል ነው። በዚህም መሠረት ሦስት ቃላት /ዘከረ፣ ገንገን እና ገመና/በሦስት አመታት ፈተናዎች ውስጥ በተደጋጋሚ ለፈተና ቀርበዋል። ተደጋጋሚ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎችን በብዛት የያዘ ፈተና የ1986 ዓ.ም. ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 9 የቃላትና 3 የፈሊጥ ጥያቄዎች ከሌሎች አመታት ፈተናዎች በቀጥታ የተወሰዱ ይመስላሉ። የተደጋገሙት ቃላትና ፈሊጦች የሚከተሉት

ናቸው። ቀጠፈ፣ እንከን፣ እንጃ ፣ገመና፣ እዛጋ፣ ገንገን፣ ዘክረ፣ እንቶ ፈንቶ፣ ቶፋ፣ በገሃድ፣ ቁርጠ ቀጥልና ቅቤ ጠባሽ። የድግግሙ ሁኔታ ለማሳየትም የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንጠቅሳለን።

{1981. ጥ.4.ገንገን ሀ. ጠረጠረ ለ. በረገገ ሐ. መረመረ መ. ገመገመ
{1986. ጥ.2. ገንገን ሀ. ሠረሠረ ለ. በረበረ ሐ. ጠረጠረ መ. ደረደረ

{1983. ጥ.1. ዘክረ ሀ. አስታወሰ ለ. አሳሰበ ሐ. አመላከተ መ. አስጠራ
{1986. ጥ.9. ዘክረ ሀ. አስተናገደ ለ. አስታመመ ሐ. አስታወሰ መ. አከረረ

{1983. ጥ. 4 እንቶፈንቶ ሀ. የማይረባ ለ. ምናምንቴ ሐ. ከንቱ አ. ዝባዝንኬ
{1986. ጥ. እንቶፈንቶ ሀ. ልቅምሥራ ለ. የእጅሥራ ሐ. ውሽልሽልሥራ መ. ጥግንስራ

ከ1986ቱ ፈተና በተጨማሪ በሌሎች አመታትም ቃላትና ፈሊጦች ሲደጋገሙ ተስተውሏል። የተደጋገሙትም የሚከተሉት ናቸው። 'ግንዛቤ' /በ1978 እና በ1982/፣ 'ዳተኛ' /በ1979 እና በ1985/፣ 'ጥርስ ገባ' /በ1979 እና በ1980/፣ 'ድበላ' /በ1982 እና በ1984/፣ 'ጥራዝ ነጠቅ' /በ1983 እና በ1985/ እና 'ነፈረቀ'/በ1980 እና በ1987/። አንድን ቃል ወይም ፈሊጥ በየፈተናዎች ለመደጋገም የመልስ ትንተና ካልተካሔደ ተጨባጭ ምክንያት አለ ለማለት ያስቸግራል። በመሆኑም የተደጋገሙት ጥያቄዎች ውጤታማና ጠቃሚ ናቸው ለማለት አያስደፍሩም።

ለማጠቃለል የቃላት መረጣ ብርቱ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ስራ ቢሆንም በፈተናዎቻችን ውስጥ ይህ ተግባር የተዘነጋ ይመስላል። በተለይ ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በመማሪያ መጽሐፍቱ ላይ አለመመስረታቸው የተማሪውን ችሎታ ለመመዘን ብቃት እንዲነድላቸው አንድ ምክንያት ሆነዋል። ሂልናዱቢን /1981/ የጠቀሱት ምሣሌ በኛም ፈተናዎች ውስጥ የሚንፀባረቅ ይመስላል።

> ...ተማሪዎች በፈታኙ ሳይታሰብባቸው ክበርካታ የእንግሊዝኛ ቃላት ውስጥ ለአምስቱ ቃላት ፍች እንዲሰጡ ቢጠየቁ፣ ተማሪው ቃላቱን አወቃቸው አላወቃቸው የዕድል ጥያቄ ነው። ምክንያቱም ተማሪ 'ሀ ' በክፍል ውስጥ የቃላት ትምህርት የተማረ 'ለ'ን እጥፍ ቃላት ቢያውቅ እንኳ ችሎታውን ሊያሳይ አይችልም። ለምን ቢባል ቃላቱ የተመረጡት በዘፈቀደነውና ለሁሉም ተማሪዎች እኩል ታዋቂነት አይኖራቸውም። ስለዚህ እድሎቹንትን ሊያሳይ ይችላል።
>
> /ሂልና ዱቢን፣ 1981:135/

### 4.1.2.3 የተገቢ አውድ አዘገጃጀት

በምርጫ ስጭ የቃላት ጥያቄዎች አዘገጃጀት ውስጥ ሦስተኛው መርህ ለተመረጡ ቃላት ተገቢ አውድ ማዘጋጀት መሆኑ በምዕራፍ ሁለት በዝርዝር ተገልጿል። በተለይ ማድሰን /1983/ ቃላትን ያለአውድ መፈተን ተገቢ አለመሆኑን አጠንክረው ይገልፃሉ። ብራይትና ግሪገር /1978/፣ላዶ/1961/ እና ሂተን /1975/ የማድሰንን ሀሳብ ይጋራሉ። ተገቢ አውድ ለቃላት ፈተናዎችን ማዘጋጀት በውጭ ምሁራን ተቀባይነት ያለው መርህ ነው።

መርሁ ለሀገራችን የቃላት ትምህርት አስጣጥም ተስማሚ የመፈተኛ ዘዴ ይመስላል። ምክንያቱም አንደኛ አብዛኞቹ መምህራን ቃላትን የሚያስተምሩበት ዘዴ አውዳዊ ነው። ሁለተኛ በሲለበሶች ውስጥ በተደጋጋሚ የሚጠቀመው ዘዴ አውዳዊ ነው። በሦስተኛም ደረጃ ተማሪው በመማሪያ መጽሐፍቱ መልመጃዎች ውስጥ ቃላትን የሚለማመደው በአውድ ነው። ስለዚህ ቃላትን በአውድ ውስጥ መፈተን የቃላት ትምህርቱን አላማና የማስተማሪያ ዘዴ መሠረት ያደረገ ስለሚሆን ተስማሚ ዘዴ ይመስላል። ይሁን እንጂ በስምንቱ አመታት ፈተናዎች ውስጥ ቃላት በአውድና ያለአውድ ሲቀርቡ እናገኛለን። ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ከላይ የተጠቀሱውን መርህ የሚጥሱ ናቸው። ስለሆነም ለቃላት ትምህርቱ አስጣጥ ተስማሚ የመፈተኛ ዘዴ መሆን ወይም አለመሆናቸውን ለመመርመር ተሞክሯል።

ለመምህራን በተዘጋጀው መጠይቅ ውስጥ ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ መሆን አለመሆኛቸውን ለማወቅ 6 ጥያቄዎች ቀርበው ነበር። እነሱም በመጠይቁ ተራ ቁጥር 14፣ 15፣ 16፣ 20፣ 23 እና 24 ላይ ይገኛሉ። የሚከተለው ሰንጠረዥ መምህራኑ ለየጥያቄው የሰጡትን መልስ በመቶኛ ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 10 ያለአውድ የቀረቡ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎችን በተመለከተ መምህራኑ የሰጧቸውን መልሶች በመቶኛ የሚያሳይ።

| | ጥያቄው | የሚስማሙ | የማይስማሙ | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 14 | የቃላትን አፈታት የማስተምርበት ዘዴ የሁ.ደ .መ.እ.ፈ. የቃላት ጥያቄዎችን በትክክል ለመመለስ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል ብዬ አምናለሁ። | 42 | 58 | 100 |
| 15 | የፈሊጦችን አፈታት የማስተምርበት ዘዴ የሁ.ደ.መ.እ.ፈ. የፈሊጥ ጥያቄዎችን በትክክል ለመመለስ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል ብዬ አምናለሁ። | 34 | 66 | 100 |
| 16 | በት/ቤት በምናዘጋጃቸው ፈተናዎች ውስጥ የሚካተቱት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የጥያቄ አቀራረብ ስልት ከሁ.ደ.መ.እ.ፈ. የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የጥያቄ አቀራረብ ስልት ጋር ተመሣሣይ ነው። | 72 | 28 | 100 |
| 20 | የሁ.ደ.መ.እ.ፈ. የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በአብዛኛው የሚቀርቡት ያለአውድ ነው። ይህ አቀራረብ ቃላትና ፈሊጦችን ከማስተምርበት ዘዴ እና ከትምህርቱ አላማ አንፃር ተስማሚ ዘዴ ነው እላለሁ። | 26 | 74 | 100 |
| 23 | ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች አላማ ግልጽ አይደለም ብዬ አምናለሁ። | 30 | 70 | 100 |
| 24 | የቃላትን ፈተና ሙሉ ለሙሉ አውዳዊ ማድረግ ስለሚያስቸግር እንደሁኔታው በአውድና ያለአውድ ጥያቄዎችን ማቅረብ ተገቢ ነው እላለሁ። | 42 | 58 | 100 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛቹ መምህራን ቃላትና ፈሊጦችን የሚያስተምሩበት ዘዴ የሁ.ደ .መ.እ .ፈ .ን በትክክል ለመመለስ ከፍተኛ እገዛ አያደርግም ብለዋል። ይህ የመምህራኑ መልስ ፈተናዎቹ ያለአውድ ከመቅረባቸውና ከአመራረጣቸው መስፈርት የተነሣ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። አብዛኛቹ መምህራን /74%/ ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ከሚያስተምሩበት ዘዴ እና ከትምህርቱ አላማ አንፃር ተስማሚ ዘዴ አለመሆናቸውን አረጋግጠዋል። ከዚሁም ጋር 70% የሚሆኑት መላሾች ያለአውድ የቀረቡት ጥያቄዎች አላማ ግልጽ አይደለም ብለዋል። በመጨረሻም ሁሉንም የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በአውድ ማቅረብ እንደሚገባ አብዛኛቹ መምህራን ተስማምተዋል።

አብዛኛቹ መምህራን ያለአውድ የቀረቡትን ጥያቄዎች ሲኮንኑ ሰንጠረዡ ያመለክታል። ሆኖም መምህራኑ ለጥያቄ 16 የሰጡት መልስ ኩነናውን የሚያፈርስ ይመስላል። ይኸውም 72% የሚሆኑት

መላሾች በክፍል ውስጥ የሚያዘጋጇቸው ጥያቄዎች ከሁ.ደ.መ.አ.ፈ.አቀራረብ ጋር ተመሣሣይ ነው ብለዋል። የሀገራችን ትምህርት ለፈተና እንደመገዛቱ መምህራኑ በሚያዘጋጇቸው ፈተናዎች ላይ የሁ.ደ .መ.አ .ፈ . የአጠያየቅ ስልት ተጽእኖ ያሳደረባቸው ይመስላል። ይህም ስለሞን /1976/የሁ.ደ.መ.አ .ፈ . በክፍል በሚዘጋጁ ፈተናዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ያለውን የሚያጠናክር ነው።

በአጠቃላይ አብዛኞቹ መምህራን ያለአውድ የሚቀርቡ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ አለመሆናቸውን አረጋግጠዋል። ይህ የአብዛኞቹ መምህራን አመለካከት ከአጥኚው ጋር የሚመሳሰል ነው። ቀደም ሲል የትምህርቱን አላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና የመማሪያ መጽሐፍቱን መልመጃዎች ስንመረምር እንዳነሳነው የትምህርቱ አሰጣጥ አውዳዊ በመሆኑ ፈተናዎቹም በአውድ ላይ ማተኮር ይጠበቅባቸዋል። ይህ እስካልሆነ ድረስ ግን የፈተናው አላማ በግልጽ አይታወቅም። ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያም ሊሆኑ አይችሉም።

በሌላ በኩል አብዛኞቹ መምህራን በአንድ ወገን ያለአውድ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን እየኮነኑና እንዲለወጡ ስምምነታቸውን እየገለጹ በሌላ ወገን ራሳቸው በሚያዘጋጇቸው ፈተናዎች ውስጥ ቃላትና ፈሊጦችን ያለአውድ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም። ፈተናው ጎጅ ጎን ካለው በተቻለ መጠን ለማስተካከል መጣር እንጂ ገና ለገና "ተማሪዎቼ፣ፈተናውን እንዲያልፉልኝ " በሚል ስሜት የአጠያየቅ ስልቱን መከተላቸው ተገቢ አይመስለንም።

ከዚህ በላይ ለማመልከት እንደተሞከረው በምርጫ ስጭ የቃላት ጥያቄዎች ውስጥ የአውድ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም። ይልቁንም የሚያጠያይቀውና ሊታሰብበት የሚገባው ጉዳይ እንደምን ተገቢ አውድ እናዘጋጅ የሚለው ነው። ተገቢ አውድ የማዘጋጀቱ ስራ ደግሞ ብርቱ ድካምና ጥንቃቄን እንደሚጠይቅ ሂዩዝ/1989/እና ሃሪስን /1983/ ይመስክራሉ። ስራው ብርቱ ድካምና ጥንቃቄን ይጠይቃል ተብሎ ግን የሚተው አይደለም። ለስራው ሰፊ ጊዜ ከሰጠነውና ከፍተኛ የሀላፊነት ስሜት ከተሰማን ማዘጋጀቱ እንደማይከብድ ምሁራኑ ያሳስባሉ።

በመሆኑም ለጥቂው ተግባር በአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተገቢ አውድ ተዘጋጅቶላቸዋል ወይ? የሚለውን መመርመር ይሆናል። በስምንቱ አመታት ፈተናዎች ውስጥ በአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች 82 ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ 65ቱ ምንባባዊ

አውድ ተዘጋጅቶላቸዋል። 2ቱ አ ጋገራዊ አውድ ሲዘጋጅላቸው ቀሪዎቹ 15ቱ ደግሞ የተለየውን ቃል አውጣ የሚል አውድ አላቸው። በመጀመሪያ ምንባባዊ አውድ የቀረበላቸውን 65 ጥያቄዎች ለመመልከት እንሞክራለን።

የምንባብ ጥያቄዎች ዋና አላማ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ለመመዘን መሆኑ ይታወቃል። ሆኖም የቃላት ጥያቄዎች በምንባብ ውስጥ ተዳብለው መቅረባቸው የተለመደ ነው። ምንባባዊ አውድ ያላቸውን የቃላት ጥያቄዎች ለመጠየቅ ሲፈለግም ሊታሰብበት የሚገባ ዋና ጉዳይ ምንባቡ ጥያቄውን ለመመለስ በቂ ድጋፍ ይሰጣል ወይ? የሚለው ነው። /ማድሰን፤1983 እና ላዶ፤1961/በዚህም መሠረት ምንባባዊ አውድ ያላቸው 65ቱ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተመርምረዋል። በውጤቱም አብዛኞቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ምንባቦቹ በቂ ድጋፍ መስጠታቸው ተረጋግጧል።

የሚከተሉትን ሁለት ምሣሌዎች ብንመለከት ምንባቦቹ እንደምን በቂ ድጋፍ እንደሚሰጡ ለማረጋገጥ ይቻላል።

<u>ምሳሌ</u> 1. 1981.ጥ.39. በስንኝ 14 ላይ " ለኔ ብጤማ "ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. ለደሃው ማለቱ ነው። ሐ . ረሀብን ላልቀመሰው ማለቱ ነው።

ለ . ረሃብ ላጠቃው ማለቱ ነው። መ. በችግር ለተጎዳው ማለቱ ነው።

በምሣሌ 1 ለቀረበው ፈሊጥ ምንባቡን ሳናነብ ለመመለስ ብንሞክር ትክክለኛውን መልስ ለማግኘት እንቸገራለን። ምክንያቱም ለፈሊጡ የተለመደው ፍች ምርጫ ' ሀ ' ነው። ሆኖም የቀረበውን ግጥም ደጋግመን ስናነበው ገጣሚው ለማለት የፈለገው ምርጫ ' ሐ' ን ነው። ስለዚህ ፈሊጡን " አውቀዋለሁ ! " በሚል ስሜት ጥያቄውን ለመመለስ ብንሞክር እንሳሳታለን። በእንፃሩ ፈሊጡን ባናውቀው እንኳ ምንባቡን በደንብ ካነበብነው የፈሊጡን ፍች በትክክል ለመመለስ አንቸገርም። ስለዚህ ጥያቄውን ለመመለስ ምንባቡ በቂ ድጋፍ ይሰጣል እንላለን።

<u>ምሳሌ</u> 2. 1985 ጥ.90 "የወላንሳነት " ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. ቀረርቶንቻማነት ለ . ለስላሳነት ሐ . ጎርባጣነት መ. ረዥምነት

በምሣሌ 2 ለቀረበው ጥያቄ ተፈታኙ ቃሉን ባያውቀውም ምንባቡን ደጋግሞ ካነበበው ለመመለስ አይቸገርም። የምንባቡ አውድ የሚከተለው ነው። "...ከንፋስ የሚወነጨፈው የደስታ መዓዛ ከተማውን ሲያወደው ሰውነት በደስታ ከመርካቱ የተነሳ መጥፎ ነገር ባፍንጫ አይገባም። በዓይን አይታይም። በጆሮ አይሰማም። በአፍ አይነገርም። ከመንገዱ ወላንሳንት የተነሳ እግር ከፈቀደው ላይ ቢያርፍ አይሰናከልም። "

/ሁ. ደ. መ. አ. ፈ. 1985 ፡ 15/

ምንባቡን ደጋግሞ በማንበብ ምርጫ 'ለ' ን ለመመለስ ስለማያዳግት ምንባቡ በቂ ድጋፍ ይሰጣል ማለት ይቻላል። ስለዚህም ለቃሉ ተገቢ አውድ ተዘጋጅቶለታል እንላለን።

በአጠቃላይ ምንባባዊ አውድ ካላቸው 65 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ ለ60 ዎቹ ጥያቄዎች ተገቢ አውድ እንደተዘጋጀላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል። ቀሪዎቹ 5 ጥያቄዎች ግን ተገቢ አውድ የላቸውም። ለዚህም ዋናው ምክንያት ምንባቡ የተፈለገውን ያህል ጊዜ ቢነበብ ጥያቄዎቹን ለመመለስ በቂ ድጋፍ ስለማይሰጥ ነው። እነዚህም ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው። 1980 . ጥ. 36፣ 1981. ጥ. 42፣ 1983.ጥ.21፣ 1986.ጥ.71ና 1987 ጥ.63 ናቸው። ዝርዝሩን ከአባሪ ሀ መመልከት ስለሚቻል አንድ ምሳሌ እንጠቅሳለን።

ምሳሌ 1987 ጥ.63."ህልውና የጨፈቀው" የሚለው ሐረግ ምን ማለት ነው።

ሀ/ ኑሮ ያንገሸገሸው ሐ/ ኑሮ እጅ እጅ ያለው

ለ/ ኑሮ ያስጨነቀው መ/ ኑሮ ያጎሳቆለው

በምሣሌው ለቀረበው ጥያቄ ምንባቡን ደጋግመን ብናነበውም የተዘጋጀው አውድ ጥያቄውን ለመመለስ በቂ ድጋፍ አይሰጥም። ስለሆነም ለቃሉ ተገቢ አውድ አልተዘጋጀለትም ማለት ይቻላል።

በአውድ ከቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱ በዐ.ነገራዊ አውድ የቀረቡ ናቸው። እነሱም የ1987 ጥያቄዎች ናቸው። ለሁለቱም ጥያቄዎች የቀረበው አውድ ፍችውን ከአገባቡ ለመረዳት ስለሚያገለግል ተገቢ አውድ የተዘጋጀላቸው ሆነው ተገኝተዋል። በተለይ ያለአውድ ከቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች አንፃር ሲታዩ የቀረቡት አውዶች ፍችን ለመገመት እንደሚረዱ አያጠራጥርም። ስለሆነም የዚህ አይነት ጥያቄዎች በርከት ብለው ቢዘጋጁ መልካም ነው።

አውድ ከቀረበላቸው የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ በመጨረሻ የምንመለከተው ልዩ የሆነውን ቃል አውጣ በሚል መመሪያ የቀረቡትን 15 ጥያቄዎች ነው። እነሱም በ1980 እና 1981 ዓ.ም. የቀረቡ ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች ተፈታኙ በተዛማጅና በተቀራራቢ ቃላት መካከል ያለውን የፍች ልዩነት መረዳት አለመረዳቱን የሚመዝኑ ናቸው።

በመሆኑም ተፈታኙ ባንድ በኩል ተቀራራቢ 3 ቃላት በሌላ በኩል ልዩ የሆነ አንድ ቃል ስለሚቀርብለት ልዩ የሆነውን ቃል ከተቀራራቢዎቹ ለመምረጥ አውድ እንዳለ ይሰማናል። በቃላት ጥያቄዎች ውስጥ ዐ.ነገራዊና ምንባባዊ አውድ መዘጋጀት የግድ ላይሆን ይችላል። ስለዚህ ይህ ዓይነቱ አጠያየቅ ለቃላት ትምህርቱ ተገቢ ከመሆኑም በላይ ለየቃላቱ አውድ እንደቀረበላቸው የሚቆጠር ነው።

ለማጠቃለል በምርጫ ሰጭ የቃላት ጥያቄ አዘገጃጀት ውስጥ ተገቢ አውድ የማዘጋጀት ተግባር ሊዘነጋ አይገባውም። ተገቢ አውድ ሲባል የትምህርቱን ዓላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና ልምምዱን መሠረት በማድረግ ዐ. ነገራዊ፣ ምንባባዊ፣ ህዳጋዊ (cloze)፣ አዛምድ፣ ልዩ የሆነውን ቃል አውጣ ወዘተ. ሊሆን ይችላል። በስምንቱ ዓመታት ፈተናዎች ውስጥ በአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተስማሚ የመፈተኛ ዘዴዎች ስለሆኑ በተለያየ የአጠያየቅ ስልት በመታገዝ ይበልጥ ልንገለገልባቸው ይገባል። ባንፃሩ ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ሙሉ-ራን ከሚያቀርቧቸው መርሆዎች እና ከአማርኛ የቃላት ትምህርት አሰጣጥ አንፃር ተስማሚ የመፈተኛ ዘዴዎች ስላልሆኑ ሊወገዱ እንደሚገባቸው የጥናቱ ውጤት አመልክቷል።

#### 4.1.2.4 የአሳሳቾች ተአማኒነት /plausibility of distractors/

በምርጫ ሰጪ የቃላት ጥያቄዎች አዘገጃጀት አራተኛው መርህ ያሳሳቾችን ተአማኒነት መጠበቅ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ፈተና አውጭው አሳሳቾችን በቅርጽ ተመሳሳይ/ ለምሳሌ ዋናውን መልስ ቅጽል ከሆነ አሳሳቾችን በሙሉ ቅጽል ማድረግ/፣ በርዝማኔና በክብደት ደረጃ ተመጣጣኝ እንዲሆኑ መጣር ይጠበቅበታል። /ማድሰን፣ 1983 እና ሂተን፣1975/ የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በምርጫ ሰጪ የጥያቄ አቀራረብ የተዘጋጁ በመሆናቸው ያሳሳቾችን ተአማኒነት መመርምር ያስፈልጋል።

የአንድን ፈተና አሳሳቾች ለመመርመር የሚደረገው ጥረት ግን ሰፊ ጊዜን የሚጠይቅ ነው። ይህም የበርካታ ተፈታኞችን ውጤት በመልስ ትንተና በመስራት የትኞቹ አሳሳቾች ይበልጥ መልስ የመምሰል ባህሪ እንዳላቸው ነቅሶ ማውጣትን ይጠይቃል። ይህ ደግሞ ራሱን የቻለ ታላቅ የጥናት ርዕስ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም አጥኚው ይዟቸው ከተነሳቸው በርካታ ጥያቄዎችና ካለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት አንፃር ርዕሰ ጉዳዩን በጥልቀት ለመመርመር አልቻለም።

ያም ሆኖ ግን የወደፊት ተመራማሪዎች በርዕስ ጉዳዩ ጥልቅ ጥናት እስኪያደርጉበት ድረስ በውጫዊ መልኩ የአሳሳቾችን ተአማኒ መሆን ወይም አለመሆን ለመመርመር ተሞክሯል። የአሳሳቾች ውጫዊ መልክ ሲባል አሳሳቾቹ ከቀናው መልስ ጋር በቅርጽ ተመሳሳይ፣ በርዝማኔና በክብደት ደረጃ ተመጣጣኝ መሆናቸውን መመርመር ማለታችን ነው።

በምርመራው አብዛኞቹ አሳሳቾች ከቀናው መልስ ጋር በቅርጽ ተመሳሳይ፣ በርዝማኔና በክብደት ደረጃ ተመጣጣኝ ሆነው ተገኝተዋል። ስለሆነም አሳሳቾቹ ተአማኒነት ያላቸው ይመስላሉ። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች እንመልከት።

ምሳሌ 1. 1981. ጥ.2. ተረበኛ

ሀ. አፈኛ ለ. ወገኛ ሐ. ቀልደኛ መ. ጉረኛ

ምሳሌ 2. 1984. ጥ. 4. ተለመዘገ

ሀ. ተቆነጠጠ ለ. ተፈተለ ሐ. ተልመዘመዘ መ. ተሳበ

በምሣሌ 1 የቀረበውን ጥያቄ ብንመለከት ትክክለኛው መልስ ምርጫ 'ሐ' ነው። የቀረቡትን አሳሳቾች ስንመለከት ደግሞ ሁሉም ከትክክለኛው መልስ ጋር በቅርጽ ይመሳሰላሉ። (ሁሉም ቅጽሎች ናቸውና/ በርዝማኔም ደረጃ ትክክለኛው መልስ በጣም ረዘም ብሎ አይታይም። ይልቁንም ተመጣጣኝነታቸው ጎልቶ ይታያል። በክብደት ደረጃም ሲታይ ትክክለኛው መልስ ከበድ ብሎ አይታይም ። ስለሆነም አሳሳቾቹ ተአማኒ ናቸው እንላለን።

ምንም እንኳ የአብዛኞቹ ጥያቄዎች አሳሳቾች ተአማኒነት ቢኖራቸውም የ2 ጥያቄዎች አሳሳቾች ግን ተአማኒነት ሲጎድላቸው ተስተውሏል። እነሱም በ1984 ፈተና ውስጥ የቀረቡት ጥ.71 እና ጥ.61 ናቸው። ለአብነት ያህል ጥያቄ 71ን እንመልከት።

ምሳሌ 1984. ጥ.71 በምንባቡ መሠረት የትውልድ 'ድልድይ' ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. ትውልድ የሰራው ድልድይ ሐ. ድልድይ ለትውልድ መሻገሪያ ያገለግላል

ለ. ትውልድ የሚሻጋገርበት ድልድይ መ/ አንዱ ትውልድ ወደሚቀጥለው ትውልድ የራሱን ባህል የሚያሸጋግርበት መንገድ

በምሳሌው የቀረበው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ምርጫ 'መ' ነው። ትክክለኛውን መልስ ካሳሳቾች ጋር ስናስተያየው ረጅም ነው። ትሮንዳይ ከና ሄግን/1977/እና ማድሰን/ 1983/ እንደሚያስገነዝቡት ትክክለኛውን መልስ ካሳሳቾች ረዘም ባለ ሁኔታ ማቅረብ የብዙ የምርጫ ሰጭ ጥያቄ አዘጋጆች ተደጋጋሚ ስህተት ነው። ከላይ በምሳሌው የሚታየውም ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ከአሳሳቾች የተለየ በመሆኑ ተፈታኙ በቀላሉ መልሱን ሊያገኘው ይችላል። ይህም የአሳሳቾችን ተአማኒነት ያደበዝዘዋል።

በአጠቃላይ ጥናቱ ባካተታቸው ፈተናዎቹ ውስጥ የምናገኛቸው አሳሳቾች በታላቅ ጥንቃቄ የተዘጋጁ ይመስላሉ። አሳሳቾች በአብዛኛው በቅርጽ ተመሳሳይ፣ በክብደት ደረጃና በርዝማኔ ተመጣጣኝ በመሆናቸው ትክክለኛው መልስ በቀላሉ እንዳይገኝ ይረዳሉ። ይህም የፈተና አዘጋጆች ተግባራቸውን በጥንቃቄ ማከናወናቸውን የሚጠቁም ይመስለናል። ያም ሆኖ ግን በአንድንድ ጥያቄዎች ውስጥ "ሁሉም መልስ ናቸው"፣/ ሁሉም 'መልስ አይደሉም "፣ 'ሐ እና ለ' ወዘተ አማራጮች ከፈተናዎቹ ቢወገዱ ያሳሳቾች ተአማኒነት ይበልጥ የተዋጠ ስለሚሆን ቢታሰብበት መልካም ነው።

## 4.1.2.5 ትክክለኛው መልስ አንድ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ

በምርጫ ሰጭ የቃላት ጥያቄ አዘገጃጀት የመጨረሻው መርህ ለጥያቄው አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ መኖሩን ማረጋገጥ ነው። በመሆኑም ሁሉም የፈተናዎቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ባለሙያዎች የሚስማሙበት አንድና የማያሻማ መልስ ማያዝ ወይም አለመያዛቸውን ለመመርመር ሞክረናል።

የትንታኔው ቀዳሚ ተግባር የሁ.ደ.መ.ፈ. ጽ/ቤት የፈተናዎቹን መልስ /key/ እንዲሰጥ ትብብር መጠየቅ ነበር። ሆኖም ተደጋጋሚ ጥረት ቢደረግም ጽ/ቤቱ ከ1987 ዓ.ም. ፈተና መልስ በስተቀር የሌሎቹን ፈተናዎች መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነም። የመልስ ቁልፎቹን ከሁ.ደ.መ.ፈ . ጽ/ቤት ለማግኘት የተደረገው ሙከራ ባይሳካም የትንታኔውን ተግባር ግን ሙሉ ለሙሉ አላሰናከለውም።

በመሆኑም በቅድሚያ አጥኚው ለስምንቱ ዓመታት የቃላትና የፊሊጥ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞከረ። ቀጥሎም 6 ባለሙያዎች ለሁሉም ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ተደረገ። ሶስቱ ባለሙያዎች ቋንቋውን ለረጅም ጊዜ ያስተማሩ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሲሆኑ ሦስቱ ደግሞ የድህረ ምረቃው ክፍል የ TEAM ተማሪዎች ናቸው። ለባለሙያዎቹም አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቷቸው ጥያቄዎች ካሉ ለቅመው እንዲያወጧቸውና ምክንያቱን እንዲገልጹ አጥኚው መመሪያ ሰጥቷቸዋል።

ባለሙያዎቹና አጥኚው አንድ ዓይነት መልስ ያልሰጡባቸው ጥያቄዎች ተለይተው ከታወቁ በኃላ ትንታኔው ተካሄደ። በሌላ አገላለጽ 6ቱ ባለሙያዎች የተለያየ መልስ የሰጡባቸው ጥያቄዎችና አጥኚው በግሉ ያስቸገሩት ጥያቄዎች ተለይተው ከታወቁ በኃላ አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ጥያቄዎች በሚል ተፈርጀው ትንታኔው ተካሂዷል።

የሚከተለው ሠንጠረዥ በፈተናዎቹ ውስጥ አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ቁጥርና መቶኛ ያሣያል።

### ሰንጠረዥ 11 አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎችን ቁጥርና መቶኛ የሚያሳይ።

| የተዘጋጀበት ዓ.ም. | በቁጥር | መቶኛ |
|---|---|---|
| 1980 | 6 | 25 |
| 1981 | 5 | 12.5 |
| 1982 | 11 | 5.0 |
| 1983 | 9 | 25.7 |
| 1984 | 6 | 18.1 |
| 1985 | 9 | 19.1 |
| 1986 | 5 | 14.3 |
| 1987 | 5 | 15.2 |
| ድምር | 55 | 204 |

ከስንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ከ269 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ 55ቱ ወይም 20.4 የሚሆኑት አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ናቸው። የጥያቄዎቹን ዝርዝር በአባሪ ሀ መመልከት ስለሚቻል እዚህ ላይ የጥያቄውን ቁጥርና ጥቂት ምሳሌዎችን ብቻ ለመመልከት ይሞከራል።

ከ1980 ፈተና ውስጥ ጥያቄ 1፣ 6፣ 8፣ 11፣ 30፣ እና 38 አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ሦስት ምሳሌዎችን እንመልከት።

ምሳሌ 1. 1980. ጥ.1. ነፈረቀ./ ተመሣሣይ ፍች ስጥ/

ሀ. አለቀሰ. ለ. ሞጨሞጨ ሐ. ተንሰቀሰቀ መ. አሳዘነ

2. 1980. ጥ.8 ፈርያዘ /ተመሣሣይፍች ስጥ/

ሀ. ሥርዓት ያዘ ለ . አቅጣጫ ያዘ ሐ . መስመር ያዘ መ. ሕግ ያዘ

3. 1980 ጥ.30. "ታጥቦ ጭቃ "ማለት ምን ማለት ነው?/ተመሣሣይ ፍች/

ሀ. ክርሞ ጥኝ ማለት ነው። ሐ . ተመልሶ እዚያው ማለት ነው።

ለ . ታጥቦ መጨቅየት ማለት ነው። መ. ቢታጠብ የማይፀዳ ማለት ነው።

በ1980 ከቀረቡት 24 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ ለስድስቱ ጥያቄዎች አንድና የማያሻማ መልስ ለመስጠት ያዳግታል። ለዚህም ምክንያቶቹ ለየጥያቄው አጥጋቢ ተመሣሣይ ወይም ተቃራኒ ፍች በአማራጮች ውስጥ አለመቅረብና አማራጮቹ ሁለት መልስ መያዝ ናቸው። ከላይ የቀረቡትን ሦስት ምሳሌዎች እንኳ ብንመለከት ለምሳሌ 1. አጥጋቢ መልስ አናገኝም። ካሉት አማራጮች የግድ መልስ እንስጥ ብንል ደግሞ ምርጫ "ሀ "እና "ሐ " መልስ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም ለምሳሌ 2 እና 3 ሁለት ትክክለኛ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት አማራጮችን እናገኛለን። እነሱም በቅደም ተከተል " ሀ ና ሐ " እና "ለ ና ሐ" ናቸው።

ከ1981 ፈተና ውስጥ ጥያቄ 5፣14፣15፣20 እና 41 መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ናቸው። የሚከተሉትን ሁለት ምሳሌዎች በመመልከት ችግሩን መረዳት ይቻላል።

ምሳሌ 1. ጥ.5 ድኅማ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. ምፅዋት ለ . ድጋፍ ሐ . ዕርዳታ መ. ልግሥና

2. ጥ.14 /ልዩ የሆነውን ቃል አውጣ /

ሀ. መዘንጠል ለ . መቀርደድ ሐ . መንደል መ. መፈንቀል

በምሣሌዎቹ ለቀረቡት ጥያቄዎች አንድ አጥጋቢና ትክክለኛ መልስ ለመስጠት እንቸገራለን። ለምሳሌ 1 ሁለት መልስ ብንሰጥ /ለ ና ሐ / ተቀባይ የማይሆንበት ምክንያት ያለ አይመስለንም። በምሳሌ 2 ለቀረበው ጥያቄም አንድ መልስ መስጠቱ ያዳግታል። ምክንያቱም ምርጫ ሀ ና ለ የሚዛመዱ ቃላት ናቸው ብንል እንኳ ምርጫ ሐና መ ከእነሱ ጋር አይዛመዱም። ስለዚህ ጥያቄው ሁለት መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን ስለያዘ አንድ መልስ ለመስጠት ያዳግታል እንላለን።

ከ1982 ፈተና ውስጥ ጥያቄ 1፣ 3፣ 6፣9፣ 10፣ 11፣12።13፣14፣15 እና 36 አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ናቸው። ከስምንቱ አመታት ፈተናዎች ውስጥ አንድ መልስ ለመስጠት በማዳገት በኩል የዚህ አመት ፈተናዎች ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ። ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው 50% ለሚሆኑት ጥያቄዎች አንድ መልስ መስጠት ያዳግታል ።የሚከተሉት ምሣሌዎች ዋቢ ይሆናሉ።

ምሣሌ 1 . ጥ.1. አገናዘበ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. አስታወሰ ለ. አያያዘ ሐ/ አዛመደ መ. አቀራኘ

2. ጥ.3. ጎመራ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. ደረሰ ለ. በሰለ ሐ. አረረ መ. ደረቀ

3. ጥ.14 ነደለ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. አፈረሰ ለ. ዘነጠለ ሐ. ሸነቆረ መ. ፈለፈለ

ከላይ ለተጠቀሱት ሦስት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ አጥጋቢ ተመሳሳይ ፍች ለመስጠት እንቸገራለን። ለእነዚህ ጥያቄዎች ከስድስት ባለሙያዎች ውስጥ አራቱ አጥጋቢ መልስ በአማራጮቹ ውስጥ እንደሌለ አረጋግጠዋል። አጥኚውም የሚያምንበት ነው። ስለዚህ ለጥያቄዎቹ አጥጋቢ ተመሣሣይ ፍች በአማራጮቹ ውስጥ ባለመቅረቡ አንድ መልስ ለመስጠት ያዳግታሉ እንላለን።

ከ1983 ፈተና ውስጥ ጥያቄ 2፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 9፣11፣ 21፣ እና 32 አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ናቸው። የሚከተሉትን ሦስት ምሣሌዎች በማጤን ችግሩን መረዳት ይቻላል።

ምሣሌ 1. ጥ.2 ጥራዝ ነጠቅ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. ደንቆሮ ለ. መሀይም ሐ. ያልተማረ መ. ባለጌ

2. ጥ.7 በዘፈቀደ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. እንዲጋጣሚ ለ. እንዳሻው ሐ. እንደተመቻለ መ. እንደተቻለ

3. ጥ.6 አሳዘነ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. አዘነ ለ. አመረረ ሐ. አለቀሰ መ. አነባ

በምሣሌዎቹ ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ምሣሌ አንድን እንኳ ብንመለከት ለጥያቄው አንድ መልስ ማግኘቱ ያስቸግራል። ምክንያቱም 'ጥራዝ ነጠቅ' ለሚለው ቃል ተመሣሣይ ፍቹ ሰምቶ የሚያወራ' ' /አምሣሉና ዳኛው 1979/ ነው። አማራጮቹ ውስጥ ይህን ፍች ካለማግኘታችንም በላይ ሁለት አማራጮችን መልስ ብናደርግ ትክክል ልንሆን እንችላለን። ይህንንም የምናደርገው የግድ መምረጥ ስላለብን ነው። እናም 'ለ ና ሐ' ቢመረጡ የሚያስኬድ ይመስላል። በርግጥ ' ማይም 'ና' መሀይም' የተለያዩ ናቸው ና ምርጫ 'ለ' አይሆንም የሚል ክርክር ማንሳት ይቻላል። እኛም የምንቀበለው ነው። ነገር ግን ምርጫ 'ሐ' ራሱ ጥራዝ ነጠቅ የሚለውን የሚፈታ አይደለም። ስለዚህ ለጥያቄው አንድ መልስ መስጠት ያዳግታል ማለት ይቻላል።

ከ1984 ፈተና ውስጥ ጥያቄ 1፣ 6፣ 16፣ 17፣ 18፣ 20፣ እና 41 አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ናቸው። የሚከተሉትን ሁለት ምሣሌዎች በመመልከት ችግሩን መረዳት ይቻላል።

ምሳሌ 1. ጥ.18 ፎከተ /ተቃራኒ ፍች ስጥ/

ሀ. ቆፈረ ለ. ፋቀ ሐ. አከከ መ. ደባበሰ

2. ጥ. 20 አደነደነ / ተቃራኒ ፍች ስጥ/

ሀ. አጎላ ለ. አከሳ ሐ. አሰባ መ. አገዘፈ

በምሣሌዎቹ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች አጥጋቢ ተቃራኒ ፍች ለመስጠት የሚያዳግት ይመስለናል። ለምሳሌ ጥያቄ 18ን ብንመለከት 'ፎከተ' ለሚለው ቃል ካሉት አማራጮች ምርጫ 'መ' ተቃራኒፍች ወይም ትክክለኛ መልስ ተብሎ የቀረበ ይመስላል። ይሁን እንጂ የፎከተ ተቃራኒ 'ደባበስ' አለመሆኑ ደግሞ ግልጽ ነው። ስለዚህ አንድ አጥጋቢ መልስ

ለጥያቄው ባለመቅረቡ አንድ መልስ ለመስጠት አዳጋች ነው እንላለን። እንደ ጥያቄ 18 ሁሉ ለጥያቄ 20ም አማራጮች አጥጋቢ ተቃራኒ ፍች ስለማያቀርቡ አንድ መልስ ለመስጠት አዳጋች ነው።

ከ1985 ፈተና ውስጥ ጥያቄ 4፣6፣7፣10፣14፣ 22፣ 23፣ 25 እና 38 አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ናቸው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች በማጤን ችግሩን በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ምሳሌ 1. ጥ.4. አንገራገረ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. አነጋገረ ለ. አመነታ ሐ. ግርግር ፈጠረ መ. ሰው ግራ አጋባ

2. ጥ. 10 ፍጆታ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. አልቂት ለ. ተራ ሐ. ፍጆት መ. ሥሪት

3.. ጥ. 25 ግልጽ /ተቃራኒ ፍች ስጥ/

ሀ. ውስብስብ ለ. ያልተደባለቀ ሐ. የማያሻማ መ. ፍንትው ያለ

በምሳሌዎቹ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች በዝርዝር ብንመለከት ችግሩን መረዳት አያዳግትም። ለምሳሌ 'አንገራገረ' የሚለውን ቃል የአማርኛው መዝገበ ቃላት ከማስፈራራት ጋር በማዛመድ ይፈተዋል። ለጥያቄው በተሠጡት አማራጮች ውስጥ ግን ይህን ቃል በአጥጋቢ ሁኔታ የሚፈታ ምርጫ አናገኝም። ስለዚህ ለጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ያዳግታል የሚለው አባባል ተቀባይነት ይኖረዋል።

በሁለተኛው ምሳሌ 'ፍጆታ' ለሚለው ቃል ከተሰጡት አማራጮች መልስ ማግኘት አዳጋች ነው። ምክንያቱም ሁሉም አማራጮች ቃሉን በተመሣሣይ ፍች የሚፈቱ አይደሉምና። በሦስተኛው ምሣሌ ለቀረበው ቃል የተለመደው ተቃራኒ ፍች 'ድብቅ' ሆኖ ሳለ በመልስነት ግን አልቀረበም። ነሉት አማራጮች ' ውስብስብ' የሚለው 'ግልጽ' ለተባለው ቃል ተቃራኒ ፍች ሆኖ በመልስነት የቀረበ ይመስላል። ነገር ግን 'ውስብስብ' በተቃራኒ ፍችነት ቢቆም ይበልጥ የሚስማማው 'ተራ' ለሚለው እንጅ ግልጸ ለተባለው ቃል አይመስለንም። ስለዚህ ለተጠቀሱት ቃላት አጥጋቢ ተመሣሣይ ወይም ተቃራኒ ፍች እስካልተሰጠ ድረስ ባለሙያዎች የሚስማሙበት አንድ መልስ አለመኖሩ አይቀሬ ነው።

ከ1986 ፈተና ውስጥ ጥያቄ 6፣12፣13፣17 እና 38 አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ናቸው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች በአስረጅነት እናቀርባለን።

ምሳሌ 1. ጥ.12 ገዘገዘ /ተቃራኒ ፍች ስጥ/

ሀ. ቆመጠ ለ. ቀራረጠ ሐ. ቸፈቸፈ መ. ስንጠቀ

2. ጥ. 17 ማንገፍገፍ /ተቃራኒ ፍች ስጥ/

ሀ. ማቅለሽለሽ ለ. ማኮሳተር ሐ. ማብዛት መ. ማበራከት

በምሳሌዎቹ ለቀረቡት ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ለመስጠት ያዳግተናል። ለ 'ገዘገዘ' ሆነ ለ'ማንገፍገፍ' ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ በተቃራኒ ፍችነት መልስ ሊሆን የሚችል አማራጭ አናገኝም። ከሌሎች አማራጮች ጋር በማነጻጸር በቅደም ተከተል ምርጫ 'ለ' እና 'መ ' መልስ ናቸው ማለት ይቻላል። ሆኖም መልሶቹ ለቃላቱ አጥጋቢ ተቃራኒ ፍች እስካልሆኑ ድረስ ባለሙያዎች የሚስማሙበት አንድ ትክክለኛ መልስ ቀርቧል ለማለት አያስደፍሩም።

ከ1987 ፈተና ውስጥ ጥያቄ 11፣ 19፣ 38፣ 34፣ እና 36 አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ናቸው። የሚከተሉት በአስረጅነት ቀርበዋል።

ምሳሌ 1. ጥ. 33 ኀመን በጤና /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. ኀመን ለጤና ይበጃል ሐ. ከአደገኛ ጊትነት በሰላም ድህነት

ለ. በኀመን ጤና ይገኛል መ. ኀመን በልቶ ያድሯል ተኝቶ

2. ጥ. 34 ውርድ ከራሴ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. አልስማማም ለ. አልገባበትም ሐ. ከራሴ ይውረድ መ. ሀና ለ .

3. ጥ. 36. አንገተ ሰባራ /ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. ዝምተኛ ለ. አቀርቅሮ የሚሄድ ሐ. ሀይነአፋር መ. በትካዜ የተሞላ

በምሣሌ አንድ ለቀረበው ጥያቄ ትክክለኛው መልስ ምርጫ 'ሐ' ይመስላል። ይሁን እንጂ የምርጫ 'መ' መኖር ደግሞ 'አንድ እና የማያሻማ ትክክለኛ መልስ አቅርብ' የሚለው መርህ እንዲጣስ መንገድ ይከፍታል። ስለዚህ ምርጫ 'መ' አሻሚነትን ስለሚያስከትል መወገድ ይኖርበታል። በምሳሌ 2 በቀረበው ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ አጥጋቢ ተመሳሳይ ፍች ወይም ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ያዳግታል። 'ውርድ ከራሴ' የሚለው 'ፈሊጥ' ኃላፊነትን ከማውረድ ወይም ካለማስጠየቅ ጋር የተያያዘ ፍች አለው። ይሁን እንጂ በአማራጮቹ ውስጥ ከላይ የተጠቀሰውን ፍች የሚያንፀባርቅ አናገኝም። ስለዚህ አንድ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ያዳግተናል።

በሦስተኛው ምሳሌ ለቀረበው ጥያቄ ደግሞ ሁለት መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች ቀርበዋል። እነሱም ምርጫ 'ሀ' እና ምርጫ 'ሐ' ናቸው። ስለዚህ ጥያቄው ሁለት መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን በመያዙ አንድ መልስ ለመስጠት ያዳግታል እንላለን።

ለማጠቃለል ከ269 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ ለ55ቱ አንድ መልስ ለመስጠት አዳጋች መሆኑን የጥናቱ የትንተና ውጤት ጠቁሟል። ለዚህም አበይት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. ለየጥያቄው አጥጋቢ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍች በአማራጮች ውስጥ አለመቅረብ፣
2. ለአንድ ጥያቄ ሁለት መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች መቅረብ እና
3. አብዛኞቹ ጥያቄዎች ያለአውድ መቅረባቸው ናቸው።

ለመምህራን በቀረበው መጠይቅ ተራ ቁጥር 21 ውስጥ የሚከተለው ጥያቄ ቀርቦ ነበር። 'አንዳንድ ሰዎች የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎችን በትክክል ለመመለስ የሚፈታተኑት ተማሪውን ብቻ ሳይሆን መምህራንንም ጭምር ነው ይላሉ እርስዎ በዚህ አስተያየት ይስማማሉ ወይም አይስማሙም። 'አብዛኞቹ መምህራን /66%/ ለዚህ ጥያቄ ስምምነታቸውን ገልፀዋል። ይህም በፈተናዎቹ ውስጥ አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ጥያቄዎች መኖራቸውን የሚጠቁም ነው።

## 4.2 ህያውነት /Reliability /

ይህ ሌላው የጥሩ ፈተና ባህሪ እንደሆነና ከአስተማማኝነት ጋርም በእጅጉ እንደሚዛመድ በምዕራፍ ሁለት መገለጹ ይታወሳል። ከህያውነት የተለያዩ አይነቶች ውስጥ ደግሞ ይህ ጥናት ውስጣዊ ዘላቂነትን /internal consistency/ እንደሚመለከት በዚያው ምዕራፍ ተገልጿል። በዚህም መሠረት በ1981 ዓ.ም. የሁ.ደ.መ.አ.ፈ. ከወሰዱ መደበኛ ተማሪዎች ውስጥ የ200 ተፈታኞችን ውጤት በመመርመር ውስጣዊ ዘላቂ ህያውነትን ለመተንተን ተሞክሯል።

የትንታኔው መሠረት የመልስ ትንተና /Item analysis / ነው። በዚህም በመጀመሪያ ተፈታኞቹ ለ33ቱ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች ከመልስ ወረቀታቸው /Answer Sheets/ ተወስዷል። ቀጥሎም እያንዳንዱ ተፈታኝ ለየጥያቄው ትክክለኛ መልስ መስጠት አለመስጠቱ በቆጠራ ተረጋግጧል። ይህም አንዱን ጥያቄ ምን ያህል ተፈታኞች እንደመለሱት ወይም እንዳልመለሱት ለማወቅ አስችሏል። በመቀጠልም የእያንዳንዱ ጥያቄ የመለየት ሐይል /Discrimination power/ ተሰልቷል። በመጨረሻም የኩደር ሪቻርድሰንን $KR_{20}$ ቀመር በመጠቀም ህያውነቱ ተሰልቷል። የሚከተለው ሰንጠረዥ 200ዎቹ ተፈታኞች ለ33ቱ ጥያቄ የሰጡትን መልስ መሠረት በማድረግ የውጤት ትንተና ያቀርባል።

ሰንጠረዥ 12 የቃላት ጥያቄዎች ውጤት ትንተና /Item Result/.

Rellability (N= 200) = 0.668

| Item No | Item Diff. (p) | Disc. Power (1) | Pq | Sof Item i. (√pq) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 0.27 | 0.27 | 0.1971 | 0.4440 |
| 2 | 0.42 | 0.33 | 0.2436. | 0.4935 |
| 3 | 0.43 | 0.37 | 0.2451 | 0.4951 |
| 4 | 0.28 | 0.22 | 0.2016. | 0.4489 |
| 5 | 0.66 | 0.35 | 0.2244 | 0.4737 |
| 6 | 0.36 | 0.22 | 0.2304 | 0.48 |
| 7 | 0.48 | 0.50 | 0.2496 | 0.4996 |
| 8 | 0.29 | 0.17 | 0.2059 | 0.4538 |
| 9 | 0.30 | 0.24 | 0.21 | 0.4582 |
| 10 | 0.36 | 0.28 | 0.2304 | 0.48 |
| 11 | 0.5 | 0.74 | 0.25 | 0.5 |
| 12 | 0.85 | 0.24 | 0.1275 | 0.3571 |
| 13 | 0.43 | 0.35 | 0.2451 | 0.4951 |
| 14 | 0.56 | 0.67 | 0.2464 | 0.4961 |
| 15 | 0.57 | 0.41 | 0.2451 | 0.4951 |
| 16 | 0.24 | 0.31 | 0.1824 | 0.4271 |
| 17 | 0.3 | 0.11 | 0.21 | 0.4582 |
| 18 | 0.56 | 0.55 | 0.2464 | 0.4964 |
| 19 | 0.41 | 0.39 | 0.2419 | 0.4918 |
| 20 | 0.43 | 0.37 | 0.2451 | 0.4951 |
| 21 | 0.63 | 0.37 | 0.2457 | 0.4957 |
| 22 | 0.51 | 0.42 | 0.2499 | 0.4999 |
| 31 | 0.49 | 0.26 | 0.2499 | 0.4999 |
| 32 | 0.42 | 0.42 | 0.2436 | 0.4935 |
| 33 | 0.63 | 0.57 | 0.2331 | 0.4828 |
| 34 | 0.57 | 0.33 | 0.2451 | 0.4951 |
| 35 | 0.55 | 0.20 | 0.2475 | 0.4975 |
| 36 | 0.42 | 0.05 | 0.2436 | 0.4935 |
| 37 | 0.42 | 0.31 | 0.2436 | 0.4935 |
| 38 | 0.35 | 0.48 | 0.2275 | 0.4769 |
| 55 | 0.51 | 0.39 | 0.2499 | 0.4999 |
| 63 | 0.26 | 0.3 | 0.1924 | 0.4386 |
| 68 | 0.49 | 0.20 | 0.2491 | 0.4999 |

Mean of P= 0.45; Mean of Dise. Power= 0.33

Where - P= proportion of correct responses

q.= Proportion of incorrect responses

I= Disc. Power

Sofitemi= The square root of pq or (√pq)

ሰንጠረዥን መሠረት በማድረግ ውስጣዊ ዘላቂነት ህያውነት በኩደር ሪቻርድሰን ቀመር ሲሰላ የሚከተለው ይሆናል።

$$KR_{20}\ r = \frac{k}{k-1}\ [1- \frac{pq]}{q^2}$$

$$= \frac{33}{32}\ 1- \frac{7,5997}{215778}$$

$$\approx 1.03125\ (1 - 35219946)$$

= 1. 03125 × 0.647800054
= 0..668

Where r = Relability
k = no. of items
p= proportion of correct resposens or Item Difficulty
q= proportion of incorrect responses
Ó2 = Variance

የሰንጠረዥ 12ን የመጀመሪያ ረድፍ /Item dificullty/ በመመልከት የትኞቹ ጥያቄዎች ከባድ፣ የትኞቹ ደግሞ ቀላል እንደሆኑ ለመረዳት ይቻላል። አብዛኞቹ ፈተታኞች የመለሷቸው ጥያቄዎች እንደ ቀላል ጥያቄ ይቆጠራሉ። አብዛኞቹ ተፈታኞች ያልመለሷቸው ጥያቄዎች ደግሞ እንደ ከባድ ጥያቄ ይቆጠራሉ። እንዲሁም አማካይ ቁጥር ያላቸው መላሾች በትክክል የመለሷቸው ጥያቄዎች እንደ መካከለኛ ጥያቄ ይቆጠራሉ። በቁጥር ሲቀመጡ ከ0.5 በላይ/Item dificullty/ ያላቸው ቀላል ጥያቄዎች፣ ከ0.2 - 0.4 ያላቸው ከባድ ጥያቄዎች እንዲሁም ከ0.4 - 0.5 ያላቸው መካከለኛ ጥያቄዎች ናቸው።/ኢብል፣1979፡178/

በዚህም መሰረት ከ33ቱ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ አሥራ አንዱ ቀላል ጥያቄዎች ይመስላሉ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው። ጥያቄ 5፣11፣12፣14፣15፣18፣21፣22፣23፣35፣ እና 55። ከነዚህም ውስጥ ጥያቄ 12 እጅግ ቀላል ጥያቄ ይመስላል። ምክንያቱም የከብደት/ቅለት ደረጃው (P) 0.85 ነውና። እንዲሁም ጥያቄ 21 በጣም ቀላል ጥያቄ ይመስላል። ምክንያቱም የከብደት /ቅለት ደረጃው (P)ከ0.63 ነውና እንደ ኢብል /1979/ እምነት የከብደት/ቅለት ደረጃው (P) ከ0.6 - 0.7 የሆኑት በጣም ቀላል ጥያቄዎች ናቸው። እንዲሁም ከ0.7 በላይ የከብደት ቅለት ደረጃ (P) ያላቸው እጅግ በጣም ቀላል ጥያቄ ናቸው። እጅግ በጣም ቀላልና በጣም ቀላል ጥያቄዎች ይመስላሉ የተባሉት ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው።

ጥ. 12 ብስራት /ተቃራኒ ስጥ/

ሀ. የምስራች ለ. ወሬ ሐ. መርዶ መ. መልእክት

ይህን ጥያቄ ከ200 ተፈታኞች ውስጥ 170ዎቹ በትክክል መልሰውታል። ቃሉ እጅግ ተዘውታሪ በመሆኑ ያፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ የሆኑም ሆኑ ያልሆኑ ተፈታኞች በትክክል ለመመለስ አልተቸገሩም። የከብደት/ ቅለት ደረጃው ከፍተኛ መሆንም ጥያቄው እጅግ በጣም ቀላል መሆኑን ይጠቁማል።

ጥ.21 'አንድ ትካር ኖሮኝ ላዋይህ መጣሁ። ' በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ በስሩ የተሰመረበት ቃል የያዘው ፍች ምንድን ነው?

ሀ. ምስጢር ለ. ወሬ ሐ. መልዕክት መ. ጉዳይ

ይህን ጥያቄ ከ200 ፈተታኞች ውስጥ 126ቱ በትክክል መልሰውታል። ቃሉ ተዘውታሪ ባይሆንም በቀረበው አውድ በመታገዝ ተፈታኞቹ ጥያቄዎን ለመመለስ አልተቸገሩም። የክብደት/ ቅለት ደረጃው ከፍተኛ መሆንም ጥያቄው በጣም ቀላል መሆኑን ይጠቁማል።

ከ33 ጥያቄዎች ውስጥ አስሩ ከባድ ጥያቄዎች ይመስላሉ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው። ጥያቄ 1፣4፣ 6፣8፣9፣10፣16፣17፣38 እና 63። ከእነዚህም ውስጥ ጥያቄ 1፣4፣8፣16 እና 63 በጣም ከባድ ጥያቄዎች ይመስላሉ። ምክንያቱም የክብደት /ቅለት ደረጃው (P) ከ0.3 በታች ነው። ለአብነት ያህል ሁለት ጥያቄዎችን እንጠቅሳለን።

ጥ.1. ሳግ / ተመሳሳይ ፍች ስጥ/

ሀ. ቅርታ ለ. ሲቃ ሐ. ትክትክ መ. ሕቅታ

ይህን ጥያቄ ከ200 ተፈታኞች ውስጥ 54ቱ ብቻ በትክክል መልሰውታል። ተፈታኞቹ ቃሉን ባለመለማመዳቸው ወይም ቃሉ ተዘውታሪ ባለመሆኑ ወይም ደግሞ ተገቢ አውድ ስላልቀረበለት ለመመለስ ተቸግረው ይሆናል። ጥያቄውን አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ተፈታኞች ብቻ በትክክል መመለሳቸው ግን የጥያቄውን ክባድነት እንደሚጠቁም ኢብል /1979/ እና መ[illegible]ህረንና ሊህማን /1973/ ይናገራሉ።

ጥ. 16 ሙሽት /ተቃራኒ ፍች ስጥ/

ሀ. ቁርስ ለ. ምሣ ሐ. ቀንኛ መ. ጉርሻ

ይህን ጥያቄ ከ200 ተፈታኞች ውስጥ 48 ተፈታኞች ብቻ በትክክል መልሰውታል። ከ48ቱ ተፈታኞች ውስጥ የ31ዱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አማርኛ ነው። ቃሉ ዘዬ /dialect/ እንደመሆኑ አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆኑ ተፈታኞች ጥያቄውን ለመመለስ የተጠቀሙ ይመስላል። ያም ሆኖ ግን የቃሉ ተዘውታሪ አለመሆን አብዛኞቹን ተፈታኞች /አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛም ይሁን ወይም አይሁን/ እንዳስቸገራቸው መገመት አያዳግትም።

ቀሪዎቹ 12 ጥያቄዎች ደግሞ ቀላልም ከባድም ሳይሆኑ መካከለኛ ደረጃ ያላቸው ይመስላሉ፡፡ ምክንያቱም የክብደት / ቅለት ደረጃቸው ከ (P) ከ0.4 - 0.5 ነውና፡፡

ጥናቱ በመሠረታዊ ጥያቄነት ከነሣቸው ነጥቦች አንዱ አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሆን ወይም አለመሆን የፈተናዎቹን የቃላትና የፊሊጥ ጥያቄዎች ለመመለስ ያለው ተጽእኖ ምን ያህል ነው? የሚል ነበር፡፡ ጥያቄው ተገቢ መልስ የሚሰጠው የተፈታኞችን መልስ በመተንተን እንደመሆኑ እዚህ ላይ ለመመለስ ይሞክራል፡፡

የ200ዎቹ ተፈታኞች አማካይ ውጤት 15.01 ነው፡፡ ውጤቱ በጥቅሉ ሲታይ ደካማ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም አብዛኞቹ ተፈታኞች ከ33ቱ ጥያቄዎች ውስጥ ግማሽ ያህሉን (16.5) እንዳልመለሱ ይጠቁማልና፡፡ አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑት ተፈታኞች አማካይ ውጤት 16.58 ነው ፡፡ ይህም ውጤት ከጠቅላላው አማካይ ውጤት (15.01) የተሻለ ሲሆን ከተፈላጊው አማካይ ውጤት (16.5) ጋር ደግሞ ተቀራራቢ ነው፡፡ ስለሆነም ተፈታኞቹ ደህና ውጤት አምጥተዋል ማለት ይቻላል፡፡

አማርኛ አፍ መፍቻቸው ያልሆኑት ተፈታኞች አማካይ ውጤት 13.44 ነው፡፡ ይህም ውጤት ከጠቅላላው አማካይ ውጤት (15.01) እና ከተፈላጊው አማካይ ውጤት ( 16.5) ጋር ሲታይ አነስተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ተፈታኞቹ ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግበዋል ማለት ይቻላል፡፡

ውስጣዊ ዘላቂ ህያውነትን / internal consistency reliability / ለመመርመር በተደረገው በኩደር ሪቻርድስን $KR_{20}$ ቀመር ውስጥ የመለያ ሐይልን እናገኛለን፡፡ የመለያ ሐይሉን ለማስላት ተፈታኞች ላይኛ (TOP ) እና ታችኛ (Least ) በሚል ይከፈላሉ፡፡ አከፋፈሉም ከፍተኛ ነጥብ ያመጡ 27 በመቶ ተፈታኞ ላይኛ ( TOP 27% )፣ ዝቅተኛ ነጥብ ያመጡ 27% ተፈታኞች ታችኛ (Least 27%) በሚል ነው፡፡ በዚህም መሠረት 200ዎቹ ተፈታኞች ላይኛና ታችኛ በሚል ተከፍለው ነበር፡፡ ከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገቡት 54 ተፈታኞች በላይኛ ሲመደቡ ዝቅተኛ ነጥብ ያስመዘገቡት 54 ተፈታኞች ደግሞ በታችኛ ተመድበዋል፡፡

በላይኛ ከተመደቡት 54 ተፈታኞች ውስጥ የ36ቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን የ12ቱ ግን አማርኛ አይደለም፡፡ በታችኛ ከተመደቡት 54 ተፈታኞች ውስጥ የ12ቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የአማርኛ ሲሆን የ42ቱ ተፈታኞች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ግን አማርኛ አይደለም፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች በቀላሉ መረዳት እንደሚቻለው አንፃራዊ /Relative/ በሆነ መልኩ የአፍ መፍቻቸው አማርኛ የሆኑ ተፈታኞች የአፍ መፍቻቸው አማርኛ ካልሆኑ ተፈታኞች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል። ይሁን እንጂ አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑት ተፈታኞችም ውጤት አጥጋቢ ወይም ከፍተኛ አለመሆኑ ተረጋግጧል። ስለዚህ የፈተናው የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ለሁሉም ተፈታኞች የከበዷቸው ይመስላል።

አማርኛ የአፍ መፍቻቸው የሆኑ ተፈታኞች ዘዬ ቃላትን በመመለስ ረገድ የአፍ መፍቻቸው አማርኛ ካልሆኑት የተሻለ ዕድል ሊኖራቸው እንደሚችል ይገመታል። የተፈታኞች የመልስ ትንተና ውጤት ይህን መላምት አጠናክሯል። በተለይ የአረርቲና የላሊበላ ተፈታኞች ዘዬ ቃላትን በመመለስ በኩል ከሌሎቹ ተፈታኞች ተሽለው ተገኝተዋል። ይህም ምናልባት ቃላቱ የተጠቀሱት አካባቢ ዘዬዎች በመሆናቸው ይሆን? የሚል ጥያቄ ያስነሳል። የአማርኛ ዘዬ ቃላት በጥልቀት ባለመጠናታቸው ጥያቄውን ሙሉ ለሙሉ ለመመለስ ባይቻልም ዘዬው የሚነገርባቸው አካባቢዎች ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግን መገመት አያዳግትም።

የፈተናው ዘዬ ቃላት የሚከተሉት ናቸው። 'ጎባን'፣ 'ልጩኛ'፣ 'ጣፍርጄ'፣ 'ወበራ'፣ ቡልኮ '፣ 'ትንኩሽት'፣ 'አተረ'፣ 'ትካር'፣ 'የሻጉሬ'፣ እና 'ሙሽት' ፣ ለእነዚህ ቃላት እያንዳንዱ ተፈታኝ የሰጠው መልስ ትክክል መሆኑና አለመሆኑ ከተቆጠረ በኋላ ውጤቱ ተሰልቷል። የሚከተለው ለየጥያቄው ትክክለኛ መልስ የሰጡ ተፈታኞችን ቁጥር በአፍ መፍቻ ቋንቋ ያመለክታል።

**ሰንጠረዥ 13 ዘዬ ቃላትን በትክክል የመለሱ ተፈታኞችን ብዛት በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚያሣይ፣**

| ቃሉ | የአፍ መፍቻው አማርኛ የሆኑ | የአፍ መፍቻቸው አማርኛ ያልሆኑ |
|---|---|---|
| 1 ጎባን | 54 | 29 |
| 2 ልጩኛ | 43 | 14 |
| 3 ጣፍርጄ | 72 | 60 |
| 4 ወበራ | 43 | 16 |
| 5 ቡልኮ | 38 | 23 |
| 6 ትንኩሽት | 46 | 27 |
| 7 አተረ | 57 | 43 |
| 8 ሙሽት | 38 | 13 |
| 9 ትካር | 67 | 61 |
| 10 የሻጉራ | 52 | 50 |

በሰንጠረዥ 13 እንደተመለከተው አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑ ተፈታኞች አማርኛ አፍ መፍቻቸው ካልሆኑ ተፈታኞቹ (በአንፃራዊነት ሲታይ ) የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል። ይህም ጥያቄዎቹ አድሎዊነት (Bias)እንዳላቸው የሚጠቁም ነው። በርግጥ ከሞላ ጎደል አፍ መፍቻቸው አማርኛ የሆኑና ያልሆኑ ተፈታኞች በተቀራራቢ ቁጥር የመለሷቸው ጥያቄዎች አሉ። እነሱም ጥያቄ 21 (ትካር ) እና ጥያቄ 22 (የሻጉራ) ናቸው። ለእነዚህም ጥያቄዎች ሀ. ነገራዊ አውድ መቅረቡ፣ የአማርኛ ቋንቋ አፍ መፍቻ መሆን ወይም አለመሆን በጥያቄዎቹ አመላለስ ላይ ጉልህ ተጽእኖ እንዳይኖር ያደረገ ይመስላል።

ሰንጠረዡ እንደሚያመለክተው ከአስሩ ዘዬ ቃላት ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተፈታኞች በትክክል የመለሱት ዘዬ ቃል 'ጣፍርዶ' ነው። ጥያቄውን በርካታ ተፈታኞች በትክክል ለመመለስ የቻሉበት አንድ ምክንያት የአማራጮቹ አቀራረብ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። እንዴት ቢባል የጥያቄው ምርጫ 'መ' ሀ ና ሐ ይላል። ይህ ደግሞ ተፈታኞችን ወደትክክለኛው መልስ ሊመራቸው ይችላል። የምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች አንድ ደካማ ጎን ግመታን ማደፋፈር እንደመሆኑ ተፈታኞቹ ጥያቄውን በግምት የመለሱት ይመስላል።

በአጠቃላይ የፈተናውን የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሆን ወይም አለመሆኑ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሌለው የትንተናው ውጤት ይጠቁማል። ያም ሆኖ ግን አማርኛ ያፍ መፍቻ ቋንቋ መሆኑ የተወሰኑ ጥያቄዎችን በትክክል ለመመለስ አስተዋጽኦ እንዳለው የትንተናው ውጤት አመልክቷል። በተለይ በፈተናው ውስጥ የሚገኙ ዘዬ ቃላትን በትክክል ለመመለስ አማርኛ የአፍ መፍቻ መሆን ( ይበልጡን ደግሞ ዘዬ ቃሉ በአካባቢው መነገር) ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ይህም አድሎዋዊነት ያላቸው ጥያቄዎች እንደተካተቱ የሚያስገነዝብ ነው።

በሰንጠረዥ 12 ሁለተኛ ረድፍ የመለየት ሀይልን ( disc. power ) እናገኛለን። ይህ መለኪያ የክብደት /ቅለት ደረጃ (P) ከሚሰጠው መረጃ የበለጠ እንደሆነ ይታመናል። በተለይ አንድ ፈተና ለሙከራ / Pilot / በሚቀርብበት ጊዜ አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰጣል። ይኸውም የመለየት ሀይላቸው በጣም ደካማና ደካማ የሆኑ ጥያቄዎችን እንድናስወግድ ወይም እንድናስተካክል ስለሚያደርግ ነው። መለኪያው በጥቅሉ የፈተናውን አስተማማኝነት /validity/ ለመመዘን

ይረዳል። ለችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የመለያ ሐይላቸው ከ0.4 .06 የሆኑ ጥያቄዎች ተመራጭነት አላቸው። ከዚህ ውጭ የሆኑ ጥያቄዎች ግን ጥሩ ጥያቄ አይደሉም/ኢብል፣1979/

በዚህም መሠረት በሠንጠረዥ 12 በቀረበው መለያ ሐይል የፈተናው የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ሲታዩ የሚከተለውን ይመስላሉ።

ከ33ቱ ጥያቄዎች የዘጠኙ ጥያቄዎች የመለያ ሐይል ( Disc power ) ከፍተኛ በመሆኑ ጥሩ ጥያቄዎች ይመስላሉ። እነሱም የሚከተሉት ጥያቄዎች ናቸው። ጥያቄ 7፣ 11፣ 14፣ 15፣ 18፣ 22፣ 32፣ 33፣ እና 38 ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ጥያቄ 11 እና ጥያቄ 14 ከፍተኛ የመለያ ሐይል ስላላቸው በጣም ጥሩ ጥያቄዎች ይመስላሉ።

ቀሪዎቹ 24 ጥያቄዎች የመለየት ሐይላቸው መካከለኛ፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ናቸው። ሆኖም አብዛኞቹ ጥያቄዎች ዝቅተኛ የመለየት ሐይል ያላቸው ናቸው። ከዝቅተኞቹ ውስጥ ደግሞ ጥያቄ 63፣ 17፣1፣8፣35፣ እና 68 እንደቅደም ተከተላቸው በጣም ዝቅተኛ የመለየት ሐይል አላቸው። በጣም ዝቅተኛ የመለየት ሐይል ያላቸው ጥያቄዎች ደገሞ ሲወገዱ የሚገባቸው ጥያቄዎች ስለሆኑ ጥያቄዎቹ ወይ መታረም አለባቸው አለዚያ መወገድ ይኖርባቸዋል።

ለማጠቃለል የኩደር ሪቻርደስንን $KR_{20}$ ቀመር በመከተል የፈተናውን የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጣዊ ዘላቂ ህያውነት /Internal - consistency reliability/ ለመመርመር ተሞክሯል። በተገኘውም ውጤት ህያውነቱ /reliability / 0.668 ነው። ይህም ውጤት የቃላት ፈተና እንዲያስገኝ ከሚጠበቀው ህያውነት በጣም ያነሠ ነው። እንደላዶ /1961/ እምነት ጥሩ የቃላት ፈተናዎች ከ0.91 በላይ ህያውነት ሊኖራቸው ይገባል። ስለዚህ የፈተናው ውስጣዊ ዘላቂ ህያውነት ደካማ ነው ማለት ይቻላል። በመልስ ትንተናው አማርኛ የእፍ መፍቻ ቋንቋ መሆን የፈተናውን የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ ያለው ሚና ጉልህ አለመሆኑ ተመልክቷል። ሆኖም አንዳንድ ጥያቄዎችን በመመለስ ረገድ /በተለይ ዘዬ ቃላትን /አማርኛ የእፍ መፍቻ ቋንቋ መሆን ጠቃሚታ እንዳለው ተጠቁሟል።

## ፲.3 ተተግባሪነት /Paracticality /

ሦስተኛው የጥሩ ፈተና ባህሪ ተተግባሪነት ነው። ይህ በአብዛኛው ከፈተና አስተዳደርና ከእርማት ጋር የተያያዘ ነው። የፈተናው ተተግባሪ አለመሆን አ ፡ ሀያውና አ ፡ አስተማማኝ ውጤት ሊያመጣ ስለሚችል በፈተናው አገባጀት ለተተግባሪነትም ትኩረት መስጠት ያሻል።

የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ተፈታኞች ቁጥር ከአመት አመት እያሻቀበ መሄድ የሚዘጋጁ ፈተናዎችን በምርጫ ሰጭ የጥያቄ አቀራረብ ብቻ እንዲገደቡ ያስገደደ ይመስላል። ለምሳሌ በ1987 ዓ.ም. የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናን የወሰዱ ጠቅላላ ተፈታኞች ቁጥር 187,177 ነበር በ1988 ግን ይህ ቁጥር ወደ 200,000 አሻቅቧል። ስለዚህ ሀገራችን ካላት የኢኮኖሚ አቅም አንፃር የእርማቱን ጣጣ በቀላሉ ለመወጣት ሲባል የሁሉም የት/ዓይነት ፈተናዎች አብጀክቲብ ናቸው ።

የቋንቋ ትምህርት በአብዛኛው ተማሪው እየሠራ የሚለማመደው እንደመሆኑ ፈተናዎችን በምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች ብቻ መገደቡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል። ለምሳሌ የአማርኛ ቋንቋ አጠቃላይ አላማ ጥሩ አድማጭ፣ተናጋሪ፣አንባቢና ፀሐፊ እንዲሆን ለማስቻል ነው። ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ከሂሎችለተማሪው ወሳኝ በሆኑ ፈተናዎች ውስጥ አለመካተታቸው ተማሪውን ከመለማመድ ሊያቅበው ይችላል። ይህ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ጎጅ ተጽእኖ ይኖረዋል። ስለዚህ በተለይ ለቋንቋ ፈተናዎቻችን የኢኮኖሚ አቅማችንንና የመተግባር ሐይላችንን እየገመገምን፣ ከምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች በተጨማሪ አጫጭር መልስ የሚሹ ፣አዛምድ ፣ህዳጋዊ/cloze/ ወዘተ ጥያቄዎች የሚታከሉበት መንገድ ቢፈለግ መልካም ነው።

የስምንቱን አመታት የሁ.ደ .መ.አ .ፈ . የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተተግባሪነት በተመለከተ ጉልህ ችግር የሚታይ አይመስልም። ሆኖም የጥያቄዎቹ አቀራረብ ምርጫ ሰጭ ብቻ መሆኑ ራሱ የተተግባሪነት ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ለምሳሌ ተማሪው በመማሪያ መጽሐፍቱ ቃላትን በአብዛኛው የሚለማመደው ውጤታማ / Productive/ በመሆን መልክ ነው። ይሁን እንጂ ፈተናዎቹ ተማሪው የተለማመደበትን ስልት እንዲተገብረው ዕድል የሚሰጡት አይደሉም።

በመማሪያ መጽሐፍቱ ከፍተኛ ቁጥር የየያዘው መልመጃ ዐ.ነገር ሥራ የሚል ነው፡፡ ተማሪው ለየቃላቱ በምንባቡ መሠረትና ከምንባቡ ውጭ ዐ.ነገር እየሠራ በቃላቱ የመጠቀም ሐይሉን ያዳብራል። ይሁን እንጂ በዚህ አይነት የተለማመደው ተማሪ ችሎታውን የሚያሣይበት ፈተና አልቀረበለትም። በሌላ አገላለጽ አብዛኞቹ የሁ.ደ .መ.አ .ፈ .የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ያለአውድ ቀርበው ፍቻቸውን እንዲሰጥ ብቻ መጠየቃቸው ተማሪው ያለውን ችሎታ እንዳይተገብር እንቅፋት ይሆናሉ። ስለዚህ ተማሪው ችሎታውን እንዲተገብር የሚያስችሉ የአጠያየቅ ስልቶች መታከል ይኖርባቸዋል።

በአጠቃላይ በቋንቋ ፈተናዎቻችን ውስጥ የእርማቱን ጣጣ በቀላሉ ለመወጣት ሲባል ብቻ ሁሉንም ጥያቄዎች ምርጫ ሰጭ /multiple choice/ማድረጉ ተገቢ አይመስልም። ስለዚህ ያለንን የኢኮኖሚ አቅም በወጉ በማጥናት በጥቂት ሰዎች ሊታረሙ የሚችሉ የአጠያየቅ ስልቶች ቢካተቱ ጥሩ ይመስለናል። ለምሳሌ በቃላት ፈተናዎቻችን ውስጥ አዛምድ፣ክፍቱን ቦታ በተስማሚ ቃል ወይም ሐረግ ሙላ፣በአንቀጹ ውስጥ የጎደለውን ቃል አሟላ ወዘተ...ጥያቄዎች ቢካተቱ በጥቂት ሰዎች ለማረም አያስቸግሩም። የአጠያየቅ ስልቱ የተለያየ መሆን ደግሞ የትምህርቱን አላማ ለመመዘን አመቺነቱ አያጠራጥርም።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ ጥናቱ የደረሰበት መደምደሚያና ከጥናቱ ጋር የተዛመደ አስተያየት በቅደም ተከተል ይቀርባል፡፡

### 5.1 ማጠቃለያ /Summary/

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና የቃላት /ፈሊጥ ጥያቄዎች ተገቢ ወይም ጥሩ የመመዘኛ መሣሪያ መሆን አለመሆናቸውን መመርመር ነበር፡፡ በዚህም መሠረት በጥናቱ የሚመለሱት መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

1. የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መማሪያ መጻሕፍት ለቃላት/ፈሊጦች ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው? ፈተናዎቹስ?
2. የፈተናዎቹ የቃላት/ፈሊጥ ጥያቄዎች ከጥሩ የፈተና ባህርያትና ከቃላት አፈታትን መርሆዎች አንፃር ሲገመገሙ ጠንካራ ጎናቸው ያይላል ወይስ ደካማ ጎናቸው?
3. አማርኛን በአፍ መፍቻነት መናገር ወይም አለመናገር የፈተናዎቹን የቃላት/ፈሊጥ ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ ያለው ተጽእኖ ምን ያህል ነው?

እነዚህን መሠረታዊ የጥናት ጥያቄዎች ለመመለስና ከጥናቱ ግብ ለመድረስ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተተንትነዋል፡፡ በዚህም በጥናቱ የታቀፉ የስምንት አመታት ፈተናዎች ተመርጠው በአቢይ የመመዘኛ መስፈርቶች/አስተማማኝነት፣ ህያውነትና ተግባራነት/እና በቃላት አፈታተን መርሆዎች ተገምግመዋል፡፡ በግምገማው የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መማሪያ መጻሕፍት፣ መጠይቆች፣ ቃለ መጠይቅና የተፈታኞች ውጤት አግባብነት ባለው ቦታ ሁሉ ተተንትነዋል፡፡ ትንተናው ከተካሄደም በኋላ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

- የቀድሞዎቹም ሆኑ የአሁኖቹ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍትና ሲለበሶች ለቃላት ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ተገኝተዋል፡፡ ሲለበሶቹ ለቃላት ትምህርት ከፊ የሚያገኙ አላማዎችና ይዘቶች በየክፍል ደረጃው ሰጥተዋል፡፡ ይህም ለዘርፉ የተሰጠውን ትኩረት ይጠቁማል፡፡ የቀድሞዎቹ መማሪያ መጻሐፍት በመልመጃዎቻቸው አማካይነት 692 ቃላትን ለልምምድ ሲያቀርቡ የአሁኖቹ መማሪያ መጻሕፍት ደግሞ 858 ቃላትን ለልምምድ አቅርበዋል፡፡ የልምምዱ ብዛትም ለቃላት ትምህርት የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት የሚጠቁም ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን ውስጥ አብዛኛዎቹ ቃላትን ለማስተማር መማሪያ መጽሐፍቱና ሲለበሶቹ ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚሰጧቸው አረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍትና ሲለበሶች ለቃላት ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸውን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

- የቀድሞዎቹም ሆኑ የአሁኖቹ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶች ለፈሊጦቹ ትምህርት የሰጡት ትኩረት የለም፡፡ የቀድሞዎቹ መማሪያ መጻሕፍት 5 ፈሊጦችን ለልምምድ ሲያቀርቡ የአሁኖቹ መማሪያ መጻሕፍት ደግሞ 53 ፈሊጦችን አቅርበዋል፡፡ የልምምዱ ማነስም ለዘርፉ የተሰጠውን አነስተኛ ትኩረት ይጠቁማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አብዛኞቹ መምህራን /ከአንድ መላሽ በስተቀር ሁሉም ማለት ይቻላል/ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መማሪያ መጽሐፍት ፈሊጦችን ለማስተማር ምንም አይነት ድጋፍ እንደማይሰጧቸው አረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መማሪያ መጻሕፍት ለፈሊጦች ትምህርት አነስተኛ ትኩረት መስጠታቸውን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

- ለጥናቱ የተመረጡት የስምንት አመታት ፈተናዎች 655 ጥያቄዎችን ይዘዋል፡፡ ከ655ቱ ጥያቄዎች ውስጥ 186ቱ ወይም 28.5% የሚሆኑት የቃላት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ በትኩረት ደረጃ ሲታይ ፈተናዎቹ ለቃላት ትምህርት ይዘት ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸውን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

- ከፈተናዎቹ 655 ጥያቄዎች ውስጥ 83ቱ ወይም 12.7% የሚሆኑት የፈሊጥ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ይህም ለይዘቱ የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ይጠቁማል፡፡ ይሁን እንጂ መማሪያ መጻሕፍቱና ሲለበሶቹ ለይዘቱ የሰጡት ትኩረት እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪው የሚፈተነው በወጉ ያልተለማመደውን ይዘት ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የማስተማሪያ

መማሪያዎቹ በቂ ትኩረት ላልሰጡት የትምህርት ይዘት ፈተናዎቹ ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸውን የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል።

- የፈተናዎቹ የቃላትና የፊሊጥ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ለመምህራኑና ለባለሙያዎች ተገቢ የመምሰል ባሕሪያቸው ወይም ላህያዊ አስተማማኝነታቸው/ Face Valiadity/ ደካማ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል።

- በፈተናዎቹ ውስጥ በአውድ ከቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ይልቅ ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በልጠው ተገኝተዋል። በቁጥር ሲታይ 187ቱ ወይም 69.5% የሚሆኑት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ያለአውድ የቀረቡ ሲሆን 82ቱ ወይም 30.5% የሚሆኑት ደግሞ በአውድ የቀረቡ ናቸው።

- ያለአውድ የቀረቡት የቃላት ጥያቄዎች የትምህርቱን አላማ፣ የማስተማሪያ መማሪያዎቹን አቀራረብና የመምህራኑን የማስተማሪያ ዘዴ መሠረት ያላደረጉ ናቸው። በዚህም የተነሳ አላማቸው ግልጽ ካለመሆኑም በላይ ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ እንዳልሆኑ የጥናቱ ውጤት አመልክቷል።

- የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ የቃላት ትምህርት አላማ ፈሊጦችን መጨመር አለመጨመሩ በግልጽ አይታወቅም። ይሁን እንጂ ፈሊጦች የቃላት አንድ ክፍል እስከሆኑ ድረስ የቃላቱ ትምህርት አላማ ለፈሊጦችም እንደሚያገለግል ይታመናል። ስለዚህ ያለአውድ የቀረቡት የፈሊጥ ጥያቄዎችም ለትምህርቱ አላማ ተስማሚ የመመዘኛ መሣሪያ አለመሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል።

- አብዛኞቹ በአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተገቢ አውድ እንደተዘጋጀላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል። እነዚህም ጥያቄዎች ለትምህርቱ አላማ፣ ለማስተማሪያ ዘዴው እና ለማስተማሪያ መማሪያዎቹ አቀራረብ ተስማሚ የመፈተኛ ዘዴ ሆነው ተገኝተዋል። ስለዚህ በአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ተገቢ ወይም ጥሩ የመመዘኛ መሣሪያዎች መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል።

አብዛኞቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ከመማሪያ መጻሕፍቱ አለመመረጣቸው ተረጋግጧል፡፡ ፈተናዎቹ ካቀረቧቸው 269 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ በመማሪያ መጻሕፍቱ መልመጃዎች የተገኙ 18 ብቻ ናቸው፡፡ ይህም የፈተናዎቹ ቃላትና ፈሊጦች በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ አለመመስረታቸውን ይጠቁማል፡፡

- ፈተናዎቹ ካቀረቧቸው 187 የቃላት ጥያቄዎች ውስጥ ቢያንስ 22ቱ ዘዬ ቃላት መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በርካታ ዘዬ ቃላትን የያዘው ፈተና የ1987 ዓ.ም. ፈተና ነው፡፡ ይህ ፈተና ከ10 የማያንሱ ዘዬ ቃላትን ይዟል፡፡ ዘዬ ቃላት በፈተናዎቹ መኖር ግን ተገቢ አለመሆኑን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ዘዬ ቃላትን ለማስተማር መማሪያ መጻሕፍቱ በቂ ድጋፍ አይሰጡም፡፡ ሁለተኛ አብዛኞቹ መምህራን ዘዬ ቃላትን አያስተምሩም፡፡ ሦስተኛ በቃላት ትምህርቱ አላማ ውስጥ ዘዬ ቃላት አልተካተቱም፡፡ አራተኛ በሀገራችን አማርኛን በአፍ መፍቻነት የሚናገሩና የማይናገሩ ተማሪዎች መኖራቸው እየታወቀ ዘዬ ቃላትን ለፈተና ማቅረብ አንደኛውን ወገን የሚጠቅም ወይም አድሎአዊነትን /bias/ የሚያሳይ ነው፡፡ ስለዚህ በሁ.ደ.መ.አ.ፈ. ውስጥ ዘዬ ቃላትን ማካተት ፍጹም ተገቢ አለመሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

- ከፈተናዎቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ 19ኙ ቃላትና ፈሊጦች በተደጋጋሚ ለፈተና እንደቀረቡ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በርካታ ተደጋጋሚ የቃላት /የፈሊጥ ጥያቄዎችን የያዘው ፈተና የ1986 ዓ.ም. ፈተና ነው፡፡ ይህ ፈተና ከያዛቸው 29 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ 12ቱ ከሌሎች ዓመታት ፈተናዎች በቀጥታ የተወሰዱ ወይም ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ አንድን ቃል ወይም ፈሊጥ በተደጋጋሚ ለፈተና ለማቅረብ አጥጋቢ ምክንያትን ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጂ በፈተናዎቹ ውስጥ የተደጋገሙት ቃላትና ፈሊጦች በአጥጋቢ ምክንያት አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አንድ ቃል ወይም ፈሊጥ ያለበቂ ምክንያት እየደጋገሙ ለፈተና ማቅረቡ ተገቢ አለመሆኑን የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል፡፡

- አብዛኞቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች አሳሳቾች / distractors/ ውጫዊ በሆነ መልክ ሲታዩ ተአማኒ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ አሳሳቾቹ ከትክክለኛው መልስ ጋር በቅርጽ ተመሳሳይ፣ በርዝማኔና በክብደት ደረጃ ተመጣጣኝ በመሆናቸው ለውጫዊ ተአማኒነታቸው ዋቢዎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የአሳሳቾችን ተአማኒነት በተሟላ መልክ ለማረጋገጥ የወደፊት ተመራማሪዎችን ጥልቅ ጥናት እንደሚጠይቅ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

- በምርጫ ሰጪ የቃላት ጥያቄዎች እያንዳንዱ ጥያቄ ባለሙያዎች የሚስማሙበት አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ መያዝ ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ ፈተናዎቹ ካቀረቡአቸው 269 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ ለ55ቱ ጥያቄዎች ባለሙያዎች የሚስማሙበት አንድ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት እንዳልተቻለ የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡ ለጥያቄዎቹ አንድ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ያልተቻለባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ሁለት መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ እነሱም አንደኛ ለጥያቄው አጥጋቢ መልስ በአማራጮች ውስጥ አለመኖርና ሁለት መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች በጥያቄው ውስጥ መገኘት ናቸው፡፡

- የፈተናዎቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የይዘት አስተማማኝነት አለመጠበቁን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡ በተለይ ያለአውድ የቀረቡት 187 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የይዘት አስተማማኝነት ደካማ ነው፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ዓላማቸው ግልጽ አይደለም፡፡ ሁለተኛ የፈተናዎቹ አቀራረብ ሥልት ከመማሪያ መጻሕፍቱ የተለያየ የመልመጃ አቀራረብ ( ዐ.ነገር ሥራ፣ አዛምድ፣ የጎደለውን አሟላ፣ አብራራ፣ ግለጽ፣ ወዘተ.) ስልት ጋር የሚመሳሰል አይደለም፡፡ ሦስተኛ አቀራረባቸው አብዛኞቹ መምህራን ቃላትን/ፈሊጦችን ከሚያስተምሩበት ዘዴ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ አራተኛ አብዛኞቹ ቃላትና ፈሊጦች ከመማሪያ መጻሕፍቱ ባለመመረጣቸው የትምህርቱ ወካይ ናሙናዎች አይደሉም፡፡ ስለዚህ ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የይዘት አስተማማኝነት በጣም ደካማ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል በአውድ የቀረቡት 82 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የይዘት አስተማማኝነት መጠበቁን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ምክንያቱም አንደኛ የጥያቄዎቹ አቀራረብ (ምንባባዊ፣ ዐረፍተ ነገራዊና የተለየውን ቃል አውጣ የሚል አውድ አላቸው) ከመማሪያ መጻሕፍቱ አቀራረብ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ሁለተኛ የጥያቄዎቹ አቀራረብ የትምህርቱን ዓላማ ለመመዘን አመቺ ናቸው፡፡ ሦስተኛ የጥያቄዎቹ አቀራረብ አብዛኞቹ መምህራን ቃላትን ከሚያስተምሩበት ዘዴ ጋር ይመሳሰላል፡፡ በነዚህ ምክንያቶች የተነሳም ጥያቄዎቹ የይዘት ተገቢነት/ content relevance/ አላቸው፡፡ ስለዚህ በአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የይዘት አስተማማኝነት ጠንካራ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

የፈተናዎቹን የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጣዊ ዘላቂ ህያውነት /Internal Consistency Reliability/ ለመመርመር የ1987 ዓ.ም. ፈተና ተመርጦ ነበር፡፡ የዚህ ፈተና ውስጣዊ ዘላቂ ሕያውነት በኩደር ሪቻርደሰን KR 20 ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት 0.668 ነው፡፡ ይህ ውጤት ላዶ /1961/ እና ሌሎች ምሁራን ጥሩ የቃላት ፈተና የህያውነት ኮኦፊሸንት 0.91 ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለበት ካሉት አንፃር ሲታይ አነስተኛ ነው፡፡ ስለዚህ የፈተናዎቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄ ውስጣዊ ዘላቂ ሕያውነት ደካማ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

አማርኛን በአፍ መፍቻነት መናገር ወይም አለመናገር የፈተናዎቹን የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ ያለው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖን ለመመርመር የ1987 ዓ.ም. ፈተና ተመርጦ ነበር፡፡ በዚህም አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑ 100 ተፈታኞች ውጤት አማርኛ አፍ መፍቻቸው ካልሆኑ 100 ተፈታኞች ውጤት ጋር ተነፃፅሯል፡፡ በተገኘውም ውጤት የፈተናውን 33 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሆን ወይም አለመሆን ጉልህ ተጽእኖ እንደሌለው ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ የፈተናውን የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ ሁለቱም ተፈታኞች መቸገራቸውን ከተገኘው ዝቅተኛ ውጤት መረዳት ተችሏል፡፡

ያም ሆኖ ግን አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑ ተፈታኞች ውጤት አንፃራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ አማርኛ አፍ መፍቻቸው ካልሆኑ ተፈታኞች ውጤት ተሸሎ ተገኝቷል፡፡ ይኸውም በሚከተሉት ነጥቦች ተንጸባርቋል፡፡ አንደኛ አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑ ተፈታኞች አማካይ ውጤት (16.55) አማርኛ አፍ መፍቻቸው ካልሆኑ ተፈታኞች አማካይ ውጤት (13.44) ይበልጣል፡፡ ሁለተኛ በለይኛ (Top 27%) ከተመደቡት 54 ተፈታኞች ውስጥ የ36ቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡ ሦስተኛ በታችኛ (List 27%) ከተመደቡት 54 ተፈታኞች ውስጥ የ12ቱ ብቻ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡

በተለይ የፈተናውን የዘጠኙ ቃላት ጥያቄዎች በመመለስ ረገድ አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑት ተፈታኞች አማርኛ አፍ መፍቻቸው ካልሆኑ ተፈታኞች በእጅጉ እንደተሻሉ የመልስ ትንተናው /Item analiysis/ ውጤት አሳይቷል፡፡ ይህም የዘጠኙ ቃላት ጥያቄዎች ወገን ጠቅመው ሌላውን እንደጎዱ ወይም አድሉአዊነት እንዳላቸው የሚጠቁም ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አውድ ለቀረበላቸው የቃላት ጥያቄዎች አማርኛ የአፍ መፍቻቸው መሆን ወይም አለመሆን ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ ምንም ተጽእኖ እንደሌለው የመልስ ትንተናው ውጤት በግልጽ

ያመለክታል፡፡ ስለዚህ አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሆን የፈተናውን የዘፈ ቃላት ጥያቄ ለመመለስ አዎንታዊ ተጽእኖ ሲኖረው ሌሎቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ግን ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተጽእኖ እንደሌለው ጥናቱ አመልክቷል፡፡

ተተግባሪነት የምርጫ ሰጭ የቃላት ፈተና ጥያቆዎች ጉልህ ችግር እንዳልሆነ በርካታ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ተተግባሪነት የምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች ጉልህ ችግር ባይሆንም የእርግጡን ጣጣ በቀላሉ ለመወጣት ሊባል ብቻ አንድ አይነት አጠያየቅ ላይ ማተኩሩ ግን ተገቢ አለመሆኑን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ ስለዚህ በጥቂት አራሚዎች ሊታረሙ የሚችሉና የተተግባሪነት ጥያቄ የማያስነሱ እንደአዛምድ፣ የጎደለውን ቃል ሙላ፣ አጫጭር መልስ የሚሹ … ወዘተ.. ጥያቄዎች በፈተናዎች ውስጥ ቢካተቱ መልካም መሆኑን ጥናቱ አመልክቷል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ /Conclusion/

1. የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ የቃላት ትምህርት አሰጣጥ በአብዛኛው (ሙሉ ለሙሉም ማለት ይቻላል ይሆናል) አንብቦ ከመረዳት ክሂል ጋር የተያያዘ፣ አውዳዊ አቀራረብን የተከተለ እና በውጤታማ / Productive/ ልምምድ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ አብዛኛቹ የሁ.ደ.መ.እፈ. የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች የአቀራረብ ስልት ግን የትምህርቱን አሰጣጥ መሠረት ያደረጉ አይደሉም፡፡ በጥናቱ ከታቀፉ 269 የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ውስጥ 187ቱ (69.5%) ጥያቄዎች ያለአውድ መቅረባቸው ይህንኑ የሚያመለክት ነው፡፡

   ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ከቃላት ትምህርቱ ዓላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴ፣ ከመማሪያ መጻሕፍቱ የመልመጃ አቀራረብና ምሁራን ስለቃላት አፈታተን ካነሷቸው መርሆዎች አንፃር ተገምግመው ጥሩ የመመዘኛ መሣሪያ አለመሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ለሁለተኛ ደረጃ ያማርኛ የቃላት ትምህርት አሰጣጥ ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ የሆነው ቃላትን በተለያየ አውድ ውስጥ መፈተን ነው፡፡ ስለዚህ ያለአውድ የቀረቡ ጥያቄዎች በአውድ መተካት ይኖርባቸዋል፡፡

2. አንድ ቃል ወይም ፈሊጥ ለፈተና ሲመረጥ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሁ.ደ.መ.እ.ፈ. የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች አመራረጥ ጥንቃቄ የጎደለው ይመስላል፡፡ በተለይ ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በምን

መስፈርት ለፈተና እንደተመረጡ ለማወቅ ያዳግታል፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ተያቂዎቹ ሲመረጡ መማሪያ መጻህፍቱን መሠረት አያደርጉም፡፡ ሁለተኛ አንድ ቃል ወይም ፈሊጥ ያለበቂ ምክንያት በተለያየ ዓመት ፈተናዎች ውስጥ እየተደጋገመ ይመረጣል፡፡ ሦስተኛ ዘዬ ቃላት ለፈተና ይመረጣሉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሦስት ነጥቦች የፈተናዎቹ የቃላት /ፈሊጦች አመራረጥ በብርቱ ጥንቃቄ እንዳልተከናወነ ይጠቁማሉ፡፡ ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ተያቂዎች በጥንቃቄ አለመመረጥ ደግሞ የፈተናውን ዓላማ ግልጽ እንዳይሆን ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህም ማለት አንድ ቃል ወይም ፈሊጥ በዘፈቀደ ተመርጦ ያለምንም አውድ ለፈተና ሲቀርብ ከተፈታኙ የሚጠበቀው ችሎታ ምን እንደሆነ በግልጽ አይታወቅም ማለት ነው፡፡ ምናልባት የፈተናዎቹ ዓላማ ተፈታኙ ሁሉንም የአማርኛ ቃላት (ዘዬ ቃላትንም ይጨምራል) እና ፈሊጦች በቃሉ ማወቅ አለማወቁን ለመመዘን ነው ቢባል ያስኬዳል፡፡ ነገርግን ይህ ዓላማ የቃላት ትምህርቱ ዓላማ ስላልሆነ ተገቢ ምዘና ተካሄዷል ለማለት አይቻልም፡፡

በመሆኑም አንድን ቃል ወይም ፈሊጥ በዘፈቀደ እየመረጡ ያለአውድ ለፈተና ማቅረብ ከተማሪው የሚጠበቀው ችሎታ ምን እንደሆነ በግልጽ አያመለክቱም፡፡ ለቃላት ትምህርቱ ዓላማም ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያዎች አይደሉም፡፡ ስለዚህ ለፈተና የሚመረጡ ቃላትና ፈሊጦች ግልጽ ዓላማ ኖሯቸው ተግቢ የመመዘኛ መሣሪያ እንዲሆኑ የትምህርቱ ዓላማና የመማሪያ መጻሕፍቱ የቃላት መልመጃዎች በወጉ መመርመር አለባቸው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ አቀራረባቸው በአውድ መተካት እንዳለበት የጥናቱ ውጤት ለመልከቷል፡፡

3. በአጠቃላይ ፈተናዎቹ ከጥሩ የፈተና ባሕርያትና ከቃላት አፈታትን መርሆዎች አንፃር ተገምግመው ከጠንካራ ጎናቸው ይልቅ ደካማ ጎናቸው አይሎ ተገኝቷል፡፡ ቃላትና ፈሊጦችን በአውድ ውስጥ አለመፈተን፣ ለፈተና የሚቀርቡ ቃላትና ፈሊጦች አመራረጥ ዘፈቀዳዊ መሆን፣ ፈተናዎቹ የተለያየ የቃላት ጥያቄ አቀራረብ ስልቶችን አለመጠቀምና አንድ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ጥያቄዎችን በብዛት ማቅረብ በግምገማው ከታዩ ደካማ ጎኖች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ስለዚህ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና የቃላት አፈታተን ከላይ የተጠቀሱትን ጉልህ ድክመቶች ቢያስወግዱ ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያዎች እንደሚሆኑ ጥናቱ አመልክቷል፡፡

## 5.3 አስተያየት /Recommendation/

የጥናቱን ውጤት መሠረት በማድረግ ወደፊት ለሚዘጋጁ ፈተናዎች መነሻ እንዲሆኑ የሚከተሉት አስተያተቶች ወይም የመፍትሔ ሀሳቦች በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

1. <u>የፈተናውን ይዘቶች በትምህርቱ ዓላማ ወይም በማስተማሪያ መማሪያዎች ይዘቶች ላይ መመስረት</u>

በመርህ ደረጃ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናዎች በሁለተና ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መማሪያ መጻሕፍት ላይ እንደሚመሰረቱ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ጽ/ቤት መመሪያ መጽሐፍ/ሀንድ ቡክ / ያረጋግጣል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት እንደተረጋገጠው አብዛኞቹ የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች በማስተማሪያ መማሪያዎች ላይ አልተመሰረቱም፡፡

ስለዚህ ፈተና አውጪዎች የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሲለበሶችና መመሪያ መጻህፍት የሚያቀርቧቸውን የቃላት ትምህርት ዓላማዎችና ይዘቶች በጥልቀት በመመርመር ለይዘቱ ወካይ የሆኑ ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት መነሳሳት ይጠበቅባቸዋል፡፡

2. <u>የተለያዩ የአጠያየቅ ስልቶችን መጠቀም</u>

በፈተናዎቹ ውስጥ ያለአውድ የቀረቡት የቃላትና የፈሊጥ ጥያቄዎች ለሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ የቃላት ትምህርት አሰጣጥ ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ ባለመሆናቸው በአውዳዊ ጥያቄዎች መተካት ይኖርባቸዋል፡፡ ቃላትና ፈሊጦችን በአውድ ለመፈተን ደግሞ የተለያዩ የአጠያየቅ ስልቶችን መጠቀም ይቻላል፡፡ የሚከተሉት የአጠያየቅ ስልቶች ለሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ የቃላት ትምህርት አሰጣጥ ተስማሚ የመመዘኛ ዘዴዎች ስለሚመስሉ ብንጠቀምባቸው መልካም ይሆናል፡፡

2.1 የቃላት /የፈሊጥ ጥያቄዎችን ከምንባብ ጥያቄዎች ጋር አዳብሎ መጠየቅ፡፡ ይህ ጥናቱ ባቀፋቸው ፈተናዎችም ውስጥ የሚታይ የአጠያየቅ ስልት ነው፡፡ የአጠቃየቅ ስልቱን

በተጠናከረ እና ምንባቦቹ ጥያቄዎቹን ለመመለስ በቂ ድጋፍ በሚሰጡበት አኳኋን መጠቀሙ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

2.2 ለቃላት /ፈሊጥ ጥያቄዎች ዐነገራዊ አውድ ማዘጋጀት በዚህ የአጠያየቅ ስልት አማራጮችን በማቅረብ በዐነገሩ ውስጥ ተፈላጊውን ቃል /ፈሊጥ ከሥሩ በማስመር ወይም ተፈላጊውን ቃል/ፈሊጥ በማጉደል ወይም አማራጮች ሳይቀርቡ በዐነገሩ ውስጥ ለጎደለው ቃል/ፈሊጥ ተፈታኙ ማሟያውን እንዲያቀርብ በማድረግ የቃላትን ፍቺ መጠየቅ ይቻላል፡፡

2.3 ህዳጋዊ ፈተናዎችን (close testing) መጠቀም-በዚህ አጠያየቅ ስልት አንድ አጭር ጽሁፍ አቅርቦ በየተወሰነ የመቁረጫ ቦታ (deletion) ቃላትን /ፈሊጦችን በመቁረጥ ከቀረቡት በርካታ አማራጮች ተፈታኙ ጽሁፉን እንዲያሟላ መጠየቅ ይቻላል፡፡

2.4 ቃላትን/ፈሊጦችን እንዲያዛምድ በመጠየቅ፡፡

2.5 ያልተሟላ ምልልስ (dialogue) ያላቸውን ዐነገሮች አቅርቦ በምልልሱ የተወሰነ ቃላትን/ፈሊጦችን በማጉደል ተፈታኙ እንዲያሟላቸው መጠየቅ፡፡

## 3. <u>በመምህራን ሥልጠና መፈተንን በተመለከተ የተጠናከረ ትምህርት መስጠት</u>

አብዛኞቹ መምህራን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ውስጥ ያለአውድ የሚቀርቡ የቃላት እና የፈሊጥ ጥያቄዎችን ቢኮንኑም በት/ቤት ደረጃ በሚያዘጋጁአቸው ፈተናዎች ውስጥ ግን ያጠያየቁን ስልት እንደሚጠቀሙበት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በብሔራዊ ደረጃ የሚዘጋጁ ፈተናዎች የአጠያየቅ ስልታቸው ስህተት ሲሆን መምህራኑ ፈተናዎቹ የሚስተካከሉበትን መንገድ መጠቆም ወይም መሻት እንጂ ያንኑ ስህተት በሚያዘጋጁአቸው ፈተናዎች ውስጥ መድገም አይጠበቅባቸውም፡፡

ይህ ስህተት በአንድ መልኩ መምህራኑ ተማሪዎቻቸው ፈተናውን እንዲያልፉላቸው ከመጓጓት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ መምህራን ከሚሰጣቸው የሥልጠና እውቀት ማነስ ስህተቱ ሊመነጭ ይችላል፡፡

ስለዚህ በቋንቋ መምህራን ማሠልጠኛዎቻችን ውስጥ መፈተንን /Testing/ እራሱን በቻለ ኮርስ መስጠት አስፈላጊ ይመስላል፡፡ ይህም አንደኛ መምህራን የሚያዘጋጁአቸውን ፈተናዎች ጥራት ለመጠበቅ፣ ሁለተኛ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናዎችን በሳይንሳዊ መንገድ እየገመገሙ የሚሻሻሉበትን መንገድ ለመጠቆም፣ ሦስተኛ ስህተት ያለባቸውን የአጠያየቅ ስልቶች ላለመድገም፣ በአጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማቃናት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ወዲህም መምህራኑ የሚያዘጋጁአቸውን ፈተናዎች በመሰብሰብ ብሔራዊ የፈተና ባንክ ለማዘጋጀት ቢያስፈልግ ጥሩ መሠረት መጣል ይቻላል፡፡

# ዋቢዎች

Aitichson, M.A.1987. "Words in the mind: An introduction to the mental lexicon". Quoted in parry, K.J. 1991.

Alderson, J.C. and Hughes, A. (eds). 1981. ELT Documents 111 Issues. in Language Testing. London: The Brithish Council.

Alemu, T. 1983. "Assessment of Grade Six and Eight English National Examination". Unpublished M.A. Thesis. Addis Ababa University.

Allen, J. P.B. and Davies, A (eds). 1977. The Edinburgh Course in Applised Lingustics; (Vo1.4), Testing and Experimental Methods. Oxford. Oxford University press.

Allen, V.F. 1983. Techniques in Teaching Vocabulary. Oxford: Oxford University press.

Anastasi, A. 1982. Psychological Testing. Fifth Edition. New York: Macmillan publishing Co., Inc.

Anderson, N., Cohen, A., perkins, K. and Bachman, L. 1991. "An investigation of the relationships among test-taking strategies, item content and item difficulty in an EFL reading test". language Testing. Vol.8.No.1:41-66.

Anderson, R.C. and Ortony, A. 1975. "On putting apples into bottles- A problem of polysemy". Cognitive Psychology. Vol.7: 167-180.

Asfaw, M. 1975. "The Relationship Between the ESLCE GPA's of Required subjects and first semester Freshman GPA's of Dismissed S'udents". The Ethiopian Journal of Education. Vol.VII .No. 2 : 48-55.

Bachman, L.F. 1990. Fundamental Consideration in Language Testing. Oxford: Oxford University press.

Baxter, J. 1980. "The Dictionary and Vocabulary behaviour: A single word or a handful?". TESOL Quarterly, Vo. 14. No. 3: 325 - 336.

Bright, J. A. and Gregor, G.P.M.C. 1978. Teaching English as a second language. London: Longman Group Ltd.

Bormuth, J.R. 1970 On the Theory of Achievement Test Items. Chicago: The University of Chicago press.

Brown J.S. and perry, F.L.J.R.1991. "A Comparison of Three Learning strategies for ESL Vocabulary Acquisition". TESOL Quarterly. Vol. 25. No.4: 655 - 669.

Carmines, E.G. and Zeller, R.A. 1985. A SAGE University paper. No. 17. Reliability and Validity Assessment. Quoted in Dejenie, L.1990.

Carrol, J.B.1968."The psychology of Language Testing", Quoted in Bachaman, L.F.1990.

Carter, R. 1987. " Is there a core vocabulary. Some implications for language teaching". Applied Lingustics. Vol. 8: 178-190.

Carter, R. and Mc Carthy, M. 1988. Vocabulary and Language Teaching . United Kingdom: Longman.

Cohen, A.D. 1980. Testing Language Ability in the classroom. Rowley, Massachusetts: Newbury House publishers. Inc.

Cooper, R.L.1968. "An elaborated language testing model", In John, A.upshur and Julia, F.(eds). Problems in foreign Language Testing Language Learning. Special issue No. 3. 15-72.

Cornu, A.M. 1978. "The first step in Vocabulary Teaching". Modern Language Journal. Montreal: August: 262:172.

Crocker, A.C. 1981. Statistics for Teachers. Third Edition. MFER- NELSON. Pub.Co.Ltd.

Crow, J.T. and Quigley, J.R. 1985. "A semantic Field Approach to passive Vocabulary Acquisition for Reading Comprehension". TESOL Quarterly. Vol. 19. No. 3: 497-513.

Davies, A. 1968. (ed.).Language Testing Symposium: A psycholinqustic Approach. London: Oxford University press.

_______ . 1977. "The construction of Language Tests". in Allen and Dauies (eds).

_______. 1984. "Validating Three Tests of English Language Prof iciency". Language Testing. Vol. 1. No. 1: 50-69.

_______.1985. "Communicative Language Testing", Journal of Applised Lingustics. (Annual publication of the Greek Applied Lingustics Assocations). No.1: 22-33.

Davis, T., Kaiser, R., Boone, J., and McGuine, J. 1990. " Caution in Testing". Journal of Developmental Education. Vol. 13. No. 3:.2.-4.

Dejenie, L. 1990. "Achievement Wash back and proficiency in School Leaving Examination: A case of Innovation in an Ethiopian Setting". un published phD. Thesis. University of Lancaster, United Kingdom.

Dessie, B. 1988. "An Evaluation of the Effectiveness of modern vocabulary Teaching methods and the extent to which these are implemented in Freshman English course". Unpublished M.A.Thesis. Addis Ababa University.

Ebel, R. L. 1979. Essentials of Educational Measurement. Engle word diffs,N.J. prentice Hall.

Eeds, M. and Cokrum,W.A. 1985. "Teaching word Meanings by Expanding schema versus Dictionary or Reading context work". Journal of Reading. Vol. 28:492-497.

Ethiopian School Leaving Certificate Examination Handbook. 1985. The Ethiopian School Leaving Certificate Examination Hand book. Addis Ababa: Addis Ababa University press.

Finnochiaro, M. and Sako, S. 1983. Foreign Language Testing: A practical Approach. Quoted in Dejenie, L. 1990.

Foder, J. A. 1981. Representations: philosophical essays on the foundations of cognitive Science. in parry. K. J. 1991.

Gay,L.R. 1980. Educational Evaluation and Measurement Competencies for Analysis and Application. Columbus: chartes E, Merill Publishing Company.

Green, J.A. 1963. Teacher-made tests. New York: Harper and Row.

Gronlund, N.E. 1988. How to Construct Achievement Tests. Fourth Edition. New Jersey: Printice Hall, Inc.

Gronlund. N.E. and Robert. L.L.. 1990. Measurement and Evaluation in Teaching. New York: Macmilan publishing Co.

Haliday, M.A.K; Mc Intosh, A. and Strevenis, p. 1964. The Lingustic Science and Language Teaching. London: Longman..

Harris, D. E. 1969. Testing English as a Second Language . New York: McGrow Hill Company. Ltd.

Harrison, A. 1983. A Language Testing Handbook. London: Macmillan press.

Hatch, E. and Farahaday, H. 1982. Research Design and Statistics for Applied Linguistics. Rowley, Massachusetts: New bury House publishers.

Heaton, J. B. 1975. Writing English Language Tests. London: Longman Group Ltd.

_____.1988. Writing English Language Tests. London: Longman.

________. 1990. Writing English Language Tests. London: Longman.

Henning, G.1987. A Guide to Language Testing Development, Evaluation, Research. Cambridge, massachusetts. Newbury House publishers.

Hill. L.A. and Dobbyu, M. 1981. Teachers Training Course, Lecture's Book., London: Cast Ltd-Macmillan publishing Company.

Hughes, A. (ed.) 1988. Testing English for University Study. ELT Document 127. Hong Kong: Modern English publication with the British Council.

________. 1989. Testing for Language Teachers. Cambridge. Cambridge University press.

Jones, R.L. 1973. "principles of Evaluation and Measurement". The Ethiopian Journal of Educlation. Vol .VL. No. 11: 43-52.

Kelly. R. 1978. "On the Construct Validation of Comprehension Tests: An exercise in Applised Linguistics". phD Thesis. Quoted in weir, C.J. 1988.

Kranowski. W.J. and Woods, A. 1984. " Statisical aspects of Reliability in Language Testing". Language Testing. Vol.1.No. 1:1-20.

Krashen, S. 1989. " We acquire vocabulary and spelling by Reading : Additional Evidence for the input Hypothesis". Modern Language Journal. Vol.73. No. 4:440-464.

Lado. R. 1961. Language Testing: the Construction and use of Foreign Language Tests. London: Longman.

_______. 1964. Language Teaching: A scientific Approach. New york: McGraw- Hill,Inc.,

Madsen, H.S. 1983. Techniques in Testing. Newyork: Oxford University press.

Martin, A.V. 1976. "Teaching Academic Vocabulary to Foreign Graduate Students". TESOL Quartely, Vol. 10. No. 1. 92-97.

Mathew, J.C. 1985. Examinations: A commentary. London: George All and un win (publishers). Ltd.

Mc Carthy, M. 1990. Vocabulary. Oxford: Oxford University press.

Mehrens. W.A. and Lehmann, I.J. 1973. Measurement and Evaluation . NewYork : Holt, Rinehart and winston. Inc.

Mehrens, W.A. and Lehmann, I.J. 1973. Measurement and Evaluation . NewYork : Holt, Rinehart and winston. Inc.

Mekonen, H. 1984. "Evaluation of the underdlined English Vocabulary Items in the English for New Ethiopia Series for Grade 9 to 12". Unpublished M.A. Thesis Addis Ababa University.

Mezynski, J. 1983. "Issues Concerning the Acquisition of knowledge Effects of Vocabulary Training on Reading comprehension." Review of Educational Research. Vol .53. No.2:253-279.

Morrow, K.E. 1979." Communicative Language Testing, revolution or evolution". In Brumfit, C.J. and Johnson, K.J. (eds). 1979.

Nevo,N. 1989. "Test-taking strategies on a multiple-choice test of Reading comprehension". Language Testing. Vol.6. No.2: 199-215.

Ogunniyi, M.B. 1990. Educational Measurement and Evaluation. Lagos: Longman Nigeria Limited.

Oller, J. W. 1979. Language Test at School: A pragmatic Approach. London: Longman Group Ltd.

Oller, J. W. (ed.)1983. Issues in Language Testing Research. Rowley, Mass Newbury House.

Parry, K.J. 1991. "Building Vocabulary Through Academic Reading". TESOL Quarterly. Vol. 25. No. 4: 629-653.

Rea, P.M. 1978. " Assessing Language as Communication". MALS Journal. New Series, No. 3 Department of English, University Brmingham.

Richards, J.C. 1976. "The Role of Vocabulary Teaching". TESOL Quarterly. Vol. 10. No. 1: 77-89.

Richards, J.C. and Rogers, T.S. 1991. Approaches and Methods in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Rivers, W.M. 1968. Teaching Foreign-Language Skills. Chicago:University of Chicago press.

Samuels, S.L. 1968. " Effect of word associations on reading speed, recall and gusessing behaviour on tests". Journal of Educational psychology. Vol. 59: 12-15.

Seid, J. 1978. English Idioms and How to Use Them. London: Oxford University Press.

Spolsky, B. 1976. " Language Testing: Art or science?" Proceedings of the Fourth International congress of Applied Lingustics. Stuttgars: Hochschulverlag.

Throndic, R. L. and Hagen. E.P. 1977. Measurement and Evaluation in Psychology and Education. Columbia University.

Wallace, M. 1982. Teaching Vocabulary. Oxford: Heinimann.

Weir, C.J. 1988. Communicative Language Testing. Exeter: A. Wheaton and Co. Ltd.

Wiersma, W. and Stephen, G.J. 1990. Educational Measurement and Testing. Second Edition-Boston: Allyn and Bacon.

Valette, R.M. 1979. Modern Language Testing. Second Edition. San Diego: Harcourt Brace Jovan voic publishers.

መንገሻ ከበደ። 1984። "የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና የምንባብ ጥያቄዎች ግምገማ"። የቢ.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ /ያልታተመ/

ሰለሞን ደስታ። 1976። "በአዲስ አበባ ከተማ በ4 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ1975 ዓ.ም. የተሰጡ የአማርኛ ፈተናዎች ግምገማ" ። የቢ.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ /ያልታተመ/

ተስፋዬ ሐይሌ። 1964። "የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ተፈታኞች ለምን በአማርኛ ጥሩ ውጤት አያመጡም?" ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ /ያልታተመ/

ተስፋዬ ሸዋዬ ። 1981። ሥነ ልሳንና ቋንቋን ማስተማር ። አዲስ አበባ፤ /ያልታተመ/

ትምህርት ሚኒስቴር ። 1970 ። "የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት /7-12ኛ ክፍል/" ። አዲስ አበባ ፤ በሥርዓተ ትምህርትና ሱፐርቪዥን መምሪያ የአማርኛ ትምህርት ቡድን የተዘጋጀ፤ /ያልታተመ/

_______ ። 1970 ። የአማርኛ መማሪያ /9-12ኛ ክፍል/ ። አዲስ አበባ ፤ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ።

_______ ። 1984 ። የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ /9-12ኛ ክፍል/ ። አዲስ አበባ፤ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ።

_______ ። 1985 ። የአማርኛ መማሪያ /9 - 12ኛ ክፍል/ ። አዲስ አበባ ፤ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ።

ንጉሤ ዳእታ ። 1978 ። "የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና አቀራረብና የመማሪያ መጻሕፍቱ ዝምድና" ። የቢ.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ /ያልታተመ/

አምሳሉ አክሊሉ እና ዳኛቸው ወርቁ። 1979 ። የአማርኛ ፈሊጦች ። አዲስ አበባ ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ።

አበበ ከበደ ። 1975 ። "የ6ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ የአማርኛ ፈተና ግምገማ" ። የቢ.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፤ /ያልታተመ /

ወርቁ ዓለሙ ። 1979። "በጎልማሶች ትምህርት መምሪያ ሥር በርቀት ትምህርት ዋና ክፍል የሚሰጠው የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ፈተና ግምገማ" ። የቢ. ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፤ /ያልታተመ/

ዋጋዬ ገ/አምላክ ። 1972 ። "ከ1963 - 1971 ዓ.ም. ለስምንተኛ ክፍል የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ብሐራዊ ፈተናዎች ግምገማ" ። የቢ.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፤ /ያልታተመ/

# አባሪ ሀ

**ከ1980– 1987 ዓ.ም የተዘጋጁትን የሁ.ደ.መ.እ.ፈ የቃላትን የፈሊጥ ጥያቄዎችን ዝርዝር በዓመተ ምህረትና በመምሪያ የሚያሳይ ፡፡**

1. 1980 ዓ.ም

**ሀ. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጐች ተመሳሳይ ፍቺ ስጥ፡፡/10/**

1. ነፈረቀ ሀ. አለቀሰ ለ. ሞጨሞጨ ሐ. ተንሰቀሰቀ መ. አላዘነ
2. መደንበር ሀ. መወላከፍ ለ.መበርገግ ሐ. መወናበድ መ. ግራመጋባት
3. አዛጋ ሀ. አንጉላጀ ለ. አሸለበ ሐ. አንኮራፋ መ. አፋሸከ
4. አድመኛ/አድምተኛ/ ሀ. ጠበኛ ለ. ሴረኛ ሐ. ተከራካሪ መ. አኟቢ
5. ነዳይ ሀ. የተጉሳቆለ ለ. የሚነዳ ሐ. የደኸያ መ. ተሳዳቢ
6. እጀ መናኛ ሀ.እጀ መጥፎ ለ. እጀ ሰላላ ሐ. እጀ ከፉ መ. እጀ ሰባራ
7. ቀትረ ቀላል ሀ. ጓዘ ቀላል ለ. ጥላ ቢስ ሐ. ገደ ቢስ መ. ልበቢስ
8. ፈር ያዘ ሀ. ሥርዓት ያዘ ለ. አቅጣጫ ያዘ ሐ. መስመር ያዘ መ. ሕግ ያዘ
9. ዋስ ማሳገት ሀ.ዋስ መያዝ ለ.ዋስ መጥራት ሐ. ዋስ መክሰስ መ.ዋስመስጠት
10. ቅንድቧን ተላጨች ሀ. ዓይኗን ተኳላች ለ. ዓይኗን ተቀነደበች ሐ. ዓይን ከፈተች መ. ዓይን አወጣች

**ለ. ከአራቱ አማራጭ መልሶች ውስጥ ከአንዱ በስተቀር ሶስቱ በትርጉም አለዝያም በአገባብ ይዛመዳሉ ከሌሎች የሚለየውን ቃል ለይተህ አውጣ /5/**

11. ሀ. መማሰን ለ.መልፋት ሐ. መዋተት መ. መባዘን
12. ሀ. አወከ ለ. አበጣበጠ ሐ. አስቸገረ መ. አስጨነቀ
13. ሀ . እንቁራሪት ለ. እንሽላሊት ሐ. እባብ መ. እስስት

14. ሀ. አደስዳሽ ለ. አስመሳይ ሐ. አደዝዳዥ መ. አውደልዳይ

15. ሀ. ለካ ለ. ከነደ ሐ. መጠነ መ. ከፈለ

**ሐ. በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ስጥ /9/**

17. በምንባቡ ውስጥ "በየቤቱ ጥግ" የተባለውን ሐረግ ሊተካ የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. በየቤቱ ስር የሚለው ነው ሐ. በየቤቱ ጓዳየሚለው ነው
ለ. በየቤቱ ጎን የሚለው ነው መ. በየቤቱ ጓሮ የሚለው ነው

18. በምንባቡ ውስጥ " የተጠለለው "የሚለውን ቃል የሚተካው የትኛው ነው?

ሀ. የተጠጋው የሚለው ነው ሐ. የተከለለው የሚለው ነው
ለ. የተከማቸ የሚለው ነው መ. የተሰበሰበው የሚለው ነው

20. በምንባቡ ሁለተኛ አንቀጽ ውስጥ "የሐሳብ ዱር" የሚለወ ሀረግ ምን ለማለት ነው?

ሀ. የሐሳብ ቅኝት ለማለት ነው ሐ. ያለፈ ትዝታ ለማለት ነው
ለ. የበዛ ሐሳብ ለማለት ነው መ. የሰመመን እንቅልፍ ለማለት ነው

30. "ታጥቦ ጭቃ" ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ. ከርሞ ጥጃ ማለት ነው ሐ. መልሶ እዚያው ማለት ነው
ለ. ታጥቦ መጨቅየት ማለት ነው መ. ቢታጠበ የማይጸዳ ማለት ነው

34. ልብስ አጣቢው "አብረን ስንሰራ " ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ. አብረን ስንኖር ማለቱ ነው ሐ. አብረን ስንቆይ ማለቱ ነው
ለ. አብረን ስንቀመጥ ማለቱ ነው መ. አብረን ስንሆን ማለቱ ነው

35. "ጨለማ የዋጠው ሤራ" ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ. የተንኮል ሲራ ማለቱ ነው ሐ. የሀዘን ሴራ ማለቱ ነው
ለ. የክፋት ሴራ ማለቱ ነው መ. የተሰወረ ሴራ ማለቱ ነው

38. "ሚዛን ገምቶ ይለወጣል" ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ. ጥቅም አይቶ ይከዳል ማለቱ ነው ሐ. ስልጣን አይቶ ይከዳል ማለቱ ነው
ለ. ኃይል አይቶ ይከዳል ማለቱ ነው መ. ጊዜ አይቶ ይከዳል ማለቱ ነው

39. " ጥርስ ያስገባሉ" ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ. ያስቀጣሉ ማለት ነው ሐ.ያስጠላሉ ማለት ነው
ለ. ያሳማሉ ማለት ነው መ. ያስጠምዳሉ ማለት ነው

51. በግጥሙ 4ኛ አንጓ "አዝመራ" የሚለው ቃል የገባው ምን እንዲወክል ተደርጎ ነው ?

ሀ. ጥበበ–ቃላት ለ. ጣዕመ –ወግ ሐ. እርኪ ጽሑፍ መ. ጣፋጭ ወሬ

## 2. 1981 ዓ.ም

**ሀ. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች ተመሳሳይ ፍች ስጥ። /10/**

1. አጋሚዶ ሀ. ቀማኛ ለ. ሽፍታ ሐ. እልከኛ መ. ጀብደኛ

2. ተረበኛ ሀ. አፈኛ ለ. ወገኛ ሐ. ቀልደኛ መ. ጉረኛ

3. ግደይ ጣለ ሀ. ገድሎ ጣለ ለ. ጥሎ ገደለ ሐ. ገድሎ አሳየ መ.ሬሳጣለ

4. ገነገነ ሀ. ጠረጠረ ለ. በረገገ ሐ. መረመረ መ. ገመገመ

5. ድጎማ ሀ. ምፅዋት ለ. ድጋፍ ሐ. እርዳታ መ. ልግስና

6. ከእጅ ወደ አፍ ሀ.ቁርሶ መጉረስ ለ. ሠርቶ መብላት
ሐ. እርሶ ማደር መ. ትርፍ ማጣት

7. አፍለኛ ሀ. ያልሻገተ ለ. ያልከመጠጠ ሐ. ያልበካ መ. ያላረረ

8. ማዕከል ሀ. እኩል መሆን ለ. አማካይ መሆን
ሐ. ድንበር መሆን መ. ዳርመሆን

9. መሬት ቁና ሆነች ሀ.መሬት ጠበበች ለ. መሬት ከብ ሆነች
ሐ.መሬት መከራ በዛባት መ. መሬት ተጨነቀች

10. የእንጨት ሽበት ሀ. የሸበተ ሰው ለ.መሬት ከብ ሆነች
ሐ. መሬት መከራ በዛባት መ. መሬት ተጨነቀች

ለ. የተለየውን ቃል አውጣ

11. ሀ. አመነኘከ ለ. ሰለቀጠ ሐ. አመሰኳ መ. አኘከ

12. ሀ. ስልባቦት ለ. ስፈፍ ሐ. አምቡላ መ. ገፈት

13. ሀ. አረንቋ ለ. ረግረግ ሐ. ማጥ መ. ድጥ

14. ሀ. መዘንጠል ለ. መቀርደድ ሐ. መንደል መ. መፈንቀል

15. ሀ. ዘገበ ለ. ሰበሰበ ሐ. ቆጠረ መ. አጠራቀመ

16. ሀ. አጓራ ለ. አካላላ ሐ. ተኩራራ መ. አገሳ

17. ሀ. ከመረ ለ. አሰለፈ ሐ. ደረደረ መ. ኩለኩለ

18. ሀ. ቅሬት ለ. እርጉዝ ሐ. ጥገት መ. ከበድ

19. ሀ. ነተረከ ለ. ነዘነዘ ሐ. ተረከ መ. ጨቀጨቀ

20 ሀ. አወናበደ ለ. ወላወለ ሐ. ዘላበደ መ. ቀላመደ

ሐ. በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ስጥ /19/

24. "ባል ሲተዋቸው" ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ. ባል ሲጠላቸው ማለቱ ነው ሐ. ባል ሲያጡ ማለቱ ነው
ለ. ባል ሲፈታቸው ማለቱ ነው መ. ባል ሲሞትባቸው ማለቱ ነው

26. "የከተማ ጫካ" እና "የከተማ ዱር" በምንባቡ ውስጥ ምን ዓይነት ትርጉም አላቸው?

ሀ. የተቀራረበ ትርጉም አላቸው ሐ. የተለያየ ትርጉም አላቸው
ለ. አንድ አይነት ትርጉም አላቸው መ. ተቃራኒ ትርጉም አላቸው

35. "ቸነፈር" የሚለውን ቃል ለተካ የሚችል የትኛው ነው ?
ሀ. መአት ለ. እልቂት ሐ. ወረርሽኝ መ. ቁጣ

36. ገጣሚው "መዓልት" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. ዓመት ለ. ወር ሐ. ቀን መ. ሳምንት

39. በስንኝ 14 ላይ "ለኔ ብጤማ" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. ለደሃው ማለቱ ነው ሐ. ረሃብን ላልቀመሰው ማለቱ ነው
ለ. ረሃብ ላጠቃው ማለቱ ነው መ. በችግር ለተጎዳው ማለቱ ነው

40. ገጣሚው "ይዘከራል" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. ይታወሳል ማለቱ ነው ሐ. ይዘወተራል ማለቱ ነው
ለ. ተዝካር የወጣለታል ማለቱ ነው መ. ይወደሳል ማለቱ ነው

41. "ይመለከት ገባ" ምን ማለት ነው ?
ሀ. ይቃኝ ጀመር ማለት ነው ሐ. ያጠና ጀመር ማለት ነው
ለ. ይመረምር ጀመር ማለት ነው መ. ይቆጥር ጀመር ማለት ነው

53. በግጥሙ ውስጥ "ቀበቶ" የተባለው ምንድን ነው ?
ሀ. ትጥቅ ነው ለ. ረሀብ ነው ሐ. ችግር ነው መ. ብሶት ነው

54. ገጣሚው "የተልኮህን አባዜ" ሲል ምን ለማለት ነው ?
ሀ. የተጣለብህን ኃላፊነት ለማለት ነው
ለ. የተፈጥሮ ድርሻህን ለማለት ነው
ሐ. የሚጠበቅብህን አስተዋጾ አለ ማለት ነው
መ. የሚጠበቅብህን እዳ ለማለት ነው

55. ገጣሚው "በትን ያሻራህን ዘር" ሲል ምን ለማለት ነው ?
ሀ. የእጅህን ፍሬ ለማለት ነው ሐ. የግልህን አስተዋጾኦ ለማለት ነው
ለ. የግንባርህ ወዝ ላማለት ነው መ. ያብራከህን ልጆች ለማለት ነው

73. "የሚራመድ" በሚለው ቃል ፈንታ ሊገባ የሚችለው የትኛው ነው ?
ሀ. የሚሮጥ ለ. የሚውል ሐ. የሚኖር መ. የሚመራ

74. "ከንጋቱ አሥር ሰዓት" የሚለውን ሐረግ የሚተካው የትኛው ነው ?
ሀ. ከጠዋቱ ባስር ሰዓት ሐ. ከሌሊቱ ባስር ሰዓት
ለ. ከቀኑ በአስር ሰዓት መ. ከዕኩለ ሌሊት በኃላ

76. "ተጥለቅልቀውና ተግበስብሰው" የሚለውን ሐረግ የሚተካው የትኛው ነው?
ሀ. ተቀስቅሰውና ተግበስብሰው ሐ. ተቀስቅሰውና ተሰባስበው
ለ. ተቀስቅሰውና ተጥለቅልቀው መ. ተቀስቅሰውና ተጠራቅመው

78."አርደው አወራርደው " የሚለው ሐረግ በምን መተካት ይገባዋል ?
ሀ. ጥለው ለ. ባርከው ሐ. ዘርፈው መ. ቆራርጠው

79. "ሲመገቡና ሲዋኩ " የሚለው ሐረግ በምን መተካት አለበት ?
ሀ. ሲበሉና ሲዋኩ ሐ. ሲበሉና ሲጮኹ
ለ. ሲበሉና ሲያወኩ መ. ሲበሉና ሲቦርቁ

80. "ድምፅ ተሰማ" የሚለው ሐረግ በምን መተካት አለበት ?
ሀ. ሰማ ለ. ሰሙ ሐ. አሰማ መ. አሰሙ

83. "በየክፍሉ " የሚለው ቃል በምን መተካት ነበረበት ?
ሀ. ከግራና ከቀኝ ለ. ከታችና ከላይ
ሐ. በየአቅጣጫው መ. ከኋላና ከፊት

89. "አስበርግጎት " የሚለው ቃል መተካት ያለበት በየትኛው ነው ?
ሀ. አስደንግጦት ለ. አስቆጥቶት ሐ. አነሳስቶት መ. አስከፍቶት

90. "ቃል በማይገኝለት ሁኔታ አመለጠ" በሚለው ውስጥ "ሁኔታ" የሚለውን ቃል
መተካት ያለበት የትኛው ነው ?
ሀ. አኳኃን ለ. ነገር ሐ. ፍጥነት መ. አመለካከት

## 3. 1982 ዓ.ም

### ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጥ /15/

1. አገናዘበ ሀ. አስታወሰ ለ. አያያዘ ሐ. አዛመደ መ. አቆራኘ
2. ገመገመ ሀ. ገመተ ለ. መዘነ ሐ. ሰፈረ መ. ለካ
3. ጎመራ ሀ. ደረሰ ለ. በሰለ ሐ. አረረ መ. ደረቀ
4. አጎራባች ሀ. ድንበርተኛ ለ. ክልልተኛ ሐ. ቀራቢ መ. ተለጣቂ
5. አዳባይ ሀ. አስገቢ ለ. አስቀማጭ ሐ. አስጠጊ መ. እኑዋሪ
6. ደበተ ሀ. ሰለቸ ለ. ተጫነ ሐ. ፈዘዘ መ. ከበደ
7. ደለበ ሀ. ወፈረ ለ. ወደለ ሐ. አማረ መ. ጠገበ
8. ደለቀ ሀ. ጮኸ ለ. ጣረ ሐ. መታ መ. በላ
9. ቀጀ ሀ. ከፈለ ለ. አወጣ ሐ. መለሰ መ. ገዛ
10. ጥርጊያ ሀ. ንፁህ ለ. ድልድል ሐ. ልስልስ መ. ቀጥተኛ
11. አካበተ ሀ. ከተተ ለ. ከመረ ሐ. ሰወረ መ. አኖረ
12. ለበጣ ሀ. ቀልድ ለ. ውሸት ሐ. ምጸት መ.ቧልት
13. ተናጋ ሀ. ተላቀቀ ለ. ተለያየ ሐ. ተናወጠ መ. ተንቃነቀ

14. ነደለ  ሀ. አፈረሰ  ለ. ዘነጠለ  ሐ. ሸነቆረ  መ. ፈለፈለ

15. አናቆረ  ሀ. አናከሰ  ለ. አባባሰ  ሐ. አጋደለ  መ. አታገለ

ለ. በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ስጥ። /፬/

23."በሀይማኖቱ ሁሉ ላልቷል" የሚለው ሐረግ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ይተካዋል።
ሀ. እምነቱን ክዷል  ለ. ሀይማኖቱን አያጠብቅም
ሐ. ሞራሉ ወድቋል  መ. ሀሊናው ሸሟል

35. "እንድንወርሳቸው" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. እንድንቀበላቸው ማለቱ ነው  ሐ. እንድንቀማቸው ማለቱ ነው
ለ. እንድንወስድባቸው ማለቱ ነው  መ. እንድንገበያቸው ማለቱ ነው

36. "ሁሉ ቀኙ" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. ሁሉም በቀኙ ያለ ማለቱ ነው  ሐ. ሁሉም ቀና የሆነለት ማለት ነው
ለ. ሁሉም ቀላል የሆነለት ማለት ነው  መ. ሁሉንም የሚያመዛዝን ማለቱ ነው

44. "ከውይይት ይልቅ" ሲል
ሀ. በይፋ ከመናገር ይልቅ ማለቱ ነው
ለ. ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ይልቅ ማለቱ ነው
ሐ. በሐሳብ ለመለዋወጥ ከመናገሩ ይልቅ ማለቱ ነው
መ. በሃሳብ ለመስጠት ከመናገር ይልቅ ማለቱ ነው

47. "አደንቋሪ ተረብ " ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. ጆሮን የሚያደነቁር ማለት ነው  ሐ. ስድብ ማለት ነው
ለ. ፋይዳ ቢስ ጮኸት ማለት ነው  መ. መሸርደድ ማለት ነው

48. "ሕሊና እየወጋ" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. አእመሮን እያስቃየ ማለቱ ነው
ለ. አእመሮን በስለት እየወጋ ማለቱ ነው
ሐ. አእምሮን በጮቤ እየወጋ ማለቱ ነው
መ. ሕሊናን በጦር እየወጋ ማለቱ ነው

78. "ካባ" የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል
ሀ. አስገዳጅ ሰውን ያመለክታል  ሐ. መኀታች ነገርን ያመለክታል
ለ. የሰው መረባረብን ያመለክታል  መ. የስጦታ ዕቃን ያመለክታል

4. 1983 ዓ.ም

**ሀ. ለሚከተለት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጥ። /12/**

1. ዘከረ ሀ. አስታወሰ ለ. አሳሰበ ሐ. አመለከተ መ. አስጠራ

2. ጥራዝ ነጠቅ ሀ. ደንቆሮ ለ. መሀይም ሐ. ያልተማረ መ. ባለጌ

3. በሞተ ከዳ
ሀ. በጠፋ ምትክ ለ. በጎደለ ምትክ ሐ. በሔደ ምትክ መ. በተሰኘበት ምትክ

4. እንቶ ፈንቶ ሀ. የማይረባ ለ. ምናምቴ ሐ. ከንቱ መ. ዝባዝንኪ

5. ጣምራ ሀ. ሁለት ለ. እጥፍ ሐ. እኩል መ. ብዙ

6. አላነዘ ሀ. አዘነ ለ. አመረረ ሐ. አለቀሰ መ. አነባ

7. ሰለባ ሀ. ግዳይ ለ. አደጋ ሐ. ስልብ መ. ውጤት

8. ሸመጠጠ ሀ. ቀላመደ ለ. አወናበደ ሐ. አንገራገረ መ. ከዳ

9. በዘፈቀደ ሀ. እንደአጋጣሚ ለ. እንዳሻው ሐ. እንደተሟላ መ. እንደተሻለ

10. በነፍስ ወከፍ ሀ. በጋራ ለ. በግል ሐ. በቡድን መ. በጥንድ

11. ቅንጣት ሀ. ኢምንት ለ. ጥቂት ሐ. ትንሽ መ. ስባሪ

12. አይነ ቁራኛ
ሀ. በአይን መቆራኘት ሐ. በአይን መከተል
ለ. በአይን መጠበቅ መ. በአይን መመልከት

**ለ. በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ስጥ። /9/**

13. "ከመሀከላቸው" የሚለው ቃል ከማን መሀል ለማለት ነው ?
ሀ. ከወላጆች ለ. ከልጆች ሐ. ከወሳኞች መ. ከተካፋዮች

16. "የፈሰሰው ደም እንዲደርቅ" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. እርቅ እንዲወርድ ሐ. ለቅሶ እንዲቀር
ለ. ቂም እንዲጠፋ መ. ገዳይ እንዳይታወቅ

20. "እንዲያ ያለው" የሚለወ ሀረግ የሚያመለክተው ምንን ነው ?
ሀ. ሰራተኛና ደሃ ተሰድቦ የጌታ ዘር መከበሩን
ለ. ሰራተኛና ደሃ ተሰድቦ የጌታ ዘርና የማይሰራ መከበሩን
ሐ. ሰራተኛና ደሃ ተንቆ በጥፍሩ ሥራ የማይነካ መከበሩን
መ. የእጅ ሥራ አዋቂና ደሃ ተንቆ የጌታ ዘር መታፈሩን

21. ደራሲው "በጎ አድራጊዎች" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. ተሸሎአቸው አዳሪዎች
ሐ. አግኝተው አዳሪዎች
ለ. ደህና አዳሪዎች
መ. ደልቷቸው አዳሪዎች

31. "እየንተሰራፉ የሂዱት" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. እየተስፋፉ የሂዱት
ሐ. የበላይነት ያገኙት
ለ. እየተዝናኑ የሂዱት
መ. ጉልበተ ያገኙት

32. "ሰው በሩቁ ሲያስተውል፣ ሲገመግም" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. ሰው ሲፈራ ለ. ሰው ሲያይ ሐ. ሰው ሲመዝን መ. ሰው ሲጠብቅ

33. "ከመሰሎቹ ጋር ተቀላቀላ" ሲል መሰሎቹ የተባሉት ምንድናቸው ?
ሀ. ጦር ለመወርወርና ለመመከት የቻሉ
ለ. የልጅነት ጊዜ ጓደኞቹ የሆኑ የሰፈር ልጆች
ሐ. ዘመዶቻቸው በሌሎች ሰዎች የተገደሉባቸው
መ. ከህብረተሰብ ተለይተው በበረሃ የሚኖሩ

34. "የዚያኑ ያህል" የሚለው የሚያመለክተው ምንን ነው ?
ሀ. የፍቅር ጥንካሬን
ሐ. የፍለጋ ጥንካሬን
ለ. የመተማመን ጥንካሬን
መ. የብረት ጥንካሬን

**ሐ. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ፍቻቸውን ስጥ። /15/**

40. "ምንአግዶኝ እስድበዋለሁ" ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. እንዴት ደፍሬ አሰድበዋለሁ
ሐ. እንዳልሰድበው ምን ሕግ ያግደኛል
ለ. ብሰድበው ማን ይከለክለኛል
መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው

41. "ምድር ሲለቅ ጉዞ ጀመሩ ማለት" ምን ማለት ነው ?
ሀ. ጉም ሲጠፋ ጉዞ ጀመሩ
ሐ. ሲመሽ ጉዞ ጀመሩ
ለ. ሲነጋ ጉዞ ጀመሩ
መ. ደመና ሲገለጥ ጉዞ ጀመሩ

42. "ሲበሉ የላኩት" ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. ዓይነአፋር ለ. ሀፈረተቢስ ሐ. ልበቢስ መ. ሆደቡቡ

43. "ወንድሜ ሆይ ! የምታወራውን ተወውና ሌላ ሌላውን አጫውተኝ ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. ጥሩ ጥሩውን አጫውተኝ
ሐ. የሚያስቀውን አጫውተኝ
ለ. ክፉ ክፉውን አጫውተኝ
መ. የሚመስለውን አጫውተኝ

44. "ከቁንጫ ሌጦ በማውጣት የሚያክለው የለም" ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. ሥራ ፈትቶ ውሸት በመናገር የሚያክለው የለም ማለት ነው
ለ. በጥቂት ገንዘብ ተነስቶ ሃብታም በመሆን የሚያክለው የለም ማለት ነው

ሐ. ጥቃቅን ስህተት በመፈለግ የሚያከለው የለም ማለት ነው
መ.ትልልቅ ሹመት በመመኘት የሚያከለው የለም ማለት ነው

45. "በቀለ የማንባር ስጋ ነው" ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. ያየውን ክፉ ነገር ከማውገዝ አይመለስም ማለት ነው
ለ. ያየውን ደግ ነገር ከማጥፋት አይመለስም ማለት ነው
ሐ. ያየውን ሁሉ ከመተቸት አይመለስም ማለት ነው
መ. ሳያፍር በፊት ለፊት ጉቦ ከመብላት አይመለስም ማለት ነው

46. "ነገር አማሰለ" ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. ነገር ሰበሰበ ማለት ነው
ሐ. ነገር አመቀ ማለት ነው
ለ. ነገር አማታ ማለት ነው
መ. ነገር ወደደ ማለት ነው

47. በዘይቤያዊ ፍቺው "የርድ ከብት" ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. በሬ ለ. እንፈፍ ሐ. የወረገኑ ከብት መ. የቁርጥ ስጋ

48. "አንደበተ ርቱእ" ሰው እንዴት ያለ ነው ?
ሀ. አንደበቱ ቀጥ ብሎ የቆመ ነው
ሐ. ተናግሮ የሚረታ ነው
ለ. መናገር የሚችል ነው
መ. ንግግሩ የሚወላውል ነው

49. "አንጀተ ጥኑ" ሰው እንዴት ያለ ነው ?
ሀ. ርህራሄ የሌለው ነው
ሐ. ቻይ ነው
ለ. ደንዳና ነው
መ. የተራበ ነው

50. "የአንጀቱን ያደረሰ ሰው" ምን ሆኗል ?
ሀ. የልቡ ደርሷል
ሐ. አንጀቱ ቀቤ ጠጥቷል
ለ. የተመኘውን አግኝቷል
መ. ሁሉም ትክክል ነው

51. "አካፋ እግር" ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. ወልጋዳ እግር ለ.ቀጭን እግር ሐ. ሰፊ እግር መ. ሀ እና ሐ

52. ከሚከተሉት ቃላትና ሀረጎች የማይገጥመው የቱ ነው ?
ሀ. ምሁር
ሐ. የቀለም ቀንድ
ለ. ሊቅ፣መጣፍ አዋቂ
መ. የማይገጥም ቃል የለም

53. "አገም ጠቀም ማድረግ" ምንድን ነው ?
ሀ. መያዝ መልቀቅ
ለ. መስደብ ማመስገን
ሐ. መውጋት መንቀል
መ. ሁሉም

54. "እንብርቱን የተተኮሰ ሰው" ምንድን ነው ?
ሀ. ሆዳም
ለ. የሰማውን የማይደብቅ
ሐ. የሚይዘውን ያጣ
መ. ምራቁን የዋጠ ጨዋ

5. 1984 ዓ.ም

ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጥ /10/

1. ጥሪት ሀ. የቁም ከብት ለ. ማንኛውም ገንዘብ
ሐ. ማንኛውም ሃብት መ. ሁሉም

2. ሞሽለቀ ሀ. ገዛ ለ. ሰረቀ ሐ. ሸጠ መ. አወላለቀ

3. "አያምስልብህ" ሀ. አያምጣብህ ለ. አያድርስብህ
ሐ. አያመሳስል መ. ሀ እና ለ

4. ነቀዘ ሀ. ቅንቅን በላው ለ. ወፍ በላው ሐ. እረኛ በላው መ. ሀ እና ሐ

5. አፍንጮ ሀ. አፍንጫ የለሽ ለ. አፍንጫ ሰልካካ
ሐ. አፍንጫ ሰንደዶ መ. ቀጥ ያለ አፍንጫ ያለው

6. "ቅልጥጥ አለ" ማለት ሀ. ግልጥ አለ ማለት ነው ሐ. ላቡ ወጣ ማለት ነው
ለ. ወዛ ማለት ነው መ. ላቡ ተንጠባጠበ ማለት ነው

7. ኮተታም ሀ. ሆዳም ለ. ጓዛም ሐ. ባለኮቴ መ. ጨቅጫቃ

8. ተለመዘገ ሀ. ተቆነጠጠ ለ. ተፈተለ ሐ. ተልመዘመዘ መ. ተሳበ

9. ክጀላ ሀ. ክልክላ ለ. ትረባ ሐ. ድረታ መ. ፍለጋ

10. ለሰስ አለ ሀ. መሬተ ለመሬት ተሳበ ሐ. ለዘብ አለ
ለ. ለብ አለ መ. ለስለስ አለ

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍች ስጥ

11. ድበላ ሀ. ቅነሳ ለ. ጭመራ ሐ. ድረባ መ. ቅየጣ

12. ደልቃቃ ሀ. ሞልቃቃ ለ. ጨዋ ሐ. ቅምጥል መ. እንቅብር

13. ጣስ ሀ. ረገጠ ለ. አከበረ ሐ. ናደ መ. አፈረሰ

14. ጠባ ሀ. መሸ ለ. ባተ ሐ. ነጋ መ. ፈገገ

15. ፈተፈተ ሀ. ነገር አበዛ ለ. አስታረቀ ሐ. አዋሸከ መ. ሀ እና ለ

16. ማለደ ሀ. ዘገየ ለ. ገሰገሰ ሐ. በሟት ሄደ መ. ጉቦ ሰጠ

17. ላሽቀ ሀ. ለፋ ለ. ላላ ሐ. ጠነከረ መ. ሟለጨ

18. ፎከተ ሀ. ቆፈረ ለ. ፋቀ ሐ. አከከ መ. ደባበሰ

19. ማደራደር ሀ. ማኮላኮል ለ. ማስማማት ሐ. መቃወስ መ. ማዋዋል

20. አደነደነ ሀ. አጎላ ለ. አካሳ ሐ. አሰባ መ. አገዘፈ

ሐ. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ፍቻቸውን ስጥ። /8/

36. "ባር ባር አለው" ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. መጠጥ መጠጥ አለው ሐ. ጸጉር አስተካካይ አስፈለገው
ለ. ፍራት ፍራት አለው መ. ነገር አማረው

37. "ሆደ መጋዝ" የሆነ ሰው
ሀ. ክፉ ሰው ነው ሐ. ጠጥቶ የማይጠግብ ሰው ነው
ለ. በልቶ የማይጠግብ ነው መ. ቆራጥ ሰው ነው።

38. "ዘር ይውጣልህ" ማለት ምን ማለት ነው
ሀ. የወለድካቸው ልጆች የበቁ የነቁ ይሁኑ ማለት ነው
ለ. የዘራኸው እህል ይብቀልልህ ማለት ነው
ሐ. የምታረባው ከብት ይብዛልህ ማለት ነው
መ. ሀ ፣ ለእና ሐ ትክክል ናቸው

39. "ዓይንህን ላፈር" ማለት ምን ማለት ነው
ሀ. ዓይንህ ውስጥ አፈር ይግባ ሐ. ዓይንህን አልየው ጥፋ
ለ. ዓይንህ አፈር ይሁን መ. ዓይንህ አፈር ይመስላል

40. ገመናው የተገለጠ ሰው፣ ሀ. ነውሩ የታየበት ሰው ነው
ለ. ጠጪነቱ የታወቀበት ነው ሐ. ሴሰኛነቱ የታየበት ሰው ነው
መ. የእጅ አመል እንዳለው የታወቀበት ሰው ነው

41. "ጥርሰ ዘርዛራ" ሰው
ሀ. ጥርሱ የወላለቀ ሰው ነው ሐ. ጥርሱ ያፈነገጠ ሰው ነው
ለ. ጥርሱ የተራራቀ ሰው ነው መ. ጥርሰ ፍንጭት ሰው ነው

42. "ዐፈር ይፈጭል" ማለት
ሀ. ያርሳል ማለት ነው ሐ. ትጉህ ሰራተኛና አዋቂ ነው ማለት ነው
ለ. ሐጻን ነው ማለት ነው መ. ነገረ ያኘካል ያደቃል ማለት ነው

43. "ዋስትናውን አስወረደ" ማለት ሀ. ተያዥነቱ ቀረ ማለት ነው
ለ. ዋስትናውን ለሌላ ሰው አሳለፈው ማለት ነው
ሐ. ዋሱን አሳገተ ማለት ነው መ. ዋስ ጠራ ማለት ነው

መ. በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ስጥ። /5/

59. "ጀንበሯ ስታዘቀዝቅ ገና ድንገዝገዝ" ሲል ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. ለአይን ሲይዝ ማለት ነው
ለ. ጨለማ ሲሆን ማለተ ነው
ሐ. ፀሀይ አልጠለቀችም ማለት ነው
መ. ሀ እና ሐ ማለት ነው

60. በምንባቡ መሠረት "ወፍ ሲንጫጫ" የሚለው አባባል ምን ማለት ነው ?
ሀ. ወፍ ሲጮህ ማለት ነው
ለ. ወፎች እየበረሩ ሲጮኹ ማለት ነው
ሐ. ሲነጋጋ ማለት ነው
መ. ሲጨልም ማለት ነው

61. "የተስፋ ቡቃያ የሚያሽትበት" የሚለው አባባል ምን ማለት ነው ?
ሀ. ቡቃያ በመሬት ላይ የሚታይበት ወቅት ማለት ነው
ለ. ተስፋ ያደረግነው ነገር ትክክለኛ መልኩን የሚያሳይበት ወቅት ማለትነው
ሐ. ቡቃያ እሸት የሚሆንበት ወቅት ማለት ነው
መ. እሸት የሚበላበተ ወቅት ማለት ነው

67. "ይቁላላ ጅራቴ" የሚለው ሐረግ በግጥሙ ውስጥ የያዘው ፍቺ ምንድን ነው ?
ሀ. ውሻው ጅራቱን ያወዛውዛል
ለ. ውሻው ጅራቱንቀስሮታል
ሐ. ለሚያዝዘኝ ሁሉ ልሽቆጥቆጥ
መ. መልሱ አልተሰጠም

71. በምንባቡ መሠረት "የትውልድ ድልድይ" ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. ትውልድ የሠራው ድልድይ
ለ. ትውልድ የሚሸጋገረበት ድልድይ
ሐ. ድልድይ ለትውልድ መሸጋገሪያ ያገለግላል
መ. አንዱን ትውልድ ወደሚቀጥለው ትውልድ የራሱን ባሕል የሚያሸጋግርበት መንገድ

## 6. 1985 ዓ.ም

### ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ስጥ /16/

1. እዳሪ
ሀ. ያልተባረከ መሬት
ለ. ያልተወቃ መሬት
ሐ. ያልታረሰ መሬት
መ. ያላመረተ መሬት

2. አክርማ ሀ. የሳር ስም ለ. የአርማ ስም ሐ. የአረም ስም መ. የእህል ስም

3. ጥራዝ ነጠቅ
ሀ. አይቶ የሚያወራ
ለ. ሰምቶ የሚያወራ
ሐ. አንብቦ የሚያወራ
መ. ከጥራዝ ነጥቆ የሚያወራ

4. አንገራገረ ሀ. አነጋገረ ለ. አመነታ ሐ. ግርግር ፈጠረ መ. ሰው ግራ አጋባ

5.አውሸለሸለ ሀ. አውተፈተፈ ለ. አውደለደለ

ሐ. አመሳሰለ　　መ. አትረፈረፈ

6. ዝብዘባ　ሀ. ጭመራ　ለ. ምዝበራ　ሐ. ብዝበዛ　መ. ንትረካ

7. ማጓን　ሀ. ማበድ　ለ. ማሰር　ሐ. ማናር　መ. ማጠር

8. ክብድነት　ሀ. እርግዝና　ለ. ልእልና　ሐ. ትልቅና　መ. ትህትና

9. ዝባዝንኪያም　ሀ. ኮተታም　ለ. ወረታም　ሐ. ንፍጣም　መ. ልጋጋም

10. ፍጆታ　ሀ. እልቂት　ለ. ተራ　ሐ. ፍጆት　መ. ሥሬት

11. መግደፍ　ሀ. መፈሰክ　ለ. መርሳት　ሐ. መጣል　መ. ሀ፣ለ እና ሐ

12. ልምጭ　ሀ. ከዘራ　ለ. አለንጋ　ሐ. አርጩሜ　መ. ዱላ

13. ዋግ　ሀ. የእህል በሽታ　ሐ. የሰው በሽታ
ለ. የከብት በሽታ　መ. መልሱ አልተሰጠም

14. ዳተኛ　ሀ. ነገተኛ　ለ. ዋዘኛ　ሐ. አመለኛ　መ. ልግመኛ

15. ዲካ　ሀ. የጫማ ምልክት　ለ. ወሰን　ሐ. መንገድ　መ. ዓላማ

16. ቧጋች　ሀ. ተሟጋች　ለ. ለማኝ　ሐ. ጎታች　መ. ሸማች

**ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸውን ስጥ። /11/**

17. ምርቃት　ሀ. ጭማሪ　ለ. በረከት　ሐ. እርግማን　መ. ምስጋና

18. የምስራች　ሀ. ብሥራት　ለ. ዜና　ሐ. መቅኖ　መ. መርዶ

19. መናድ　ሀ.ማንፏቀቅ　ለ. መደርደር　ሐ. መቅረጽ　መ. ማፍረስ

20. መክሰም　ሀ. ማድረቅ　ለ. ማለምለም　ሐ. መበተን　መ. ማክሳት

21. አደባባይ　ሀ ማጀት　ለ. መጅሊስ　ሐ. ሸንጎ　መ. ደፋ

22. መቀለስ　ሀ. ማቅናት　ለ. ማጉበጥ　ሐ. ማቅለል　መ. መሥራት

23. ደስተኛ　ሀ. ጥጋበኛ　ለ. አሳረኛ　ሐ. ዱለኛ　መ. እልኸኛ

24. ማላቅ　ሀ. ማክበር　ለ. ማሳነስ　ሐ. ሊቅ ማድረግ　መ. ማተለቅ

25. ግልጽ　ሀ. ውስብስብ　ለ. ያልተደባለቀ　ሐ. የማያሻማ　መ. ፍንትው ያለ

26. በዓል ሀ. የደስታ ቀን
ሐ. የድል ቀን
ለ. የአዘቦት ቀን
መ. የእረፍት ቀን

27. ብርቅ ሀ. አዲስ ለ. እንግዳ ሐ. ያልታየ መ. የሰለቸ

ሐ. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ስጥ። /15/

38. ገርገብ አለ ሀ. ጠገብ አለ ለ. ፈዘዝ አለ ሐ. ሞቅ አለ መ. ሀ እና ሐ

39. ጥላ ቢስ
ሀ. ጥላ የሌለው ለ. ሞገስ የሌለው ሐ. ክብደት የሌለው መ. ምስል የሌለው

40. ሙጢ አፍ
ሀ. አፉ ወደፊት ያሞጠመጠ
ለ. አፈ ሹል የሆነ
ሐ. አፉ የሚያርፍ
መ. ነገረኛ

41. ዋጋ ቆረጠ ሀ. ዋጋ ቀነሰ ለ. ዋጋ ሰበረ ሐ. ዋጋ ወሰነ መ. ሀ፣ለ እናሐ

42. ማር አላሰ
ሀ. ማር ጨመረ ለ. በማር ለሰው አበላ ሐ. ማር ሸጠ መ. መርዝ አዘጋጀ

43. እግረ ደረቅ ሀ. ከሲታ ለ. ገደቢስ ሐ. ገላቢስ መ. ነገረኛ

44. ወሬው ጠፋ
ሀ. የወሬው ፕሮግራም አለቀ
ሐ. ስለ ሰውየው ማወቅ አልተቻለም
ለ የሚወራ ወሬ አልገኝ አለ
መ. ወሬው ድርግም አለ

45. ለድሮው ይወደኝ ነበር
ሀ. ድሮ ይወደኝ ነበር፤ አሁን ግን አይወደኝም።
ለ. ድሮ ሳደግሁለት ይወደኝ ነበር፤ አሁን ግን አይወደኝም።
ሐ. ድሮ ስለምንተዋወቅ ይወደኝ ነበር አሁን ግን ጠልቶኛል።
መ. መጀመሪያ ይወደኝ ነበር፤ አሁን ግን አይወደኝም

46. አጣርቶ ያነባል
ሀ. ፊደል በደንብ ለይቷል
ሐ. ሲያነብ አይሳሳትም
ለ. ሲያነብ ንጹህ አድርጎ ነው
መ. ፊደል እየጠራ ያነባል

47. ገመና ከታች
ሀ. ገንዘብ አበዳሪ
ሐ. ሽማግሌ ጠሪ
ለ. ሚስጥር ደባቂ
መ. ሰው አስሪ፣ ጠቋሚ

48. እንዝርት ቂጥ

ሀ. አንስተኛ መቀመጫ ያለው
ለ. መቀመጫው የሚሽከረከር
ሐ. ቁንጥንጥ
መ. የሾረ የሰለጠነ

49. በገ-ፊጅ
ሀ. አንድ በግ ሙሉ የሚበላ ሰው
ለ. አንድ በግ ሙሉ የሚቀቅል ድስት
ሐ. አንድ ድስት የበግ ወጥ የሚበላ ሰው
መ. አንድ ድስት ሙሉ የበግ ወጥ የያዘ ድስት

50. ቆቡን ጣለ
ሀ. ቆብ ጠፋበት
ለ. አለማዊ ሆነ
ሐ. ቆቡን ወረወረ
መ. መነከስ

51. ሳር ቅጠሉ ይወደዋል
ሀ. እንኳን ሰው ሳር ይወደዋል
ለ. ሰው ሁሉ ይወደዋል
ሐ. እንኳን ሰው ቅጠሉ ሁሉ ይወደዋል
መ. እንኳን ሰው ሳርና ቅጠሉ ይወደዋል

52. ነገረ ውሽልሽል
ሀ. ቁመ ነገር የሌለበት
ለ. ተውሽልሽሎ ያላማረ
ሐ. በቁም ነገር የተምነሸነሸ
መ. ቁመ ነገር የለሸለሸበት

**መ. በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ስጥ። /5/**

85. "ደንቦልቦል ያለ ባታቸውን" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. ቀጭን ባታቸውን ማለቱ ነው
ለ. ቀጠንና ወፈር ያለ ባታቸውን ማለቱ ነው
ሐ. ወፍራም ባታቸውን ማለቱ ነው
መ. ሰላላ መላላ ባታቸውን ማለቱ ነው

86. "ደረታቸውን ጣል አድርገው" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
ሀ. ደረታቸውን ሸፍነው
ለ. ደረታቸውን ገልጠው
ሐ. ደረታቸውን ጥለው
መ. ደረታቸውን እየመቱ

87. "ፈለል ፈለል እያለና እንቡር እንቡር" ያለው ምን ለመግለጽ ነው ?
ሀ. የጡታቸውን ጉች ጉች ማለት ለመግለጽ ነው
ለ. የጡታቸውን ትልቅነት ለመግለጽ ነው
ሐ. የጡታቸውን ንቅናቄ ለመግለጽ ነው
ሐ. የጡታቸውን ትንሽነት ለመግለጽ ነው

89. "ውስጡን ለቄስ" የሚለው አባባል ምን ማለት ነው ?
ሀ. የውስጥ የውስጡን ለቄስ ማለት ነው
ለ. ቄስ ወደ ውስጥ ይግቡ ማለት ነው
ሐ. የተደበቀ ሚስጥር ማለት ነው
መ. ግልጽ የሆነ ሚስጥር ማለት ነው

90. "ወላንስነት" ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ. ኮረኮንቻማነት ለ. ለስላሳነት ሐ. ጎርባጣነት መ. ሬኽምነት

7. 1986 ዓ.ም

ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ስጥ። /10/

1. እንከን ሀ. ስጦታ ለ. ስሐ ሐ. ጥርጣሬ መ. ንጹህ

2. ገነገነ ሀ. ሰረሰረ ለ. በረበረ ሐ. ጠረጠረ መ. ደረደረ

3. ዘላበደ ሀ. አወራ ለ. አወላወለ ሐ. አሳበቀ መ. ቀባጠረ

4. አድመኛ ሀ. ሴረኛ ለ. ሽረኛ ሐ. ተደባዳቢ መ. ተከራካሪ

5. ገመና ሀ. ሚስጥር ለ. ነውር ሐ. ሽታ መ. ግም

6. ቀጠፈ ሀ. ቆረጠ ለ. ዋሸ ሐ. ደለዘ መ. ሀ እና ለ

7. ረከሰ
ሀ. ሀጥያት ሰራ ለ. ዋጋው ቀነሰ ሐ. ተወደደ መ. ሀ እና ለ

8. አፋሸገ ሀ. አጣለ ለ. አዛጋ ሐ. አዘናጋ መ. አጋጨ

9. ዘከረ ሀ. አስተናገደ ለ.አስታመመ ሐ. አስታወሰ መ. አከረረ

10. አንጃ ሀ. የተለየ ለ.ግራንጃ ሐ. ዘመድ መ. መጢ

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸውን ስጥ። /10/

11. በገሀድ ሀ. በቀን ለ. በፊት ለፊት ሐ. በሚስጥር መ. በጠራራ ፀሀይ

12. ገዘገዘ ሀ. ቆመጠ ለ. ቆራረጠ ሐ. ቸፈቸፈ መ. ሰነጠቀ

13. ፀና ሀ. በዛ ለ. አየለ ሐ. ጠነከረ መ. አንገራገረ

14. ቆንቋና ሀ. ቸር ለ. ስግብግብ ሐ. ነገረኛ መ. አሳባቂ

15. ጥንድ ሀ. መንታ ለ. የጋራ ሐ. ማምራ መ. ነጠላ

16. ጨከነ ሀ. ቆረጠ ለ. ላሸቀ ሐ. ራራ መ. አመረረ

17. ማንገፍገፍ
ሀ. ማቅለሽለሽ ለ. ማኮሳተር ሐ. ማብዛት መ. ማበራከት

18. አዋቀረ ሀ. ገነባ ለ. አዋደደ ሐ. አፈረሰ መ. ማገረ

19. ፋፋ ሀ. ፋንጋ ሆነ ለ. ቀጨጨ ሐ. ወፈረ መ. አማረበት

20. ፈረፈረ ሀ. ዘነጣጠለ ለ. በታተነ ሐ. ጠረጠረ መ. ጨበጠ

**ሐ. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ስጥ።**

33. እጅ በእጅ ሀ. ነገ ለ. ወዲያው ሐ.ቶይቶ መ. ዛሬ

34. ያፍገደብ
ሀ. የንግግር ወሰን ለ. ያፍ ስፋት ሐ. ያፈ ጥበት መ. ለ እና ሐ

35. ዳር ዳር አለ ሀ. መሃሉን ተወ ለ. በጎን አለፈ ሐ. ፈራ መ. አመሃኘ

36. አግድም አደግ
ሀ. የተቀጣ ለ. ያልተቀጣ ሐ. የተንደላቀቀ መ. ያልተንደላቀቀ

37. ቅሌን ጨረቄን አለ
ሀ. ኮተት ሰበሰበ ሐ. ሰበብ አበዛ
ለ. እቃውን እንደ በአንድ አነሳ መ. ተጨቃጨቀ

38. እንቶ ፈንቶ
ሀ. ልቅም ሥራ ለ. የእጅ ሥራ ሐ. ውሽልሽል ሥራ መ. ጥግን ሥራ

39. ሆዱን ሰጠ
ሀ. ቃል ገባ ለ. ምስጥሩን ገለጠ ሐ. ለምግብ ተገዛ መ. ተቀጠረ

40. ቅቤ ጠባሽ
ሀ. ደፋር፣ጎበዝ ለ. ቀላል፣የተዋረደ
ሐ. አስመሳይ፣ አቆላማጭ መ. ሙያተኛ፣ ወጥ ሰሪ

41. ቆርጦ ቀጣይ ሀ. ቀዶ ጠጋኝ ለ. ውሸታም ሐ. ልብስ ሰፊ መ. ሀ እና ለ

**መ. በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ስጥ።**

56. " አጣማጅ " የሚለው ቃል የሚወክለው ማንን ነው ?
ሀ. ለብዙ ጊዜ ያረሰን በሬ ነው ሐ. ሽማግሌን ነው
ለ. ወይፈንን ነው መ. ወጣትን ነው

57. " መቀናጆ " የሚለው ቃል የሚወክለው ማንን ነው ?
ሀ. ለብዙ ጊዜ ያረሰን በሬ ሐ. ሽማግሌን ነው
ለ. ለብዙ ጊዜ ያላረሰን በሬ መ. ወጣትን ነው

60. "ሥራ ቤት" የሚለው ሐረግ የሚወክለው ማንን ነው ?
ሀ. እናጢን ነው
ለ. ቤት ለመሥራት ያሰበን ሰው ነው
ሐ. የቤት ውስጥ ሰራተኛን ነው
መ. ገንበኛን ነው

66. "ዘመናችን ሰነፈ" የሚለው ሐረግ ያዘለው ሐሳብ ምንድን ነው ?

ሀ. "ዘመነኞች ሰነፉ" የሚል ነው
ለ. "ዘመኑ አዝጋሚ ሆነ" የሚል ነው
ሐ. "ዘመነኞች መጠየቅና መመሪመር ተሳናቸው" የሚል ነው
መ. "ዘመነኞች አልሰለጠኑም " የሚል ነው

73. "ጭዳ" የሚለው ቃል የትኛውን ሐሳብ ያመለክታል
ሀ. የዓመት ባዓል እርድን ያመለክታል
ለ. ለባዕድ አምልኮ የሚደረግ እርድን ያመለክታል
ሐ. ለመስተንግዶ የሚደረግ ዕርድን ያመለክታል
መ. ባዕድ ስራሽ ነገሮችና ባሕል መዋጣችንን ያመለክታል

74. " ምስ " የሚለው ቃል ያዘለው ሐሳብ ምንድን ነው ?

ሀ. "የፀፀት ማስታገሻ " የሚል ነው
ለ. "የራሀብ ማስታገሻ ምግብ" የሚል ነው
ሐ. "የልምድ ማስታገሻ" የሚል ነው
መ. "የሀዘን ማስታገሻ " የሚል ነው

8. 1987 ዓ.ም

**ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ስጥ። /10/**

1. ሳግ
ሀ. ትርታ ለ. ሲቃ ሐ. ትክትክ መ.ሕቅታ

2. ጎባን
ሀ. አይታ ለ. ውሽማ ሐ. ጣውንት መ. ምራት

3. አግቦ
ሀ. ሸር ለ. ቧልት ሐ. ቀልድ መ. አሽሙር

4. ልጨኛ
ሀ. ከዳተኛ ለ. አስማተኛ ሐ. ቁምነገረኛ መ. የተሳጨ

5. ጣፍርዴ
ሀ. ባለጌ ለ. ዋልጌ ሐ. ስድ መ. ሀ እናሐ መልስ

6. ፋና ወጊ
   ሀ. ጠበንጃ ያዥ
   ለ. መብራት ያዥ
   ሐ. ጻዊት ያዥ
   መ. ፋካ ወጊ

7. ማገገም
   ሀ. ማገርሸት  ለ. መዳን  ሐ. መሻል  መ. መጋደም

8. ወበራ
   ሀ. ተራወጠ  ለ. ቀበጠ  ሐ. ተቁነጠነጠ  መ. ናጠጠ

9. ቡልኮ
   ሀ. ጋቢ  ለ. ነጠላ  ሐ. ኩታ  መ. ብርድ ልብስ

10. ትንኩሽት
   ሀ. ለኳሽ  ለ. አጫሽ  ሐ. ተጨዋች  መ. ልብ አድርቅ

**ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸውን ስጥ ::/10/**

11. አተረ  ሀ. አተር ሆነ  ለ. ጠጠረ  ሐ. ቆሰለ  መ. ሚሸሸ

12. ብሥራት  ሀ.የምሥራች  ለ. ወሬ  ሐ. መርዶ  መ. መልዕክት

13. ቁባት  ሀ. ውሽማ  ለ. ጭንገረድ  ሐ. ቅምጥ  መ. ሚስት

14. ሽርክት  ሀ. ግርድፍ  ለ. ክርትፍ  ሐ. ስልቅ  መ. ክክ

15. ነፈረቀ  ሀ. ተንከተከተ  ለ. አለቀሰ  ሐ. ተንሰቀሰቀ  መ. ተንጫነጨ

16. ሙሽት  ሀ. ቁርስ  ለ. ምሣ  ሐ. ቀንኛ  መ. ጉርሻ

17. ሥርጥ  ሀ. አሳባሪ  ለ. መውረጃ  ሐ. መዞርያ  መ. መውጫ

18. ወረዛ  ሀ. ጨቀየ  ለ. ረጠበ  ሐ. መጠጠ  መ. ደረቀ

19. ኩርማን  ሀ. ትልቅ  ለ. ቅንጣት  ሐ. ቅንጣቢ  መ. አያሌ

20. ቀምጣላ  ሀ. ሞልቃቃ  ለ. ጎስቋላ  ሐ. ደልቃቃ  መ. ኮስማና

**ሐ. ለተሰመረበት ቃል ትክክለኛውን መልስ ስጥ። /2/**

21. " አንድ <u>ትካር</u> ኖሮኝ ላዋይህ መጣሁ " በሚለው ዐረፍተነገር ውስጥ ከሥሩ የተሠመረበት ቃል የያዘው ፍቺ ምንድን ነው ?

ሀ. "ሚስጥር " የሚል ፍቺ ይዟል
ሐ. "መልዕክት" የሚል ፍቺ ይዟል
ለ." ወሬ" የሚል ፍቺ ይዟል
መ. "ጉዳይ" የሚል ፍቺ ይዟል

22. "ይህች ደንታ ቢስ ዓለም እንዱ ሊላውን የሺኑራ የሚያደበት ናት::" በሚለው ዐረፍተነገር ከሥሩ የተሰመረበት ቃል የያዘው ፍቺ ምንድን ነው ?

ሀ. "አሎልቆ ያያል" የሚል ፍቺ ይሄል ሐ. "ዙሮ ያያል" የሚል ፍቺ ይሄል
ለ. "የጎሪጥ ያያል" የሚል ፍቺ ይሄል መ. "አሻግሮ ያያል" የሚል ፍቺ ይሄል

**መ. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ስጥ:**

31. ለይስሙላ ሀ. ለመንቧተሩ ለ. ለወጉ ሐ. ለመሽቆምቆሙ መ.ለመግደርደሩ

32. አደብ ግዛ ሀ. ጭምት ሆነ ለ. ለሕግ ተገዛ ሐ. ልብ ገዛ መ. ታዛዥ ሆነ

33. ጎመን በጤና
ሀ. ጎመን ለጤና ይበጃል ሐ. ከአደገኛ ጌትነት በሰላም ድህነት
ለ. በጎመን ጤና ይገኛል መ. ጎመን በልቶ ያድራል ተኝቶ

34. ውርድ ከራሴ
ሀ. አልስማማም ለ.አልገባበትም ሐ. ከራሴ ይውረድ መ. ሀ እና ለ

35. የወገብ ቅማል
ሀ. ጎልቶ የሚታይ ሐ. ወገብ የሚበላ ቅማል
ለ. ወገብ ላይ የሚገኝ ቅማል መ. ከያዘ የማይለቅ

36. አንገተ ሰባራ
ሀ. ዝምተኛ ለ. አቀርቅሮ የሚሄድ ሐ. ዐይን አፋር መ. በትካዜ የተሞላ

37. አካልና ጥላ
ሀ. ቆሎ ተጓራሽ ለ. እሳትና ጭድ ሐ. ሆድና ጀርባ መ. እጅናጓንት

38. የቁራ መልዕክተኛ
ሀ.በዋል ፈሰስ ለ. የልብ አድራሽ
ሐ. ሲበሉ የላኩት መ. ሳይልኩት ወዷት ሳይጠሩትአቤት

**ሠ. በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ስጥ :: /3/**

55. " ዐይኔን ከፈትክልኝ " ማለት ምን ማለት ነው ?
ሀ.ችግሬን ተረዳህልኝ ሐ. ዐይኔን አበራህልኝ
ለ. ዐይነ ጥላዬን ገፈፍክልኝ መ. ማንነቴን እንድገነዘብ አደረኸኝ

63. "ህልውና የጨፈቀው " የሚለው ሐረግ ምን ማለት ነው ?
ሀ. ኑሮ ያንገሸገሸው ሐ. ኑሮ እጅ እጅ ያለው
ለ. ኑሮ ያስጨነቀው ሐ. ኑሮ ያጓሳቆለው

68. " የተጠረመሰ " የሚለው ቃል የሚገልጸው ምንን ነው ?

ሀ. የሰውን የራስ ቅል ነው

ለ. የሰው ምላስ ፊት ነው

ሐ. የሰውን ፊጣጣና ማዕዘንማ አካል ነው

ሐ. የሰውን ግንባር ገጽታ ነው

# አባሪ ለ

## የቀድሞዎቹና የአሁኖቹ መማሪያ መጻሕፍት በተለያዩ መመሪያዎች ስር ያቀረቧቸው ቃላትና ፈሊጦች ዝርዝር

1. በሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች ዐረፍተ ነገር ስርተህ አሳይ።

### 1.1 9ኛ ክፍል የቀድሞዎቹ /ቀ/ 69

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ማገባደድ | ቅለት | ውዱ | አቡሻክር | ወዝቶ | ሀልውና |
| አቋም | ቅርስ | ተዋኃዶ | ስል | አወሳ | ተሳነ |
| አቀናዘረ | መነገለ | ልዕልና | እንግልት | መነገለ | ብሶት |
| ረገድ | ወጣት | ደርሻለሁ | አኃዝ | መናኸርያ | ወዘፈ |
| ዝና | ድርደራ | ተመስጦ አፍላ | ዝቃጭ | ውጥንቅጥ | ጭንጋፍ |
| ሲፋጭ | አጀለ | | ትንፋግ | ጥምር | መገርጣት |
| በገሀድ | ቅን | መገልገል | አጢኖታል | ጭብጥ | ተውረገረገ |
| ቋጥኝ | አከማቸ | ሞንደል ሞንደል | ብሔርተኛ | ማስረጃ | ለዛ |
| ድኝ | ማስደንበር | ተንቆጠቆጠ | ውርጭ | አግበሰበሰ | ማቀቀ |
| ሐሩር | ገቢር | አንዳገር | ፀረ ጉልተኛ | መበየፍ | ቀመረ |
| ሴራ | ጠንቅ | ገነነ | ደነዘዘ | ወዳጅ | ስቆቃው |
| ሠነድ | ቅፃር | | መቅን | እርቃን | |
| | | | | ሥጋ | |

### 1.2 9ኛ ክፍል የአሁኖቹ /አ/ –59

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| መደዳ | ተስፋ | ጥንብ | ተተራመሰ | ጥቢኛ | ጫረ |
| ጥናት | ይገባል | ኮበሌ | መምራት | ሐምሌገም | እንፈንፈ |
| የሚበጅ | ስንዝር | አንጎላጀ | ተንቀዋለለ | ሲል መገበር | መብስከስከ |
| ይጠቅማል | አንጋች | አማላጅ | መመልከት | ኩል መስለ | ድል መታ |
| መለወጥ | ጾፍ | ተከለከለ | አምባር | ቁንን | ትቢያ |
| ደስታ | ባንዳ | ጨበጠ | ሽብር | ላሽ | ጠንቀኛ |
| አቋም | ቅርስ | ስለት | ማውጣት | በተስፋ ዐይን | ስንፍ |
| ተኮፈሰ | አበጋዝ | አለፈ | ማውረድ | ደረሰ | ጭቶ |
| ቋጥኝ | አቆለቆለ | መስለ | መስተንግዶ | ራስ | ትናት |
| ጀሮ–ደግፍ | | ደራ | ማርከፍከፍ | ሲያስላስል | እንግዳ |
| | | | ነቀየ–ቅድሳት | | |

## 1.3 10ኛ ክፍል የቀድሞዎች /ቀ/ - 101-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ገነነ | ፈገመ | ይይዛል | ዘለፈ | ይስላሉ | ሂደት |
| መመደብ | ሰከነ | ተወጥሮ | ጋፈፈ | ዋጋ | ቀንደኛ መስራች |
| ከረረ | ሲያምታታ | ተዛበቱ | ይበረታል | ተውተረተ | ፍትህ |
| ጓጎለ | መቅበጥበጥ | አጀለ | መሪ | ረ | ቋጨ |
| ግብ | ፈና | አጠፍተው | አፈጀ | ተብላላ | አዝርዕት |
| | | | | ደፋ | |
| ዕፅዋት | ደነበረ | አወደ | አስተጋባ | ገበቴ | አድማስ |
| መቆለል | ፈንጋይ | የውል | ቅጽበት | ሕልውና | መደንደን |
| ወኔ | ማጤን | የታፈረ | እንደበት | አጽናፍ | ከንድ ማንሳት |
| ቡቃያ | ገነፈለ | ዘቀጠ | ተጋተረ | ጣዕረ ሞት | ርዕየተ ዓለም |
| ጎሞራ | መሠሪ | ብልሐት | ጥላት | ተቆረቆረ | የአስተሳሰብ ነቀርሳ |
| አቋም | መኖ | ዕረፍት | ግልባጭ | ጠጠረ | የሰደድ እሳት |
| አጋለጠ | በግኖ | ጽንስ | የሒስ | ንድፈ | አድር ባይ ተራማጅ |
| ጆቢራ | አቀናበረ | ግማድ | ብዕር | ሐሳብ | ምጣኔ ሐብት |
| አጅሬ | አርማ | በዓይነቁራኛ | አትሮንስ | ተሐድሶ | የፓርቲ ተቀናቃኞች |
| አውታር | ተከኖ | እፁብ | ነቁጥ | በውሕደት | ስንቅ አቀባይ |
| ስርጥ | ተጋተረው | መዋዕለ ዜና | ሲነግ | መፈክር | የቀድሞ ወጉን |
| ዘይቤ | ፍትሕ | አጣቢቅኝ | ትርፍርፍ | አሚካላ | ወግ ማስያዝ |
| | | | | | አነብናቢ አወናባጅ |

## 1.4. 10ኛ ክፍል የአሁኖቹ /አ/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ነፍስ | አያሌ | ተከና | አጣደፈ | ቆዳ የለበሰ | ደስታው የሸሸበት |
| ቆረቆረ | አቃሰተ | ዘነጋ | እሽሩሩ እያለ | አጽም | ስማቸው |
| ሕይወት | መጫኛ | ከተኛበት | ተጎናፀፈ | አፍን ይዞ | የመንቀሳቀሻ ሕወት |
| ባህር | አስተባበለ | ቀስቀስ | ሀሳቡንጥሉ | ሲወድቅ ሲነሳ | ወርቅ |
| ሶፋ | ተቀጠፈ | አጣጣረ | የችግር ዘመን | መፈንጠዝ | ዓለም |
| ተወጥሮ | ተንከራተተ | ማዕበል | መንፈስ | እንቅልፍ | ግብ |
| ሲሰናዱ | ራቁት | ዕብደት | ማድረግ | ከበረ | የቀበጠ ጠባይ |
| ሲበላ | መቀስቀስ | መዘርጋት | ከገነኑት | ሲያምታታው | በደረቱ ላይ አድርጎ |
| ይበረታሉ | ጠነቆለ | ጉዞኞች | | | |

## 1.5. 11ኛ ክፍል የቀድሞዎች /ቀ/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እከል | ረጋ | ንጥረ ነገር | መቀነባበር | ገለጠ | ማዋሐድ |
| መምራት | አደናቀፈ | ፈታ | ቅጽበት | የማይበገር | ወረት |
| መሰለ | መዛመት | ተገነባ | ከበረ | መዳበር | ተዘፈዘፈ |
| አበጠ | ድርድር | አደሰ | መዋቅር | ተቀናጣ | ወትሮ |
| ዕጢ | ቀሰቀሰ | ጥገኛ | ማመንጨት | መቃኘት | የጾም መፍታት |
| የሚጠራበት | ተከሰተ | ሕዋሳት | ፍጅት | ተናጠል | ተዛባ |
| የዘር አቧራ | አቶሰቶሰ | አወሳ | መውረስ | መርመጥመጥ | ሰረገ |
| በውል | ቅራኔ | ትንንቅ | ርካሽ | ገጽ | ቤዛ |
| አወደሰ | አስመለሰው | መጋጠሚያ | ትንታኔ | ኢ ሰብአዊ | መውረስ |
| ትልታይ | አጠነፈረ | ተንከባከበ | አንተረከከ | ግሳንግስ | ግብአተ መሬት |
| ዘይቤ | ስሌት | ዕቅድ | ታዳጊ | ጨቋኝ | ባሕርይ |
| ተጨባጭ | አንበረከከው | መዘበረ | መከረር | ሲቃ | አብሰለሰለ |
| ተቀናቀነ | ጠበቀ | የሚለየው | ጉልተኛ | ቸነፈር | ቅጥ የሌለው |
| እትብት | መሰናክል | ሰበቀ | ጎመደ | መፈንገል | መደብ-አልባ |
| ተገላቢጦሽ | ማፍራት | ሂደት | መከለስ | ተጨቋኝ | አረምሞ |
| ጨቅላ | ተንኮተኮተ | መቁረጥ | እያደለቡ | ሰቀቀን | ቅንጣት |
| ተፅኖ | ነቃ | አቅርብ | ጽንሰ | ማስተዋል | መሠረት |
| መከትከት | ተወራጨ | ትንታግ | ሐሳብ | ማሸንቀጠር | መፍጨርጨር |
| ነባራዊ | ፀር | በድን | ፈለሰ | ሲል | ፍትጋ |
| እስተኔ | ጠቀሰ | ተፈፀመ | ፈላሻ ዘር | ወጣገብ | ውጥንቅጥ |
| መስመር | ተከናወነ | ለከፈ | ተላለፈ | አዘቅት | ቅራኔ |
| ሔደ | ማጥ | ቅይጥ | ዝቃጭ | | |
| | | | ማኮማተር | | |

## 1.6 11ኛ ክፍል የአሁኖቹ /አ/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀጠፈ | የሚያስችል | ተዋረደ | ቦዘ | ቡትቶ | እጽመ-ርስት |
| ያለት | መጣላቸው | ረጅም ዘመን | ይቀምማል | ደረሰ | እጁን ዘርግቶ |
| ምሰሶ | ሲያስተጋባ | አጉረጠረጠ | ባል | ግለ ህልውና | ተገ-ሲል |
| ተረጋገጠ | አጋተ | ያሳሳል | እንደ ሰማ | አስተዋጽኦ | ነውረኛ ልጅ |
| አጥግቦት | መለሰ | ተራ | አቋም | ሲያስላስል | ቢሮክራሲ |
| ተፈታ | ጎዶጎደ | ፈቱን አባርቶ | ማጋዝ | እንዲቀዘቅዝ | ለራሱ መናገር |
| ወጣ | ተባረከ | ሰነፍ ተማሪ | መረዳት | ተሸቀርቅሮ | የበቀል እርምጃ |

## 1.7 12ኛ ክፍል የቀድሞዎች /ቀ/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እስተዋጽኦ | ሰፍኖ | ነፍስ | ትይዩ | አቆለቆለ | የሚቀናጅ |
| ማጋዝ | ማንፀባረቅ | መሸቀል | ሕይወት | ማውጣት ውረድ | አቋም |
| መረዳት | ራስ | መዋቅር | ገፈፈ | ገኖ | እኳያ |
| ተረጋገጠ | አወጣጥ | ጭፍን | ተፍጨረጨረ | ሥጋ | ይደርሳል |
| ትክሻ | እናት | ማለም | ሲያስላስል | እንጀራ | የሚያስችል |
| ማዳበር | መስተንግዶ | | | | |

## 1. 8. 12ኛ ክፍል የአሁኖቹ /አ /

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አጠና | ማማር | ፍሬ | ተረዳ | ጎረነነ | አያት |
| ይጠባል | ሕይወት | ተማረ | ከዳ | ሲያስላስል | ወፍ |
| ከፍች | ገፋፈ | ሥጋ | አፈርሳታ | በሬ | ገባለት |
| ጥሬ | ሽምጥ | መሳል | አቆለቆለ | በረገደ | በተስፋ ዐይን |
| መመርመር | ሲለካ | መጥለፍ | ድል | ተወረሰ | ውል |
| ጥራት | እናት | አለመ | ገጠገጠ | ማርከፍከፍ | አወሳ |
| ነፍስ | አለ | ራስ | አረዳ | ክንፍ | ቀና |
| ግርግም | ጠራ | ዋና | ማውጣት ማውረድ | አውጫጭኝ | ወገግታ |
| የሚገባ | ጨበጠ | ማፍላት | ጠርዝ | መስተንግዶ | ትክሻ |
| | | | ምሥጥር አትችልም | እንጀራ | |

## 2. ለሚከተሉት ቃላት ፍች ስጥ

### 2.1 9ኛ ክፍል /ቀ/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጨቆነ | ዳበረ | መደብ | ፈጨ | መናኛ | ገነፈለ |

## 2.2. 9ኛ ክፍል /አ/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ደጸ | ኅብረ | ቡድን | ትዕቢት | ቅናት | ጥንት |
| የሚበጅ | ቀለማት | ትቢያ | በኩር | ሲገለጥ | በውበት ላይ ውበት |
| መለወጥ | ተመኘ | የሚበላ | በለብ ወረዛ | በእንድንትሆንን | እየበዛና እየሰፋ |
| ተስፋ | ቁንን | ስታጌጥ | ስንፈት | ቀባጠረ | ተጓዳኝ ትምህርት |
| ስንዝር | ዋና | ዝንባሌ | ሲፈንጥቅ | ስውር | ምርጫና ዝንባሌ |
| ምርኮ | ትዝታ | ተነባበረ | ሽፈተ | ማዘናጋት | በንዴት እቃጠላለሁ |
| ማቅናት | ጫረ | ቅንነት | መቃቀር | እምባጓሮ | የዘመናት ቅምር |
| ፍትሕ | ለጋ | ሲጠራ | ደምቀው | ቀማሚ | ብርሃን ሲፈንጥቅ |
| ዶፍ | አጠናከረ | መንፈሱ | ገርገብ አለ | ደፈጣ | ውሉ እያውቅ |
| ኀደለ | መብሰክሰክ | ታወከ | የልጅ ነገር | ለጋስ | እሰሳ |
| መገበር | አለ | ፍከራ | ተከዘ | ተብረከረከ | እንጀቱ አረረ |
| አፈጠነ | ደግነት | ወግ | ክርክር | ጎንለጎን | መላስ |
| ቀረርቶ | ደብድቦ | ምሬት | አመረረ | ምስራች | ተከልለው |
| ይምራሽ | ኅደለ | ደለቀ | ማዕረግ | ቆፍጣና | ውሳኔ |
| እሸታ | ነቀፈ | | | | |

## 2.3 10ኛ ክፍል /ቀ/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጉማጅ | የጡትን ጫፍ ማብሰልሰል | መቀላቀል | ማሳጣት | አፈቀላጤው | ተግባር |
| መተፋፈግ | መታጨት | ጠፍ ጨረቃ | አዲስ ሕፃን | መፍጀት | መስተጋብ |
| ረባዳ | ጡትን በፀሐይ ማስመታት | ግፈት | ድንግል | መመንጠር | ደሳሳ ጎጆ |
| ነጋ | ከጾም ነጻ መሆን | ሂደት | መጥመቅ | እውነታ | ነባራዊ |
| ማርጋት | ፈሳሽ ነገር መውሰድ | ማማሰል | የበኩር ልጅ | ደርግ | እብቅ |

## 2.4 10ኛ ክፍል /አ/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| መጋረጃ | ተጋርጦ | ትንሳኤ | ክበለሉ | ወኔ | እፎይ አለ |
| ጥሻ ድባብ | የኤክስፐርት ቡድን | መላ | ቧልት | ምግባረ ሰናይ | ስቀቀን |
| | የዕድሜ እጋማሽ | ተደፋ | ይዘከራል | እብሽ | መግለት |
| ቀላ | ጉዳይም ሳትለው | ምፅዋት | ታዳጊ አገሮች | ሳለ | ሲሳብ |
| ጠባሳና አሻራ | የአእምሮ ስንኩልነት | ጠብቀው | አቅም | መደረግ | እመረ |
| ላልተው | ተደራራቢ ችግሮች | መዝረፍ | መኸረጠ | ተፀፀተ | ቸንፈር |
| ወደር የለሽ ሚና | እፎይታ ያላጀበው ኑሮ | ተሳለ | ትምጥል | ደለለ | ሜራ |
| አለፈ | የኢኮኖሚ ውድቀት | የወንዝ ቤዛ | ስተቴ | ማገርና ዋልታ | ቀየ |
| ሁነኛ ፍሬ | ተምካሻ | አጣና | ሽመቀቀ | ተረዳ | አሸለበ |
| አልሻም | ብካይ | መንስኤ | አቅሮ | ስንኩል | ዕልቂት |
| ያላሰለስ ጥረት | እሽሙር | እንባ እንቀኝ | መጠጥ | ፀጥ አለች | ሽሙጥ |
| ስሌት | ቋም | እለተ ዕረፍት | ተበተነ | ትንተና | ጦሶ |
| ሰው ለማድረግ | ወላጅ | | | | |

## 2.5 11ኛ ክፍል /ቀ/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሳይንስ አባል | ሽለቆውን መትል | የመደብ ንቃት | ተገ አለ | የዕርዳታ ያለህ | ተራራ |
| የኑሮ መታወክ | የማይታረቅ ቅራኔ | የህይወት ማለፍ | እሳት | እካለ ቡድን | ገደል |
| ግብረ አበር | እንደ እንጉሳዩ ብቅ አለ | እሳት ወለድ | ሐዲድ | ፍሳሽ ዋጋ | እፈለጠ |
| ሠረጎ ገብ | የነበልባል ግግጅ | ሜዳ | ባቡር | ተጻራሪ | ፈፋ |
| አቀበት | ለውጤ እሳት | የመደብ ድል | አፈታሪክ | ምልክት | |

## 2.6 11ኛ ክፍል /አ/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ከየጎራው | ዕደ ጥበብ | ግት ለብሳ ግት መስላ | የአስተሳሰብ አድማስ | ደመነፍስ በመራችው | ሲያውክ |
| ትንሳኤ | እከለፋ | ከፍተኛ የአእምሮ ተግባር | ግስንግስ | ሲንር | ልቡ ማይሳይ |
| ቡድን | ሲመኸርርጥ | ወፍ ሳይንጫጫ | ጭፍጋግ | ቁጃር | እልፍኝ |
| ሙሉ | ተሲያት | ሰብእዊ ባህርይ | መአዛ | ደምግባት | ሐቅ |
| ሰውነት | ትቢያ | ትንጠራወተው | ሽል | | ጎረሰ |
| ስርቻ | ውርዝና | ሙሉ አካልን | የፈላ እንባ | ተከሰተ | እንረበረበ |
| እየተትጉለጎለ | አይጣል | ህልቆ መስፈርት | የሆይታ ቋት | ሽሙ | ተኸረበረበ |
| የሃዘን በትር | እጦተ ቢስ | የእንጀራ እናት | አካልዋ እየቀለጠ | የዘመኑ ሰው | የጥጋብ ቅርስ |
| ቅያ | | ያለግዜው ተቀጨ | እንካ ሰላንቲያ | ጎረፈ | የቡኮ እቃ |
